# መጽሐፈ ነገሥት - ሁለተኛ

## መግቢያ

### አስተዋፅኦ

ከዚህ ቀጥሎ የመጽሐፉ አስተዋፅኦ ባጭር ባጭሩ ቀርቦአል:: የተሟላውን አስተዋፅኦ በተመለከተ በአንደኛ ነገሥት መግቢያ ሥር አስተዋፅኦ የሚለውን ክፍል ይመ::

3. ከአክአብ/ከአሳ እስከ ኢዮራም/ኢዮሳፍጥ ዘመነ መንግሥት ድረስ ያለው የኤልያስ፣ የኤልሳዕና የሌሎቹ ነቢያት አገልግሎት (1ነገ 17፥1-2ነገ 8፥15)
   ሀ. ኤልያስና ሌሎች ነቢያት በአክአብ ዘመነ መንግሥት (1ነገ 17፥1-22:40)
   ለ. የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ (1ነገ 22፥41-50)
   ሐ. የእስራኤል ንጉሥ አካዝያስ፤ የኤልያስ የመጨረሻው ትንቢት (1ነገ22፥51-2ነገ 1፥18)
   መ. ኤልያስ ወደ ሰማይ ተወሰደ፤ ኤልሳዕ በኤልያስ እግር ተተካ (2ነገ 2፥1-18)
   ሠ. ኤልሳዕ በኢዮራም ዘመነ መንግሥት (2ነገ 2፥19-8፥15)
4. እስራኤልና ይሁዳ ከኢዮራም/ኢዮራም ዘመነ መንግሥት እስከ እስራኤል ምርኮ (2ነገ8፥16-17፥41)
   ሀ. የይሁዳ ንጉሥ ኢዮራም (8፥16-24)
   ለ. የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስ (8፥25-29)
   ሐ. የኢዩ ዐመፅና አገዛዙ (ም 9-10)
   መ. ጎቶልያና የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአስ፤ የቤተ መቀደሱ መታደስ (ም 11-12)
   ሠ. የእስራኤል ንጉሥ ኢዮአካዝ (13፥1-9)
   ረ. የእስራኤል ንጉሥ ዮአስ፤ ኤልሳዕ የመጨረሻ ትንቢት (13፥10-25)
   ሰ. የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ (14፥1-22)
   ሸ. የእስራኤል ንጉሥ ዳግማዊ ኢዮርብዓም (14፥23-29)
   ቀ. የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ (15፥1-7)
   በ. የእስራኤል ንጉሥ ዘካርያስ (15፥8-12)
   ተ. የእስራኤል ንጉሥ ሰሎም (15፥13-16)
   ቸ. የእስራኤል ንጉሥ ምናሔም (15፥17-22)
   ኀ. የእስራኤል ንጉሥ ፋቂስያስ (15፥23-26)
   ነ. የእስራኤል ንጉሥ ፋቁሔ (15፥27-31)
   ኘ. የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአታም (15፥32-38)
   አ. የይሁዳ ንጉሥ አካዝ (ም 16)
   ከ. የእስራኤል ንጉሥ ሆሴዕ (17፥1-6)
   ኸ. የእስራኤል ምርኮ፤ በምድሪቱ ላይ ዳግም መስፈራቸው (17፥7-41)
5. ይሁዳ ከሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት እስከ ባቢሎን ምርኮ (2ነገ 18-25)
   ሀ. ሕዝቅያስ (ም 18-20)
   ለ. ምናሴ (21፥1-18)
   ሐ. አሞጽ (21፥19-26)
   መ. ኢዮስያስ (22፥1-23፥30)
   ሠ. ኢዮአክስ ወደ ግብፅ ተሰደደ (23፥31-35)
   ረ. ኢዮአቄም፤ የመጀመሪያው የባቢሎን ወረራ (23፥36-24፥7)
   ሰ. ኢዮአቄም፤ ሁለተኛው የባቢሎን ወረራ (24፥8-17)
   ሸ. ሴዴቅያስ (24፥18-20)
   ቀ. የይሁዳን ሕዝብ ተማርኮ ወደ ባቢሎን መወሰዱ (25፥1-21)
   በ. ትሩፋኑ ወደ ግብፅ መወሰዳቸው (25፥22-26)
   ተ. ዮአኪን በባቢሎን ከፍ ከፍ አለ (25፥27-30)

## የእግዚአብሔር ፍርድ በአካዝያስ ላይ

1 አክዓብ ከሞተ በኋላ ሞዓብ በእስራኤል
ላይ ዐመፀ:: [2]በዚህ ጊዜ አካዝያስ በሰ
ማርያ ካለው እልፍኝ ሰገነቱ ላይ ሳለ፣ ከዓ
ይነ ርግቡ ሾልኮ ወድቆ ነበርና ታመመ፤
ስለዚህ፣ "ሂዱችሁ ከዚህ ሕመም እድን እን
ደሆነ የአቃሮንን አምላክ ብዔልዜቡልን
ጠይቁ" ሲል መልእክተኞች ላከ::
[3]*የእግዚአብሔር* መልአክ ግን ቴስብያዊ
ውን ኤልያስን እንዲህ አለው፤ "ተነሥተህ
የሰማርያን ንጉሥ መልእክተኞች ለመገናኘት
ውጣና፣ 'የአቃሮንን አምላክ ብዔልዜቡልን
ለመጠየቅ የምትሄዱ በእስራኤል አምላክ
ስለሌለ ነውን?' ብለህ ጠይቃቸው:: [4]ስለዚህ
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ 'ከተኛህበት
ዐልጋ አትነሣም፤ በእርግጥ ትሞታለህ::' "
ከዚያም ኤልያስ ሄደ::
[5]መልእክተኞቹ ወደ ንጉሡ ሲመለሱ
"ለምን ተመልሳችሁ መጣችሁ?" ሲል ጠየ
ቃቸው::
[6]እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱለት፤
"አንድ ሰው ሊገናኘን መጥቶ፣ 'ወደ ላካችሁ
ንጉሥ ተመልሳችሁ ሂዱና፣ "*እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ 'የአቃሮንን አምላክ ብዔል
ዜቡልን ለመጠየቅ ሰዎች የምትልከው በእ
ስራኤል አምላክ ስለ ሌለ ነውን? ስለዚህ
ከተኛህበት ዐልጋ አትነሣም፤ በእርግጥ
ትሞታለህ::"'"
[7]ንጉሡም፣ "ለመሆኑ ሊገናኛችሁ መጥቶ
እንዲህ ያላችሁ ሰው እንዴት ያለ ነው?"
ሲል ጠየቃቸው::
[8]እነርሱም "ሰውየው ጠጕራም ልብስ የለ
በሰ ነው፤ በወገቡም ላይ ጠፍር ታጥቆአል"
አሉት::
ንጉሡም፣ "ዐወቅሁት፤ ቴስብያዊው ኤል
ያስ ነው" አላቸው::
[9]ከዚያም ንጉሡ አንድ የአምሳ አለቃ
ከአምሳ ወታደሮቹ ጋር ወደ ኤልያስ ላከ::
የአምሳ አለቃውም ኤልያስ ወደ ተቀመጠ
በት ኰረብታ ጫፍ ወጥቶ፣ "አንተ የእግዚአ
ብሔር ሰው፤ ንጉሡ፣ 'ና ውረድ' ይልሃል"
አለው::
[10]ኤልያስም መልሶ የአምሳ አለቃውን፣
"እኔ የእግዚአብሔር ሰው ከሆንሁ፣ እሳት ከሰ
ማይ ወርዳ፣ አንተንና አምሳውን ሰዎችህን
ትብላ!" አለው:: ከዚያም እሳት ከሰማይ
ወርዳ የአምሳ አለቃውንና ሰዎቹን ፈጽማ
በላች::
[11]እንደገናም ንጉሡ ሌላ የአምሳ አለቃ
ከአምሳ ሰዎቹ ጋር ላከ፤ የአምሳ አለቃውም፣
"አንተ የእግዚአብሔር ሰው፤ ንጉሡ፣ 'አሁኑኑ
ና ውረድ' ይልሃል" አለው::
[12]ኤልያስም መልሶ፣ "እኔ የእግዚአብሔር
ሰው ከሆንሁ እሳት ከሰማይ ወርዳ አንተንና
አምሳውን ሰዎችህን ትብላ!" አለው፤ ከዚ
ያም እሳት ከሰማይ ወርዳ እርሱንና ሰዎቹን

1፥1 ዘፍ19፥37፤ 2ነገ3፥5
1፥2 ቍ16፤መሳ 18፥5፤ 1ሳሙ6፥2፤ኢሳ 2፥6፤14፥29፤ማር3፥22
1፥3 ቍ15፤1ሳሙ 28፥8፤1ነገ17፥1
1፥4 ቍ6:16፤ መዝ41፥8
1፥6 ቍ4
1፥8 1ነገ18፥7፤ ማቴ3፥4፤ማር1፥6
1፥9 ዘፀ18፥25፤ 2ነገ6፥14፤ኢሳ3፥3
1፥10 1ነገ18፥38፤ ራእ11፥5፤13፥13

1፥1 *አክዓብ ከሞተ በኋላ፤* 1ነገ 22፥37 ይመ:: *ሞዓብ ... ዐመፀ፤* ሞዓብ በዳዊት ተሸንፎ ተገዥ ሆኖ ነበር (2ሳሙ 8፥2 ይመ)፤ ይሁን እንጂ የሰሜንና የዮርዳኖስ አካባቢ ነገዶች ዐምፀው ኢዮርብዓምን ንጉሣቸው ባደረጉ ጊዜ፣ ሞዓብ በሰሜኑ መንግሥት መገዛት ሳይጀምር አልቀረም:: የሞዓብ ንጉሥ የሜሻን የድንጋይ ላይ ቅርጽ ጽሑፍ በኦምሪ ልጅ፣ (ምናልባትም አክዓብን ሳይሆን ልጁን ኢዮራምን ሊሆን ይችላል) ዘመነ መንግሥት ሞዓባውያን ሜደባ የተባለውን ግዛት ከእስራኤል ነጻ ማውጣት መቻላቸውን ያመለክታል::

1፥2 *ብዔልዜቡል፤* የመሳፍ 10፥6 ማብ ይመ:: *አቃሮን፤* ከአምስቱ የፍልስጥኤም ዋና ዋና ከተሞች በስተ ሰሜን ያለው ሲሆን (ኢሱ 13፥3፤ 1ሳሙ 5፥10 እና ማብ ይመ)፣ ከደቡብ ኢየሩ ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ይርቃል:: *እድን እንደ ሆነ፤* አካዝያስ ሕመሙ እጅግ የከፋ ስለ ሆነ የመዳን ተስፋው ተሟጦ የፈራ ይመስላል፤ ስለዚህም ፈውስን ሳይሆን ንግር ፈልጎ ወደ ጣዖት ዘወር አለ::

1፥3 *የእግዚአብሔር መልአክ፤* 1ነገ 19፥7 ይመ፤ እንዲሁም የዘፍ 16፥7 ማብ ይመ:: እግዚአብሔር በተለመደ መንገድ ለነቢይ በቀጥታ ይናገራል (1ነገ 17፥2:8፤18፥1፤19፥9፤21፥17 ይመ)፤ በዚህ ጊዜ መልእክቱ የተላለፈበት መንገድ የተለወጠው ንጽጽሩን ለማጕላት ይመስላል፤ ይህም ንጽጽር በእግዚአብሔር መልአክና በአካዝያስ መልእክተኞች መካከል ነው (ቍ 2-3:5):: *ቴስብያዊው ኤልያስ፤* የ1ነገ 17፥1 ማብ ይመ:: *የሰማርያን ንጉሥ፤* የ1ነገ 21፥1 ማብ ይመ::

1፥4 *በእርግጥ ትሞታለህ፤* አካዝያስ የፈለገውን ንግሩ አግኝቶአል፤ ሆኖም ግን ንግር የመጣው ከብዔልዜቡል ሳይሆን፣ በኤልያስ በኩል ከእግዚአብሔር ነው::

1፥5 *ለምን ተመልሳችሁ መጣችሁ?* አካዝያስ ይህን ጥያቄ የጠየቃቸው ሰዎቹ በዚህ ፍጥነት አቃሮን ደርሰው መመለስ እንደማይችሉ ስለ ተረዳ ነበር::

1፥8 *ጠጕራም ልብስ የለበሰ፤* 1ነገ 19፥19 ይመ:: የኤልያስ ልብስ ከበግ፣ ከፍየል ወይም ከግመል ጠጕር የተሠራ ሊሆን ይችላል (ከማቴ 3፥4 ጋር ያነጻጽሩ):: አለባበሱ በዘመኑ ከነበረው በቀጭኑ ከተፈተለ ሐር ከሚሠራው ልብስ (ኤር 13፥1)፣ በተለይም በእርሱ ጊዜ የነበሩ ቍሳዊ አመለካከት የነበራቸው ሀብታሞች፣ ንጉሡና በከፍተኛ ደረጃ ያሉ ሰዎች ከሚለብሱት ጋር የሚቃረንና እነርሱንም የሚቃወም ነበር (ከማቴ 11፥7-8፤ ሉቃ 7፥24-25 ጋር ያነጻጽሩ):: *ቴስብያዊው ኤልያስ ነው አላቸው፤* ነቢዩ ከአባቱ ከአክዓብ ጋር ብዙ ጊዜ ይገናኝ ስለ ነበር፣ አካዝያስ ኤልያስን በደንብ ያውቀው ነበር::

1፥9 *አንድ የአምሳ አለቃ ከአምሳ ወታደሮች ጋር ወደ ኤልያስ ላከ፤* በዚያን ዘመን በነበሩ የጣዖት አምላኪ ሕዝብ ዘንድ፣ ሰውየውን አስፈራርቶ ርግማኑን በማስቀረት ወይም ሰውየውን በመግደል በአስማት ኀይል የሚደረግ ርግማን ከንቱ ማድረግ ይቻላል ተብሎ ይታመን ነበር:: ስለዚህ አካዝያስ ይህን ሐሳብ ተቀብሎ፣ ኤልያስ የተናገረውን ቃል ለማክሸፍ ወታደሮቹን ልኮ ኤልያስን በማስመጣት ለማሰር ወሰነ:: *አንተ የእግዚአብሔር ሰው፤ ንጉሡ፣ 'ና ውረድ' ይልሃል፤* አካዝያስ ነቢዩን በንጉሥ ሥልጣን ሥር እንዲሆን ያሰበ ይመስላል:: ይህ ደግሞ በቃል ኪዳኑ ሕግ ውስጥ የእስራኤል ነገሥታት ምንጊዜም በነቢያት ከሚነገረው የእግዚአብሔር ቃል ሥልጣንና ምክር ሥር መሆን አለባቸው የሚለውን የሚቃወም ነው (1ሳሙ 10፥25፤12፥23 እና ማብ ይመ)::

1፥10 *እሳት ከሰማይ ወርዳ የአምሳ አለቃውንና ሰዎቹን ፈጽማ በላች፤* 1ነገ 18፥38 ይመ:: የኤልያስና የሙሴ አገልግሎት በዚህ ይመሳሰላል (ዘሌ 10፥2፤ ዘኍ 16፥35 ይመ):: ይህ በእስራኤል የበላይ ማን እንደ ሆነ ፊት ለፊት የተገለጸበት ሁኔታ ነው:: በእስራኤል፣ ንጉሥ ከእግዚአብሔር ንጉሥነትና ሥልጣን ሥር መሆኑን፣ እግዚአብሔርንም ወክሎ የሚያስተዳድር እንጂ እንደ አሕዛብ ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም እንደሌለበት አካዝያስ ተገንዝቦ ይሆን (1ሳሙ 12:14-15 እና ማብ ይመ)? በቀርሜሎስ ተራራ እግዚአብሔር ራሱን ገልጦ፣ የነቢዩን እውነተኛነት ከሰማይ በወረደ እሳት አረጋገጠለት (1ነገ 18፥38-39 ይመ):: እንደ ገናም በዚህ ስፍራ ለአካዝያስ የነቢዩን ሥልጣን በእሳት አረጋገጠለት:: ደቀ መዛሙርቱ እሳት ከሰማይ ወርዶ የሰማርያን ሰዎች እንዲበላ (ሉቃ 9፥51-56) ኢየሱስን በጠየቁ ጊዜ ማውገዙ የኤልያስን ድርጊት ለመቃወም አልነበረም፤ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በኤልያስ ዘመን የነበረውን ወሳኝ ሁኔታና በራሳቸው ዘመን ደግሞ የሰማርያ ሰዎች ሊያምኑ ያልቻሉበትን ሁኔታ ለይቶ ማወቅ ስላቃታቸው ነበር::

1፥11 *ንጉሡ ሌላ የአምሳ አለቃ ... ላከ፤* ምንም እንኳን አካዝያስ አስደንጋጩን የእግዚአብሔርን ኀይል ቢያይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ላለመቀበል ልቡን አደነደነ::

ፈጽማ በላች::
13ስለዚህም ንጉሡ ሦስተኛውን የአምሳ
አለቃ ከአምሳ ሰዎቹ ጋር ላከ:: ይህም
ሦስተኛው የአምሳ አለቃ ወጥቶ፣ በኤልያስ
ፊት በጒልበቱ ተንበርክኮ እንዲህ ሲል
ለመነ፤ "አንተ የእግዚአብሔር ሰው፤ እባክህ
የእኔና የእነዚህ የአምሳዎቹ አገልጋዮችህ
ነፍስ በፊትህ የከበረች ትሁን:: 14እነሆ፤ እሳት
ከሰማይ ወርዳ፣ የፊተኞቹን ሁለት አምሳ
አለቆችና ሰዎቻቸውን ሁሉ በላች፤ አሁን
ግን ሕይወቴ በፊትህ የከበረች ትሁን::"
15የእግዚአብሔርም መልአክ ኤልያስን፣
"አብረኸው ውረድ፤ ደግሞም አትፍራው"
አለው:: ስለዚህ ኤልያስ ተነሣ፤ አብሮትም
ወደ ንጉሡ ወረደ::
16ንጉሡንም፣ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
'ለመሆኑ የአቃሮንን አምላክ ብዔልዜቡልን
ስለራስህ ለመጠየቅ መልእክተኞች የላክኸው
በእስራኤል አምላክ ስለ ሌለ ነውን? ይህን
በማድረግህም ከተኛህበት ዐልጋ ፈጽሞ አት
ነሣም፤ በእርግጥ ትሞታለህ'" ብሎ ነገ
ረው:: 17ስለዚህ አካዝያስ ኤልያስ እንደ
ተናገረው እንደ እግዚአብሔር ቃል ሞተ::
አካዝያስ ወንድ ልጅ ስላልነበረው፣ የኢ
ዮሣፍጥ ልጅ ኢዮራም በይሁዳ በነገሠ በሁ
ለተኛው ዓመት ወንድሙ ኢዮራም በእግሩ
ተተክቶ ነገሠ:: 18ሌላው አካዝያስ በዘመኑ
ያከናወናቸውና የፈጸማቸው ሥራዎች ሁሉ
በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ የተጻፉ አይደ
ሉምን?

## ኤልያስ ወደ ሰማይ ዐረገ

2 እግዚአብሔር ኤልያስን በዐውሎ ነፋስ
ወደ ሰማይ የሚወስድበት ጊዜ ሲደ
ርስ፣ ኤልያስና ኤልሳዕ ከጌልገላ ተነሥተው
ይጓዙ ነበር:: 2ኤልያስም ኤልሳዕን፣ "እግዚ
አብሔር እኔን ወደ ቤቴል ልኮኛልና አንተ
በዚሁ ቈይ" አለው::
ኤልሳዕ ግን፣ "ሕያው፣ እግዚአብሔርን፣
በሕያው ነፍስህም እምላለሁ ካንተ አልለ
ይም" አለው፤ ስለዚህ አብረው ወደ ቤቴል
ወረዱ::
3በቤቴል የነበሩ የነቢያት ማኅበር ወደ
ኤልሳዕ ወጥተው፣ "እግዚአብሔር፣ ጌታህን
ኤልያስን ዛሬ ከአንተ ነጥሎ እንደሚወስ
ደው አውቀሃልን?" አሉት::
ኤልሳዕም፣ "አዎን ዐውቄአለሁ፤ እናንተ
ግን ዝም በሉ" አለ::
4ከዚያም ኤልያስ፣ "ኤልሳዕ ሆይ፤ እግ
ዚአብሔር እኔን ወደ ኢያሪኮ ልኮኛልና
አንተ በዚሁ ቈይ" አለው::
እርሱም፣ "ሕያው እግዚአብሔርን፣ በሕ
ያው ነፍስህም እምላለሁ፤ ከአንተ አልለይም"
ሲል መለሰ:: ስለዚህ አብረው ወደ ኢያሪኮ
ሄዱ::
5በኢያሪኮ የነበሩትም የነቢያት ማኅበር
ወደ ኤልሳዕ ወጥተው፣ "ለመሆኑ እግዚአ
ብሔር ፣ ጌታህን ኤልያስን ዛሬ ከአንተ
ነጥሎ እንደሚወስደው ዐውቀሃልን?" አሉት::
እርሱም፣ "አዎን ዐውቄአለሁ፤ እናንተ
ግን ዝም በሉ" ሲል መለሰ::
6ከዚያም ኤልያስ፣ "እግዚአብሔር እኔን
ወደ ዮርዳኖስ ልኮኛልና አንተ እዚሁ ቈይ"
አለው::
እርሱም፣ "ሕያው እግዚአብሔርን፣ በሕ
ያው ነፍስህም እምላለሁ፤ ከአንተ አልለ
ይም"ሲል መለሰ:: ስለዚህ ሁለቱም አብረው
ሄዱ::
7ከነቢያትም ማኅበር አምሳው ሄደው፣
ኤልያስና ኤልሳዕ ከቆሙበት ከዮርዳኖስ
ትይዩ ራቅ ብለው ቆሙ:: 8ኤልያስም ካባ
ውን አውልቆ ጠቀለለውና ውሃውን መታበት፤
ከዚያም ውሃው ግራና ቀኝ ተከፈለ፤ ሁለቱም
በደረቅ ምድር ተሻገሩ::
9ከተሻገሩ በኋላም ኤልያስ ኤልሳዕን፤
"ከአንተ ከመወሰዴ በፊት ምን ላድርግልህ
እንደምትፈልግ ንገረኝ" አለው::
ኤልሳዕም፣ "መንፈስህ በዕጥፍ እንዲ
ያድርብኝ እለምንሃለሁ" ብሎ መለሰ::

1፥13 ምዝ72፥14
1፥15 ቍ3፤ኢሳ 51፥12፤57፥11፤ ኤር1፥17፤ሕዝ2፥6
1፥16 ቍ2፡4
1፥17 2ነገ3፥1፤ 8፥15፡16፤ኤር 20፥6፤28፥17
2፥1 ቍ11፤ዘፍ 5፥24፤ዘዳ11፥30፤ 1ነገ19፥11፡16፡21፤2 ነገ4፥38፤ኢሳ5፥28፤ 66፥15፤ኤር4፥13፤ ናሆ1፥3
2፥2 ቍ6፤ሩት 1፥16
2፥3 1ሳሙ10፥5
2፥4 ኢሱ3፥16
2፥5 ቍ3
2፥6 ቍ2፤ኢሱ 3፥15፤ሩት1፥16
2፥8 ቍ14፤ዘፀ14፥ 21፡22፡29፤1ነገ19፥19
2፥9 ዘኁ11፥17፤ ዘዳ21፥17

1፥13 *በኤልያስ ፊት በጒልበቱ ተንበርክኮ፤* በሦስተኛው ጊዜ የተላከው የአምሳ አለቃ፣ ኤልያስ የእግዚአብሔር ቃል መልእክተኛ መሆኑን ስለ ተረዳ፣ ለሕይወቱ በመፍራት በትሕትና ተንበርክኮ ጠየቀ::

1፥15 *የእግዚአብሔርም መልአክ ኤልያስን፤* የቍ 3 ማብ ይመ::

1፥17 *እንደ እግዚአብሔር ቃል አካዝያስ ሞተ፤* አካዝያስ ፊቱን ከእስራኤል አምላክ ወደ ጣዖት እምልኮ ዘወር ስላደረገ በመጨረሻ ተቀጣ፤ አካዝያስ ራሱን ለማዳን ቢሞክርም የእግዚ አብሔር ቃል የታመነና የማይሻር መሆኑ ታየ:: ኢዮራም፣ የአካዝያስ ታናሽ ወንድም ነው (3፥1፤ 1ነገ 22፥51 ይመ):: *የኢ ዮሣፍጥ ልጅ ኢዮራም...በሁለተኛው ዓመት፤* ኢዮራምና አባቱ ኢዮሣፍጥ የገዙት በአንድ ዘመን ነበር፤ ይህም በ853-848 ዓ.ቅ.ክ ነው (የ8፥16 ማብ ይመ):: እዚህ ላይ የተጠቀሰው በጋራ የገዙበትን ሁለተኛ ዓመት ነው:: የኢዮሣፍጥ ዐሥራ ስምንተኛው የንግሥና ዓመት (3፥1)፣ ኢዮራም በሞግዚትነት በጋራ ከገዛበት ሁለተኛው ዓመት ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ይህም በ852 ዓ.ቅ.ክ ነበር::

1፥18 *የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ 14፥19 ማብ ይመ::

2፥1 *ጌልገላ፤* በዮርዳኖስ ሸለቆ ያለው ሳይሆን (ኢሱ 4፥19)፣ ከቤቴል በስተሰሜን ምዕራብ ዐሥራ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ በሚገኘው በተራራማው በኤፍሬም አገር ያለው ነው::

2፥2 *ካንተ አልለይም፤* የኤልያስ አገልግሎት የሚያበቃበት ጊዜ እንደ ደረሰና መሄጃውም እንደ ተቃረበ ኤልሳዕ ዐውቆአል (ቍ 5):: ስለዚህ እግዚአብሔር እስኪወስደው ድረስ ላለመለየት ወሰነ፤ ለኤልያስና ለኤልያስ አገልግሎት ራሱን ሙሉ በሙሉ የሰጠበት ፍቅር አልተለወጠም ነበር (ቍ 9፡1ነገ 19፥21 ይመ)::

2፥3 *የነቢያት ማኅበር፤* የ1ነገ 20፥35 ማብ ይመ:: ቃል በቃል ሲወሰድ፣ "የነቢያት ልጆች" ማለት ነው፤ የነቢያት ልጆች ተብለው የተጠሩትም በሥጋ ከነቢያት የተወለዱ ማለት ሳይሆን በታዋቂ ነቢያት ሥር ያሉ ነቢያት ማለት ነው:: በኤልያስና በኤልሳዕ ዘመን የነቢያት ማኅበር እዚህ በቤቴል፣ በኢያሪኮና (ቍ5) በጌልገላ (4፥38) ነበር:: ኤልያስ በእግዚአብሔር አመራር ለመጨረሻ ስንብት መጀመሪያ ወደ ጌልገላ (ቍ1)፣ ከዚያም ወደ ቤቴልና (ቍ2) ወደ ኢያሪኮ (ቍ4) ሄደ::

2፥7 *አምሳው፤* ኤልያስና ኤልሳዕ የዮርዳኖስን ወንዝ ከፍለው የተሻገሩበትን ታምራት የሚመሰክሩ ሰዎች ናቸው::

2፥8 *ኤልያስም ካባውን አውልቆ ... ውሃውን መታበት፤* ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ይዞ የኤርትራን ባሕር ከፍሎ ለመሻገር በትሩን ሲጠቀም (ዘፀ 14፥16፡21፡26)፣ ኤልያስ መጐናጸፊያውን ተጠቅሞአል::

2፥9 *መንፈስህ በዕጥፍ እንዲያድርብኝ፤* ኤልሳዕ በዚህ ስፍራ የጠየቀው የኤልያስን አገልግሎት ዕጥፍ ያህል ሊያገለግል ፈልጎ

10ኤልያስም፣ "አስቸጋሪ ነገር ጠይቀሃል፤
ይሁን እንጂ እኔ ከአንተ ስወሰድ ብታየኝ፣
እንዳልከው ይሆንልሃል፤ ያለበለዚያ ግን አይ
ሆንም" አለው።
11እያዘገሙም ሲነጋገሩ ሳሉ፣ የእሳት
ሠረገላና የእሳት ፈረሶች ድንገት በመካከላ
ቸው ገብተው ሁለቱን ለዩአቸው፤ ኤልያስም
በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ዐረገ። 12ኤልሳዕም
ይህን አይቶ፣ "አባቴ! አባቴ! የእስራኤል
ሠረገሎችና ፈረሰኞች!" ብሎ ጮኸ፤ ዳግ
መኛም ኤልያስን አላየውም፤ ከዚያም የገዛ
ልብሱን ይዞ ከሁለት ቦታ ቀደደ። 13እር
ሱም ከኤልያስ የወደቀውን ካባ አንሥቶ፣ ተመ
ልሶም በዮርዳኖስ ወንዝ ዳር ቆመ። 14ከኤ
ልያስ፣ የወደቀውንም ካባ ይዞ ውሃውን
መታና፣ "የኤልያስ አምላክ እግዚአብሔር
ወዴት ነው?" አለ። ውሃውን ሲመታውም
በግራና በቀኝ ተከፍሎለት ተሻገረ። 15ከኢያ
ሪኮም መጥተው ይህን ያዩ የነበሩት የነቢያት
ወገኖች፣ "የኤልያስ መንፈስ በኤልሳዕ ላይ
ዐርፎአል" አሉ፤ ሊያገኙትም ሄደው በፊቱ
ወደ መሬት ዝቅ ብለው እጅ ነሡ። 16ከዚ
ያም፣ "እነሆ እኛ አገልጋዮችህ እዚህ አምሳ
ጠንካራ ሰዎች አሉን፤ ምናልባትም የእግዚ
አብሔር መንፈስ ጌታህን አንሥቶ ከአ
ንዱ ተራራ ላይ አስቀምጦት ወይም ከአንዱ
ሸለቆ አግብቶት ይሆናልና እስቲ ሄደው
ይፈልጉት" አሉት። ኤልሳዕም፣ "አይሆንም፤
አትላኳቸው" አለ።

2፥11 ቍ 1፤ዘፍ 5፥24፤2ነገ6፥17፤ መዝ68፥17፤104፥3፡4፤ኢሳ66፥15፤ ዕን3፥8፤ዘካ6፥1
2፥12 ዘፍ37፥29፤ 2ነገ6፥17፤13፥14
2፥14 ቍ 8፤1ነገ 19፥19
2፥15 ዘኍ11፥17፤ 1ሳሙ10፥5
2፥16 1ነገ18፥12፤ ሐሥ8፥39
2፥17 መሳ3፥25
2፥21 ዘፀ15፥25፤ 2ነገ4፥41፤6፥6
2፥22 ዘፀ15፥25
2፥23 ዘፀ22፥28፤ 2ዜና30፥10፤36፥16፤ ኢዮ19፥18፤መዝ 31፥18

17አይሆንም ለማለት ዕፍረት እስኪሰማው
ድረስ ግድ አሉት፤ ስለዚህ፣ "በሉ እንግዲ
ያው ላኳቸው" አለ። እነርሱም አምሳ ሰዎች
ላኩ፤ ሰዎቹም ሦስት ቀን ሙሉ ፈልገው
ሳያገኙት ቀሩ። 18በኢያሪኮ ቈይቶ ወደ
ነበረው ወደ ኤልሳዕ በተመለሱም ጊዜ፣
"ቀድሞውንስ ቢሆን አትሂዱ ብያችሁ አል
ነበረምን?" አላቸው።

### የውሃው መፈወስ

19የከተማዪቱም ሰዎች ኤልሳዕን፣ "እነሆ
ጌታችን፤ እንደምታያት ይህች ከተማ ለኑሮ
የተመቸች ናት፤ ይሁን እንጂ ውሃው መጥፎ
ሲሆን ምድሪቱም ፍሬ የማትሰጥ ናት"
አሉት።
20እርሱም፣ "እስቲ በአዲስ ማሰሮ ጨው
ጨምራችሁ አምጡልኝ" አለ፤ እንዳለውም
አመጡለት። 21ከዚያም ወደ ውሃው ምንጭ
ሄዶ ጨው ጣለበትና "እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ 'ይህን ውሃ ፈውሸዋለሁ፤ ከእንግዲህ
ወዲያ ለሞት ምክንያት አይሆንም፤ ምድሪ
ቱንም ፍሬ እንዳትሰጥ አያደርጋትም' አለ።"
22ኤልሳዕ እንደ ተናገረውም ውሃው እስከዛሬ
ድረስ የተፈወሰ ነው።

### በኤልሳዕ ላይ አፌዙበት

23ኤልሳዕም ከዚያ ተነሥቶ ወደ ቤቴል
ወጣ፤ በመንገድ ላይ ሲሄድ ሳለም ልጆች
ከከተማ ወጥተው፣ "አንተ መላጣ፤ ውጣ!

አልነበረም፤ ነገር ግን ለበኵር ልጅ የሚሆነውን የውርስ ሕግ በማሰብ የኤልያስን አገልግሎት ለመቀጠል ነው (ዘዳ 21፥17 እና ማብ ይመ)።

2፥10 *አስቸጋሪ ነገር*፡ ተተኪው ይሆን ዘንድ ኤልሳዕን እንዲቀባ ለኤልያስ ቢነገረውም (1ነገ 19፥16፡19-21)፣ ይህ ጉዳይ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ላይ ብቻ መወሰኑን ኤልያስ የሰጠው መልስ ያመለክታል። *ብታየኝ ... ይሆንልሃል፤ ያለዚያ ግን አይሆንም*፤ ኤልሳዕ ለጠየቀው ጥያቄ መልሱ ኤልያስ ሲወሰድ በማየት ወይም ባለማየት ላይ የሚወሰን ቢሆንም፣ ፈጻሚው ግን እግዚአብሔር ነው።

2፥11፤ ኤልያስ ልክ እንደ ሄኖክ (የዘፍ 5፥22-24 ማብ ይመ) ሳይሞት ወደ ሰማይ ተወሰደ። ክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ በምድር የሚገኙ አማኞችም ሳይሞቱ በእግዚአብሔር ወደ ሰማይ ይወሰዳሉ (1ቆሮ 15፥51፤ 1ተሰ 4፥7)። *የእሳት ሠረገላና የእሳት ፈረሶች*፤ የእግዚአብሔር ሰማያዊ ሰራዊት፣ የሙሴን አገልግሎት ይደገፉ እንደነበር ሁሉ (ዘፀ 15፥1-10 ይመ) የኤልያስን አገልግሎት በመደገፍ አብሮ በመሥራት ይሳተፉ ነበር፤ በዚህ ስፍራ ኤልያስ ወደ ሰማይ ሲወሰድና ሲያጅቡት ኤልሳዕ የማየት እድል ገጥሞታል (ከ6፥17 ጋር ያነጻጽሩ)።

2፥12 *የእስራኤል ሠረገሎችና ፈረሰኞች*፤ ኤልሳዕ፣ ኤልያስ የሕዝቡ እውነተኛ ጥንካሬ እንደ ሆነ በሚገባ ገልጾአል። ጣዖትን ከሚያመልከው ከእስራኤል ንጉሥ ይልቅ ኤልያስ የእግዚአብሔር ወኪል ነበር። ይህንኑ የመሰለ አገላለጽ ስለ ኤልሳዕም በመጨረሻ ተነግሮአል (13፥14)።

2፥13 *ካባ አንሥቶ* የቍ 8 ማብ ይመ። የኤልያስን ካባ ኤልሳዕ መወሰዱ የአገልግሎት ተተኪ መሆኑን ያመለክታል (1ነገ 19፥19 ይመ)።

2፥14 *ውሃውን ሲመታውም በግራና በቀኝ ተከፍሎለት*፤ ቍ8 ይመ። ኤልሳዕ፣ የኤልያስ ተተኪ መሆኑን ለማጽደቅ፣ የኤልያስን አገልግሎት ልዩ ያደረገው መለኮታዊ ኀይሉ በኤልሳዕም እንደሚሠራ እግዚአብሔር አረጋገጠለት። የሙሴ ተተኪ የሆነው ኢያሱ ዮርዳኖስን እንደ ተሻገረ፣ የኤልያስ ተተኪ ይሆነው ኤልሳዕም ዮርዳኖስን ተሻግሮአል። ኤልሳዕ ማለት "አምላክ ያድናል" ሲሆን፣ "ኢያሱ" ማለት ደግሞ "እግዚአብሔር ያድናል" ማለት ነው፤ ስለዚህ "ኤልሳዕ" ና "ኢያሱ" ተመሳሳይ ትርጕም አላቸው።

2፥15 *በፊቱ ወደ መሬት ለጥ ብለው እጅ ነሡ*፤ ኤልሳዕ፣ የኤልያስ ተተኪ መሆኑን መቀበላቸውን ያመለክታል። ጣዖት አምላኪ የሆነ መንግሥት ባለበት ዘመን ኤልሳዕ የእግዚአብሔር ወኪል ሆነ።

2፥16 *ምናልባትም የእግዚአብሔር መንፈስ ጌታህን አንሥቶ... አስቀምጦት*፤ ቀደም ባሉት ዓመታት አብድዩ ይህን የመሰለ ነገር ተናግሮአል (1ነገ 18፥12 ይመ)። *አትላኳቸው*፤ ሰዎቹ ኤልያስን ፍለጋ ቢወጡ ትርፉ ድካም ብቻ እንደ ሆነ ኤልሳዕ ዐውቆአል።

2፥17 *ላኳቸው*፤ የነቢያት ልጆች በፊት የሰጣቸውን መልስ ስላልተቀበሉ፣ አሁን ኤልያስን ፍለጋ እንዲወጡ ኤልሳዕ ፈቀደላቸው፤ በዚህም የተናገረው ቃል ሥልጣንና እውነተኛነት እንዲረጋገጥላቸው አደረገ።

2፥19 *ከተማዪቱ* ኢያሪኮን ማለት ነው (ቍ 18 ይመ)። *ይሁን እንጂ ውሃው መጥፎ ሲሆን ምድሪቱም ፍሬ የማትሰጥ ናት*፤ የኢያሪኮ ነዋሪዎች ከጳጳሴ ርግማን ነበረባቸው (ዘዳ 28፥15-18፤ ከዘፀ 23፥25-26፤ ዘሌ 26፥9፤ ዘዳ 28፥1-4 ጋር ያነጻጽሩ)፤ 1ነገ 16፥34፤ ኢያ 6፥26 ይመ።

2፥20 *በአዲስ ማሰሮ*፤ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚውል ዕቃ ያልረከሰ ንጹሕ መሆን ስላለበት ነው (ዘሌ 1፥3፡10፤ ዘኍ 19፥2፤ ዘዳ 21፥3፤ 1ሳሙ 6፥7 ይመ)። *ጨው ጨምራችሁ*፤ ኤልሳዕ ጨውን ሊጠቀም ያሰበው ከማጣፈጡና ምግብን እንዳይበላሽ ከማድረጉ አንጻር ሊሆን ይችላል፤ በደብልዋ ግን ጨውን በዚህ ስፍራ የተጠቀመው እግዚአብሔር ለኪዳኑ ታማኝ መሆኑን ለማመልከት ነው (የዘሌ 2፥13፤ ዘኍ 18፥19 ማብ እና 2ዜና 13፥5 ይመ)።

2፥21 *ይህን ውሃ ፈውሼዋለሁ፤* ከጨዉ የተነሣ ውሃው ስለ መፈወሱ የተገለጠ ነገር የለም፤ ቃሉ እዚህ ላይ በግልጽ መንገሩ እግዚአብሔር ራሱ ውሃውን እንደ ፈወሰው ያመለክታል። በዚህ ምሳሌያዊ መንገድ ኤልሳዕ፣ በአገልግሎቱ መጀመሪያ አለመታዘዛቸውን እልፍ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ቸርነትና የእግዚአብሔርን ጸጋ ሊያሳይ ችሎአል (13፥23 ይመ)።

2፥23 *ውጣ* ቤቴል የሰሜን ነገሥታት የጣዖት ማምለኪያ ማእከል ስትሆን (1ነገ 12፥29፤ አሞ 7፥13)፣ ኤልያስና ኤልሳዕ በብዛት የሚጎበኙት በሰማርያ ነበር፤ ምናልባትም መኖሪያቸው እዚያው ሰማርያ ሳይሆን አይቀርም (የ5፥3 ማብ ይመ)። የቤቴል ወጣቶች ኤልሳዕን "ውጣ" ያሉት፣ ምናልባት ወደ ሰማርያ ሄዶ ኤልያስ የጀመረውን የጣዖት አምልኮን የመቃወም አገልግሎቱን እንደሚቀጥል አስበው ይሆናል። በሌላ አንጻር ደግሞ "ውጣ" ሲሉ፣ በግልጽ ኤልያስ ወደ ሰማይ እንደ ወጣ አንተም ወደ ሰማይ ውጣ ማለታቸው ሊሆን ይችላል። *አንተ መላጣ* መመለጥ

አንተ መላጣ ውጣ!" እያሉ አፌዙበት::
[24]ኤልሳዕም ዘወር ብሎ ተመለከታቸውና
*በእግዚአብሔር* ስም ረገማቸው፤ ከዚያም
ሁለት እንስት ድቦች ከዱር ወጥተው ከል
ጆቹ አርባ ሁለቱን ሰባበሯቸው:: [25]እርሱም
ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ሄደ፤ ከዚያም ወደ
ሰማርያ ተመለሰ::

**ሞዓብ ዐመፀ**

**3** የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በነገሠ በዐሥራ
ስምንተኛው ዓመት፤ የአክአብ ልጅ ኢዮ
ራም በእስራኤል ላይ በሰማርያ ነገሠ ዐሥራ
ሁለት ዓመትም ገዛ:: [2]እርሱም *በእግዚአ
ብሔር* ፊት የተጠላ ክፉ ድርጊት ፈጸመ፤
ክፉ ድርጊቱ ግን አባትና እናቱ እንደ ፈጸ
ሙት ዐይነት አልነበረም፤ አባቱ ያሠራ
ውንም የበአልን ሐውልት አስወገደ:: [3]ነገር
ግን የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም እስራኤልን
ባሳተበት ኀጢአት ተያዘ፤ ከዚያም አልተ
ላቀቀም::
[4]በዚህ ጊዜ የሞዓብ ንጉሥ ሞሳ በግ ያረባ
ነበር፤ እርሱም መቶ ሺህ ጠቦትና የመቶ
ሺህ አውራ በግ ጠጕር ለእስራኤል ንጉሥ
ይገብር ነበር:: [5]አክዓብ ከሞተ በኋላ ግን
የሞዓብ ንጉሥ በእስራኤል ንጉሥ ላይ
ዐመፀ:: [6]ስለዚህ በዚያኑ ጊዜ ንጉሥ ኢዮራም
ከሰማርያ ተነሥቶ በመሄድ እስራኤልን ሁሉ
አሰባሰበ:: [7]ለይሁዳ ንጉሥ ለኢዮሣፍጥ፣ "የሞ
ዓብ ንጉሥ ስለ ዐመፀብኝ አብረኸኝ ትዘም
ታለህን?" ሲል መልእክት ላከበት::
እርሱም፣ "አዎን አብሬህ እዘምታለሁ፤

2፥24 ዘዳ4፥11፤ ዘጸ18፥19
2፥25 1ነገ18፥20
3፥1 2ነገ1፥17
3፥2 ዘፀ23፥24፤ 1ነገ15፥26፤16፥30
3፥3 1ነገ12፥30
3፥4 ዘፍ19፥37፤ 2ነገ1፥1፤ዕዝ 7፥17፤ኢሳ16፥1
3፥5 2ነገ1፥1
3፥7 1ነገ22፥4
3፥9 1ነገ22፥47
3፥11 ዘፍ20፥7፤ 25፥22፤1ነገ19፥ 16፤22፥5
3፥12 ዘኁ11፥17

እኔ እንደ አንተው ነኝ፤ ሕዝቤ እንደ ሕዝ
ብህ፤ ፈረሶቼም እንደ ፈረሶችህ ናቸው" በማ
ለት መለሰለት::
[8]ኢዮሣፍጥም፣ "የምንዘምተው በየትኛው
መንገድ ነው" ብሎ ጠየቀው፤
ኢዮራምም "በኤዶም ምድረ በዳ አልፈን
ነው" ሲል መለሰለት::
[9]ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ ከይሁዳ ንጉ
ሥና ከኤዶም ንጉሥ ጋር ለመዝመት ተነሣ::
ሰባት ቀን ከዞሩም በኋላ ለሰራዊቱም ሆነ
ለእንስሶቻቸው የተረፈ ውሃ አልነበረም::
[10]የእስራኤልም ንጉሥ፣ "ወዮ! *እግዚአ
ብሔር* እኛን ሦስት ነገሥታት የጠራን ለሞ
ዓብ አሳልፎ ሊሰጠን ነውን?" አለ::
[11]ኢዮሣፍጥ ግን፣ "በእርሱ አማካይነት
*እግዚአብሔርን* ለመጠየቅ እንድንችል፣ *የእግዚ
አብሔር* ነቢይ እዚህ የለምን?" በማለት ጠየቀ::
ከእስራኤል ንጉሥ የጦር አለቆችም አንዱ፣
"ቀድሞ የኤልያስን እጅ ያስታጥብ የነበረው[ሀ]
የሣፋጥ ልጅ ኤልሳዕ በዚህ አለ" ብሎ መለ
ሰለት::
[12]ኢዮሣፍጥም፣ "*የእግዚአብሔር* ቃል ከእ
ርሱ ዘንድ ይገኛል" አለ፤ ስለዚህ የእስራ
ኤል ንጉሥ፣ ኢዮሣፍጥና የኤዶም ንጉሥ
አብረው ወደ እርሱ ወረዱ::
[13]ኤልሳዕም የእስራኤልን ንጉሥ፤ "ከአንተ
ጋር ምን የሚያገናኘን ጉዳይ አለና መጣህ፤
አሁን የአባትህና የእናትህ ነቢያት ወዳሉበት
ሂድ" አለው::

[ሀ]11 የኤልያስ አገልጋይ ነው::

በጥንት አይሁዶች ዘንድ የተለመደ አልነበረም:: የሚያድግ፣ ረጅም ጠጕር የኀይልና የጥንካሬ ምልክት ነው ይባልም ነበር (2ሳሙ 14፥26 እና ማብ ይመ):: ስለዚህ የቤቴል ወጣቶች ኤልሳዕን "መላጣ" ብለው መሰደባቸው የከተማዪቱ ሕዝብ በአጠቃላይ የእግዚአብሔርን ወኪል አለመቀበላቸውን ያመለክታል (ከኢሳ 3፥17፡24 ጋር ያነጻጽሩ)::

2፥24 *በእግዚአብሔር ስም ረገማቸው፤* የኤልሳዕ የርግማን ቃል በዘሌ 26፥21-22 ላይ ያለው የኪዳን ርግማን ይመስላል:: ውጤቱም አገሪቱ በእምቢተኝነትና በጣዖት አምልኮ ብትጸና ፍርድ እንደሚጠብቃት ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአል (2ዜና 36፥16 ይመ):: ስለዚህ ኤልሳዕ በመጀመሪያ የፈጸማቸው ድርጊቶች ለቀጣይ አገልግሎቱ ጠቋሚዎች ናቸው፤ እነዚህም ቃሉን ለሚቀበሉ የእግዚአብሔር የኪዳን በረከት እንደሚመጣላቸው (ቍ 19-22)፣ በእርሱ ላይ ለሚያምፁ ግን የኪዳኑ ርግማን እንደሚወርድባቸው ያመለክታሉ::

3፥1 *የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በነገሠ በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት፣ የአክዓብ ልጅ ኢዮራም ... ነገሠ፤* የ1፥17 ማብ ይመ:: *ዐሥራ ሁለት ዓመት፤* ከ852-841 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው::

3፥2 *አባቱና እናቱ እንደፈጸሙት ዐይነት አልነበረም፤* አክዓብና (የ1ነገ 16፥30-34 ማብ ይመ) ኤልዛቤል (1ነገ 18፥4፡ 19፥1-2፡21፥7-15 ይመ) እንደፈጸሙት አልነበረም:: *አባቱ ያሠራውንም የበአልን ሐውልት፤* አክዓብ በሰማርያ ለኤልዛቤል በሠራላት ቤተ መቅደስ ውስጥ (የ1ነገ 14፥23 ማብ ይመ)፣ አክዓብ ሠርቶ ያቆመው በወንድ ምስል የተሠራውን ጣዖት የሚያመለክት ነው (1ነገ 16፥32-33 ይመ):: በ10፥27 እንደምንመለከተው ይህ ሐውልት ምናልባትም ተመልሶ በኤልዛቤል ሳይተከል አልቀረም::

3፥3 *የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም እስራኤልን ባሳተበት ኀጢአት፤* የ1ነገ 14፥16 ማብ ይመ፤ 1ነገ 12፡26-33 ይመ::

3፥4 *የሞዓብ ንጉሥ ሞሳ፤* የ1፥1 ማብ ይመ:: *መቶ ሺህ ጠቦትና የመቶ ሺህ አውራ በግ ጠጕር፤* እስራኤል ከሞዓባውያን በዓመት የምታገኘው ትልቅ ግብር ነው (ኢሳ 16፥1 ይመ):: እ.ኤ.አ በ1868 የተገኘ በድንጋይ ላይ የተጻፈ ጽሑፍ የሞዓብ ንጉሥ ሞሳ ለእስራኤል የሚከፍለውን ዓመታዊ ግብር አልከፍልም በማለት ማመፁን ያመለክታል::

3፥5 *የሞዓብ ንጉሥ ... ዐመፀ፤* የ1፥1 ማብ ይመ::

3፥7 *የሞዓብ ንጉሥ ስለ ዐመፀብኝ አብረኸኝ ትዘምታለህን?* ኢዮራም ሞዓብን መውጋት የፈለገው ከበስተ ጀርባው ስለ ነበር (ቍ 8)፣ ሰራዊቱ በይሁዳ ማቋረጥ ነበረበት:: *እኔ እንደ አንተው ነኝ፤ ሕዝቤ እንደ ሕዝብህ፣ ፈረሶቼም እንደ ፈረሶችህ ናቸው፤* 1ነገ 22፥4 ይመ:: ኢዮሣፍጥ ቀደም ብሎ ከሰሜን ነገሥታት ከአክዓብና (2ዜና 18፥1፤19፥1-2) ከአካዝያስ (2ዜና 20፥35-37) ጋር በመተባበሩ በእግዚአብሔር ነቢያት ተገሥጾ ነበር:: ይሁን እንጂ በዚህ ስፍራ ሞዓብን ለመውጋት እንደ ገና ከኢዮራም ጋር ተስማማ:: ምናልባትም እየተጠናከረ የመጣውን የሞዓብን ኃይልና በይሁዳም ላይ የተቃጣውን ጥቃት በራሱ ላይ እንደሚደርስ ስለፈራ (2ዜና 20 ይመ)፣ እንዲሁም ኢዮራም ከአባቶቹ ይልቅ ለርሱ የተሻለ ሆኖ ስላገኘው ነው (ቍ 2 ይመ)::

3፥8 *በኤዶም ምድረ በዳ፤* ይህ መንገድ የእስራኤልንና የይሁዳን ሰራዊት ከሙት ባሕር በስተደቡብ ወዳለው አቅጣጫ ይወስዳቸዋል፤ ይህም የሞዓብን ሰሜናዊ ድንበር ለመከበብና ምናልባት ከበስተጀርባ ሊመጣባቸው የሚችለውን የደማስቆ ሶርያውያንን ጥቃት ሊከላከልላቸው ይችላል:: በይሁዳ ተገዥነት ሥር የነበሩት ኤዶማውያን የእስራኤል ሰራዊት በግዛታቸው ሲያቋርጥ የሚቋቋሙበት ኀይል አልነበራቸውም::

3፥9 *የኤዶም ንጉሥ፤* በዚህ ስፍራ ንጉሥ ተብሎ ቢጠራም፣ በኢዮሣፍጥ የተሾመ ገዥ ነበር (8፥20፤ 1ነገ 22፥47 ይመ)::

3፥11 *የእግዚአብሔር ነቢይ በዚህ የለምን?* 1ነገ 22፥7 ይመ:: ያቀዱት ዕቅድ ሳይሳካ ሲቀር ሦስቱ ነገሥታት የእግዚአብሔርን ቃል ፈለጉ (ቍ 12):: *የሣፋጥ ልጅ ኤልሳዕ በዚህ አለ፤* ኤልያስ፣ ለኢዮሣፍጥ ልጅ ለኢዮራም አባቱ ከሞተ በኋላ ደብዳቤ እንደ ላከለት በ2ዜና 21፥12-15፤ ላይ ተጠቅሶአል፤ ኤልሳዕም በዚህ በዘመቻው ወቅት ሸምግሎ የነበረውን ኤልያስን በመወከል ከሰራዊቱ ጋር ሳይዘምት አልቀረም:: ይህ ታሪክ የተገለጸው ኤልሳዕ የኤልያስ ተተኪ ከሆነና የአገልግሎቱን ለየት ያለ ባሕርይ ከሚያሳዩት ሁለት ክሥተቶች በኋላ ነው::

3፥13 *የአባትህና የእናትህ ነቢያት ወዳሉበት ሂድ፤* 1ነገ 22፥6 ይመ::

የእስራኤልም ንጉሥ መልሶ፣ “ይህማ
አይሆንም፤ በሞዓብ እጅ አሳልፎ ሊሰጠን
እኛን ሦስት ነገሥታት አንድ ላይ የጠራን
*እግዚአብሔር* ነው” አለ።
[14]ኤልሳዕን እንዲህ አለው፤ “የማገለግለው
ሕያው *እግዚአብሔርን*፣ የይሁዳን ንጉሥ
ኢዮሣፍጥን ባላከብር ኖሮ፣ አንተን አላይም፣
እንዲያውም ጉዳዩ አልልህም ነበር። [15]አሁንም
ባለ በገና አምጡልኝ።”
ባለ በገናው በሚደረድርበት ጊዜ፣ *የእግዚአ
ብሔር* እጅ በኤልሳዕ ላይ መጣ፤ [16]እንዲህም
አለ፤ “*እግዚአብሔር* የሚለው እንዲህ ነው፤
‘በዚህ ሸለቆ ብዙ ጒድጓዶች ቈፍሩ። [17]*እግ
ዚአብሔር* እንዲህ ይላልና፤ ‘ነፋስም ሆነ
ዝናብ አታዩም፤ ሸለቆው ግን በውሃ ይሞ
ላል፤ እናንተ፣ የቀንድ ከብቶቻችሁና ሌሎች
እንስሶቻችሁም ትጠጣላችሁ። [18]ይህ *በእግዚአ
ብሔር* ፊት ቀላል ነገር ነው። ሞዓብንም በእ
ጃችሁ አሳልፎ ይሰጣችኋል።
[19]የተመሸጉትን ከተሞችና ያማሩትን
ከተሞቻቸውን ሁሉ ድል ታደርጋላችሁ።
ውብ ዛፎቻቸውን ሁሉ ትቈርጣላችሁ፤ ምን
ጮቻቸውን በሙሉ ትደፍናላችሁ፤ መልካ
ሙንም ዕርሻ በድንጋይ ታበላሹታላችሁ።”
[20]በማግስቱ *መሥዋዕት* በሚቀርብበት
ጊዜ፣ እነሆ፤ ከኤዶም በኩል ውሃ እየጐረፈ
መጣ፤ ምድሪቱም ውሃ በውሃ ሆነች።
[21]በዚህ ጊዜ ነገሥታቱ ሊወጓቸው መም
ጣታቸውን ሞዓባውያን ሁሉ ሰምተው ነበ
ርና፣ ልጅም ሆነ ሽማግሌ፣ *መሣሪያ* መያዝ
የቻለ ሁሉ ተጠርቶ በመውጣት በጠረፉ
ላይ ይጠባበቅ ጀመር። [22]በማግስቱ ጠዋት
ማልደው ሲነሡም፣ ፀሓይ በውሃው ላይ
ታንጸባርቅ ነበር። ማዶ ላሉት ሞዓባውያንም፣
ውሃው እንደ ደም ቀልቶ ታያቸው። [23]ስለ
ዚህ፣ “ያ እኮ ደም ነው! ያለ ጥርጥር
ነገሥታቱ እርስ በርስ ተዋግተው ተራር
ደዋል። እንግዲህ ሞዓብ ወደ ምርኮህ
ዙር!” ተባባሉ።
[24]ሞዓባውያን ወደ እስራኤል ሰፈር ሲወ
ጡም፣ እስራኤላውያን ተነሥተው ወጓቸው፤
ሞዓባውያንም ከፊታቸው ሸሹ። ከዚያም እስ
ራኤላውያን ምድሪቱን ወረው ሞዓባውያንን
ፈጇቸው። [25]ከተሞቹን ደመሰሱ፤ መልካ
ሙን የዕርሻ መሬት ሁሉ እስኪሸፍነው
ድረስ፤ እያንዳንዱ ሰው አንዳንድ ድንጋይ
ጣለበት፤ ምንጮቹን በሙሉ ደፈኑ፤ ጥሩ
ጥሩውንም ዛፍ ሁሉ ቈርጠው ጣሉ። ቂር
ሐራሴት ብቻ ከነድንጋይዋ ቀርታ ነበር፤
እርሷም ቢሆን ባለ ወንጭፉ ሰራዊት ከቦ
አደጋ ጣለባት።
[26]የሞዓባውያን ንጉሥ በጦርነቱ መሸነፉን
እንዳወቀ፣ ሰይፍ የታጠቁ ሰባት መቶ ሰዎች
ይዞ የኤዶም ንጉሥ ወዳለበት ጥሶ ለመግ
ባት ሞከረ፤ ነገር ግን አልተሳካላቸውም።
[27]ከዚያም በእግሩ ተተክቶ የሚነግሠውን፣
የበኵር ልጁን ወስዶ በከተማዪቱ ቅጥር
ላይ የሚቃጠል *መሥዋዕት* አድርጎ አቀረ
በው። በእስራኤልም ላይ ታላቅ ቍጣ ሆነ፤
ከዚያም ለቀው ወደ ገዛ ምድራቸው ተመ
ለሱ።

### የመበለቲቱ ዘይት

**4** የነቢያት ማኅበር ወገን ከሆነው የአንደ
ኛው ሚስት፣ “አገልጋይህ ባሌ ሞቶአል፤
እርሱም *እግዚአብሔርን* የሚፈራ ሰው እንደ
ነበር አንተ ታውቃለህ፤ አሁን ግን ባለ ዕዳ
ሁለት ወንዶች ልጆቼን ባሪያ አድርጎ ሊወ
ስዳቸው *መጥቶአል*” ስትል ወደ ኤልሳዕ
ጮኸች።
[2]ኤልሳዕም፣ “ታዲያ እኔ ምን እንዳደርግ
ልሽ ትፈልጊያለሽ? በቤትሽ ምን እንዳለ ንገ

3፥15 1ሳሙ10፥5፤ ኤር15፥17፤ሕዝ1፥3
3፥17 መዝ107፥35፤ኢሳ12፥3፤32፥2፤35፥6፤41፥18፤65፥13
3፥18 ዘፍ18፥14፤ 2ነገ20፥10፤ኢሳ 49፥6፤ኤር32፥17፡27፤ ማር10፥27
3፥20 ዘፀ17፥6፤ 29፥41
3፥25 ኢሳ15፥1፤ 16፥7፤ኤር48፥31፡36
3፥27 ዘዳ12፥31፤ 2ነገ16፥3፤21፥6፤ 2ዜና28፥3፤መዝ 106፥38፤ኤር19፥45፤ ሚክ6፥7
4፥1 ዘፀ22፥26፤ ዘሌ25፥3943፤1ሳሙ 10፥5፤ነህ5፥35፤ ኢዮ22፥6፤24፥9
4፥2 1ነገ17፥12

3፥14 *የይሁዳን ንጉሥ ኢዮሣፍጥን ባላከብር ኖሮ፣ አንተን አላይም እንዲያውም ጉዳዩ አልልህም ነበር*፤ ከኢዮሣፍጥ የተነሣ እንጂ ኢዮራም የእግዚአብሔርን ቃል በረከት ሊካፈል አይገባውም ነበር።

3፥15 *ባለ በገና አምጡልኝ*፤ ኤልሳዕ በተረጋጋ መንፈስ የእግዚአብሔርን ቃል መቀበል እንዲችል ነው።

3፥16 *በዚህ ሸለቆ*፤ የእስራኤል ሰራዊት በስተ ምሥራቅ ባለው በሞዓብ ኰረብታና በስተ ምዕራብ ባለው በይሁዳ ምድር መካከል ከሙት ባሕር በስተደቡብ በሚገኘው ሰፊ ሸለቆ ሰፍሮ ነበር።

3፥17 *በውሃ ይሞላል*፤ የእግዚአብሔር ቃል ተስፋንና ምሪትን የሚሰጥ ነው። እግዚአብሔር በቸርነቱ ለሕዝቡ የሚያስፈልገውን ይሰጣል፤ ስለዚህ ሕዝቡ ቃሉን በእምነትና በመታዘዝ ሊቀበል ይገባዋል (ቍ 16)።

*3፥19*፤ የእስራኤልና የይሁዳ ሰራዊት ዐመፀኛዪቱን ሞዓብን ይደመስሳሉ።

3፥20 *መሥዋዕት በሚቀርብበት ጊዜ*፤ ዘፀ29፥38-39፤ዘኍ 8፥3-4 ይመ። *ከኤዶም በኩል ውሃ እየጐረፈ መጣ*፤ ከኤዶምያስ ኰረብቶች የወረደው ጐርፍ ደረቅ የሆነውንና ወደ ሙት ባሕር የተዘረጋውን ሸለቆ አራሰው የቍ16 ማብ ይመ?።

3፥23 *ነገሥታቱ እርስ በርስ ተዋግተው ተራርደዋል*፤ ሞዓባውያን እንደ ደም የቀላ ውሃ መመልከታቸው ቀድሞ ጠበኛ በነበሩት ነገሥታትና አሁን ኅብረት በፈጠሩት መካከል ጠብ እንደተፈጠረ እንዲያስቡ አደረጋቸው።

3፥25 *ጥሩ ጥሩውንም ዛፍ ሁሉ ቈርጠው ጣሉ*፤ ልምላሜን ለማጥፋት ጠላት ሆን ብሎ የሚከተለው መመሪያ ሲሆን፣ በመሠረቱ እንዲህ ማድረግ አይፈቀድም ነበር (ዘዳ 20፥19 ይመ)። *ቂርሐራሴት*፤ የሞዓብ ዋና ከተማ ሲሆን (ኢሳ 16፥7፡11፤ ኤር 48፥31፡36)፣ ከሙት ባሕር በስተ ምሥራቅ 18 ኪሎ ሜትር ከአርኖን ወንዝ በስተ ደቡብ 24 ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኘው ዛሬ ኬራክ ተብሎ የሚጠራው ነው።

3፥26 *የኤዶም ንጉሥ ወዳለበት ጥሶ ለመግባት*፤ የሞዓብ ንጉሥ ከመጨነቁ የተነሣ ኤዶምን በእስራኤልና በይሁዳ ሰራዊት ላይ ለማሳመፅ ያደረገው ሙከራ ነበር።

3፥27 *የበኵር ልጁን ወስዶ በከተማዪቱ ቅጥር ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ አቀረበው*፤ የሞዓብ ንጉሥ ሞሳ፣ አማልክት በዚያ ቀውጢ ወቅት እንዲረዱት፣ ዐልጋ ወራሽ የሆነውን ትልቁን ልጁን የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ (16፥3፤ ኤር 7፥31 ይመ) ለሞዓባውያን አምላክ ለካሞሽ (1ነገ 11፥7፤ ዘኍ 21፥29፤ ኤር 48፥46) አቀረበው። *በእስራኤል ላይ ታላቅ ቍጣ ሆነ*፤ በዕብራይስጥ እግዚአብሔር በቍጣው ሲጐበኝ የሚል ትርጓሜ አለው። ድሉ ሙሉ በሙሉ በእስራኤላውያን እጅ ሊገባ በተቃረበበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር በአክዓብ ሥርወ መንግሥት ላይ ደስ አለመሰኘቱን የሚያመለክት ፍርድ ስላዩ የእስራኤል ነገሥታት ዘመቻውን ትተው ወደ ኋላ የተመለሱ ይመስላል።

4፥1 *የነቢያት ማኅበር*፤ የ2፥3 እና የ1ነገ 20፥35 ማብ ይመ። *ሁለት ወንድ ልጆቼን ባሪያ አድርጎ ሊወስዳቸው*፤ ዕዳን ለመክፈል ለባለ ዕዳ የጒልበት ሥራ በመሥራት መገዛት በሙሴ ሕግ የተፈቀደ ነበር (ዘፀ 21፥1-2፤ ዘሌ 25፥39-41፤ ዘዳ 15፥1-11 ይመ)። ሕጉ ለተወሰነ ጊዜ የመደበኛ ዕዳ ከፋዮች ከቅጥር ሠራተኞች እኩል እንዲቈጠሩ ቢያዝም፣ ባለዕዳዎች ዕዳ ከፋዮችን ያላግባብ ይጉዷቸው ነበር (ነህ 5፥5፡8፤ አሞ 2፥6፡8፥6)።

ሪኝ" አላት፡፡
እርሷም፣ "አገልጋይህ ከጥቂት ዘይት
በቀር በቤቷ ምንም ነገር የላትም" አለች፡፡
3ኤልሳዕም እንዲህ አላት፤ "እንግዲያው
ሂጂና ከጎረቤቶችሽ ሁሉ ጥቂት ሳይሆን
ብዙ ማድጋ ተዋሺ፤ 4ገብተሽም መዝጊያ
ውን ባንቺና በልጆችሽ ላይ የኋሊት ዝጊው፤
ዘይቱንም በማድጋዎቹ ሁሉ ጨምሪ፤ እያ
ንዳንዱ ማድጋ ሲሞላም ወደ አንድ በኩል
አኑሪው፡፡"
5ስለዚህ ትታው ሄዳ መዝጊያውን በራ
ሷና በልጆቿ ላይ የኋሊት ዘጋችው፡፡ ማድጎ
ቹን እያቀረቡላትም እርሷ ትሞላ ጀመር፡፡
6ማድጋዎቹ ሁሉ ከሞሉ በኋላ ልጇን፣ "ሌላ
ማድጋ አምጣ" አለችው፡፡
እርሱ ግን፣ "ምንም የቀረ ማድጋ የለም "
ሲል መለሰላት፡፡ ከዚያም ዘይቱ መውረዱን
አቆመ፡፡
7እርሷም ሄዳ ይህንኑ ለእግዚአብሔር ሰው
ነገረችው፡፡ እርሱም፣ "ሄደሽ ዘይቱን በመ
ሸጥ ዕዳሽን ክፈይ፤ የተረፈውም ለአንቺና
ለልጆችሽ መተዳደሪያ ይሁን" አላት፡፡

## የሱነማዪቱ ልጅ ከሞት ተነሣ

8አንድ ቀን ኤልሳዕ ወደ ሱነም ሄደ፡፡
በዚያም አንዲት ሀብታም ሴት ነበረች፤
እርስዋም ምግብ እንዲበላ አጥብቃ ለመነ
ችው፤ በዚያም ባለፈ ቍጥር ምግብ ለመብ
ላት ወደ ቤቷ ይገባ ነበር። 9ሴቲቱም ባልዋን
እንዲህ አለችው፤ "ይህ አዘውትሮ በደጃችን
የሚያልፍ ሰው፣ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው
መሆኑን ዐውቃለሁ፤ 10ስለዚህ በሰገነቱ ላይ
አንዲት ትንሽ ክፍል ቤት ሠርተን ዐልጋና
ጠረጴዛ፣ ወንበርና ፋኖስ እናስገባለን፤ ከዚ
ያም ወደ እኛ በሚመጣበት ጊዜ ሁሉ ማረ
ፊያ ትሆነዋለች፡፡"
11አንድ ቀን ኤልሳዕ ወደዚያው መጥቶ
ወደ ማረፊያ ክፍሉ በመውጣት ጋደም አለ፡፡
12አገልጋዩን ግያዝንም፣ "ሱነማዪቱን ጥራት"
አለው፤ በጠራትም ጊዜ መጥታ በፊቱ
ቆመች፡፡ 13ኤልሳዕም፣ "'ለእኛ ስትይ በጣም
ተቸግረሻል፣ ምን እንዲደረግልሽ ትፈልጊ
አለሽ? ለንጉሡ ወይስ ለሰራዊቱ አዛዥ የምን
ነግርልሽ ጉዳይ አለን?' ብለህ ጠይቃት"
አለው፡፡
ሴቲቱም መልሳ፣ "እኔ እኮ የምኖረው
በገዛ ወገኖቼ መካከል ነው" አለችው፡፡
14ኤልሳዕም፣ "ታዲያ ምን ይደረግላት"
ሲል ጠየቀ፡፡
ግያዝም፣ "ልጅ እኮ የላትም፤ ባሏም ሽምግ
ሎአል" አለ፡፡
15ኤልሳዕም፣ "በል እንግዲያው ጥራት"
አለው፤ እርሱም ጠርቶአት መጥታ እበራፉ
ላይ ቆመች፡፡ 16ኤልሳዕም የዛሬ ዓመት በዚሁ
ጊዜ ወንድ ልጅ ትታቀፊያለሽ" አላት፤
እርስዋም፣ "አይደለም ጌታዬ፣ አንተ
የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ኋላ አገልጋይህን
መዋሸት እንዳይሆንብህ?" አለችው፡፡
17ሴትዮዋም ፀነሰች፤ ኤልሳዕ እንደ ነገራ
ትም በተባለው ጊዜ ወንድ ልጅ ወለደች፡፡
18ሕፃኑ አደገ፤ አንድ ቀንም አባቱ ከዐጫ
ጆች ጋር ወደ ነበረበት ቦታ ሄደ፡፡ 19አባ
ቱንም፣ "ራሴን! ራሴን!" አለው፡፡
አባቱም አገልጋዩን፣ "ተሸክመህ ወደ
እናቱ አድርሰው" አለው፡፡
20አገልጋዩም አንሥቶ እናቱ ዘንድ አደ
ረሰው፤ ልጁም እስከ እኩለ ቀን ድረስ በእ
ናቱ ጭን ላይ ተቀመጠ፤ ከዚያም ሞተ፡፡
21ወደ ላይ ወጥታም በእግዚአብሔር ሰው ዐልጋ
ላይ አስተኛችው፤ በሩንም ዘግታበት ወጣች፡፡
22ከዚያም ባሏን ጠርታ፣ "ወደ እግዚአብሔር
ሰው በፍጥነት ደርሼ እንድመለስ አንድ አገ
ልጋይና አንድ አህያ ላክልኝ" አለችው፡፡
23ባሏም፣ "ዛሬ ወደ እርሱ መሄድ ለምን
አስፈለገሽ? መባቻ ወይም ሰንበት አይደል"

4፥7 1ነገ12፥22
4፥8 ኢሱ19፥18
4፥10 ማቴ 10፥41፤ሮሜ12፥13
4፥12 2ነገ8፥1
4፥16 ዘፍ18፥10
4፥18 ሩት2፥3
4፥21 ቍ32
4፥23 ዘኁ10፥10፤ 1ዜና23፥31፤መዝ81፥3

4፥4 *መዝጊያውን ባንቺና በልጆችሽ ላይ የኋሊት ዝጊው፤* ይህ ታምር ለሰው ሁሉ እንዲታይ ሳይሆን፣ ሴትዮዋ በግሏ እግዚአብሔር የሚያደርግላትን ቸርነትና ምሕረት የምታይበት ነው (ከመዝ 68፥5 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ የእግዚአብሔር ነቢይ የተናገረውን ቃል ለማመንና ለመታዘዝ ወደ ኋላ አላለችም፡፡

4፥6፤ የእግዚአብሔር በረከት ከሴትዮዋ እምነትና መታዘዝ በላይ ነበር፡፡

4፥8 *ሱነም፤* የ1ነገ 1፥3 ማብ ይመ፡፡ ከመጊዶን በስተ ምሥራቅ ከኢይዝራኤል ሸለቆ ከፍ ብሎ 11 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ስፍራ ነው፡፡

4፥9 *ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው፤* ኤልሳዕ ልዩ በሆነ መንገድ ለእግዚአብሔር ሥራ የተለየ ሰው እንደ ሆነ ሴትዮዋ ተረድታለች፡፡ በብሉይ ኪዳን በየትም ስፍራ ለነቢይ፣ "ቅዱስ" የሚል ተጨማሪ ቅጽል ተጽፎ አይገኝም፡፡

4፥10 *ወደ እኛ በሚመጣበት ጊዜ ሁሉ ማረፊያ ትሆነዋለች፤* በምታደርገው መስተንግዶ ሴትዮዋ የኤልሳዕ አገልግሎት ውጤታማ እንዲሆን ረድታለች፡፡

4፥12 *ግያዝ ለመጀመሪያ ጊዜ ስሙ በዚህ ስፍራ ተጠቅሶአል፤* ባሕርዩ ከኤልሳዕ ፈጽሞ የተለየ ቢሆንም፣ ኤልሳዕ ኤልያስን እንዳ ገለገለው ግያዝ ኤልሳዕን አገልግሎታል (5፥19-27፡6፥15 ይመ)፡፡

4፥13 *የምኖረው በገዛ ወገኖቼ መካከል ነው፤* ይህች ሱነማዊት በቤተሰቧና በነገዷ መካከል ስለምትኖር ችግር አልነበረ ባትም፤ ስለዚህም ከከፍተኛ የመንግሥት ባለ ሥልጣኖች እርዳታ እንዲደረግላት የምትፈልግ አልነበረችም፡፡

4፥14 *ልጅ እኮ የላትም፤ ባልዋም ሽምግሎአል፤* እጅግ ተስፋ የሚያስቈርጥ ጉዳይ ነው፤ የቤተሰቡን ስም የሚያስጠራ ባለመኖሩ፣ የቤተሰቡ ንብረት ባልና ሚስቱ ከሞቱ በኋላ ለሌሎች ይተላለፋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለዚች ወጣት ሴት የሸመገለው ባሏ ከሞተ በኋላ የሚንከባከባትና የሚጠብቃት ሰው አይኖርም፤ ምክንያቱም ልጆች ለመበለቶች ዋስትና ስለሆኑ ለዚህ አልታደለችም ማለት ነው (8፥1-6 እና የ1ነገ 17፥22 ማብ ይመ)፡፡

4፥16 *የዛሬ ዓመት በዚሁ ጊዜ፤* ዘፍ 17፥21፡18፥14 ይመ፡፡ *ኋላ አገልጋይህን መዋሸት እንዳይሆንብህ? አንተ የእግዚአብሔር ሰው፤* የሴትዮዋ መልስ ልጅ ለመውለድ የነበራትን ጽኑ ምኞትና ኤልሳዕም የተናገረው ቃል ባይፈጸም ስሜቷ እንዳይጐዳ መፍራቷን ያመለክታል፡፡

4፥17 *ኤልሳዕ እንደ ነገራትም፤* የኤልሳዕ ቃል በመፈጸሙ እውነተኛነቱ ተረጋገጠ፤ ሴትዮዋም ወንድ ልጅ በመውለዷ የእግዚብሔር ቸርነት ተገለጠላት፡፡

4፥20 *ልጁም ... ሞተ፤* የእግዚአብሔር ቃል እውነተኛነትና የአምላክ ቸርነት ታላቅነት ማስረጃ የሆነው ልጅ፣ የሴትዮዋን እምነት ለመፈተን በሞት ተወሰደ፡፡ በዚህ ከባድ ኀዘን ውስጥ ሴትዮዋ በወሰደችው ርምጃ እምነቷ የቱን ያህል ታላቅ እንደ ሆነ አሳየች፡፡

4፥21 *በእግዚአብሔር ሰው ዐልጋ ላይ አስተኛችው፤* በዚህ መንገድ የልጇን ሞት ከሌሎቹ ቤተሰቦቿ ሰውራ፣ ልጅ እንደምትወልድ የእግዚአብሔርን ቃል የነገራት ነቢዩን ፍለጋ ወጣች፡፡

4፥23 *ዛሬ ወደ እርሱ መሄድ ለምን አስፈለገሽ፤* የጥያቄው

አላት::
እርሷም፣ "ምንም አይደል፤ ልሂድ" አለ
ችው::
24ከዚያም አህያውን ጭና አገልጋይዋን፣
"ቶሎ ቶሎ ንዳ፤ እኔ ካልነገርኩህ በቀር
ለእኔ ብለህ አታዝግም" አለችው:: 25ስለዚህ
ተነሥታ የእግዚአብሔር ሰው ወዳለበት ወደ
ቀርሜሎስ ተራራ ሄደች::
የእግዚአብሔር ሰው በሩቁ ሲያያት አገልጋ
ዩን ግያዝን እንዲህ አለው፤ "ሱነማዪቱን
አየሃት፤ ያቻትና! 26በል ሩጠህ ሂድና፣ ምነው
ደኅና አይደለሽምን? ባልሽ ደኅና አይደለ
ምን? ልጅሽስ ደህና አይደለምን? ብለህ ጠይ
ቃት::"
እርሷ፣ "ሁሉ ነገር ደህና ነው" አለች
27የእግዚአብሔር ሰው ወዳለበት ተራራ ስት
ደርስም እግሩ ላይ ተጠመጠመች፤ ግያዝ
ሊያስለቅቃት ሲመጣ፣ የእግዚአብሔር ሰው
ግን፣ "እጅግ አዝናለችና ተዋት! እግዚአ
ብሔር ይህን ለምን ከእኔ እንደሰወረውና
እንዳልነገረኝ አልገባኝም" አለ::
28እርሷም፣ "ጌታዬ፤ ለመሆኑ እኔ ልጅ
እንድትሰጠኝ ጠይቄህ ነበርን? 'አጕል
ተስፋ እንዳትሰጠኝ' አላልሁህምን?" አለችው::
29ኤልሳዕም ግያዝን፣ "እንግዲህ ወገብህን
ታጠቅ፤ በትሬን ያዝና ሩጥ፤ መንገድ ላይ
ሰው ብታገኝ ሰላም አትበል፤ ማንም ሰው
ሰላም ቢልህ መልስ አትስጥ፤ በትሬንም
በልጁ ፊት ላይ አድርግ" አለው::
30የልጁ እናት ግን፣ "ሕያው እግዚአብሔ
ርን ፤ በሕያው ነፍስህም እምላለሁ፣ ፈጽሞ
ትቼህ አልሄድም" አለችው፤ ስለዚህ ተነሥቶ
ተከተላት::
31ግያዝም ቀድሞአቸው ሄዶ በትሩን በልጁ
ፊት ላይ አደረገ፤ ነገር ግን ድምፅም፣ ምላ
ሽም አልነበረም:: ስለዚህ ግያዝ ወደ ኤል
ሳዕ ተመልሶ፣ "ልጁ አልነቃም" አለው::
32ኤልሳዕ ወደ ቤት ሲገባም ልጁ ሞቶ
በዐልጋው ላይ ተጋድሞ ነበር:: 33ወደ ውስ
ጥም ገባ፤ ከዚያም በሩን በራሱና በልጁ ላይ
ዘግቶ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ::
34በዐልጋው ላይ ወጥቶም በልጁ ላይ ተጋ
ደመና አፉን በአፉ፣ ዐይኑን በዐይኑ፣ እጁን
በእጁ ላይ አደረገ:: ሙሉ በሙሉ እንደተ
ዘረጋበትም፣ የልጁ ሰውነት መሞቅ ጀመረ::
35ኤልሳዕም ተነሥቶ በቤቱ ውስጥ ወዲያና
ወዲህ ከሄደ በኋላ ወደ ዐልጋው ወጥቶ እን
ደገና በልጁ ላይ ሙሉ ለሙሉ ተዘረጋበት፤
ልጁም ሰባት ጊዜ አስነጠሰውና ዐይኖቹን
ከፈተ::
36ኤልሳዕም ግያዝን ጠርቶ፣ "ሱነማዪቱን
ጥራት፤" አለው፤ እርሱም ጠራት:: እንደ
መጣችም፣ "በይ ልጅሽን ውሰጂ" አላት::
37እርሷም ገብታ በእግሩ ላይ ወደቀች፤ በም
ድርም ላይ ተደፋች፤ ልጇንም ይዛ ወጣች::

**መርዛሙ ወጥ**

38ኤልሳዕ ወደ ጌልገላ ተመለሰ፤ በዚያም
አገር ራብ ነበረ:: የነቢያት ማኅበር በፊቱ
ተቀምጠው ሳለ አገልጋዩን፣ "ትልቁን
ምንቸት ጣድና ለእነዚህ ሰዎች ወጥ ሥራ
ላቸው" አለው::
39ከእነርሱም አንዱ ቅጠላ ቅጠል ለማም
ጣት ወደ ሜዳ ወጥቶ፤ ዱር በቀል ሐረግ
አገኘ፤ ከሐረጉም ላይ የቅል ፍሬ ለቅሞ
በልብሱ ሙሉ ይዞ ተመለሰና ቈራርጦ
በወጡ ምንቸት ውስጥ ጨመረው፤ ምን
እንደሆነ ግን ማንም አላወቀም:: 40ሰዎቹ
እንዲመገቡትም ወጡ ወጣ፤ ገና እንደ
ቀመሱትም፣ "የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፤ በም
ንቸቱ ውስጥ የሚገድል መርዝ አለ!" ብለው
ጮኹ፤ ሊመገቡትም አልቻሉም:: 41ኤልሳ
ዕም፣ "እስቲ ዱቄት አምጡልኝ" አለ:: ያን
ንም በምንቸቱ ውስጥ ጨምሮ፣ "እንዲመገ
ቡት ለሰዎቹ አቅርቡላቸው" አለ:: በምን
ቸቱም ውስጥ ጒዳት የሚያስከትል ነገር
አልተገኘም::

4፥25 1ነገ18፥20
4፥27 1ሳሙ1፥15
4፥29 ዘፀ4፥2፤1ነገ
18፥46
4፥32 ቍ21
4፥33 1ነገ17፥20፤
ማቴ6፥6
4፥34 1ነገ17፥21፤
ሐሥ20፥10
4፥35 ኢሱ6፥15፤
2ነገ8፥5
4፥36 ዕብ11፥35
4፥38 ዘሌ26፥26፤
2ነገ2፥1፤8፥1
4፥41 ዘፀ15፥25፤
2ነገ2፥21

አቀራረብ ሴትዮዋ ወደ ኤልሳዕ መሄዷዋ የተለመደ ቢሆንም በዚህ
ወቅት ግን ኤልሳዕን ለመጐብኘት መነሣቷ ያልተለመደ ነበር::
*መባቻ ወይም ሰንበት አይደል፤* መባቻና ሰንበት ሥራን ባለመሥ
ራት የሚከበሩ በዓላት ናቸው (የዘኍ2፥3 ማብ፤ዘፀ16፥23:20:9-10፤
1ሳሙ20፥5፤ዘሌ23፥3 ይመ)::
4፥26 *ምነው ደኅና አይደለሽምን?* ሴትዮዋ ልጅ እንደም
ትወልድ ለነገራት ለነቢዩ ካልሆነ በቀር ሐዘኗን ለማንም መግለፅ
አልፈለገችም ነበር::
4፥27፤ ኤልሳዕ የሴትዮዋ ልጅ መሞቱን ገና አላወቀም
ነበር::
4፥28 *'አጕል ተስፋ እንዳትሰጠኝ' አላልሁህምን?* ሴቲቱ
አጥብቃ የተከራከረችው እግዚአብሔር እንደ ቸርነቱና እንደተና
ገረው ቃል  የሰጣትን ልጅ ለምን እንደወሰደባት ለመረዳት ነበር::
4፥29 *በትሬንም በልጁ ፊት ላይ አድርግ፤* በትሩ በልጁ
ፊት ከተቀመጠ እግዚአብሔር ልጁን ወደ ሕይወት እንደሚመ
ልሰው ኤልሳዕ ማመኑን ያመለክታል:: ይህ ማለት ኤልሳዕ በበ
ትሩ ላይ የአስማት ኀይል አለ ብሎ ማመኑን የሚያመለክት ሳይ
ሆን፣ በትሩ የእርሱን መገኘት የሚወክልና የእግዚአብሔር መለኮ
ታዊ ኀይል ምልክት እንደ ሆነ ማመኑን ነው (የ2፥8 ማብ ይመ፤
ከዘፀ14፥16፤ ከሐሥ 19፥12 ጋር ያነጻጽሩ)::
4፥30 *ፈጽሞ ትቼህ አልሄድም፤* ሴትዮዋ የግያዝ መላክ
በቂ ነው ብላ ስላላመነችች፣ ኤልሳዕ ራሱ ሱነም ድረስ አብሮአት
እንዲሄድ አጥብቃ ለመነችው::
4፥33 *በሩን በራሱና በልጁ ላይ ዘግቶ ወደ እግዚአብሔር
ጸለየ፤* ኤልያስ እንዳደረገው (1ነገ17፥20-22 ይመ)፣ ኤልሳዕም
የሞተው ልጅ ሕይወት እንዲመለስ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ::
4፥34 *በልጁ ላይ ተጋደመ፤* የ1ነገ 17፥21 ማብ ይመ::
ምናልባት ኤልሳዕ ከዚህ በፊት ያደረገውን ኤልያስ የሚያውቅ
ይመስላል::
4፥37 *በእግሩ ላይ ወደቀች፤ በምድርም ላይ ተደፋች፤* ሱነ
ማዊቱ ሴት እግዚአብሔር በቸርነቱ ያደረገላትን በመረዳት፣ የሰ
ራፕታዋ መበለት በቃሏ የገለጸችውን ምስጋና (1ነገ 17፥24
ይመ)፣ በጸጥታ እግዚአብሔር በተጠቀመበት ኤልሳዕ ፊት ገለጸች::
4፥38 *በዚያም አገር ራብ ነበረ፤* በ8፥1 ላይ የተጠቀሰው ራብ
ሊሆን ይችላል:: ራብ ኪዳናዊ ርግማንና (ዘሌ26፥19-20:26፤ዘዳ
28፥18:23-24፤ 1ነገ8፥36-37 ይመ) ሕዝቡም ኪዳናዊ ግዴታውን
ባለመፈጸሙ የሚመጣ የእግዚአብሔር ቍጣ መግለጫ ነው::
*የነቢያት ማኅበር፤* የ2፥3 ማብ ይመ::
4፥39 *ዱር በቀል ሐረግ ... ቅል፤* ምን ዐይነት ተክል እንደ
ሆነ አልታወቀም::
4፥41 *ዱቄት፤* ዱቄቱ በራሱ ወጡ እንዲጣፍጥና እንዲበላ
አያደርገውም (2፥21 እና ማብ ይመ)፤ ነገር ግን ሌሎች ከኪ
ዳናዊ ርግማን የተነሣ ሲሠቃዩ ለኪዳኑ ታማኝ ለሆኑ እግዚአብሔር
ያደረገው ታምራትና ልዩ በረከት የመጣበት መንገድ ነው::

## አንድ መቶ ሰው ተመገበ

42አንድ ሰው ከበኵራቱ ፍሬ የተጋገረ
ሃያ የገብስ ሙልሙልና ጥቂት የእሸት ዛላ
ዎች በአቍማዳ ይዞ ከበአልሻሊሻ ወደ እግዚ
አብሔር ሰው መጣ። ኤልሳዕም አገልጋዩን፣
"ሰዎቹ እንዲበሉት ስጣቸው" አለው። 43አገ
ልጋዩም፣ "ይህን እንዴት አድርጌ ለመቶ
ሰው አቀርባለሁ?" ሲል ጠየቀ፤
ኤልሳዕ ግን፣ "እንዲበሉት ለሰዎቹ ስጣ
ቸው፤ *እግዚአብሔር*፣ 'በልተው ይተርፋቸዋል'
ይላልና አለው። 44ከዚያም አቀረበላቸው፤ *እግዚአ
ብሔር* እንደ ተናገረውም በልተው ተረፋቸው።

## ንዕማን ከለምጽ ተፈወሰ

5በዚህ ጊዜ ንዕማን የሶርያ ንጉሥ ጦር
አዛዥ ነበረ፤ *እግዚአብሔር* በዚህ ሰው
አማካይነት፣ ሶርያ ድልን እንድትጐናጸፍ
ስላደረጋት በጌታው ዘንድ ታላቅና የተከ
በረ ሰው ነበር። ጀግና ወታደር ቢሆንም
ነገር ግን ለምጽ^ ወጥቶበት ነበር።
2አደጋ ጣዮች ከሶርያ ወጥተው፣ ከእስራ
ኤል ምድር አንዲት ልጃገረድ ማረኩ፤ እር
ሷም የንዕማንን ሚስት ታገለግላት ነበር።
3እመቤቷንም፣ "ጌታዬ በሰማርያ ያለውን
ነቢይ ሄዶ ቢያገኘው እኮ ከዚህ ለምጹ ይፈ
ውሰው ነበር" አለቻት።
4ንዕማንም ወደ ጌታው ሄዶ ከእስራኤል
የመጣችው ልጃገረድ ያለችውን ነገረው።
5የሶርያም ንጉሥ፣ "በል እንግዲያው አሁኑኑ
ሂድ፤ እኔም ለእስራኤል ንጉሥ ደብዳቤ እጽፋ
ለሁ" አለው፤ ስለዚህ ንዕማን ዐሥር መክሊት*
ብር፣ ስድስት ሺህ ሰቅል** ወርቅና ዐሥር
ሙሉ ልብስ ይዞ ሄደ። 6ለእስራኤልም
ንጉሥ የያዘው ደብዳቤ፣ "ከአሠቃቂ የቆዳ
በሽታው እንድትፈውሰው ይህን ደብዳቤ
አስይዤ አገልጋዬን ንዕማንን ወዳንተ ልኬ
ዋለሁ" የሚል ነው።
7የእስራኤልም ንጉሥ ደብዳቤውን ወዲያው
እንደ አነበበ ልብሱን ቀዶ፣ "ከለምጽ እንድ
ፈውሰው ይህን ሰው ወደ እኔ መላኩ እኔ
ገድዬ ማዳን የምችል አምላክ ሆኜ ነውን?
እንግዲህ ጠብ ሲፈልገኝ እዩ!" አለ።
8የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ፣ የእስራኤል
ንጉሥ ልብሱን መቅደዱን በሰማ ጊዜ እን
ዲህ ሲል ላከበት፤ "ልብስህን ለምን ቀደ
ድህ? ሰውየው ወደ እኔ ይምጣ፤ ከዚያም
በእስራኤል ነቢይ መኖሩን ያውቃል።" 9ስለ
ዚህ ንዕማን በፈረሶቹና በሠረገሎቹ ሆኖ
በኤልሳዕ ቤት ደጃፍ ሲደርስ ቆመ። 10ኤል
ሳዕም፣ "ሂድና በዮርዳኖስ ሰባት ጊዜ ታጠብ፤
ሥጋህ ይፈወሳል፤ አንተም ትነጻለህ" ብሎ
እንዲነግረው መልእክተኛ ላከበት።
11ንዕማን ግን ተቈጥቶ እንዲህ በማለት
ሄደ፤ 'እኔ እኮ በእርግጥ ወደ እኔ መጥቶ
በመቆም የአምላኩን *የእግዚአብሔርን* ስም
የሚጠራ፣ በእጁም ዳሶ ከለምጽ በሽታዬ የሚ

^1 በዚህ ስፍራ እንዲሁም በቍጥር 3፡6፡7፡11 እና 12 ላይ የዕብራ ይስጡ ቃል ቆዳን የሚያጠቁ በሽታዎች ሁሉ የሚያሳይ ነው።
*5 340 ኪሎ ግራም ያህል ነው። **5 70 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

4፥42 1ሳሙ9፥4፡7፤ማቴ14፥17፤15፥36
4፥43 ማቴ14፥20፤ ሉቃ9፥13፤ዮሐ6፥12
5፥1 ዘፍ10፥22፤ ዘፀ4፥6፤ዘኁ12፥10፤ 2ሳሙ10፥19፤ሉቃ4፥27
5፥2 2ነገ6፥23፤13፥20፤24፥2
5፥3 ዘፍ20፥7
5፥5 ቍ 22፤ዘፍ 24፥53፤መሳ14፥12፤ 1ሳሙ9፥7
5፥7 ዘፍ30፥2፤ዘዳ 32፥39፤1ነገ20፥7፤ 2ነገ19፥14
5፥8 1ነገ22፥7
5፥10 ዘፍ33፥3፤ ዘሌ14፥7፤ዮሐ9፥7
5፥11 ዘፀ7፥19

4፥42 *ከበኵራቱ ፍሬ*፤ በሰሜኑ መንግሥት ያሉ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች የመከሩን በኵራት (ዘሌ 2፥14፡23፥15-17፤ ዘጸ 18፥3-5) በቤቴልና በዳን ላሉ ጣዖት አምላኪ ካህናት (1ነገ 12፥28-31 ይመ) ከማምጣት ይልቅ፣ ለኤልሳዕና አብረውት ላሉ ሰዎች የእህል ቍርባን አቀረቡላቸው (ቍ23 ይመ)። የኪዳን ባለቤት የሆነውን አምላካቸውን የሚወክለው ኤልሳዕ እንጂ ጣዖትን የሚያመልከው ንጉሥና ካህናቱ እንዳልሆኑ ተረዱ።

4፥43 *እግዚአብሔር ... ይላልና*፤ እንጀራው የተባዛው እግዚአብሔር በኤልሳዕ በኩል በተናገረው ቃል መሠረት እንጂ ሌላ ነገር በመሐል ጣልቃ ገብቶ አልነበረም (ከቍ41 ጋር ያነጻጽሩ፤ 2፥20 ይመ፤ ከማር 6፥35-43 ጋር ያነጻጽሩ)።

5፥1 *የሶርያ ንጉሥ*፤ ደማማዊ ቤን ሐዳድ ሊሆን ይችላል (የ8፥7፤ 13፥3፤1ነገ20፥1 ማብ ይመ)። *እግዚአብሔር ... ሶርያ ድልን እንድትጐናጸፍ ስላደረጋት*፤ በዚህ ስፍራ እንጂ በሌሎች ጽሑፎች ያልተገለጸ ነገር ግን ሶርያውያን በአሶራውያን ላይ በ853 ዓ.ቅ.ክ ከነበረው ከቃርቃር ጦርነት በኋላ ያገኙትን ድል ሊሆን ይችላል (የ1ነገ 22፥1 ማብ ይመ)። በተራኪው ሥነ መለኮታዊ አመለካከት ሦርያውያን ድል ሊቀዳጁ የቻሉት፣ የእስራኤል ብቻ ሳይሆን የነገሥታትንና የሕዝቦችን ዕጣ ፈንታ በሚወስነው በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር እንደሆነ ነው። (ሕዝ 30፥24፤ አሞ 2፥1-3፤ 9፥7 ይመ)።

5፥2 *አደጋ ጣዮች ከሶርያ*፤ በአክዓብ ዘመን እስራኤልና ሶርያውያን የሰላም ስምምነት ቢያደርጉም (1ነገ 20፥34 ይመ)፣ አክዓብ የሞተበትን ሬሞት ገለዓድን ለመቈጣጠር መጠነኛ የድንበር ግጭቶች በሁለቱ አገሮች መካከል ነበሩ (የ1ነገ22፥4 ማብ እና 1ነገ22፥35 ይመ)። *ከእስራኤል ምድር አንዲት ልጃገረድ*፤ በሰማርያ ካለው ከእስራኤል ንጉሥ ይልቅ፣ በሶርያውያን ተማርካ የነበረችው ይህች ልጅ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል በኤልሳዕ አማካይነት የሚሠራውን ኀይል ያወቀችና ቡተማረከበት በሶርያውያን መካከል ይህን እውነት ለመናገር ያለ ይሉኝታ የቆመች ነበረች።

5፥3 *በሰማርያ ያለውን ነቢይ*፤ በሰማርያ ይኖር የነበረውን ኤልሳዕን ለማመልከት ነው (ቍ 9፡2፥25፡6፥19 ይመ)።

5፥5 *ለእስራኤል ንጉሥ ደብዳቤ እጽፋለሁ*፤ መጠነኛ የሆኑ የድንበር ግጭቶች ቢከሠቱም፣ በሁለቱ መንግሥታት መካከል የነበረው የሰላም ስምምነት አልፈረሰም ነበር። በዚህ ጊዜ የነበረው የእስራኤል ንጉሥ ኢዮራም ነው (1፥17፤3፥1፤9፥24 ይመ)። *ዐሥር መክሊት ብር*፤ አማራጭ ትርጕሙን ይመ ሦስት መቶ አርባ ኪሎ ግራም ያህል ነው። የዚህን ብር፤ መጠን አምሪ የሰማርያን ተራራ ለመግዛት ከከፈለው ጋር በማወዳደር (1ነገ16፥24) የቱን ያህል ብዙ እንደ ነበር መገመት ይቻላል።

5፥6 *ከለምጹ እንድትፈውሰው*፤ የሶርያው ንጉሥ ቤን ሐዳድ፣ እስራኤላዊቱ ልጃገረድ የተናገረችለት ነቢይ በእስራኤል ንጉሥ ሥር እንዳለና በብዙ ስጦታም አገልግሎቱን ሊገዛ እንደሚችል ገምቷል። እንዲህ የገመተውም እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ከመገኘቱ የተነሣ ለሕዝቡ የሚሰጠውን የፈውስ በረከት በምድራዊ ሀብት ሊገዛ አስቦ ነው።

5፥7 *ጠብ ሲፈልገኝ እዩ*፣ ኢዮራም ደብዳቤውን ካነበበ በኋላ ሁኔታውን በማሰብ ቤንሐዳድ ጦርነት ሊያውጅበት ሰበብ መፈለጉን ገመተ። ይህም ንጉሡ ኢዮራም እግዚአብሔር በኤልሳዕ በኩል ያስቀመጠውን የማዳን ኀይል ማየት እስከማይችል ድረስ፣ ልቡን የሞላው ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ ሽኩቻ ብቻ እንደ ነበር ያመለክታል።

5፥8 *ልብስህን ለምን ቀደድህ*? ኢዮራም ስለ ፈራና (የ1ሳሙ 17፥1 ማብ ይመ) የእግዚአብሔርን ነቢይ ማማከር ስላልቻለ ኤልሳዕ ገሠፀው (በኢዮራምና በኤልሳዕ መካከል የነበረውን ውጥረት ለመረዳት 3፥13-14 ይመ)።

5፥9 *በፈረሶቹና በሠረገሎቹ*፤ በዚህ ሁሉ ዐጀብ የመጣው፣ ከክብሩ የተነሣ ፈውስ እንዲታዘዝለት ለማድረግ ነው።

5፥10 *በዮርዳኖስ ሰባት ጊዜ ታጠብ*፤ ትእዛዙ የሚያመለክተው ፈውስ የሚመጣው ከእስራኤል አምላክ ኀይል የተነሣና ንዕማንም የሚፈወሰው የእግዚአብሔርን ነቢይ ቃል የታዘዘ እንደ ሆነ ብቻ መሆኑን ነው። የሚፈውሰው ነቢዩ ራሱ አልነበረም። በምሥራቅ አገር ሃይማኖቶች የመታጠብ ሥርዓት ለመንጻት ይደረግ ነበር፤ ሰባት ቍጥርም የፍጹምነት ምልክት ነው። ስለዚህ በመታጠብና በተፈለገው ፈውስ መካከል ምንም ግንኙነት እንደ ሌለ ለማመልከት ንዕማን በዮርዳኖስ ወንዝ ድፍርስ ውሃ ውስጥ መታጠብ ነበረበት። ምናልባትም እስራኤላውያን እንዳደረጉት ሁሉ (ኢሱ 3፥4) ከእስራኤል አምላክ ፈውስን ለማግኘት በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል ማለፍ አስፈላጊ መሆኑን ለማመልከት ይሆናል።

5፥11 *በእጁ ዳሶ ከለምጽ በሽታዬ የሚፈውሰኝ*፤ ንዕማን የጠበቀው ነቢዩ በአስማት አሠራር እንደሚፈወሰው ነበር እንጂ

ፈውሰኝ መስሎኝ ነበር። 12ለዚህ ለዚህ የደ
ማስቆ ወንዞች አባናና ፋርፋር ከየትኞቹም
የእስራኤል ውሆች አይሻሉምን? ለመታጠብ
ለመታጠብማ በእነርሱ ታጥቤ መንጻት አል
ችልምን?" ስለዚህ በቍጣ ተመለሰ።
13የንዕማን አገልጋዮች ግን ወደ እርሱ
ቀርበው፣ "አባት ሆይ፤ ነቢዩ ከዚህ ከበድ
ያለ ነገር እንድታደርግ ቢነግርህ ኖሮ አታ
ደርገውም ነበርን? ታዲያ፣ 'ታጠብና ንጻ'
ቢልህ ምኑ አስቸገረህ?" አሉት። 14ስለዚህ
ንዕማን ወረደ፤ የእግዚአብሔር ሰው እንደነገረ
ውም በዮርዳኖስ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ
አለ፤ ሥጋውም እንደ ትንሽ ልጅ ሥጋ
ሆነ፤ ነጻም።
15ከዚያም ንዕማን ከጭፍሮቹ ሁሉ ጋር
ወደ እግዚአብሔር ሰው ተመልሶ ሄደ፤ በፊቱም
ቆሞ፣ "እነሆ በእስራኤል አገር እንጂ በዓለም
ሁሉ ሌላ አምላክ አለመኖሩን ተረድቻለሁ፤
ስለዚህ አሁንም ከአገልጋይህ ስጦታ እንድ
ትቀበል እለምንሃለሁ" አለው። 16ነቢዩም፣
"የማገለግለውን ሕያው *እግዚአብሔርን*፣ ምንም
ነገር አልቀበልም" ሲል መለሰ። ምንም እንኳ
ንዕማን አስጨንቆ ቢለምነውም አልተቀበ
ለም። 17ንዕማንም እንዲህ አለው፤ "ስጦታ
ውን የማትቀበል ከሆነ፣ ለማንኛውም አም
ላክ የሚቃጠል ወይም ሌላ መሥዋዕት ስለ
ማላቀርብ፣ ሁለት የበቅሎ ጭነት ዐፈር
እንድወስድ ትፈቅድልኝ ዘንድ እለምንሃ
ለሁ። 18ነገር ግን *እግዚአብሔር* ስለ አንድ
ነገር ብቻ አገልጋይህን ይቅር ይበለው፤
ይኸውም ጌታዬ ለመስገድ ወደ ሬሞን
ቤተ ጣዖት በሚገባበት ጊዜ ክንዴን ሲደ
ገፍ እኔም እንደ እርሱ በዚያ ብሰግድ፣
በሬሞን ቤተ ጣዖት በመስገዴ *እግዚአብሔር*
አገልጋይህን ይቅር ይበለው።"
19ኤልሳዕም፣ "በሰላም ሂድ" አለው።

5፥12 ምሳ14፥17፡ 29፥19፥11፡29፥11፤ ኢሳ8፥6
5፥13 2ነገ6፥21፤ 13፥14
5፥14 ዘፍ33፥3፤ ዘዐ4፥7፤ዘሌ14፥7፤ ኢሱ6፥15፤ ኢዮ33፥25
5፥15 ኢሱ2፥11፤ 4፥24፤1ሳሙ9፥7፤ 17፥46
5፥16 ቍ20፡26፤ ዘፍ14፥23፤ዳን5፥17
5፥17 ዘዐ20፥24
5፥18 2ነገ7፥2
5፥19 1ሳሙ1፥17፤ ሐሥ15፥33
5፥20 ዘዐ20፥7
5፥22 ቍ5፤ዘፍ 45፥22
5፥26 ቍ16፤ ኤር45፥5

ንዕማን ጥቂት ራቅ ብሎ እንደ ሄደ፣ 20የእ
ግዚአብሔር ሰው አገልጋይ ግያዝ፣ "ጌታዬ፣
ይህ ሶርያዊ ንዕማን ያመጣውን ባለመቀበል
በነጻ ሰደደው፤ ሕያው *እግዚአብሔርን*! ተከ
ትዬ ሄጄ ከእርሱ አንድ ነገር ማግኘት አለ
ብኝ" ብሎ አሰበ።
21ስለዚህ ግያዝ ንዕማንን ተከተለው፤ ንዕ
ማንም ግያዝ እየሮጠ ወደ እርሱ መምጣቱን
ባየ ጊዜ፣ ሊገናኘው ከሠረገላው ወርዶ፣
"ምነው፤ በደኅና መጣህን?" ሲል ጠየቀው።
22ግያዝም፣ "ሁሉም ደኅና ነው፤ ግን
ጌታዬ፣ 'ከነቢያት ማኅበር ሁለት ወጣቶች
ከኰረብታማው አገር ከኤፍሬም ወደ እኔ
አሁን በድንገት ስለመጡ፣ 'እባክህ አንድ
መክሊት* ብርና ሁለት ሙሉ ልብስ ስጣ
ቸው ብለህ ንገር' ብሎ ልኮኛል' አለው።
23ንዕማንም፣ "እባክህ ሁለት መክሊት
ውሰድ" በማለት ግያዝን አስጨንቆ ለመ
ነው። ከዚያም ሁለቱን መክሊት ብር፣ በሁ
ለት ከረጢት ውስጥ አስሮ ሁለት ሙሉ
ልብስ ጨምሮ ለሁለት አገልጋዮቹ አስያዘ፤
እነርሱም ያን ተሸክመው ከግያዝ ፊት ፊት
ሄዱ። 24ግያዝም ወደ ኰረብታው እንደ
ደረሰ፣ ዕቃዎቹን ከአገልጋዮቹ ተቀብሎ
በቤቱ ውስጥ አስቀመጠ፤ ሰዎቹንም አሰናብ
ቶአቸው ሄዱ። 25ከዚያም ገብቶ በጌታው
በኤልሳዕ ፊት ቆመ።
ኤልሳዕም፣ "ግያዝ ሆይ፤ የትነበርህ?"
ሲል ጠየቀው።
ግያዝም፣ "አገልጋይህ የትም አልሄደም"
ብሎ መለሰ።
26ኤልሳዕ ግን እንዲህ አለው፤ "ያ ሰው
ሊገናኝህ ከሠረገላው ሲወርድ መንፈሴ ከአ
ንተ ጋር አልሄደምን? እንዲያው ለመሆኑ
ጊዜው ገንዘብና ልብስ፣ የወይራ ዘይት ተከ

*22 34 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

የእግዚአብሔርን ቃል ተቀብሎ በመታዘዙ የእግዚአብሔር ኀይል እንደሚፈውሰው አልነበረም።

5፥12 *አባናና ፋርፋር*፤ አባና፣ ግሪኮች ወርቃማው ወንዝ ብለው የሚጠሩት ነው። ከሊባኖስ ተራሮች ተነሥቶ በደማስቆ ከተማ መሐል የሚፈሰው የዛሬው የባራዳ ወንዝ የቀድሞው አባና ነው። የፋርፋር ወንዝ ከደማስቆ በስተ ደቡብ ከሚገኘው ከኬብሮን ተራራ ተነሥቶ ወደ ምሥራቅ ይፈሳል።

5፥14 *ሥጋውም እንደ ትንሽ ልጅ ሥጋ ሆነ*፤ አዲስ እንደ ተወለደ ሕፃን ማለት ነው (ቍ15 እና ማብ ይመ)። የእግዚአብሔርን ቃል ሲታዘዝ፣ የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታ ተቀበ ለ። ንዕማን በዚህ ስፍራ የዐመፀኛይቱ እስራኤል ምሳሌ ሲሆን፣ የእግዚአብሔር በረከት በታማኝነትና በመታዘዝ መንገድ ብቻ እንደሚገኝም የሚያስረዳ ቋሚ ምስክር ነው። የኪዳኑ ሕዝብ በኪዳኑ ጸንተው በታማኝነት ካልቆሙ፣ ከኪዳኑ ውጪ የሆነውን ሕዝብ እግዚአብሔር በማስነሣት ቃሉን እንዲታዘዙ ያደርጋል (የ1ነገ17፥9-24 ማብ እና ማቴ8፥10-12፤ ሉቃ4፥27 ይመ)።

5፥15 *በእስራኤል አገር እንጂ፣ በዓለም ሁሉ ሌላ አምላክ አለመኖሩን ተረድቻለሁ*፤ ንዕማን የተናገረው የእምነት ቃል፣ አምላክ እግዚአብሔርና በኣል ነው ወይስ እግዚአብሔር ብቻ እያሉ የሚወላውሉትን እስራኤላውያንን የሚያሳፍር ነው (1ነገ 18፥21 ይመ)።

5፥16 *ምንም ነገር አልቀበልም*፤ የእግዚአብሔር ቃል በመናገሩ ኤልሳዕ የውለታ ስጦታን ለመቀበል አልፈለገም (ማቴ 10፥8 ይመ)። ንዕማን የተፈወሰው በእግዚአብሔር መለኮታዊ ኃይል እንጂ በኤልሳዕ ልዩ ችሎታ አልነበረም።

5፥17 *ሁለት የበቅሎ ጭነት ዐፈር እንድወስድ ትፈቅድልኝ ዘንድ እለምንሃለሁ*፤ በጥንቱ ዓለም አንድ አምላክ ባለበት አገር ዐፈር ላይ ብቻ ሊመለክ ይገባዋል ተብሎ ይታመን ነበር (ቍ15 ይመ)። ንዕማን ከእስራኤል ምድር ዐፈር ሊወስድ የፈለገው፣ በደማስቆ እግዚአብሔር የሚመለክበትን ስፍራ ለማ ዘጋጀት አስቦ ነው።

5፥18 *ጌታዬ*፤ የሶርያን ንጉሥ ቤን ሃዳድን ማለቱ ነው። *ሬሞን*፤ ሃዳድ ተብሎም ይጠራል፤ ደግሞም በከነዓንና በፊንቄ በኣል ይባላል። ይህ የሶርያ አምላክ የነጐድጓድና የጦርነት አምላክ ነው። ሬሞን ማለት 'ነጐድጓድ አውራጅ' ማለት ነው። ሐዳድና ሬሞን የሚሉት ስሞች ብዙ ውን ጊዜ ተያይዘው ይቀርባሉ (የዘካ 12፥11 ማብ ይመ)።

5፥19 *በሰላም ሂድ*፤ ኤልሳዕ በንዕማን ኅሊና ለተፈጠረው ጥያቄ ቀጥተኛ መልስ አልሰጠውም (ቍ18)፤ ይሁን እንጂ ጣዖት አምላኪ ወደ ሆነው ኅብረተሰብና ወደ መንግሥት ኀላ ፊነቱ ሲመለስ ለሚመጣ በት ችግር ንዕማንን ለእግዚአብሔር አመራርና ጸጋ አሳልፎ ሰጠው።

5፥20 *ሕያው እግዚአብሔርን*፤ የተለመደ መሐላ ነው (የ1ሳሙ 14፥39 ማብ ይመ)።

5፥22 *ከነቢያት ማኅበር*፤ የ2፥3 ማብ ይመ። *አንድ መክሊት ብርና ሁለት ሙሉ ልብስ*፤ ግያዝ ለግል ጥቅሙ ሲል ንዕማንን አታለለ። በሐሰት ያደረገው ክፋት በንዕማን ፈውስ የተገለጠውን የእግዚዙብሔርን ቸርነት ሸፈነ፤ ከዚህም በላይ በእውነተኛው ነቢይ በኤልሳዕና ራሳቸውን በሚያገለግሉ ሐሰተኛ ነቢያትና የጣዖት ሟርተኞች መካከል ያለውን ልዩነት በዚህ ድርጊቱ አደበዘዘ።

5፥24 *በቤቱ*፤ የኤልሳዕን ቤት ለማለት ነው (ቍ9 ይመ)።

5፥26 *ጊዜው ገንዘብና ... የሚቀበሉበት ነውን?* ለሌላ ሰው በተደረገው የእግዚአብሔርን ጸጋ፣ ግያዝ የግል ጥቅሙ ሊያመ ቻች ፈለገ። ይህ ማለት ደግሞ በእግዚአብሔር ጸጋ መነገድ ማለት

ልና የወይን ተክል ቦታ፣ የበግና የከብት
መንጋ፣ ወንድና ሴት አገልጋይ የሚቀበሉ
በት ነውን? 27ስለዚህ የንዕማን ለምጽ በአ
ንተ ላይ ይጣበቃል፤ ለዘላለምም ወደ ዘርህ
ይተላለፋል::" ከዚያም ግያዝ ከኤልሳዕ ፊት
ወጣ፤ እንደ በረዶ እስኪነጣ ድረስ ለምጻም
ሆኖ ነበር::

### መጥረቢያው ተንሳፈፈ

6 የነቢያት ማኅበር ኤልሳዕን እንዲህ
አሉት፤ "እነሆ፣ በፊትህ የምንቀመጥ
በት ስፍራ ጠቦናል፤ 2ስለዚህ ወደ ዮርዳኖስ
ሄደን፣ እያንዳንዳችን ምሰሶ ቈርጠን እናምጣ፣
በዚያም የምንቀመጥበትን መኖሪያ እንሥራ::"
እርሱም፣ "ይሁን ሂዱ" አላቸው::
3ከመካከላቸውም አንዱ፣ "አንተስ ከአገል
ጋዮችህ ጋር አትመጣምን?"አለው::
ኤልሳዕም፣ "እሺ እሄዳለሁ" አለ፤ 4አብሮ
አቸውም ሄደ:: ወደ ዮርዳኖስም ሄደው ዛፎች
መቍረጥ ጀመሩ:: 5ከእነርሱም አንዱ ዛፍ
እየቈረጠ ሳለ፣ መጥረቢያው በሮ ከውሃው
ውስጥ ወደቀ፤ እርሱም፣ "አዮ ጕድ ጌታዬ፤
የተውሶ መጥረቢያ እኮ ነው!" ብሎ ጮኸ::
6የእግዚአብሔርም ሰው፣ "በየት በኩል ነው
የወደቀው?" ሲል ጠየቀ:: ቦታውን ባሳየውም
ጊዜ ኤልሳዕ እንጨት ቈርጦ ወደ ውሃው
ውስጥ በመጣል መጥረቢያውን እንዲንሳፈፍ
አደረገው:: 7ከዚያም፣ "ብል አውጣና ውሰደው"
አለው፤ ሰውየውም እጁን ዘርግቶ ወሰደው::

### ኤልሳዕ ሶርያውያንን አሳወረ

8በዚህ ጊዜ የሶርያ ንጉሥ ከእስራኤል
ጋር ይዋጋ ነበር፤ ከጦር አለቆቹ ጋር ከተ
መካከረ በኋላም፣ "በዚህ፣ በዚህ ቦታ እሰፍ
ራለሁ" አለ::
9የእግዚአብሔርም ሰው፣ "ሶርያውያን በዚያ
ታች ወርደዋልና በዚያ በኩል እንዳታልፍ
ተጠንቀቅ" ሲል ለእስራኤል ንጉሥ ላከበት::
10ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ የእግዚአብሔር
ሰው የነገረውን ቦታ አስቃኘ፤ ኤልሳዕም
ንጉሡን እንደዚህ ካሉት ቦታዎች ራሱን
እንዲጠብቅ ከአንድ ሁለት ጊዜ በላይ
አስጠነቀቀው::
11ይህም የሶርያን ንጉሥ እጅግ ስላበሳጨው፣
የጦር አለቆቹን ጠርቶ፣ "ከመካከላችን ከእ
ስራኤል ንጉሥ ጋር የተወዳጀ እንዳለ ለምን
አትነግሩኝም?" ሲል ጠየቃቸው::
12ከጦር አለቆቹም አንዱ፣ "ንጉሥ ጌታዬ
ሆይ፤ ከእኛ በኩል ማንም ሰው የለም፤ ነገር
ግን አንተ በእልፍኝህ ሆነህ እንኳ የምትና
ገረውን አንዲቱም ሳትቀር ለእስራኤል ንጉሥ
የሚነግረው በእስራኤል ያለው ነቢዩ ኤልሳዕ
ነው" አለው::
13ንጉሡም፣ "ሰዎች ልኬ እንዳስይዘው፣
የት እንደሚገኝ ፈልጉ" ሲል አዘዘ:: ከዚ
ያም፣ "በዶታይን ይገኛል"የሚል ዜና ደረ
ሰው:: 14ስለዚህ ፈረሶችና ሠረገሎች እንዲ
ሁም ብዙ ሰራዊት ወደዚያ ላከ:: እነርሱም
በሌሊት ደርሰው ከተማዪቱን ከበቡ::
15የእግዚአብሔር ሰው አገልጋይ በማለዳ
ተነሥቶ ወደ ውጭ ሲወጣ፣ በፈረሶችና በሠ
ረገሎች የተጠናከረ ሰራዊት ከተማዪቱን
ከቧት ነበር:: አገልጋዩም "ጌታዬ ሆይ፤ ምን
ማድረግ ይሻለናል?" ሲል ጠየቀ::
16ነቢዩም፣ "ከእኛ ጋር ያሉት ከእነርሱ
ጋር ካሉት ይበልጣሉና አትፍራ" አለው::
17ኤልሳዕም፣ "*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ያይ
ዘንድ እባክህ ዐይኖቹን ክፈትለት" ብሎ
ጸለየ፤ *እግዚአብሔርም* የአገልጋዩን ዐይኖች
ከፈተለት፤ ሲመለከትም፤ የእሳት ፈረሶችና
ሠረገሎች በኤልሳዕ ዙሪያ ተራራውን ሞል
ተውት አየ::

5፥27 ዘፀ4፥6፤ ዘኍ12፥10፤ቈላ3፥5
6፥1 1ሳሙ10፥5
6፥6 ዘፀ15፥25፤ 2ነገ2፥21
6፥9 ቍ12
6፥10 ኤር11፥18
6፥12 ቍ9
6፥13 ዘፍ37፥17
6፥14 2ነገ1፥9
6፥16 ዘፍ15፥1፤ 2ዜና32፥7፤መዝ 55፥18፤1ዮሐ4፥4፤ ሮሜ8፥31
6፥17 2ነገ2፥11:12

ነው (የ2ቆሮ 2፥17 ማብ ይመ):: "ገንዘብ" ተብሎ በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሰው፣ የተለያየ ክብደት ያላቸውን ወርቆችንና ብሮችን እንጂ በኋላ የተሠሩትን የገንዘብ ሳንቲሞች የሚያመለክት አይደ ለም:: *ልብስ ... ሴት አገልጋይ!* ግያዝ በምስጢር በሁለቱ የብር መክሊት ሊገዛ ያሰበውን የሚያመለክት ይመስላል (የቍ5 ማብ ይመ)::

5፥27 *ለምጽ!* በዕብራይስጥ ለምጽንና ሌሎችን የቆዳ በሽታዎች ሁሉ ያመለክታል:: *ለዘላለምም ወደ ዘርህ ይተላለፋል!* የእግዚ አብሔርን ሕግ በጣሰ ሰው ላይ ቅጣቱ ወደ ልጆቹ እንዴት እንደ ሚተላለፍ ዘፀ20፥5 እና ማብ እንዲሁም የኢሱ7፥24 ማብ ይመ:: *እንደ በረዶ እስኪነጣ፤* ዘፀ4፥6 ይመ::

6፥1 *የነቢያት ማኅበር፤* የ2፥3 ማብ ይመ::

6፥2 *በፊትህ የምንቀመጥበት ስፍራ!* አንዳንዶች የነቢያት ጉባኤ በማኅበር በአንድ ቤት ይኖሩ ነበር የሚል ሐሳብ ይሰጣሉ:: የዕብ ራይስጡ፣ "በፊትህ የምንቀመጥበት ስፍራ" የሚለው መሰብሰቢያ አዳራ ሽን ያመለክታል:: በ4፥1-7 ላይ የነቢያት ማኅበር የተለያየ የመኖሪያ ቤት እንዳላቸው ተመልክቷል (የ1ሳሙ19፥18 ማብ ይመ)::

6፥5 *የተውሶ፤* በዚያ ዘመን መጥረቢያ እጅግ ውድ የብረት መሣሪያ ስለ ነበር፣ የነቢያት ማኅበር የመግዛት አቅም አልነበራቸውም:: መጥረቢያው ውሃ ውስጥ ወድቆ ስለጠፋ፣ ተውሶ ያመጣው ሰው ዋጋውን ለመክፈል ለአበዳሪው ተቀጥሮ የመሥራት ግዴታ ነበረበት::

6፥6 *ኤልሳዕ እንጨት ቈርጦ ወደ ውሃው ውስጥ በመጣል መጥረቢያው እንዲንሳፈፍ አደረገው፤* ይህ አስደናቂ ታምር እግ ዚአብሔር ታማኝ ለሆኑ ልጆቹ የቱን ያህል እንደሚጠነቀቅ ያሳያል::

6፥8 *የሶርያ ንጉሥ!* ዳግማዊ ቤንሃዳድ ሊሆን ይችላል (የ5፥1 ማብ ይመ):: *ከእስራኤል ጋር ይዋጋ ነበር፤* ይህ የሚያመለክተው ትልቅ ጦርነትን ሳይሆን፣ መጠነኛ የድንበር ግጭትን ነው (ቍ23 እና የ5፥2 ማብ ይመ)። የእስራኤላውያንን ደካማነትና የሶርያውያንን ብርታት የሚያመለክት አንድ ክሥተት አለ፤ ይኸውም ሶርያውያን ከሰማርያ በስተ ሰሜን ዐሥራ ሰባት ኪሎ ሜትር ርቃ ወደምትገኘው ወደ ዶታ ይን ሰራዊታቸውን ያለምንም ችግር መላካቸው ነው (ቍ13-14 ይመ)::

6፥9 *የእግዚአብሔርም ሰው፤* ኤልሳዕ ነው (ቍ10 ይመ):: *ለእስራኤል ንጉሥ!* ምናልባት ኢዮራምን ነው (1፥17፤3፥1፤9፥24 ይመ)::

6፥11 *ከመካከላችን ከእስራኤል ንጉሥ ጋር የተወዳጀ እንዳለ ለምን አትነግሩኝም?* የሶርያውያን ሰራዊት ያቀደውን እቅድ እስራኤላውያን በተደጋጋሚ ማወቅ መቻላቸው፣ ምናልባት ከሶርያ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች መሐል ከድቶ ምስጢሩን የገለጠ ሳይኖር አይቀርም ብሎ የሶርያ ንጉሥ ጠረጠረ::

6፥13 *ልኬ እንዳስይዘው፤* የሶርያ ንጉሥ ኤልሳዕን በመያዝ ከእስራኤል ንጉሥ ጋር ያለውን ግንኙነት አስቀረዋለሁ ብሎ አሰበ:: *በዶታይን፤* በኢይዝራኤልና በሰማርያ መካከል፣ ባለው አ ማካይ ቦታ በኰረብታ ላይ ያለች ስፍራና አብዛኛዎቹ የመንግ ሥት መኖሪያ ቤቶች የሚገኙባት ነች (1፥2፡3፥1፡ 8፥29፡ 9፥15፡ 10፥1፡ 1ነገ 21፥1 ይመ)::

6፥16 *ከእኛ ጋር ያሉት ከእነርሱ ጋር ካሉት ይበልጣሉ፤* ከሚታየው ከሶርያ ሰራዊት ኀይል ይልቅ በማይታየው በሰማያዊው ሰራዊት ዘንድ ታላቅ ኀይል እንዳለ ኤልሳዕ ተረድቶአል (2ዜና 32፥7-8፤1ዮሐ 4፥4)::

6፥17 *የእሳት ፈረሶችና ሠረገሎች ... ተራራውን ሞልተውት አየ፤* እግዚአብሔር የኤልሳዕን ጸሎት ሲመልስ፣ አገ ልጋዩ በኤልሳዕ ዙሪያ ሆነው የሚጠብቁትን ታላቅ የሰማይ ሠራዊት አየ (ዘፍ 32፥1-2፤ መዝ 34፥7፤91፥11-12፤ማቴ 18፥10፤26፥53 እና የ2ነገ 2፥11 ማብ ይመ)::

18ሶርያውያንም ወርደው ወደ እርሱ ሲመጡ
ኤልሳዕ፣ “ይህን ሕዝብ ዕውር አድርገው”
ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። ስለዚህ ኤል
ሳዕ በጠየቀው መሠረት እግዚአብሔር ዕውር
አደረጋቸው።
19ኤልሳዕም፣ “መንገዱ በዚህ አይደለም፤
ከተማዪቱም ይህች አይደለችም፤ ወደ ምት
ፈልጉት ሰው መርቼ እንዳደርሳችሁም እኔን
ተከተሉኝ” አላቸው። ከዚያም መርቶ ወደ
ሰማርያ ወሰዳቸው።
20ወደ ከተማዪቱም ከገቡ በኋላ ኤልሳዕ፣
“እግዚአብሔር ሆይ፤ እንዲያዩ የእነዚህን
ሰዎች ዐይን ክፈት” አለ። እግዚአብሔርም
ዐይኖቻቸውን ከፈተ። እነርሱም በሰማርያ
ውስጥ መሆናቸውን አዩ።
21የእስራኤልም ንጉሥ ባያቸው ጊዜ፣
“አባቴ ሆይ፤ ልግደላቸውን? ልፍጃቸውን”
ብሎ ኤልሳዕን ጠየቀው። 22እርሱም፣ “አትግ
ደላቸው፤ ለመሆኑ በሰይፍህና በቀስትህ የማረ
ክሃቸውን ትገድላቸው ዘንድ ይገባሃልን?
አሁንም የሚበሉትንና የሚጠጡትን አስቀ
ርብላቸው፤ በልተው ጠጥተውም ወደ ጌታ
ቸውም ይሂዱ” አለው። 23ስለዚህ ታላቅ
ግብዣ አዘጋጅቶላቸው ከበሉና ከጠጡ
በኋላ አሰናብቶአቸው ወደ ጌታቸው ሄዱ።
የሶርያ አደጋ ጣዮችም የእስራኤልን ምድር
ለመውረር ከዚያ በኋላ አልተመለሱም።

## በተከበበችው ሰማርያ የተከሠተ ራብ

24ከጥቂት ጊዜ በኋላም የሶርያ ንጉሥ
ቤንሐዳድ ሰራዊቱን ሁሉ ሰበሰበ፤ ወጥቶም
ሰማርያን ከበባት። 25ከተማዪቱን እንደ ከበ
ባትም የአንድ አህያ ጭንቅላት በሰማኒያ
ሰቅል[ሌ] ብር፣ የጎሞር አንድ ስምንተኛ[ሰ]
የርግብ ኵስ[ሸ] በአምስት ሰቅል[ተ] ብር እስኪ
ሸጥ ድረስ ታላቅ ራብ ሆነ።
26የእስራኤልም ንጉሥ በቅጥሩ ላይ በሚ
መላለስበት ጊዜ አንዲት ሴት ድምፅዋን
ከፍ አድርጋ “ጌታዬ፣ ንጉሥ ሆይ፤ እባክህ
ርዳኝ!” አለች።
27ንጉሡም፣ “እግዚአብሔር ካልረዳሽ እኔ
እንዴት ልረዳሽ እችላለሁ? ከዐውድማው
ነው ወይስ ከወይን መጥመቂያው የምረዳሽ?”
ሲል መለሰላት። 28ከዚያም፣ “ለመሆኑ ችግ
ርሽ ምንድነው?” ሲል ጠየቃት።
እርሷም እንዲህ ስትል መለሰችለት፤
“ይህች ሴት፣ ‘ዛሬ እንድንበላው ልጅሽን
አምጪው፤ ነገ ደግሞ የእኔን ልጅ እንበላዋ
ለን’ አለችኝ። 29ስለዚህ ልጄን ቀቅለን በላ
ነው። በማግሥቱም፣ ‘እንድንበላው ልጅሽን
አምጪው’ አልኋት፤ እርሷ ግን ደበቀችው።”
30ንጉሡም ሴቲቱ ያለችውን ሲሰማ ልብ
ሱን ቀደደ፤ በቅጥሩ ላይ በሚመላለስበትም
ጊዜ በውስጥ ማቅ መልበሱን ሕዝቡ አየ።
31ንጉሡም፣ “የሣፋጥ ልጅ የኤልሳዕ ራስ ዛሬ
በዐንገቱ ላይ ካደረ፣ እግዚአብሔር ይህን ያድ
ርግብኝ፤ ከዚህም የባሰ ያምጣብኝ” ብሎ ዛተ።
32በዚህ ጊዜ ኤልሳዕ በቤቱ ተቀምጦ
ነበር፤ ሽማግሌዎችም አብረውት ተቀምጠው
ነበር። ንጉሡም መልእክተኛ ቀድሞት እን

6፥18 ዘፍ19፥11፤ ሐሥ13፥11
6፥21 2ነገ5፥13
6፥22 ዘዳ20፥11፤ 2ዜና28፥8-15
6፥23 2ነገ5፥2
6፥24 ዘዳ28፥52፤ 1ነገ15፥18፤2ነገ8፥7
6፥25 ዘሌ26፥26፤ ሩት1፥1፤ኢሳ 36፥12
6፥29 ዘሌ26፥29፤ ዘዳ28፡53-55
6፥30 ዘፍ37፥34፤ 2ነገ18፥37፤ኢሳ22፥15
6፥32 ቍ31፤1ነገ 18፥4፤ሕዝ8፥1፤ 14፥1፤20፥1

[ሌ]25 1 ኪሎ ግራም ያህል ነው። [ሰ]25 0.3 ሊትር ያህል ነው።
[ሸ]25 ወይም፣ ጥሬ [ተ]25 55 ግራም ያህል ነው።

6፥18 ***ይህን ሕዝብ ዕውር አድርገው፤*** ኤልሳዕ አስቀድሞ አገልጋዩ ያላየውን የሰማይ ሰራዊት እንዲያይ ዐይኑ እንዲከፈት ጸለየ፤ አሁን ደግሞ የሰማርያ ሰራዊት ዐይናቸው እንዲታወር ጸለየ (ዘፍ 19፥11 ይመ)።

6፥19 ***መንገዱ በዚህ አይደለም፤ ከተማይቱም ይህቺ አይደ ለችም፤*** የኤልሳዕ አነጋገር የሶርያ ወታደሮችን ኤልሳዕ ወደሚ ገኝበት ከተማ እየተመሩ እንደ ሆነ እንዲያምኑ አደረገ። በመሠ ረቱ የተናገረው ሐሰት አልነበረም፤ ምክንያቱም ኤልሳዕ እስከ ሰማ ርያ አድርሷቸዋል። ይህንንም የተናገረው የሶርያ ወታደሮችን በማ ታለል የሰሜኑ መንግሥት መናገሻ ወደ ሆነችው ወደ ተመሸገ ችው የሰማርያ ከተማ ዘልቀው ወጥመድ ውስጥ እንዲገቡ ለማድ ረግ ነው (ዘፀ1፥19-20፤ኢሱ2፥6፤1ሳሙ16፥1-2 ይመ)።

6፥20 ***እነርሱም በሰማርያ ውስጥ መሆናቸውን አዩ፤*** የእግዚአብሔር ኀይል፣ ሊማርኩ የመጡትን በኤልሳዕ በኩል እን ዲማረኩ አደረጋቸው።

6፥21 ***የእስራኤልም ንጉሥ፤*** ኢዮራምን ነው (የቍ9 ማብ ይመ)።

6፥22 ***አትግደላቸው፤*** የሶርያ ወታደሮች የተማረኩት በእግዚአብሔር ኀይል እንጂ በኢዮራም ወታደራዊ ችሎታ አልነበረም። የእግዚአብሔር ዓላማም፣ የእስራኤል ብሔራዊ ደህን ነት የተመሠረተው በወታደራዊ ኀይል ሳይሆን በእግዚአብሔር ኀይል እንደ ሆነ፣ ለሶርያውያንና ለንጉሣቸው እንዲሁም ለእስራ ኤላውያንና ለንጉሣቸው ለማሳወቅ ነው።

6፥23 ***የሶርያ አደጋ ጣዮችም የእስራኤልን ምድር ለመውረር ከዚያ በኋላ አልተመለሱም፤*** የቍ 8፤ 5፥2 ማብ ይመ። ለጊዜው ሶርያውያን የእስራኤልን አምላክ ኀይል መቃወም ጥቅም እንደሌለው ተገነዘቡ።

6፥24 ***ቤን ሐዳድ፤*** ቀደም ባለው ታሪክ ሰማርያን ከብበአት የነበረው ቤን/ሐዳድ ነው (የ1ነገ13፥3፤ 1ነገ 20፥1 ማብ ይመ)። ይህ ከበባ በግምት በ 850 ዓ.ቅ.ክ ይሆናል።

6፥25 ***የአህያ ጭንቅላት፤*** በሙሴ ሕግ መሠረት አህያ ርኩስ ስለሆነ ለመብል ከሚሆኑ መካከል አይደለም (ዘሌ11፥2-7፤ዘዳ14፥4-8 ይመ)። የራቡ ጽናት የሰማርያን ነዋሪዎች ሕጉን እንዲተው ብቻ ሳይሆን፣ ጨርሶ ለምግብነት ለማይውለው ለአህያ ሥጋም ውድ ዋጋ እንዲከፍሉ አድርጓአቸዋል። ***ሰማንያ ሰቅል ብር፤*** አንድ ኪሎ ግራም ብር ያህል ማለት ነው። የ5፥5 ማብ ይመ።

6፥27 ***እግዚአብሔር ካልረዳሽ እኔ እንዴት ልረዳሽ እችላለሁ?*** በአንድ በኩል እግዚአብሔር እስራኤልን ካልረዳ እርሱ በራሱ መርዳት አለመቻሉን ኢዮራም ተገንዝቦአል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከእስራኤል አለመታዘዝና ጣዖት አምልኮ የተነሣ መሆኑን በመዘ ንጋት፣ ለራብ መጽናት እግዚአብሔር ራሱ ተጠያቂ ሊሆን ይገባ ዋል የሚል ይመስላል።

6፥28 ***ነገ ደግሞ የእኔን ልጅ እንበላዋለን፤*** የንጉሡና የሕ ዝቡ ኃጢአት እጅግ ብዙ ስለ ነበር በዘሌ 26፥29፤ ዘዳ 28፥53፡57 የተጠቀሱት የኪዳኑ ርግማኖች በሙሉ ደረሱባቸው (ከሰቆ4፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

6፥30 ***ልብሱን ቀደደ፤*** የኪዳኑ ርግማን የደረሰው በኀጢ አት ምክንያት መሆኑን በመረዳት ለንስሐ የተደረገ ሳይሆን፣ በኤልሳዕና በእግዚአብሔር ላይ ያለውን ቍጣ ለመግለጥ ነው (ቍ 31 ይመ)። ***ማቅ፤*** በሐዘን ጊዜ የሚለበስ ሸካራ ልብስ ነው (የዘፍ 37፥34 እና ማብ ይመ)። ኢዮራም በልብሱ ውስጥ ለምን ማቅ እንደ ለበሰ የተገለጠ ነገር የለም፤ ምናልባት ከእግዚአብሔር ተቀባይነትን ለማግኘት በግሉ ሃይማኖታዊ ሥርዐትን በመፈጸም እግዚአብሔርን የፈተነበት ሁኔታ ሊሆን ይችላል።

6፥31 ***እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ፤ ከዚህም የባሰ ያም ጣብኝ፤*** የተለመደ ርግማን ያዘለ መሓላ ነው (የ1ሳሙ3፥17 ማብ ይመ)። ***የኤልሳዕ ራስ ዛሬ በአንገቱ ላይ ካደረ፤*** በከተማ ውስጥ ለሚፈጠረው ማንኛውም ችግር፣ ኢዮራም ተጠያቂ ያደረገው ነቢዩ ኤልሳዕን ብቻ ነው፤ አክዓብ በኤልያስ ላይ የነበረው ተመሳሳይ አመለካከት ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (1ነገ 18፥10፡16፤ 21፥20 ይመ)።

6፥32 ***ሽማግሌዎች፤*** የከተማዪቱ መሪዎች ማለት ነው (የዘፀ3፥16፤ 2ሳሙ3፥17 ማብ ይመ)፤ እነርሱም የተቀመጡት ከንጉሡ ጋር ሳይሆን ከኤልሳዕ ጋር ነበር።

ዲሄድ አደረገ:: የተላከውም ሰው ከመድረሱ
በፊት ኤልሳዕ ለሽማግሌዎቹ፣ "ይህ ነፍሰ
ገዳይ ራሴን ለመቊረጥ ሰው መላኩን ታያ
ላችሁ? እነሆ፤ አሁንም መልእክተኛው ሲደ
ርስ በሩን ዘግታችሁ እንዳይገባ አድርጉ::
የጌታው የእግሩ ኮቴ ከኋላው ይሰማ የለ
ምን?" አላቸው::
33ኤልሳዕ ከሽማግሌዎቹ ጋር በመነጋገር
ላይ ሳለም፣ መልእክተኛው ወደ እርሱ ወረደ::
ንጉሡም ደርሶ፣ "ይህ ጥፋት የመጣው *ከእ
ግዚአብሔር* ነው፤ ታዲያ እኔ *ከእግዚአብሔር*
ምን እጠብቃለሁ?" አለ::

7 ኤልሳዕም፣ "እንግዲህ *የእግዚአብሔርን*
ቃል ስማ፤ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
'በነገው ዕለት በዚሁ ሰዓት፣ በሰማርያ
በር አንድ መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት በአ
ንድ ሰቅል፣ ሁለት መስፈሪያ ገብስም በአ
ንድ ሰቅል ይሸጣል"አለ::
2ንጉሡ በክንዱ ላይ የተደገፈውም የጦር
አለቃ፣ የእግዚአብሔርን ሰው፣ "እንዲያው ለመሆኑ፣
*እግዚአብሔር* የሰማይትን መስኮቶች ቢከፍት
እንኳ ይህ ሊሆን ይችላልን?" ሲል ጠየቀው::
ኤልሳዕም፣ "ይህን አንተው ራስህ በዐይ
ንህ ታየዋለህ፤ ይሁን እንጂ ከዚያ አንዳች
አትቀምስም" አለው::

### ከበባው ተወገደ

3በዚህ ጊዜ የለምጽ በሽታ የያዛቸው አራት
ሰዎች በከተማዪቱ መግቢያ በር አጠገብ ነበሩ፤
እነርሱም እርስ በርሳቸው እንዲህ ተባባሉ፤
"እስክንሞት ድረስ በዚህ የምንቀየው ለምን
ድን ነው? 4ታዲያ፣ 'ወደ ከተማዪቱ እንግባ
ብንል' በዚያም ራብ ስላለ እንሞታለን፤ በዚ
ሁም ብንሆን ያው መሞታችን እንደሁ አል
ቀረም፤ ስለዚህ ወደ ሶርያውያኑ ሰፈር ዝም
ብለን እንሂድ፤ ዝም ካሉን መትረፋችን
ነው፤ ከገደሉንም ያው መሞት ነው::"
5ከዚያም መሸትሸት ሲል ተነሥተው
ወደ ሶርያውያን ሰፈር ሄዱ፤ ወደ ሰፈሩ
ጥግ ሲደርሱም አንድም ሰው በዚያ አልነበ
ረም:: 6ይህ የሆነበትም ምክንያት እግዚአ
ብሔር የሠረገሎችንና የፈረሶችን እንዲሁም
የብዙ ሰራዊት ድምፅ ሶርያውያን እንዲ
ሰሙ አድርጎ ስለነበር ነው፤ እርስ በእርሳ
ቸው፣ "እነሆ፣ የእስራኤል ንጉሥ በእኛ ላይ
አደጋ ለመጣል፣ የኬጢያውያንንና የግብፃ
ውያንን ነገሥታት ቀጥሮ አምጥቶብናል"
ተባባሉ:: 7ከዚያም መሸትሸት ሲል ተነሥ
ተው ሸሹ፤ ድንኳኖቻቸውን፣ ፈረሶቻቸው
ንና አህዮቻቸውንም አልወሰዱም ነፍሳቸ
ውን ብቻ ለማዳን ሲሉ ሰፈሩን እንዲሁ
እንዳለ ትተው ሄዱ::
8 ለምጽ ያለባቸውም ሰዎች ወደ ሰፈሩ
አጠገብ ከደረሱ በኋላ፣ ከድንኳኖቹ ወደ
አንዱ ገብተው በሉ፤ ጠጡም፤ ከዚያም
ብር፣ ወርቅና ልብስ ይዘው በመሄድ ደበቁት::
ተመልሰው በመምጣትም ወደ ሌላው ድን
ኳን ገብተው ሌሎች ነገሮችን ወስደው እን
ደዚሁ ደበቁ::
9እርስ በርሳቸውም፣ "ያደረግነው ትክክል
አይደለም፤ ዕለቱ የምሥራች ቀን ነው፤
እኛ ግን የራሳችን ብቻ አደረግነው፤ እስኪ
ነጋም ከቈየን በደለኞች እንሆናለን፤ ስለዚህ
ወደ ቤተ መንግሥት በፍጥነት ሄደን እን
ንገር" ተባባሉ::
10ስለዚህ ሄደው የከተማዪቱን መግቢያ
በር ጠባቂዎች ጮኸው በመጥራት፣ "ወደ
ሶርያውያን ሰፈር ገባን፤ እዚያም ከታሰሩ
ፈረሶችና አህዮች በቀር አንድም ሰው አል
ነበረም፤ የማንም ድምፅ አልተሰማም፤ ድን
ኳኖቹም እንዳሉ ናቸው" ብለው ነገሯአቸው::
11የበሩ ጠባቂዎችም ይህንኑ አስተጋቡ፤ ዜና
ውም በቤተ መንግሥቱ ተሰማ::
12ንጉሡም በሌሊት ተነሥቶ ለጦር አለቆቹ
እንዲህ አላቸው፤ "ሶርያውያን ያደረጉብንን
እነግራችኋለሁ፤ መራባችንን ስለሚያውቁ፣
'መቼም መውጣታቸው አይቀርም፤ ከዚያም
ከነሕይወታቸው እንማርካቸዋለን፤ እኛም
ሰተት ብለን ወደ ከተማዪቱ እንገባለን' በማ
ለት በጦር ለመደበቅ ከሰፈራቸው ወጥተዋል::"
13ከጦር አለቆቹም አንዱ እንዲህ አለ፤
"ጥቂት ሰዎች በከተማዪቱ ውስጥ ከተረፉት
ፈረሶች አምስቱን ይዘው ይሂዱ፤ ዕጣ ፈን
ታቸውም በዚህ ከቀሩት እስራኤላውያን
ሁሉ ዕድል ጋር አንድ ነው፤ የሚጠብቃቸው
ቢኖር እንዳለቁት እንደነዚህ እስራኤላውያን
መሆን ብቻ ነው፤ ስለዚህ እንላካቸውና የሆ
ነውን እንይ::"
14ስለዚህ ሁለት ሠረገሎች ከነፈረሶቻቸው
መረጡ፤ ንጉሡም፣ "ሂዱና የሆነውን ነገር

6፥33 ዘሌ24፥11፤ ኢዮ 2፥9፤ 14፥14፤ ኢሳ 40፥31
7፥1 ቍ16
7፥2 ቍ17፡19፤ ዘፍ7፥11፤2ነገ5፥18፤ መዝ78፥23፤ ሚል3፥10
7፥3 ዘሌ13፥45-46፤ ዘኍ5፥14
7፥6 ዘፀ14፥24፤ ዘኍ13፥29፤2ሳሙ10፥6፤ኤር46፥21፤ ሕዝ1፥24
7፥7 መሳ7፥21፤ መዝ48፥46፤ምሳ28፥1፤ ኢሳ30፥17
7፥8 ኢሳ33፥23፤ 35፥6
7፥12 ኢሱ8፥4

ግ1 በዚህ እንዲሁም በቍጥር 16 እና 18 ላይ 73 ሊትር ያህል ነው::
ተ1 በዚህ እንዲሁም በቍጥር 16 እና 18 ላይ 11 ኪሎ ግራም ያህል ነው
ቶ1 በዚህ እንዲሁም በቍጥር 16 እና 18 ላይ 15 ሊትር ያህል ነው
ገ3 በዚህ እና በቍጥር 8 ላይ የዕብራይስጡ ቃል ቆዳን የሚያጠቁን በሽታዎች ሁሉ የሚያሳይ ነው::

6፥33 *ታድያ እኔ ከእግዚአብሔር ምን እጠብቃለሁ?* በከተማዪቱ ለተፈጠረው አስከፊ ሁኔታ፣ ኤልሳዕ ያታለለውና እግዚአብሔርም ከእርሱ የራቀ ስለ መሰለው ኢዮራም መልእክተኛን ላከ::

7፥1 *አንድ መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት በአንድ ሰቅል፤* ሦስት ኪሎ ያህል ዱቄት ሊሆን ይችላል፤ በዚህ የራብ ወቅት ዋጋው እጥፍ ቢሆንም ትልቅ መሻሻልና ለውጥ ያለው ነበር::

7፥2 *የሰማያትን መስኮቶች፤* ቍ19፤ዘፍ 8፥2፤ ኢሳ 24፥18 ይመ::

7፥3 *በከተማይቱ መግቢያ በር፤* የሙሴ ሕግ የሚያሠቅቅ የቆዳ በሽታ የነበረባቸው ሰዎች በኅብረተሰቡ መካከል መኖር የለባቸውም ይላል (ዘሌ 13፥46፤ ዘኍ 5፥2-3 ይመ)::

7፥6 *እግዚአብሔር ... ድምፅ ሶርያውያን እንድሰሙ አድርጎ ስለነበር፤* 2ሳሙ 5፥24 እና ማብ ይመ:: *የኬጢያውያንን... ነገሥታት፤* በኬጢያውያን ሥርወ መንግሥት የሚመሩ የትንንሽ ከተሞች ነገሥታት ናቸው፤ በግምት በ1200 በዓ.ቅ.ክ የኬጢያውያን መንግሥት ሲወድቅ፣ በሰሜን ሶርያ የተነሡ ነገሥታት ነበሩ::

7፥12 *ሶርያውያን ያደረጉብንን፤* አራቱ የሚያሠቅቅ የቆዳ በሽታ የነበረባቸው ሰዎች ያመጡት ወሬ፣ የሶርያውያን ወታደሮች የጦር ስልት እንጂ የኤልሳዕ ትንቢት መፈጸም አይደለም ማለቱ ከኢዮራም የማያምን ልብ የወጣ አስተሳሰብ ነው (ቍ1 ይመ)::

እዩ" ብሎ ከሶርያውያን ሰራዊት በኋላ እን
ዲሄዱ ላካቸው። 15እነርሱም እስከ ዮርዳኖስ
ድረስ ተከተሏቸው። ሶርያውያን በጥድፊያ
ሲሸሹ፣ የጣሉትንም ልብስና ዕቃ በየ መን
ገዱ ላይ ተበታትኖ አገኙ፤ መልክተኞቹም
ተመልሰው ይህንኑ ለንጉሡ ነገሩት። 16ከዚ
ያም ሕዝቡ ወጥቶ የሶርያውያንን ሰፈር በዘ
በዘ፤ ስለዚህ *እግዚአብሔር* እንደ ተናገረው
አንድ መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት በአንድ
ሰቅል፣ ሁለት መስፈሪያ ገብስም በአንድ
ሰቅል ተሸጠ።

17በዚህ ጊዜ ንጉሡ እጁን ይደገፈው
የነበረውን የጦር አለቃ፣ የቅጥሩ በር ኀላፊ
አድርጎት ነበርና በበሩ መተላለፊያ ላይ
ሕዝቡ ሲጋፋ ረጋገጠው፤ ያ የእግዚአብሔር ሰው
ንጉሡ ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ አስቀድሞ
እንደተናገረውም የጦር አለቃው ሞተ።
18እንዲሁም የእግዚአብሔር ሰው ለንጉሡ፣ "ነገ
በዚሁ ሰዓት በሰማርያ በር ላይ አንድ መስ
ፈሪያ ዱቄት በአንድ ሰቅል፣ ሁለት መስፈ
ሪያ ገብስም በአንድ ሰቅል ይሸጣል" ያለ
ውም ተፈጸመ።

19የጦር አለቃው ለ*እግዚአብሔር* ሰው፣
"እግዚአብሔር የሰማይን መስኮቶች ቢከፍት
እንኳ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?" ብሎት
ስለነበር፣ የ*እግዚአብሔር* ሰው፣ "ይህን አን
ተው ራስህ ታያለህ፤ ከዚህ ግን አንዳች
አትበላም" ሲል መልሶለት ነበር። 20በበሩ
መተላለፊያ ላይ ሕዝቡ ረጋግጦት ስለሞ
ተም፣ የተነገረበት በትክክል ደረሰ።

## የሱነማዪቱ ርስት ተመለሰ

8 በዚህ ጊዜ ኤልሳዕ፣ ልጇን ከሞት ያስነ
ሣላትን ሴት፣ "*እግዚአብሔር* በምድ
ሪቱ ላይ የሰባት ዓመት ራብ ስለ ወሰነ፣
ተነሺና ለጊዜው መቈየት ወደምትችዪበት
ቦታ ከቤተሰብሽ ጋር ሂጂ" አላት። 2ሴቲቱም
ተነሥታ የእግዚአብሔር ሰው እንደ ነገራት
አደረገች፤ ከነቤተሰቧም ሄዳ፣ በፍልስጥኤም
ምድር ሰባት ዓመት ተቀመጠች።

3ከሰባት ዓመት በኋላም፣ ከፍልስጥኤም
ምድር ተመልሳ መጣች፤ ስለ ቤቷና ስለ
መሬቷ አቤቱታ ለማቅረብ፣ ወደ ንጉሡ
ሄደች። 4በዚህ ጊዜ ንጉሡ የእግዚአብሔርን
ሰው አገልጋይ ግያዝን፣ "ኤልሳዕ ያደረጋቸ
ውን ታላላቅ ሥራዎች ሁሉ እስቲ ንገረኝ"
እያለው ነበር። 5ኤልሳዕ ልጇን ከሞት
ያስነሣላት ሴት ስለ ቤቷና ስለ መሬቷ ለማ
መልከት ወደ ንጉሡ ዘንድ የቀረበችውም፣
ኤልሳዕ የሞተውን ልጅ እንዴት እንዳስ
ነሣ፣ ግያዝ ለንጉሡ በሚነግርበት ወቅት
ነበር።

ግያዝም፣ "ንጉሥ ጌታዬ ሆይ፤ ሴቲቱ
ይህች ናት፤ ኤልሳዕ ከሞት ያስነሣው ልጇም
ይህ ነው" አለ። 6ንጉሡም ስለዚሁ ጒዳይ
ጠየቃትና ነገረችው።

ከዚያም ንጉሡ፣ "የነበራትን ሁሉ እን
ዲሁም ትታ ከሄደችበት ጊዜ አንሥቶ እስካ
ሁን ድረስ ያለውን የዕርሻዋን ሰብል በሙሉ እን
ድትመልስላት" ሲል አንድ ሹም አዘዘላት።

## አዛሄል ቤንሀዳድን ገደለ

7ኤልሳዕ ወደ ደማስቆ ሄደ፤ በዚያን ጊዜም
የሶርያ ንጉሥ ቤንሀዳድ ታሞ ነበር፤ ለንጉ
ሡም፣ "የእግዚአብሔር ሰው ወደዚህ መጥቶ
አል ብለው ነገሩት። 8እርሱም አዛሄልን፣
"ገጸበረከት ይዘህ ሂድና የእግዚአብሔርን ሰው
ተገናኘው። በእርሱም አማካይነት፣ 'ከዚህ
በሽታ እድናለሁን?' ብለህ *እግዚአብሔ
ርን* ጠይቅ" አለው።

9አዛሄልም ደማስቆ ካፈራቻቸው ምርጥ
ነገሮች ሁሉ የአርባ ግመል ጭነት ገጸ
በረከት ይዞ ኤልሳዕን ለመገናኘት ሄደ።
ሄዶም እፊቱ ቆመና፣ "የሶርያ ንጉሥ ልጅህ
ቤንሀዳድ፣ 'ከዚህ በሽታ እድናለሁን?' ሲል

7፥15 ኢዮ27፥22
7፥16 ቍ1፤ኢሳ
33፥4፡23
7፥17 ቍ2
7፥19 ቍ2
8፥1 ዘፍ12፥10፤
ዘሌ26፥26፤ዘዳ
28፥22፤ሩት1፥1፤
2ነገ4፥8-37
8፥5 2ነገ4፥35
8፥7 2ሳሙ8፥5፤
2ነገ6፥24
8፥8 ዘፍ32፥20፤
መሳ18፥5፤1ሳሙ9፥7፤
1ነገ19፥15

7፥16-20 *እግዚአብሔር እንደ ተናገረው ... ያ የእግዚ
አብሔር ሰው ... አስቀድሞ እንደ ተናገረው... የእግዚአብሔር
ሰው... ያለውም ተፈጸመ፤* ነቢዩ ኤልሳዕ የተናገረው የትንቢት
ቃል እውነተኛነት በአጽንዖት ይገልጻል። በኤልሳዕ ትንቢት መፈ
ጸም እስራኤል ከጠላቶቻቸው ነጻ የሚወጡት በእግዚአብሔር
የቸርነት ስጦታ ብቻ እንደ ሆነና፣ የእግዚአብሔርንም ቃል
መቃወም መለኮታዊ ፍርድን እንደሚያመጣባቸው ተምረዋል።

8፥1 *እግዚአብሔር በምድሪቱ ላይ ... ራብ ስለ ወሰነ* ራቡ
በኀጢአታቸው ምክንያት የመጣ የኪዳን ርግማን መሆኑን በሰሜን
መንግሥት ያሉ ሰዎች ሁሉ መገንዘብ ነበረባቸው (የ4፥38 ማብ
ይመ)። *ሰባት ዓመት፤* ይህ ራብ ሶርያውያን ሰማርያን ከመክበባቸው
በፊት የተከሠተ ይሁን ወይም በኋላ የሆነ አይታወቅም (4፥38፡
6፥24-7፥20 ይመ)።

8፥2 *ሴቲቱም ... ከነቤተሰቧም ሄዳ፤* ከኤልሳዕ ቃል የተነሣ
ሴቲቱ ከቤተሰቧ ጋር ራቡን ለማምለጥ ቻለች።

8፥3 *ወደ ንጉሡ ሄደች፤* የ1ነገ 3፥16 ማብ ይመ። *ስለ
ቤቷና ስለ መሬቷ አቤቱታ ለማቅረብ፤* ምናልባት እርሷ ባልነበረ
ችበት ጊዜ ንብረቷ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ በሰው ተወስዶ ሊሆን
ይችላል ወይም ከንጉሡ ርስት ተቈጥሮ ይሆናል።

8፥4 *ግያዝ* 5፥27 ይመ። *ኤልሳዕ ያደረጋቸውን ታላላቅ
ሥራዎች ሁሉ እስቲ ንገረኝ፤* በዚህ ጊዜ ንጉሡ ስለ ኤልሳዕ
አገልግሎት አለማወቁ፣ ምናልባት ይህ ሁኔታ የተፈጸመው በኢዮራም
ዘመን ከመሆኑ ይልቅ በኢዩ ዘመን ሳይሆን አይቀርም፤ ምክንያቱም
ንጉሡ ኢዮራም ከኤልሳዕ ጋር ግንኙነት ነበረው (3፥13-14፤ 5፥7-10፤
6፥10-23፤6፥24-7፥20 ይመ)፤ እንዲሁም የ5፥7 ማብ ይመ።

8፥5 *ግያዝ ለንጉሡ በሚነግርበት ወቅት፤* ሴቲቱ ወደ ንጉሡ
ስትቀርብና ግያዝም በኤልሳዕ አገልግሎት እንዴት ልጇ በተአምራት
እንደ ተፈወሰ ሲናገሩ ሁኔታው ተገጣጠመ።

8፥6 *የነበራትን ሁሉ ... እንድትመልስላት፤* መበለቲቱና
ልጇ በነቢያት የሚነገረውን የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው
የሚታዘዙ ሰዎች ስለሚያገኙት በረከት ሕያው ምሳሌ ናቸው።

8፥7 *ኤልሳዕ ወደ ደማስቆ ሄደ፤* በኮሬብ ተራራ ለኤልያስ
ከተሰጡት ሦስት ኀላፊነቶች ኤልሳዕ አንዱን የሚፈጽምበት ጊዜ ነበር
(1ነገ 19፥15-16 እና ማብ ይመ)። በአሦር ገዢ በሥልሳዊ ስልም
ናስር ታሪክ፣ አሦራውያን የደማስቆውን ቤንሃዳድን በ846 ዓ.ቅ.ክ.ና የደ
ማስቆውን አዛሄልን በ842 ዓ.ቅ.ክ. ድል እንዳደረጉ ተጽፎአል። ስለዚህ
ኤልሳዕ ወደ ደማስቆ የሄደበት ጊዜ በግምት በ843 ዓ.ቅ.ክ. ይሆናል።

8፥8 *በእርሱም አማካይነት ... እግዚአብሔርን ጠይቅ፤* በ1፥1-4
ያለውን ሁኔታ በሚቃረን መልኩ ጣዖት አምላኪው ንጉሥ የትንቢትን
ቃል ከእስራኤል አምላክ ሲጠይቅ በዚህ ክፍል ተገልጾአል። *ከዚህ በሽታ
እድናለሁን?* አካዝያስ በ1፥2 ከጠየቀው ጥያቄ ጋር ተመሳሳይ ነው።

8፥9 *ደማስቆ ካፈራቻቸው ምርጥ ነገሮች ሁሉ የአርባ
ግመል ጭነት ገጸ በረከት፤* ደማስቆ በግብፅ፣ በትንሹ እስያና
በመስጴጦምያ መካከል ይካሄድ ለነበረው ንግድ መናኸሪያ ከተማ
ነበረች። ቤንሃዳድ መጠኑ፣ ከፍ ያለው ይህ ገጸ በረከት፣ ኤልሳዕን
መልካም የሆነ የትንቢት ቃል እንዲናገር ያደርገዋል ብሎ ያሰበ
ይመስላል። *ልጅህ ቤንሃዳድ፤* በአባትና በልጅ ግንኙነት ዐይነት
በዚህ ስፍራ መገለጹ፣ ቤን ሃዳድ የኤልሳዕን የበላይነት ማመኑን

ወደ አንተ ልኮኛል” አለው። 10ኤልሳዕም፣ “ሂድና፣ ‘*መዳኑንስ* በእርግጥ ትድናለህ’ በለው፤ ነገር ግን እንደሚሞት *እግዚአብሔር* ገልጦልኛል’” ሲል *መለሰለት*። 11እስኪያፍር ድረስም፣ አዛሄልን ትኵር ብሎ ተመለከ ተው፤ ከዚያም የእግዚአብሔር ሰው እንባውን አፈሰሰ።

12አዛሄልም፣ “ጌታዬ የሚያለቅሰው ለምን ድን ነው?” ሲል ጠየቀ።

ኤልሳዕም መልሶ፣ “በእስራኤላውያን ላይ የምታደርሰውን ጕዳት ስለማውቅ ነው፤ ምሽጎቻቸውን በእሳት ታቃጥላለህ፤ ጕል ማሶቻቸውን በሰይፍ ትገድላለህ፤ ሕፃናታ ቸውን በምድር ላይ ትፈጠፍጣለህ፤ ያረገዙ ሴቶቻቸውንም ሆድ ትቀድዳለህ” አለው።

13አዛሄልም፣ “ለመሆኑ እንደ ውሻ የሚ ቈጠር አገልጋይህ ይህን ጀብዱ መፈጸም እንዴት ይችላል?” አለ።

ኤልሳዕም መልሶ፣ “አንተ በሶርያ ላይ እንደምትነግሥ *እግዚአብሔር* አሳይቶኛል” አለው።

14ከዚያም አዛሄል ከኤልሳዕ ዘንድ ወጥቶ ወደ ጌታው ተመለሰ፤ ቤንሀዳድም፣ “ለመ ሆኑ ኤልሳዕ ምን አለህ?” ሲል ጠየቀው፤ አዛሄልም፣ “በእርግጥ ከበሽታህ እንደም ትድን ነግሮኛል” አለው። 15በማግስቱ ግን ወፍራም ልብስ ወስዶ በውሃ ከነከረ በኋላ የንጉሡን ፊት ሸፈነው፤ ንጉሡም በዚሁ ሞተ፤ ከዚያም አዛሄል በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

8፥10 ኢሳ38፥1
8፥11 መሳ3፥25፤ ሉቃ19፥41
8፥12 ዘፍ34፥29፤ 1ነገ19፥17፤2ነገ 15፥16፤መዝ137፥9፤ ኢሳ13፥16፤ ሆሴ13፥16፤አሞ 1፥13፤ናሆ3፥10፤ ሉቃ19፥44
8፥13 1ሳሙ 17፥43፤2ሳሙ3፥8፤ 1ነገ19፥15
8፥15 2ነገ1፥17
8፥16 2ነገ1፥17፤ 2ዜና21፥14
8፥18 ቍ26፤ 2ነገ11፥1
8፥19 ዘፍ6፥13፤ 2ሳሙ21፥17፤ ራእ21፥23
8፥20 1ነገ22፥47
8፥22 ዘፍ27፥40፤ ዘኍ33፥20፤ ኢሱ21፥13፤ 2ነገ19፥8

## የይሁዳ ንጉሥ ኢዮራም

8፥16-24 ተጓ.ምብ 2ዜና21፥5-10፡20

16የእስራኤል ንጉሥ የአክዓብ ልጅ ኢዮ ሆራም በነገሠ በአምስተኛው ዓመት፣ የኢ ዮሣፍጥ ልጅ ኢዮራም በይሁዳ ነገሠ። 17እርሱም ሲነግሥ ዕድሜው ሠላሳ ሁለት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ስምንት ዓመት ገዛ። 18*ያገባት* የአክዓብ ልጅ ስለነበረች የአክዓብ ቤት እንዳደረገው ሁሉ፣ እርሱም የእስራኤልን ነገሥታት መን ገድ ተከተለ፤ *በእግዚአብሔርም* ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ። 19ይሁን እንጂ ስለ ባሪያው ስለ ዳዊት ሲል፣ *እግዚአብሔር* ይሁዳን ሊያጠፋ አልፈለገም፤ ምክንያቱም ለዳዊትና ለዘሩ መብራት እንደማያሳጣ ተስፋ ሰጥቶ ነበርና።

20በኢዮራም ዘመነ መንግሥት፣ ኤዶምያስ በይሁዳ ላይ ዐምፆ የራሱን ንጉሥ አነገሠ። 21ስለዚህም ኢዮራም ሠረገሎቹን ሁሉ አስ ልፎ ወደ ጸዒር ዘመተ። ኤዶማውያንም እርሱንና የሠረገላ አዛዦቹን ከበቡ፤ እርሱና የሠረገላ አዛዦቹ ግን በሌሊት ተነሥተው ከበባውን ጥሰው ወጡ፤ ሰራዊቱም ሸሽቶ ተመለሰ። 22ኤዶምያስም እስከ ዛሬ ድረስ በይሁዳ ላይ እንደ ዐመፀ ነው፤ ልብናም በዚሁ ጊዜ ዐምፆ ነበር።

[1]10 ዕብራይስጡ “ሂድና፣ *በእርግጥ ለትድንም* በለው እንደሚሞት እግዚአብሔር ገልጦልኛል” ይላል።

ያመለክታል (6፥21፤1ሳሙ 25፥8 ይመ)።

8፥10 *መዳኑንስ በእርግጥ ትድናለህ*፤ ይህ አገላለጽ የቤን ሃዳድ መሞት በእግዚአብሔር ዘንድ የተቈረጠ መሆኑን የሚያመ ለክት ነው።

8፥12 *በእስራኤላውያን ላይ የምታደርሰውን ጕዳት*፤ በአ ዛሄል ሰይፍ በእስራኤል ላይ የሚመጣውን የእግዚአብሔርን ፍርድ ለኤልሳዕ እግዚአብሔር ቍልጭ አድርጎ አሳይቶት ነበር (9፥14-16፡10፥32፤12፥17-18፤13፥3፡22 ይመ)። *በእሳት ታቃጥላለህ ... ያረገዙ ሴቶቻቸውንም ሆድ ትቀድዳለህ*፤ በዚያ ዘመን ድል አድራጊ ወታደሮች እንዲህ ዐይነት ድርጊት ያደርጉ ነበር (15፥16፤ ሆሴ 10፥14፤13፥16 አሞ1፥13 ይመ)። የኤልሳዕ ቃል እንዲህ ዓይነት ድርጊቶችን የሚያስቀር ሳይሆን፣ አዛሄል ወደ ፊት እስራኤልን እንደሚወጋ የሚያመለክት ነው።

8፥13 *እንደ ውሻ የሚቈጠር አገልጋይህ ይህን ጀብዱ መፈጸም እንዴት ይችላል?* ክፉ ነገር እንደሚያደርግ መገለጹ አዛሄልን አላስደነገጠውም፤ ነገር ግን የተጨነቀው ይህን ሁሉ ለማድ ረግ የሚያስችለውን ኀይል ማግኘት እንዴት እንደሚችል ነበር። (“ውሻ” ለሚለው ተለዋጭ ዘይቤ የ2ሳሙ9፥8 ማብ ይመ)። *በሶርያ ላይ እንደምትነግሥ*፤ የኤልሳዕ ትንቢት በሕጉ መሠረት አዛሄል የቤንሃዳድ ወራሽ ሆኖ መንገሥ እንደማይገባው ያመለ ክታል። በአሦራውያን የድንጋይ ላይ ቅርጽ ጽሑፍ አዛሄል “የማ ንም ልጅ እንደ ሆነ የማይታወቅ” ተብሎአል፤ ይህም የተራ ሰው ልጅ ማለትና በኀይል ሥልጣንን የነጠቀ መሆኑን የሚያ መለክት ነው። አዛሄል በግምት ከ843-796 በዓ.ቅ.ክ ሶርያን ገዝቶአል።

8፥15 *ሞተ*፤ አዛሄል ንጉሥ እንደሚሆን ኤልሳዕ ትንቢት መናገሩ፣ አዛሄል ንጉሡን በመግደል መንግሥቱን የነጠቀበትን ድርጊት ሕጋዊ አያደርገውም። ይልቁንም አዛሄል ቤንሃዳድን መግደሉና በኋላም በእስራኤል ላይ የፈጸመው የዐመፅ ድርጊት፣ ኀጢአት ከተሞላው ከራሱ ልብ የወጣ ክፋት ነበር (ኢሳ 10፥5-19 ይመ)። የአዛሄልም ዘመነ መንግሥት በግምት በ842 እስከ 806 ዓ.ቅ.ክ. ወይም እስከ 769 ዓ.ቅ.ክ. ዘለቋል፤ ከዚያም ቤንሃዳድ በሚባል ልጁ ተተካ (13፥24 ይመ)።

8፥16 *ኢዮራም በነገሠ በአምስተኛው ዓመት*፤ በ848 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው። ኢዮራም ከ853 ዓ.ቅ.ክ ጀምሮ ከአባቱ ጋር በጋራ ይገዛ ነበር (የ1፥17 ማብ ይመ)፤ አሁን በዚህ በተጠቀሰው ዓመት ግን ራሱ ለብቻው መግዛት ጀመረ።

8፥17 *በኢየሩሳሌምም ... ስምንት ዓመት ገዛ*፤ ኢዮራሆም ብቻውን የገዛበት ዘመን ከ848 -841 ዓ.ቅ.ክ. ነበር።

8፥18 *የአክዓብ ቤት እንዳደረገው ሁሉ*፤ አክዓብ ወደ ሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት የበአልን አምልኮ እንዳስገባ ሁሉ (11፥18 ይመ)፣ ኢዮሆራምም በደቡቡ የይሁዳ መንግሥት እንዲሁ አደረገ። በሰሜኑ መንግሥት የአክዓብ ልጅ ኢዮራም የበአልን አምልኮ ሲከለክል (3፥1-2 ይመ)፣ በተቃራኒው በደቡብ መን ግሥት በተመሳሳይ ጊዜ፣ በኢዮሣፍጥ ልጅ በኢዮሆራም ዘመን መስፋፋት ቀጠለ። *ያገባት የአክዓብ ልጅ ስለነበረች*፤ የኢ ዮራሆም ሚስት ጎቶልያ ስትሆን፣ አክዓብ ከኤልዛቤል ሳይሆን ከሌላ ሴት የወለዳት ሳትሆን አትቀርም (ቍ26፤ 2ዜና18፥1 ይመ)። ጎቶልያ በኢዮራሆም አገዛዝ ላይ ያደረገችው ተጽዕኖ ኤልዛቤል በአክዓብ አገ ዛዝ ላይ ካደረገችው ጋር በእጅጉ ይመሳሰላል (1ነገ16፥31፤18፥4፤19፥1-2 2ዜና21፥6 ይመ)።

8፥19 *ስለ ዳዊት ... መብራት*፤ የ1ነገ 11፥36 ማብ ይመ፤ መዝ 132፥ 17 ይመ። እግዚአብሔር ለዳዊት ቤት ከገባው ኪዳን የተነሣ፣ በአክዓብ ቤት ያመጣውን ፍርድ ከይሁዳና ከመንግሥቱ አስቀረ (2ሳሙ 7፥16፡29፤2ዜና 21፥7 ይመ)።

8፥20 *የራሱን ንጉሥ አነገሠ*፤ ከዚህ ቀደም ኤዶም ለይሁዳ በመገበር በተወካይ ይገዛ ነበር (የ3፥9 ማብ እና 1ነገ 22፥47 ይመ)።

8፥21 *ሰራዊቱም ሸሽቶ ተመለሰ*፤ ኢዮሆራምና ሰራዊቱ የኤዶምያስን ከበባ ቈርጠው ማለፍ ቢችሉም፣ በጽኑ ስለ ተሸነፉ ወደ ግዛታቸው ለማፈግፈግ ተገደዱ።

8፥22 *እስከ ዛሬ ድረስ*፤ የአንደኛና የሁለተኛ ነገሥትን መጽሐፍ የጻፈው ሰው፣ የኢዮሆራምን ታሪክ እስከ ጻፈበት እስከዚህ ጊዜ ድረስ ማለት ነው። በኋላም የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ በኤዶምያስ ላይ ከፍተኛ ጥቃት አደረሰ (14፥7)፤ በእርሱ እግር የተተካውም ዓዛርያስ የኤ ዶምያስን ግዛት አቋርጦ እስከ ኤላት የሚዘልቀውን የንግድ መስመር ተቈጣጠረ (14፥22፤2ዜና 26፥2)። *ልብናም በዚሁ ጊዜ ዐመፆ ነበር*፤ ከለኪሶ አጠገብ ከምት ገኘው ከፍልስጥኤም ድንበር ቅርብ የሆነች አገር ነበረች (19፥8 ይመ)። የልብና ዐመፅ በ2ዜና 21፥16-17 ላይ ከተጠቀሰው ከፍልስጥኤማውያንና ከዐረባውያን ዐመፅ ጋር የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም።

23በኢዮራም ዘመነ መንግሥት የተከናወ
ነው ሌላው ነገር ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት
ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን? 24ኢዮራ
ምም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ እንደ እነር
ሱም ሁሉ በዳዊት ከተማ ተቀበረ። ልጁ
አካዝያስም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስ

8፥25-29 ተጓ ምብ - 2ዜና22፥1-6

25የእስራኤል ንጉሥ የአክዓብ ልጅ ኢዮ
ራም በነገሠ በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት፣
የኢዮሆራም ልጅ አካዝያስ በይሁዳ ነገሠ።
26አካዝያስ ሲነግሥ ዕድሜው ሀያ ሁለት
ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም አንድ
ዓመት ገዛ። እናቱ ጎቶልያ ትባላለች፤ እር
ስዋም የእስራኤል ንጉሥ የዖምሪ የልጅ ልጅ
ነበረች። 27አካዝያስ ከአክዓብ ቤተሰብ ጋር
በጋብቻ የተሳሰረ ስለ ነበር፣ የአክዓብ ቤት
እንዳደረገው ሁሉ፣ እርሱም በአክዓብ ቤት
መንገድ ሄደ፤ *በእግዚአብሔርም ፊት* ክፉ
ነገር አደረገ።

28አካዝያስም ከአክዓብ ልጅ ከኢዮራም
ጋር ሆኖ በሶርያ ንጉሥ በአዛሄል ላይ ለመ
ዝመት ወደ ሬማት ዘገለዓድ ሄደ፤ ሶርያው
ያንም በዚያ ኢዮራምን አቈሰሉት። 29ስለዚህ
ንጉሥ ኢዮራም፣ በሬማት ከአዛሄል ጋር ባደ
ረገው ጦርነት ሶርያውያን ካደረሱበት ቍስል
ለማገገም ወደ ኢይዝራኤል ተመለሰ።

ከዚያም የአክዓብ ልጅ ኢዮራም ስለ ታመመ
የይሁዳ ንጉሥ የኢዮሆራም ልጅ አካዝያስ
ሊጠይቀው ወደ ኢይዝራኤል ወረደ።

## ኢዩ ተቀብቶ በእስራኤል ላይ ነገሠ

9 ነቢዩ ኤልሳዕ ከነቢያት ማኅበር አን
ዱን ጠርቶ እንዲህ አለው፤ "ወገብህን
ታጥቀህ፣ ይህን የዘይት ማሰሮ በመያዝ
በሬማት ወደምትገኘው ገለዓድ ሂድ። 2በዚ
ያም ስትደርስ የናሜሲን የልጅ ልጅ፣ የኢዮ
ሣፍጥን ልጅ ኢዩን ፈልገው። ወደ እርሱም
ቀርበህ ከጓደኞቹ ለብቻ ከነጠልኸው በኋላ፣
ወደ እልፍኝ አስገባው። 3ከዚያም ማሰሮ
ውን ይዘህ ዘይቱን በራሱ ላይ አፍስስና፣

8፥25 2ነገ9፥29
8፥26 ቍ18፤1ነገ
16፥23
8፥27 1ነገ15፥26፤
16፥30
8፥28 ዘዳ4፥43፤
2ነገ9፥1:14
8፥29 1ነገ19፥15:
17፤21፥29፤2ነገ9፥21፤
10፥13
9፥1 1ሳሙ10፥1:
5፤1ነገ18፥46፤2ነገ
8፥28
9፥3 1ነገ19፥16

9፥6 1ነገ19፥16
9፥7 ዘዳ4፥24፤ዘዳ
32፥43፤1ነገ18፥4፤
ራእ6፥10
9፥8 1ሳሙ25፥22፤
2ነገ10፥17
9፥9 1ነገ13፥34፤
14፥10፤16፥3
9፥10 1ነገ21፥23
9፥11 1ሳሙ10፥
11፤ዮሐ10፥20

*'እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ "እነሆ፤ እኔ
በእስራኤል ላይ እንድትነግሥ ቀባሁህ"'
ብለህ ዐውጅ። ከዚያም በሩን ከፍተህ ሩጥ፤
ፈጽሞ አትዘግይ።"

4ስለዚህ ጕልማሳው ነቢይ በሬማት ወደ
ምትገኘው ገለዓድ ሄደ። 5በዚያ እንደደረ
ሰም፣ የሰራዊቱ ጦር መኰንኖች በአንድ
ነት ተቀምጠው ነበር፤ እርሱም "መኰንን
ሆይ፤ ወደ አንተ ተልኬአለሁ" አለ።

ኢዩም፣ "ለማንኛችን ነው?" ሲል ጠየቀ።

እርሱም፣ "መኰንን ሆይ፤ ለአንተ ነው"
ብሎ መለሰ።

6ኢዩም ተነሥቶ ወደ ቤት ገባ፤ ከዚያም
ነቢዩ ዘይቱን በኢዩ ላይ አፈሰሰና እንዲህ
አለ፤ "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ '*በእግዚአብሔር* ሕዝብ በእስራኤል
ላይ እንድትነግሥ ቀብቼሃለሁ። 7የአገል
ጋዮቼን የነቢያትን ደም እንዲሁም *የእግዚ
አብሔርን* አገልጋዮች ደም ሁሉ ከኤልዛቤል
እጅ እበቀል ዘንድ አንተ የጌታህን የአክዓ
ብን ቤት ትመታለህ። 8የአክዓብ ቤት በሙሉ
ይጠፋል፤ ባሪያም ይሁን ተወላጅ፣ በእስራ
ኤል የሚገኘውን የመጨረሻ ወንድ ልጅ
ሁሉ ከአክዓብ እቈርጣለሁ። 9ከእንግዲህ
የአክዓብን ቤት፣ እንደ ናባጥ ልጅ እንደ
ኢዮርብዓም ቤት፣ እንደ አኪያም ልጅ እንደ
ባኦስ ቤት አደርገዋለሁ። 10ኤልዛቤልን ግን
በኢይዝራኤል እርሻ ውሾች ይበሏታል፤
የሚቀብራትም አይኖርም።'" ይህን ተናግ
ሮም መዝጊያውን ከፍቶ ሮጠ።

11ኢዩ ወጥቶ የጦር አለቆች ወደሆኑት
ጓደኞቹ እንደ ደረሰ፣ ከመካከላቸው አንዱ
"ሁሉም ነገር ሰላም ነው? ይህ እብድ ወደ
አንተ የመጣው ለምንድን ነው?" ሲል ጠ
የቀው።

ኢዩም "ሰውየውንም ሆነ የሚናገረውን
እናንተም ታውቃላችሁ" ሲል መለሰ።

12እነርሱም፣ "ይህማ ትክክል አይደለም
ይልቅስ እውነቱን ንገረን" አሉት።

ኢዩም እንዲህ አለ፤ "እርሱ የነገረኝማ ይህ

8፥23 *በኢዮሆራም ዘመነ መንግሥት የተከናወነው ሌላው ነገር፤* 2ዜና 21፥4-20 ይመ። *በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ 14፥29 ማብ ይመ።

8፥24 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1ነገ1፥21፤2ዜና21፥20 ማብ ይመ።

8፥25 *ኢዮራም በነገሠ በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት፤* በ 841 በዓ.ቅ.ክ ማለት ነው። በ9፥29 የተጠቀሰው የመጀመሪያው ዓመት ኢዮራም ወደ ሥልጣን የወጣበትን ጊዜ ሲያመለክት፣ ሁለተኛው ዓመት ደግሞ መንግሥቱን መግዛት የጀመረበትን የመጀመሪያውን ዓመት ያሳያል። እነዚህ ላይ ግን የዘመነ መንግሥቱን የመጀመሪያውን ዓመት ያመለክታል።

8፥26 *ሲነግሥ ዕድሜው ሃያ ሁለት ዓመት ነበረ፤* የ2ዜና 22፥2 ማብ ይመ። *ጎቶልያ፤* የቍ18 ማብ ይመ።

8፥27 *በአክዓብ ቤት መንገድ፤* 2ዜና 22፥3-5 ይመ።

8፥28 *አካዝያስም ... ከኢዮራም ጋር ... በአዛሄል ላይ ለመዝመት ወደ ሬማት ዘገለዓድ ሄደ፤* ኢዮሳፍጥ፣ ከአክዓብ ጋር ሆኖ ሶርያውያንን ሊዋጋ ወደ ሬማት ዘገለዓድ ሄደ (1ነገ 22)፣ አሁንም አካዝያስ አጎቱን ኢዮራምን በመከተል ተመሳሳይ ነገር አደረገ። በፊተኛው ጊዜ አክዓብ በጦርነቱ ሞተ (1ነገ 22፥37)፤ በዚህ ጊዜ ግን ኢዮራም ቈሰለ፤ በኢይዝራኤል በማገገም ላይ እን ዳለ (የ1ነገ 21፥1 ማብ ይመ)፣ እርሱና የወንድሙ ልጅ አካዝያስ ሁለቱም በኢዩ ተገደሉ (9፥14-28 ይመ)።

9፥1 *ከነቢያት ማኅበር፤* የ2፥3 ማብ ይመ።

9፥3 *እንድትነግሥ ቀባሁህ፤* የ1ሳሙ2፥10:9፥16:1ነገ19፥16 ማብ ይመ።

9፥7 *የአክዓብን ቤት ትመታለህ፤* ከብዙ ዓመት በፊት በአክዓብ ቤት ላይ ኤልያስ ፍርድን ሲናገር ኢዩ ራሱ ሰምቶአል፤ ስለዚህም ይህን ፍርድ ለመፈጸም በእግዚአብሔር መሾሙን ዐውቆአል (ቍ25፥26፤1ነገ21፥21-24 ይመ)። *የእግዚአብሔርን አገልጋዮች ደም ሁሉ ከኤልዛቤል፤* በኤልዛቤል ትእዛዝ ያላግባብ የፈሰሰውን እንደ ናቡቴና ቤተ ሰቡ ያለ የንጹሐንን ሰዎች ደም የሚያመለክት ነው (1ነገ 21፥13)።

9፥8 *ባሪያም ይሁን ተወላጅ፤* የ1ነገ14፥10 ማብ ይመ።

9፥9 *እንደ ኢዮርብዓም ቤት፤* 1ነገ14፥7-11:15፥27-30 ይመ። *እንደ ባኦስ ቤት፤* 1ነገ 1፥1-4:8-12 ይመ። ከዓመታት በፊት ኤልያስ ተመሳሳይ ቃል ለአክዓብ ተናግሮ ነበር (1ነገ 21፥21-24)።

9፥11 *ይህ እብድ፤* በሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ያሉ የጦር መሪዎች፣ በንቀት የነቢያትን ልጆች የሚጠሩበት ስያሜ ይመስላል።

ነው፤ ‘እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ “የእስ
ራኤል ንጉሥ እንድትሆን ቀብቼሃለሁ።’ ”
13ከዚያ ሁሉም ቶሎ ብለው ልብሳቸውን
እያወለቁ በሚራመድበት ደረጃ ላይ አነጠፉ፤
ከዚያም መለከት ነፍተው፣ “ኢዩ ነግሦአል”
አሉ።

## ኢዩ ኢዮራምንና አካዝያስን ገደለ

9፥21-29 ተጓ ምብ - 2ዜና22፥7-9

14ስለዚህ የናሜሲ የልጅ ልጅ፣ የኢዮሣ
ፍጥ ልጅ ኢዩ በኢዮራም ላይ አሤረ። በዚህ
ጊዜ ኢዮራምና እስራኤል ሁሉ በሬማት
የምትገኘውን ገለዓድን ከሶርያ ንጉሥ ከአዛ
ሄል ጥቃት ለማዳን ይጠብቁ ነበር። 15ንጉሥ
ኢዮራም ግን የሶርያን ንጉሥ አዛሄልን ጦር
ነት በገጠመው ጊዜ፣ ሶርያውያን ካደረሱ
በት ቍስል ለማገገም ወደ ኢይዝራኤል ተመ
ልሶ ነበር። ኢዩም፣ “እንግዲህ ሐሳባችሁ
እንዲህ ከሆነ፣ ይህን ነገር ወደ ኢይዝራ
ኤል ሄዶ እንዳይናገር፣ ማንም ሰው ከዚ
ህች ከተማ ሾልኮ እንዳይወጣ ጠብቁ”
አለ። 16ከዚያም በሠረገላው ተቀምጦ ወደ
ኢይዝራኤል ገሠገሠ፤ ይህን ያደረገውም ኢዮ
ራም በዚያ ስለተኛና የይሁዳ ንጉሥ አካዝ
ያስም እርሱን ለመጠየቅ ወደዚያው ስለወ
ረደ ነው።

17በኢይዝራኤል ግንብ ማማ ላይ የቆመው
ጠባቂ የኢዩ ወታደሮች መቅረባቸውን አይቶ፣
"እረ ወታደሮች መጡ!” በማለት ጮኸ
ተናገረ።

ኢዮራምም፣ “አንድ ፈረሰኛ ተጠርቶ፤
እንዲገናኛቸው ላኩትና፣ ‘የመጣችሁት በሰ
ላም ነውን?’ ብሎ ይጠይቅ” ሲል አዘዘ።

18ፈረሰኛውም ኢዩን ለመገናኘት ጋልቦ
ሄደና፣ “ንጉሡ፣ ‘የመጣችሁት በሰላም ነውን?’
ብሎአል” አለው።

ኢዩም፣ “ስለ ሰላም መጨነቅ የአንተ
ጕዳይ አይደለም! ይልቅስ ወደ ኋላ እለፍና
ተከተለኝ” አለው።

ጠባቂውም፣ “መልእክተኛው ከእነርሱ
ዘንድ ደርሶአል፤ ነገር ግን ተመልሶ አልመ
ጣም” ብሎ አሳወቀ።

19ስለዚህ ንጉሡ ሌላ ፈረሰኛ ላከ፤ ወደ
እነርሱ ዘንድ እንደ ደረሰም፣ “ንጉሡ፣
‘የመጣችሁት በሰላም ነውን?’ ይላል” አለው።

ኢዩም “ስለ ሰላም መጨነቅ የአንተ

9፥13 2ሳሙ15፥10፤ማቴ21፥8፤ ሉቃ19፥36
9፥14 ዘዳ4፥43፤ 2ነገ8፥28
9፥15 2ነገ8፥29
9፥16 2ዜና22፥7
9፥17 1ሳሙ 14፥16፤16፥4፤ ኢሳ21፥6
9፥20 2ሳሙ18፥27
9፥21 1ነገ21፥17፡ 15-19
9፥22 1ነገ18፥19፤ ራእ2፥20
9፥23 2ነገ11፥14
9፥24 1ነገ22፥34
9፥25 1ነገ21፥19- 22
9፥26 1ነገ21፥19- 29
9፥27 መሳ1፥27፤ 2ነገ23፥29

ጕዳይ አይደለም! ይልቅስ ወደ ኋላ እለፍና
ተከተለኝ” አለው።

20ጠባቂው፣ “መልእክተኛው ከእነርሱ ዘንድ
ደርሶአል፤ ነገር ግን ይህም ተመልሶ አል
መጣም፤ የወታደሮቹ መሪ ሠረገላ አነዳዱ
ልክ እንደ ናሜሲ ልጅ እንደ ኢዩ አነዳድ
ነው፤ ሲነዳም እንደ እብድ ነው” ሲል
አሳወቀ።

21ኢዮራምም፣ “በሉ ሠረገላዬን አዘጋጁ”
ብሎ አዘዘ። ሠረገላው እንደ ተዘጋጀም፣
የእስራኤል ንጉሥ ኢዮራምና የይሁዳ ንጉሥ
አካዝያስ በየሠረገሎቻቸው ሆነው ኢዩን
ለመገናኘት ሄዱ፤ የኢይዝራኤላዊው የናቡቴ
ርስት በነበረው እርሻ ላይም ተገናኙት።
22ኢዮራምም ኢዩን ገና ሲያየው፣ “ኢዩ፣
የመጣኸው በሰላም ነውን?” ሲል ጠየቀው።

ኢዩም፣ “የእናትህ የኤልዛቤል የጣዖት
አምልኮና መተት እንዲህ በዝቶ እያለ ምን
ሰላም አለ!” ሲል መለሰ።

23ኢዮራምም ሠረገላውን አዙሮ በመሸሽ፣
“አካዝያስ ሆይ፤ ይህ ክዳት ነው!”አለ።

24ከዚያም ኢዩ ቀስቱን በማስፈንጠር ኢዮ
ራምን በትከሻና ትከሻው መካከል ወጋው፤
ፍላጻውም ዘልቆ ልቡን ስለ ወጋው፣ ሠረገ
ላው ውስጥ ዘፍ ብሎ ወደቀ። 25ኢዩም የሠ
ረገላ ኀላፊውን ቢድቃርን እንዲህ አለው፤
“አንሣውና በኢይዝራኤላዊው በናቡቴ ዕርሻ
ላይ ጣለው፤ አንተና እኔ አባቱን አክዓብን
በየሠረገሎቻችን ሆነን ተከትለነው ስንሄድ፣
እግዚአብሔር ይህን ትንቢት እንዲህ ሲል
እንደ ተናገረበት አስታውስ፤ 26‘ትናንት
የናቡቴንና የልጆቹን ደም አይቻለሁ፤ ይላል
እግዚአብሔር፤ ይህንንም በዚሁ ዕርሻ ላይ
በእርግጥ አንተው እንድትከፍል አደርግሃ
ለሁ፤ ይላል እግዚአብሔር፤’˥ አሁንም በእግ
ዚአብሔር ቃል በተነገረው መሠረት አንሣ
ውና በዚሁ ዕርሻ ውስጥ ጣለው።”

27የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስም ይህን ሲያይ፣
ወደ ቤት ሀጋን በሚያወጣው መንገድ
ሸሸ፤^ኢዩም እያሳደደ ድምፁን ከፍ አድ
ርጎ፣ “እርሱንም ግደሉት!” አለ። እነርሱም
በይብለዓም ከተማ አጠገብ በጉር ዐቀበት
መንገድ ላይ በሠረገላው ውስጥ እንዳለ
አቈሰሉት፤ እርሱ ግን ወደ መጊዶ ሸሽቶ፤

˥26 1ነገ2፥19 ይመ ^27 *ወይም በአትክልቱ ስፍራ በሚገኘው በኩል ሸሸ።*

9፥15 *ወደ ኢይዝራኤል ሄዶ እንዳይናገር፣ ማንም ሰው ከዚህች ከተማ ሾልኮ እንዳይወጣ፤* ኢዩ በጀመረው ዐመፅ ድል እንዲያደርግና የሕዝብ ዐመፅም እንዳይነሣ ለማገድ፣ ኢዮራምን ድንገት ሳያስበው መያዝ አስፈላጊ ነበር።

9፥16 *ኢይዝራኤል፤* ከሬማት ዘገለዓድ 72 ኪሎ ሜትር ያህል የሚርቅ ስፍራ ነው። *አካዝያስም እርሱን ለመጠየቅ ወደዚያው ስለወረደ፤* 8፥29 ይመ።

9፥18 *ይልቅስ ወደ ኋላ እለፍና ተከተለኝ፤* ኢዮራምን ለመያዝ አስቦ የተነሣበት ዓላማ እንዲታወቅበት ኢዩ ጨርሶ ጊዜ አልሰጠም።

9፥21 *የናቡቴ ርስት በነበረው ዕርሻ፤* የ1ነገ21፥2-3፡13፡19 ማብ ይመ።

9፥22 *የጣዖት አምልኮና መተት፤* እነዚህ ሁለት ኀጢአቶች የሞት ቅጣት የሚገባቸው ናቸው (ዘዳ13፤18፥10-12 ይመ)፤ እነዚህ ክፉ ሥራዎች በሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት እስከተስፋፉ ድረስ፣ ሰላም በምንም መንገድ ሊገኝ አይችልም።

9፥26 *በእግዚአብሔር ቃል በተነገረው መሠረት፤* ኢዩ ከዓመታት በፊት በኤልያስ የተነገረውን የትንቢት ቃል ለመፈጸም የተቀመጠ ሰው አድርጎ ራሱን ይመለከት ነበር (1ነገ 21፥18-24 ይመ)። የአክዓብ ደም በናቡቴ ዕርሻ ውስጥ ባይፈስም (የ1ነገ 21፥29 እና ማብ ይመ)፣ በኢዮራም ሞት የኤልያስ ትንቢት ተፈጽሞአል ብሎ ኢዩ አሰበ (የ1ነገ 21፥19 ማብ ይመ)።

9፥27 *ወደ መጊዶ ሸሸቶ፣ በዚያው ሞተ፤* የአክዓብን ቤት ለማጥፋት ሲል (ሆሴ 1፥4)፣ ኢዩ በአክዓብ ልጅ በጎቶልያ በኩል የዳዊትን ቤት (8፥18፡26 ይመ) አጥፍቶ ይሁን ወይም አይሁን አይታወቅም።

እዚያው ሞተ። [28]አገልጋዮቹም በሠረገላ
አድርገው ወደ ኢየሩሳሌም ወሰዱት፤ በዳዊ
ትም ከተማ ከአባቶቹ ጋር በመቃብሩ
ቀበሩት። [29]አካዝያስ በይሁዳ የነገሠው፣
የአክዓብ ልጅ ኢዮራም በነገሠ በዐሥራ
አንደኛው ዓመት ነበር።

## ኤልዛቤል ተገደለች

[30]ከዚያም ኢዩ ወደ ኢይዝራኤል ሄደ፤
ኤልዛቤልም ይህን በሰማች ጊዜ ዐይኗን
ተኳኵላ፣ ጠጕሯንም አስማምራ በመስኮት
ትመለከት ነበር። [31]ኢዩ የቅጥሩን በር
አልፎ ሲገባ፣ "ጌታህን የገደልህ አንተ
ዘምሪ የመጣኸው በሰላም ነውን?"[ሀ] ስትል
ጠየቀችው።
[32]ቀና ብሎ ወደ መስኮቱ ተመለከተና፣
"ማነህ አንተ? ማነው የሚተባበረኝ ሲል
ጮኾ ተጣራ። ሁለት ሦስት ጃንደረቦችም
ቍልቍል ወደ እርሱ ተመለከቱ፤ [33]ኢዩም፣
"ወደ ታች ወርውሩአት!" አለ። እነርሱም
ወረወሯት። ፈረሶቹ ሲረጋግጧትም ደሟ
በግንቡና በፈረሶቹ ላይ ተረጨ።
[34]ኢዩም ገብቶ በላ፤ ጠጣም። ከዚያም፣
"ምንም ቢሆን የንጉሥ ልጅ ናትና ይህችን
የተረገመች ሴት በሚገባ ቅበሯት" አለ።
[35]ሊቀብሯት ሲወጡ ግን ከራስ ቅሏ፣ ከእግ
ሯና ከእጇ በቀር ሌላ ያገኙት አልነበረም።
[36]ተመልሰውም ይህን ሲነግሩት፣ ኢዩ እን
ዲህ አለ፤ "እግዚአብሔር ለባሪያው ለቴስቢ
ያዊው ለኤልያስ፣ 'በኢይዝራኤል ምድር
ዕርሻ ውስጥ ውሾች የኤልዛቤልን ሥጋ ይበ
ሉታል፤[ለ] [37]ሥጋዋም በኢይዝራኤል ምድር
ዕርሻ ውስጥ እንደ ፍግ ስለሚሆን፣ ማንም
ሰው፣ 'ይህች ኤልዛቤል ናት' ሊል አይች
ልም ብሎ የተናገረው ቃል ይህ ነው።"

## የአክዓብ ቤተሰቦች ተገደሉ

**10** በዚህ ጊዜ አክዓብ በሰማርያ ሰባ
ወንዶች ልጆች ነበሩት፤ ስለዚህ ኢዩ
ደብዳቤ ጽፎ ለኢይዝራኤል ሹማምንት፣[መ]
ለሽማግሌዎችና የአክዓብን ልጆች ለሚያሳ
ድጉ ሞግዚቶች ወደ ሰማርያ ላከ፤ መልእክ
ቱም እንዲህ የሚል ነበር፤ [2]"የጌታችሁ
ልጆች ከእናንተ ጋር ስለሆኑ፣ ሠረገሎችና
ፈረሶች፣ የተመሸገች ከተማና መሣሪያም
ስላላችሁ፣ ይህ ደብዳቤ እንደደረሳችሁ ወዲ
ያውኑ [3]ከጌታችሁ ልጆች መካከል ብልጫ
ያለውንና ተገቢ ነው የምትሉትን መርጣ
ችሁ በአባቱ ዙፋን አስቀምጡት። ከዚያም
ስለ ጌታችሁ ቤት ተዋጉ"
[4]እነርሱ ግን እጅግ ፈርተው ነበርና፣
"ሁለት ነገሥታት ሊቋቋሙት ያልቻሉትን
ሰው እኛ እንዴት ልንቋቋመው እንችላለን?"
አሉ።
[5]ስለዚህ የቤተ መንግሥቱ አዛዥ፣ የከተ
ማዪቱ ገዥ፣ ሽማግሌዎችና የልጆቹ ሞግዚ
ቶች፣ "እኛ ያንተው አገልጋዮች ነን፤ ትእዛ
ዝህን ሁሉ እንፈጽማለን፤ እኛ ማንንም አና
ነግሥም፤ ደስ የሚያሰኝህን ሁሉ አንተው
አድርግ" በማለት ይህን መልእክት ለኢዩ
ላኩ። [6]ከዚያም ኢዩ፣ "እንግዲህ የእኔ
ወገን ከሆናችሁና ከታዘዛችሁኝ የጌታችሁን
ልጆች ራስ ቈርጣችሁ ነገ በዚህ ሰዓት
ይዛችሁልኝ ወደ ኢይዝራኤል እንድትመጡ"
ሲል ደግሞ ጻፈላቸው።
በዚህም ጊዜ ሰባው የንጉሡ ልጆች
በከተማዪቱ ውስጥ ታዋቂ በሆኑ አሳዳጊ
ዎቻቸው ዘንድ ነበሩ። [7]ደብዳቤውም በደረ
ሳቸው ጊዜ፣ ሰዎቹ ሰባውን ልዑላን በሙሉ
ወስደው ገደሏቸው። ራሳቸውንም በቅርጫት
አድርገው ኢዩ ዘንድ ወደ ኢይዝራኤል
ላኩ። [8]መልእክተኛው እንደ ደረሰም፣ ለኢዩ፣
"የንጉሡን ልጆች ራስ አምጥተዋል" ብሎ
ነገረው።

9፥28 2ነገ14፥20፤ 23፥30
9፥29 2ነገ8፥25
9፥30 ኤር4፥30፤ ሕዝ23፥40
9፥31 1ነገ16፥9-10
9፥33 መዝ7፥5
9፥34 1ነገ16፥31
9፥36 1ነገ21፥23፤ መዝ68፥23፤ኤር 15፥3
9፥37 መዝ83፥10፤ ኢሳ 5፥25፤ኤር 8፥2፤9፥22፤16፥4፤ 25፥33፤ሶፎ1፥17
10፥1 ቍ5፤መሳ 8፥30፤1ነገ13፥32፤ 21፥1
10፥5 ኢሱ9፥8
10፥7 2ሳሙ4፥8፤ 1ነገ21፥21

[ሀ]31 ወይም፣ *ጌታውን የገደለው ዘምሪ ሰላም አለውን?* [ለ]36 1ነገ 21፥23 ይመ [መ]1 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ነገር ግን አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉሞችና የቩልጌት ቅጂ፣ *የከተማዪቱ* ይላሉ።

9፥31 *ጌታህን የገደልህ አንተ ዘምሪ፤* ምሬት በተሞላበት ሽሙጥ፣ ኤልዛቤል ኢዩን ዘምሪ ብላ ጠራችው። ከአርባ አምስት ዓመት በፊት ዘምሪ ኤላን በመግደል ዙፋን ያዘ፤ የባአስንም ቤት ሙሉ በሙሉ አጠፋ። ይሁን እንጂ ዘንበሪ ወደ ሥልጣን ከመ ምጣቱ በፊት ዘምሪ የገዛው ለሰባት ቀን ብቻ ነበር (1ነገ 16፥8-20 ይመ)።

*9፥36-37 ለባሪያው ለቴስቢያዊው ለኤልያስ ... የተናገረው ቃል ይህ ነው፤* ኤልዛቤል በዘመኗ ሁሉ የናቀችው የእግዚአብሔር ቃል (1ነገ 21፥23)፣ በአሟሟቷ ተረጋገጠ።

10፥1 *ሰማርያ፤* ኢዩ መንግሥቱን በአስተማማኝ ሁኔታ የመያዝ፣ የሰሜኑን መንግሥትም ሙሉ በሙሉ የመቈጣጠር ከፍተኛ ፍላጎት ነበረው፤ ይሁን እንጂ በሰማርያ ያሉትን ምሽጎች ማፍረስ ባለመቻሉ (1ነገ 16፥24 ማብ ይመ)፣ የአክዓብን ቤት ሙሉ በሙሉ ለመደምሰስ ከፍተኛ ችግር ገጥሞት ነበር። *አክዓብ ... ሰባ ወንዶች ልጆች ነበሩት፤* የአክዓብ ሚስቶች ቍጥር ምን ያህል እንደ ሆነ አይታወቅም (1ነገ 20፥5)። ልጆቹ ሰባ መሆ ናቸው፣ የልጆቹንና የልጅ ልጆቹን ቍጥር አጠቃሎ በመያዝ ይሆናል። *ሹማምንት፤* በንጉሡ የተሾሙትን መኳንንት ለማለት ነው (1ነገ 4፥1-6 ይመ)። *ሽማግሌዎች፤* በቤተሰብና፣ በነገድ ከነበራቸው ቦታ የተነሣ የአካባቢ መሪዎች የሆኑትን ለ ማመልከት ነው (የዘፀ 3፥16፤ 2ሳሙ 3፥17 ማብ ይመ)። *የአክዓብን ልጆች ለሚያሳድጉ፤* በንጉሣውያን ቤተሰብ ያሉትን ልዑላን የመንከባ ከብና የማሳደግ ኀላፊነት የነበራቸውን ለማለት ነው።

10፥3 *ስለ ጌታችሁ ቤት ተዋጉ፤* ኢዩ የበላይነቱን ለማረ ጋገጥና የሰማርያ መሪዎች እንዲገዙለት ወታደራዊ ኀይልን ለመጠቀም ያቀነባበረው ዘዴ ነው።

10፥4 *እጅግ ፈርተው፤* የሰማርያ መሪዎች በኢዩ የድፍረት ጥያቄ እጅግ ተሸብረው ነበር።

10፥5 *የቤተ መንግሥቱ አዛዥ፤* የ1ነገ 4፥6 ማብ ይመ። *የከተማዪቱ ገዥ፤* የከተማዪቱን ሕዝባዊ ሰራዊት ለመምራት በንጉሡ የተሾመ የጦር አዛዥ ሊሆን ይችላል። *ሽማግሌዎችና የልጆቹ ሞግዚቶች፤* የቍ 1 ማብ ይመ።

10፥6 *የጌታችሁን ልጆች ራስ ቈርጣችሁ ... እንድታመጡ* ኢዩ ይህን አስቸጋሪ ትእዛዝ የሰጠው ሆን ብሎ ነበር። "የጌታ ችሁ ልጆች ራስ" የሚለው ሐረግ ከሰባው የአክዓብ ልጆች ዋና የሆኑትን፣ ምናልባትም ለአዐልጋ ወራሽነት የሚመርጡትንና ከመካከላቸውም ልዩ ተሰጥዎ ያላቸውን የሚያመለክት፣ ያለዚያም ደግሞ የሰባውን ልጆች በሙሉ ራስ መቍረጥ ማለት ይሆናል።

10፥7 *ሰባውን ... ገደሏቸው፤* የከተማዪቱ መሪዎች መልእክቱን ቃል በቃል ፈጸሙት፤ ኢዩም ያለ ጥርጥር ተስፋ ያደረገው ይህንኑ ነበር። *ራሳቸውንም በቅርጫት አድርገው ወደ ኢዩ ዘንድ ... ላኩ፤* የሰማርያ መሪዎች ኢዩ እንዳዘዛቸው የልዑላኑን ራስ ይዘው ራሳቸው ወደ ኢይዝራኤል አላመጡም (ቍ6 ይመ)፤ ምናልባት ለሕይወታቸው ሰግተው ይሆናል።

10፥8 *በከተማዪቱ መግቢያ በር ላይ፣ ሁለት ቦታ ከምራችሁ ... አቈዩአቸው፤* ይህ አሠቃቂ ድርጊት ከአሦራውያንን የጭካኔ ሥራ በተለይም ጭካኔ ከተሞላው ከአሹርናሲፓልና ከሜልሳዊ ስልምናሶር አገዛዝ የተወረሰ ይመስላል።

ከዚያም ኢዩ፣ “በከተማዪቱ መግቢያ በር
ላይ ሁለት ቦታ ከምራችሁ እስከ ነገ
ጧት ድረስ አቈዩአቸው” ብሎ አዘዘ::
9በማግስቱም ጧት ኢዩ ወጥቶ በሕዝቡ ሁሉ
ፊት በመቆም እንዲህ አለ፤ “እናንተ ንጹሓን
ናችሁ፤ ጌታዬን ያሤርሁበትና የገደልሁት
እኔ ነኝ:: እነዚህን ሁሉ ግን የፈጃቸው ማን
ነው?
10እንግዲህ *እግዚአብሔር* በአክዓብ ቤት
ላይ ከተናገረው ቃል አንዲቱ እንኳ በም
ድር ላይ ወድቃ እንደማትቀር ዕወቁ::
*እግዚአብሔር* በባሪያው በኤልያስ የተናገረ
ውን ፈጽሞአል::” 11ስለዚህ ኢዩ ከአክዓብ
ቤት የቀረውን ሁሉ፣ ታላላቆቹን ሰዎች
በሙሉ፣ የቅርብ ወዳጆቹንና ካህናቱን
አንድም ሳይቀር በኢይዝራኤል ገደላቸው::
12ከዚያም ኢዩ ተነሥቶ ወደ ሰማርያ
ሄደ፤ ቤትኤከድ ወደተባለው የበግ ጠባቂ
ዎችም ቤት ሲደርስ፣ 13ከይሁዳ ንጉሥ
ከአካዝያስ ሥጋ ዘመዶች ጥቂቶቹን አግኝቶ፣
“እናንተ እነማን ናችሁ?” ሲል ጠየቃቸው፤
እነርሱም፣ “እኛ የአካዝያስ ሥጋ ዘመ
ዶች ነን፤ ንጉሣዊውን ቤተሰብና የእቴጌ
ይቱን ልጆች ለመጠየቅ ወደዚህ ወርደን
መጥተናል” አሉ::
14እርሱም፣ “ከነሕይወታቸው ያዟቸው!”
ሲል አዘዘ፤ ስለዚህ ከነሕይወታቸው ወስደው
በቤት ኤከድ ጕድጓድ አጠገብ አርባ ሁለ
ቱን ሰዎች ገደሏቸው፤ አንድ እንኳ አላስቀ
ረም::
15ከዚያም ተነሥቶ ሲሄድ የሬካብ ልጅ
ኢዮናዳብ ወደ እርሱ ሲመጣ መንገድ ላይ
አገኘው:: ኢዩም ሰላምታ ሰጥቶት “ልቤ
ለልብህ ታማኝ የሆነውን ያህል ያንተስ
ልብ ለልቤ እንዲሁ ታማኝ ነውን?” ሲል
ጠየቀው::
ኢዮናዳብም፣ “አዎን፤ ነው!” ብሎ መለሰ::
ኢዩም፣ “እንግዲያውስ እጅህን ስጠኝ”
አለው:: እጁንም ሰጠው፤ ከዚያም ኢዩ
ደግፎ ወደ ሠረገላው አወጣው::
16ኢዩም፣ “በል አብረን እንሂድና *ለእግዚ
አብሔር* ያለኝን ቅናት እይልኝ” አለው፤
ከዚያም በሠረገላው ይዞት ሄደ::
17ኢዩ ወደ ሰማርያ በደረሰ ጊዜ፣ ከአክዓብ
ቤተሰብ በዚያ የቀረውን ሁሉ ገደለ:: ለነቢዩ
ለኤልያስ በተነገረውም *የእግዚአብሔር* ቃል
መሠረት አጠፋቸው::

## የበኣል አገልጋዮች ተገደሉ

18ከዚያም ኢዩ ሕዝቡን ሁሉ በአንድነት
ሰብስቦ እንዲህ አለ፤ “አክዓብ በኣልን ያገ
ለገለው በጥቂቱ ነው፤ ኢዩ ግን ይበልጥ
ያገለግለዋል:: 19አሁንም የበኣልን ነቢያት
ሁሉ አገልጋዮቹንና ካህናቱንም በሙሉ
ጥሩልኝ:: ለባኣል ትልቅ መሥዋዕት ስለ
ማቀርብ አንድ ሰው እንኳ እንዳይቀር:: የማ
ይመጣ ሰው ቢኖር ግን በሕይወት አይኖ
ርም፤ ኢዩ ግን ይህን ማድረጉ የበኣልን
አገልጋዮች ለማጥፋት ተንኰል መፍጠሩ
ነበር::
20ኢዩም፣ “ለበኣል ክብር ጉባኤ ጥሩ”
አለ፤ እነርሱም ይህንኑ ለሕዝቡ አስታወቁ::
21ከዚያም በመላው እስራኤል መልእክት
ላከ፤ የበኣል አገልጋዮች በሙሉ መጡ፤
ማንም አልቀረም፤ ሁሉም ወደ በኣል ቤተ
ጣዖት ገቡ፤ የበኣል ቤተ ጣዖት ዳር እስከ
ዳር ሞላ:: 22ኢዩም የልብስ ቤቱን ኀላፊ፣
“ለበኣል አገልጋዮች ሁሉ አልባሳት አውጣ”
አለው፤ እርሱም አልባሳቱን አወጣላቸው::
23ከዚያም ኢዩ ከሬካብ ልጅ ከኢዮናዳብ
ጋር ወደ በኣል ቤተ ጣዖት ገባ:: የበኣልንም
አገልጋዮች፣ “እንግዲህ የበኣል አገልጋዮች
ብቻ እንጂ *የእግዚአብሔር* አገልጋዮች እዚህ
አብረዋችሁ አለመኖራቸውን አረጋግጡ”
አላቸው:: 24ከዚያም የሚቃጠል መሥዋዕ
ትና ሌላም መሥዋዕት ለማቅረብ ገቡ::
በዚህ ጊዜም ኢዩ፣ “በእጃችሁ አሳልፌ
ከሰጠኋችሁ ሰዎች አንድ እንኳ እንዲ
ያመልጥ ያደረገ በገመዱ ይገባበታል” ብሎ
በማስጠንቀቅ ውጭ ሰማንያ ሰዎች አዘጋጅቶ
ነበር::
25ኢዩ የሚቃጠለውን መሥዋዕት አቅርቦ
እንዳበቃ ጠባቂዎቹንና የጦር አለቆቹን፣
“ግቡና ግደሏቸው፤ ማንም እንዳያመልጥ”

10፥10 1ነገ 21፥29፤2ነገ9፥7-10
10፥11 ቍ14፤ ኢዮ18፥19፤ ሆሴ1፥4፤ሚል4፥1
10፥13 1ነገ 2፥19፤2ነገ8፥29፤ 2ዜና22፥8
10፥14 ቍ11
10፥15 1ዜና2፥55፤ዕዝ 10፥19፤ ኤር35፥2፡6፡14-19፤ሕዝ17፥18
10፥16 ዘኍ25፥13
10፥17 2ነገ9፥8
10፥18 መሳ2፥11
10፥19 1ነገ18፥19
10፥20 ዘፀ32፥5
10፥24 ኢሱ2፥14
10፥25 ዘፀ22፥20፤ 1ነገ18፥40፤2ነገ 11፥18

10፥9 *የገደልሁት እኔ ነኝ፤* የኢዮራምን መንግሥት ለመ ገልበጥ ኢዩ በግሉ ያደረገውን ሁሉ ፊት ለፊት ለሕዝብ ተና ገረ:: *እነዚህን ሁሉ ግን የፈጃቸው ማን ነው?* ኢዩ ባስተላለፈው ግልጽ ባልሆነ ትእዛዝ ለተገደሉት (የቍ6 ማብ ይመ) ለሰባው የአክዓብ ልጆች ተጠያቂ እርሱ ሳይሆን የሰማርያ መሪዎች መሆ ናቸውን ለማመልከት የቀረበ ነው::

10፥10 *በባሪያው በኤልያስ የተናገረውን፤* 1ነገ21፥20-24፡29 ይመ:: ኢዩ እስከ አሁን ለፈጸመው ብቻ ሳይሆን፣ ወደፊትም የአክዓብን ቤትና ተባባሪዎቹን ለማጥፋት በሚወስደው ርምጃ ሁሉ የአምላክ ፈቃድ የሚከናወንበት መሆኑን ለሕዝቡ አስታወቀ::

10፥11 *ታላላቆቹን ሰዎች በሙሉ፣ የቅርብ ወዳጆቹንና ካህናቱን፤* ኢዩ የተሰጠውን የኀላፊነት ገደብ አልፎ የማይገባውን አደረገ (9፥7፤ሆሴ1፥4 ይመ)፤ ይህንንም ያደረገው ከፖለቲካ አኳያ ከነበረው የግል የሥልጣን ፍላጎት የተነሣ ብቻ ነው:: ቀደም ሲል ኢዩ፣ አክዓብን አገልግሎ ነበር (9፥25 ይመ)::

10፥13 *ከአካዝያስ ሥጋ ዘመዶች፤* 2ዜና 21፥17 ይመ:: *ንጉሣዊውን ቤተሰብና የእቴጌይቱን ልጆች፤* የኢዮራምንና የኤልዛቤልን መሞት ያልሰሙ፣ ከይሁዳ የሆኑ የንጉሣዊ ቤተ ሰብ አባል ናቸው ::

10፥15 *የሬካብ ልጅ ኢዮናዳብ፤* ኢዮናዳብ በእስራኤል የሃ ይማኖት አክራሪዎች እንቅስቃሴ መሪ ሲሆን፣ ይህም እንቅስቃሴ የበኣል አምልኮን፣ በአንድ ስፍራ ተቀምጦ ዕርሻ ማረስን፣ ቤት መሥራትን፣ እህል መዝራትንና ወይን መጥመቅን የሚቃወም ነበር:: የኢዮናዳብ ተከታዮች ሬካባውያን በመባል ይታወቁ ነበር (ኤር35፥6-10)፤ እነርሱም ይህን መመሪያ ከሁለት መቶ ዓመት በላይ ተከትለዋል::

10፥16 *በሠረገላው ይዞት ሄደ፤* ኢዮናዳብን በሠረገላው ላይ አስቀምጦ በሕዝብ ፊት መታየቱ፣ ኢዩ በገጠር ነዋሪዎች ዘንድ የእግዚአብሔር ተከታይ እንደ ሆነ አስመስክሮለታል::

10፥18 *አክዓብ በኣልን ያገለገለው በጥቂቱ ነው፤ ኢዩ ግን ይበልጥ ያገለግለዋል፤* ኢዩ በሰማርያ ተረጋግቶ ከተቀመጠ በኋላ፣ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ያደረገው ሁሉ የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ ብቻ እንዳደረገው ያሳያል::

10፥19 *በሕይወት አይኖርም፤* ይህ አባባል የኢዩን ዝና አይቀንስም::

ሲል አዘዘ:: እነርሱም በሰይፍ ፈጇቸው፤ ጠባ
ቂዎቹና የጦር ሹማምንቱም ሬሳውን በሙሉ
ወደ ውጭ አውጥተው ጣሉ:: ከዚያም ወደ
ውስጠኛው የበኣል ቤተ ጣዖት ገቡ:: 26ከድ
ንጋይ የተሠሩትንም ማምለኪያ ምስሎች
ከበኣል ቤተ ጣዖት አውጥተው አቃጠሉ::
27 የበኣልን ማምለኪያ ምስል ቀጠቀጡ፤ የበ
ኣልንም ቤተ አምልኮ አፈረሱ፤ ይህንንም
ሕዝቡ እስከ ዛሬ ድረስ የኵስ መጣያው
አድርጎታል::
28በዚህ ሁኔታም ኢዩ የበኣልን አምልኮ
ከእስራኤል አስወገደ:: 29ይሁን እንጂ ኢዩ
የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም፣ በቤቴልና በዳን
የወርቅ ጥጃዎች እንዲያመልኩ እስራኤልን
ካሳተበት ኀጢአት አልራቀም::
30እግዚአብሔርም ኢዩን፣ “ቤቴ መልካም
የሆነውን ነገር ስላደረግህና በአክዓብም ቤት
ላይ እንዲደርስ በልቤ ያለውን ሁሉ ስለፈ
ጸምህ፤ ዘርህ እስከ አራት ትውልድ ድረስ
በእስራኤል ዙፋን ላይ ይቀመጣል”አለው::
31ነገር ግን ኢዩ የእስራኤልን አምላክ
የእግዚአብሔርን ሕግ በፍጹም ልቡ ለመጠ
በቅ ጥንቃቄ አላደረገም፤ ኢዮርብዓም፣ እስ
ራኤልን ካሳተበት ኀጢአት አልራቀምና::
32በዚያ ዘመን እግዚአብሔር የእስራኤልን
ምድር መቀናነስ ጀመረ:: አዛሄልም እስራ
ኤልን ዳር እስከ ዳር መታ:: 33ይኸውም
ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ያለውን የገለዓ
ድን ምድር ሁሉ ሲሆን፣ ይህም በአርኖን
ወንዝ አጠገብ ካለው ከአሮዔር አንሥቶ
የጋድን፣ የሮቤልንና የምናሴን አገር ገለዓ
ድንና ባሳንን ነበር::
34የቀረው በኢዩ ዘመነ መንግሥት የሆነው፣
ያደረገውም ሁሉ፣ ያከናወነውም ሥራ በሙሉ
በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ
አይደለምን?
35ኢዩ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በሰማርያ
ቀበሩት:: ልጁ ኢዮአካዝም በእግሩ ተተክቶ
ነገሠ:: 36ኢዩ በሰማርያ ተቀምጦ በእስራኤል
ላይ የነገሠው ሃያ ስምንት ዓመት ነበር::

10፥26 ዘፀ23፥24
10፥27 1ነገ16፥32
10፥28 1ነገ19፥17
10፥29 ዘፀ32፥4፤ 1ነገ12፥30፡32
10፥30 2ነገ15፥12
10፥31 ዘዳ4፥9፤ 1ነገ12፥30፤ምሳ4፥23
10፥32 1ነገ19፥17፤2ነገ13፥25፤መዝ 107፥39
10፥33 ዘኍ21፥13፤ 32፥34፤ዘዳ2፥36፤ መሳ11፥26፤ኢሳ17፥2
10፥34 1ነገ15፥31
11፥1 2ነገ8፥18
11፥2 መሳ9፥5፤ 2ነገ12፥1
11፥4 ቍ19

## ጎቶልያና ኢዮአስ

11፥1-21 ተጓ ምብ - 2ዜና10-23:21

11የአካዝያስ እናት ጎቶልያ ልጇ መሞ
ቱን በሰማች ጊዜ፣ ንጉሣዊውን ቤተ
ሰብ በሙሉ አጠፋች:: 2የንጉሥ ኢዮራም
ልጅ፣ የአካዝያስ እኅት ዮሳቤት ግን የአካ
ዝያስን ልጅ ኢዮአስን ሊገደሉ ከነበሩት
ልዑላን መካከል ሰርቃ ወሰደችው:: እንዳይ
ገድሉትም ከጎቶልያ በመደበቅ እርሱንና ሞግ
ዚቱን በአንድ እልፍኝ ሸሸገቻቸው:: 3ጎቶልያ
አገሩን በምትገዛበት ጊዜም ከሞግዚቱ ጋር ስድ
ስት ዓመት በእግዚአብሔር ቤት ተሸሸገ::
4በሰባተኛውም ዓመት ዮዳሄ ልኮ ካራ
ውያንንና ዘብ ጠባቂዎቹን የሚያዙትን
የመቶ አለቆች እርሱ ወዳለበት ወደ እግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስ እንዲመጡ አደ

10፥26 *ኣቃጠሉ፤* የአሼራን ምስል ዐምድ (የ1ነገ14፥15 ማብ ይመ)፣ ከማምለኪያ ዐምዱ ጋር ሊያመለክት ይችላል (1ነገ 16፥32-33 ይመ)::

10፥27 *የበኣልን ማምለኪያ ምስል፤* የ1ነገ14፥23 ማብ ይመ:: *እስከ ዛሬ ድረስ፣* የ8፥22 ማብ ይመ::

10፥29 *ኢዮርብዓም ... እስራኤልን ካሳተበት ኀጢአት፤* 1ነገ12፥26-32፡13፥33-34፤14፥16 ይመ::

10፥30 *በአክዓብም ቤት ላይ እንዲደርስ በልቤ ያለውን ሁሉ ስለ ፈጸምህ፤* በአክዓብ ቤት ላይ ፍርድን ለማምጣት፣ ኢዩ የእግዚአብሔር መሣሪያ ነበር፤ ይህን በማድረጉም ተመስግኖአል:: ይሁን እንጂ “የኢይዝራኤል እልቂት” በተባለው ከአክዓብ ጋር የተባበሩትን ሁሉ፣ እንዲሁም አካዝያስንና አርባ ሁለቱን የይሁዳ ልዑላን በመግደሉ በነቢዩ በሆሴዕ ተወግዞአል (ሆሴ1፥4 ይመ):: *አራት ትውልድ፤* በረከቱ በአራት ትውልድ መወሰኑ ኢዩ ለተ ወሰነ ጊዜም ቢሆን በመንግሥቱ ላይ መቈየቱን የሚያመለክት ነው:: ሆኖም ግን የእርሱ ሥርወ መንግሥት በሰሜኑ መንግሥት ከነበሩት ሌሎች ሥርወ መንግሥቶች ይልቅ ለረዥም ጊዜ ያውም ለአንድ መቶ ዓመት ያህል የዘለቀ ነበር:: ሥርወ መንግሥቱም የኢዮአካዝን፣ የኢዮአስን፣ የዳግማዊ ኢዮርብዓምንና የዘካርያስን ዘመነ መንግሥት ያጠቃልላል (የ15፥12 ማብ ይመ)::

10፥31 *የእግዚአብሔርን ሕግ በፍጹም ልቡ ለመጠበቅ ጥንቃቄ አላደረገም፤* የኢዩ ጽኑዕ ፍላጎት እግዚአብሔርን ለማገልገል ሳይሆን፣ ከፖለቲካ አኳያ በሰሜን መንግሥት ያለውን ሥልጣን እንዴት አድርጎ በአስተማማኝ ሁኔታ እንደሚይዝ ማመቻቸት ነበር:: በዚህ ሁኔታ በአክዓብ ቤት ላይ የመጣውን የእግዚአብሔርን ፍርድ ለራሱ ጥቅም በማድረጉ ተጠያቂ ነው::

10፥32 *እግዚአብሔር የእስራኤልን ምድር መቀናነስ ጀመረ፤* በዘሌዋውያን 26 እና በዘዳግም 28 የተዘረዘረው የኪዳኑ ርግማን ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው እስራኤል ከከነዓን እንዲወጡ በተገደዱ ጊዜ ነው:: ኢዩ በሚገዛበት ዘመንም በሰሜኑ መንግሥት ይህ ርግማን ጀምሮ ነበር (17፥7-18 ይመ)::

*10፥33፤* በዮርዳኖስ አካባቢ ያለው ምድር ሁሉ ለደማ ስቆ ሶርያውያንና ለአዛሄል አልፎ ተሰጠ::

10፥34 የቀረው በኢዩ ዘመነ መንግሥት የሆነው፤ በአሦር ገዥ በስልምናሶር ሣልሳዊ “ጥቁር ሐውልት” ላይ ኢዩ በ841 ዓ.ቅ.ክ በሰሜን መንግሥት ዙፋን ላይ ከወጣ በኋላ ብዙ ሳይቈይ ለአሦር ይገብር እንደ ነበር ተገልጾአል:: በዚሁ በአሦራውያን የድንጋይ ላይ ቅርጽ ጽሑፍ ኢዩን በስሕተት “የዘምሪ ልጅ” በሚል ተጠቅሶአል፤ ይህ ደግሞ ኢዩ ከሰማርያ ወይም ከእስራኤል ወገን መሆኑን ለመግለጽ የአሦሩ ገዥ ስልምናሶር የተጠቀመበት ዘዴ ሊሆን ይችላል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ግን በኢዩ ዘመነ መንግሥት ለአሦራውያን ግብር ስለ መክፈሉ የተጠቀሰበት ስፍራ የለም:: *በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ* የ1ነገ14፥19 ማብ ይመ::

10፥35 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1ነገ1፥21 ማብ ይመ:: *ልጁ ኢዮአካዝም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፤* ስለ ኢዮአካዝ ዘመነ መንግሥት 13፥1-9 ይመ::

10፥36 *ሃያ ስምንት ዓመት፤* ከ841-814 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው::

11፥1 *ጎቶልያ፤* የ8፥18 ማብ ይመ:: *ልጇ መሞቱን፤* 9፥27 ይመ:: *ንጉሣዊውን ቤተ ሰብ በሙሉ አጠፋች፤* ይህን ያደረገችው በይሁዳ ያለውን ዙፋን ለራሷ ለማድረግ ነው:: በዚህ ጊዜ በይሁዳ የሚገኙት ንጉሣዊ ቤተሰብ ቍጥራቸው እጅግ ተመናምኖ ነበር:: የጎቶልያ ባል የነበረውና የአካዝያስ አባት የሆነው ኢዮሆራም፣ የአባቱን የኢዮሣፍጥን ዙፋን ሲይዝ ወንድሞቹን በሙሉ ገድሎ ነበር (2ዜና21፥4 ይመ):: ኢዩ አርባ ሁለቱን የይሁዳ ንጉሣዊ ቤተሰቦ ችን በገደለ ጊዜ፣ ምናልባት የኢዮሆራም ወንድሞች ልጆችንም (10፥12-14፤2ዜና 22፥8-9) ጨምሮ ገድሎ ይሆናል:: ደግሞም የዐረብ ዘራፊዎች፣ የአካዝያስን ወንድሞች ገድለዋል (2ዜና 22፥1)፤ የጎቶልያም የማጥራት ግድያ በአካዝያስ ልጆች ላይ ይኸውም በልጅ ልጆቿ ላይ ያነጣጠረ ይመስላል:: አካዝያስ በሃያ ሁለት ዓመቱ ገና ወጣት ሳለ ሞተ (8፥26 ይመ):: የዳዊትን ቤት ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት የተወሰደው ርምጃ በመሲሑ በኩል የሚከናወነውን የእግዚአብሔርን የመቤዠት ዕቅድ መቃወም ነው (2ሳሙ 7፥11፡16፤ 1ነገ 8፥25 እና ማብ ይመ)::

11፥2 *የንጉሥ ኢዮራም ልጅ፣ የአካዝያስ እኅት፤* ዮሳቤት፣ ንጉሥ ኢዮሆራም ከጎቶልያ ሳይሆን ከሌላ ሴት የወለዳት በእናቷም በኩል የአካዝያስ እኅት ሳትሆን አትቀርም:: ዮሳቤት የሊቀ ካህናቱ የዮዳሄ ሚስት ነበረች (2ዜና22፥11 ይመ):: *እርሱንና ሞግዚቱን፤* የልጁ ዕድሜ ከአንድ ዓመት በላይ አልነበረምና ጡት መጥባት አላቋረጠም፤ ስለዚህ ሞግዚቱ አብራ ተሸሸገች (ቍ3፡21ይመ)::

11፥4 *በሰባተኛውም ዓመት፤* ጎቶልያ በገዛችበት ዘመን ማለት ነው:: *ዘብ ጠባቂዎቹን የሚያዙትን የመቶ አለቆች፤* በ2ዜና 23፥1 ላይ እስራኤላዊ የሆኑ የአምስት አዛዦች ስም ተጠቅሶአል:: *ካራውያን፤* በደቡብ ምዕራብ ትንሹ እስያ ካለችው ከካርያ የመጡ ቅጥር ወታደሮችና የቤተ መንግሥቱ የክብር ዘቦች ነበሩ:: *እርሱ ወዳለበት ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንዲመጡ አደረገ፤* በ2ዜና 23፥2 ላይ እንደተገለጸው በዚህ ሤራ

ረገ:: ከእነርሱም ጋር ቃል ኪዳን በማድረግ
*በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ውስጥ አስማ
ላቸው፤ ከዚያም የንጉሡን ልጅ አሳያቸው::
[5]እንዲህም ሲል አዘዛቸው፤ "እናንተ የምታ
ደርጉት ይህ ነው፤ በሦስት ምድብ ሆናችሁ
በሰንበት ዕለት ዘብ ከምትጠብቁት መካ
ከል አንዱ እጅ ቤተ መንግሥቱን ይጠ
ብቅ፤ [6]ሌላው ከሦስት አንዱ የሱርን በር
ይጠብቅ፤ የቀረው ሌላው አንድ ሦስተኛው
እጅ ደግሞ ቤተ መቅደሱን ተራ ገብቶ
ከሚጠብቀው ከዘብ ጥበቃው ኋላ ያለውን
በር ይጠብቅ:: [7]እናንተ እንደ ተለመደው
በሰንበት ዕለት ከዘብ ጥበቃ ነጻ የምትሆ
ኑት ሁለት ሦስተኛው እጅ ግን ንጉሡ ያለ
በትን ቤተ መቅደስ ጠብቁ:: [8]ሁላችሁም
መሣሪያችሁን ይዛችሁ በንጉሡ ዙሪያ ሁኑ፤
የሚቀርባችሁ ቢኖር[o] ግን ይገደል:: ንጉሡ
በሚወጣበትም ሆነ በሚገባበት ጊዜ ሁሉ
አትለዩት::"
[9]የመቶ አለቆቹም ካህኑ ዮዳሄ ያዘዘውን
ሁሉ አደረጉ፤ እያንዳንዳቸውም በሰንበት
ዕለት ለዘብ ጥበቃ የሚገቡትንና ከዘብ ጥበቃ
የሚወጡትን ጭፍሮቻቸውን ይዘው ወደ
ካህኑ ወደ ዮዳሄ መጡ:: [10]ካህኑም *በእግዚ
አብሔር* ቤት የነበረውን የንጉሥ ዳዊትን
ጦርና ጋሻ ለመቶ አለቆቹ ሰጣቸው:: [11]ወታ
ደሮቹም እያንዳንዳቸው መሣሪያቸውን ይዘው፣
ከቤተ መቅደሱ በስተ ደቡብ አንሥቶ እስከ
ሰሜን ድረስ በመሠዊያውና በቤተ መቅ
ደሱ አጠገብ በንጉሡ ዙሪያ ቆሙ::
[12]ዮዳሄም የንጉሡን ልጅ አውጥቶ ዘው
ዱን ጫነለት፤ የኪዳኑንም መጽሐፍ ሰጠው፣
መንገሡን ዐወጀ፤ ኢዮአስም ተቀብቶ ነገሠ::
ከዚያም ሕዝቡ፣ "ንጉሡ ሺህ ዓመት ይን
ገሥ" እያሉ በማጨብጨብ ደስታቸውን
ከፍ ባለ ድምፅ ገለጹ::
[13]ጎቶልያም የሰራዊቱንና የሕዝቡን ጩኸት
በሰማች ጊዜ ሕዝቡ ወዳለበት ወደ ቤተ
መቅደሱ ሄደች:: [14]እነሆ፤ በወጉ መሠረት
ንጉሡ በዐምዱ አጠገብ ቆሞ፣ ሹማምንቱና
መለከት ነፊዎቹ ከአጠገቡ ሆነው አየች::
የአገሩም ሕዝብ ሁሉ ይፈነጥዝ፣ መለከ
ትም ይነፋ ነበር:: ጎቶልያም ልብሷን ቀዳ፣
"ይህ ክዳት ነው! ክዳት ነው!" በማለት
ጮኸች::
[15]ካህኑ ዮዳሄም ጭፍሮቹን የሚያዙትን
የመቶ አለቆች፣ "በረድፍ በተሰለፉት ጭፍ
ሮች መካከል አውጧት፤[u] የሚከተላትንም
ሁሉ በሰይፍ በሉት" ሲል አዘዘ፤ ይህ የሆ
ነውም ካህኑ አስቀድሞ፣ "*በእግዚአብሔር*
ቤት መገደል የለባትም" በማለቱ ነበር:: [16]ስለ
ዚህ ፈረሶች ወደ ቤተ መንግሥቱ በሚገቡ
በት ስፍራ ስትደርስ፣ ይዘው እዚያው ገደ
ሏት::
[17]ዮዳሄም *የእግዚአብሔር* ሕዝብ ይሆኑ
ዘንድ *በእግዚአብሔርና* በንጉሡ በሕዝቡም
መካከል ቃል ኪዳን እንዲኖር አደረገ፤ እን
ደዚሁም በንጉሡና በሕዝቡ መካከል ቃል
ኪዳን መሠረተ::
[18]የአገሩም ሕዝብ ሁሉ ወደ በኣል ቤተ
ጣዖት ሄደው አፈራረሱት፤ መሠዊያዎቹንና
ምስሎቹን ሁሉ ሰባበሩ፤ የበኣልን ካህን
ማታንንም በመሠዊያዎቹ ፊት ለፊት ገደ
ሉት::
ከዚያም ካህኑ ዮዳሄ *የእግዚአብሔርን*
ቤተ መቅደስ የሚጠብቁ ዘበኞችን መደበ::
[19]ከዚያም መቶ አለቆቹን፣ ካራውያንንና
ዘበኞቹን እንዲሁም የአገሩን ሕዝብ በሙሉ
በመያዝ ሁሉም በአንድነት ሆነው፣ ንጉ
ሡን *ከእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ወስደው
በዘብ ጠባቂዎች ቅጥር በር በኩል ታች
ወዳለው ቤተ መንግሥት ይዘውት ገቡ፤ ንጉ
ሡም በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ፤ [20]የአገሩም
ሕዝብ ሁሉ ደስ አለው፤ ጎቶልያ ቤተ
መንግሥቱ ውስጥ በሰይፍ ተገድላ ስለ
ነበር፣ ከተማዪቱ ጸጥ አለች:: [21]ኢዮአስ
በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሰባት ዓመት ነበር::

## ኢዮአስ ቤተ መቅደሱን አደሰ

12፥1-21 ተጓ ምብ - 2ዜና24፥1-14፤24፥23-27

**12** ኢዩ በነገሠ በሰባተኛው ዓመት ኢዮ
አስ ነገሠ፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም
አርባ ዓመት ገዛ:: እናቱ ሳብያ የተባለች፤

[o]8 *ወይም፣ ወደ ትግራችሁ የሚደርስ ቢኖር* [u]15 *ወይም፣ ከትግ ራችሁ መካከል*

11፥5 1ነገ14፥27፤ 1ዜና9፥25
11፥10 2ሳሙ8፥7
11፥12 ዘፀ25፥16፤ 1ሳሙ9፥16፤10፥24፤ 1ነገ1፥39፤2ነገ23፥3፤ መዝ47፥1፤98፥8፤ ኢሳ55፥12
11፥14 ዘዳ37፥29፤ 1ነገ1፥39፤7፥15፤2ነገ 9፥23
11፥15 1ነገ2፥30
11፥16 ዘፍ4፥14፤ ነህ3፥28፤ኤር31፥40
11፥17 ዘፀ24፥8፤ 2ሳሙ5፥3፤2ነገ23፥3፤ 2ዜና15፥12፤23፥3፤ 29፥10፤34፥31፤ዕዝ 10፥3፤ኤር34፥8
11፥18 ዘዳ12፥3፤ 1ነገ16፥32፤18፥40፤ 2ነገ10፥25፤23፥20
11፥19 ቍ4
11፥20 ምሳ11፥10፤ 28፥12፤ 29፥2
12፥1 2ነገ11፥2

ሌዋውያንና የይሁዳ ቤተሰብ መሪዎች ይገኙበታል::

11፥10 *በእግዚአብሔር ቤት የነበረውን የንጉሥ ዳዊትን ጦርና ጋሻ፤* ዳዊት ምናልባት ከሱባ ንጉሥ ከአድርአዛር ጋር በተ ዋጋ ጊዜ የማረካቸውና ለእግዚአብሔር አሳልፎ የሰጣቸው ጦሮ ችና የወርቅ ጋሻዎች ሳይሆኑ አይቀሩም (2ሳሙ8፥7-11)::

11፥12 *የኪዳኑንም፤* ምናልባት (1) ዐሥርቱን ትእዛዛት (2) የሙሴን ሕግ በሙሉ (3) ወይም በኪዳኑ ውስጥ የንጉሥን ግዴታ የሚያመ ለክት ሊሆን ይችላል (ዘዳ17፥14-20፤የ1ሳሙ10፥25 ማብ ይመ):: ሦስተ ኛው ግምት በይበልጥ ትክክል ይመስላል:: *ተቀብቶ፤* የ1ሳሙ 2፥10፤ 9፥16፤1ነገ1፥39 ማብ ይመ:: *ንጉሡ ሺህ ዓመት ይነገሥ፤* 1ሳሙ 10፥24፤1ነገ1፥34፡39 ይመ::

11፥14 *በዐምዱ፤* ያቁምና በለዝ ከተባሉት በቤተ መቅደሱ ስበሰብ በግራና በቀኝ ከቆሙት ከሁለቱ የናስ ዐምዶች አንዱን ሳይሆን አይቀርም (23፥3፤ 1ነገ 7፥15-22፤ 2ዜና 23፥13 ይመ):: *የአገሩም ሕዝብ ሁሉ፤* ዮዳሄ የኀይል ርምጃ በመውሰድ ንጉሡን ለማንገሥ የፈለገበት ቀን ሰንበት ነበር፤ ይህም ከዋነኛ በዓሎች አንዱ ከመሆኑ የተነሣ፣ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ብዙዎች ከየአካባቢው መጥተው በኢየሩሳሌም የሚሰበሰቡበት ቀን ነበር::

11፥17 *የእግዚአብሔር ሕዝብ ይሆኑ ዘንድ፤ በእግዚአብሔርና በንጉሡ በሕዝቡም መካከል ቃል ኪዳን እንዲኖር አደረገ፤* የሙሴ ኪዳን ታድሶ እስራኤል እንደገና የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆነችበት ወቅት ነው (ዘፀ19፥5-6፤ዘዳ4፥20 ይመ):: የይሁዳ ሕዝብና ነገሥታቱ እግዚአብሔርን በሙተው የተግዘበት ታሪክ፣ የደበቡ መንግሥት ከእግዚአ ብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት በማደስ ቢታማኝነት እንዲጓዙ አነሣሥቶ አቸዋል (የ1ሳሙ 11፥14-15፡12፥14-15፡24-25 ማብ ይመ):: *በንጉሡና በሕዝቡ መካከል ቃል ኪዳን እንዲኖር አደረገ፤* እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር ካላቸው ኪዳናዊ ግንኙነት ጋር የሚነጻጸር፣ ንጉሡና ሕዝቡ አንዱ ለሌላው ሊኖረው በሚገባው ኀላፊነትና ግዴታ ላይ ቃል ኪዳን መደረጉን ያመለክታል (የ1ሳሙ10፥25፤2ሳሙ5፥3 ማብ ይመ)::

11፥18 *ምስሎቹን፤* የድንጋይ ዐምዶችና (የ1ነገ14፥23 ማብ ይመ) የአሼራ ምስል ዐምድ (የ1ነገ14፥15 ማብ ይመ) ናቸው::

11፥19 *መቶ አለቆቹን፣ ካራውያንንና ዘበኞቹን፤* የቍ4 ማብ ይመ::

11፥21፤ ቍ3 ይመ:: እግዚአብሔር ለዳዊት በኢየሩሳሌም መብራትን አኖረለት (1ነገ 11፥36 ይመ)::

12፥1 *ኢዩ በነገሠ በሰባተኛው ዓመት፤* በ835 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው (የ10፥36 ማብ ይመ):: *አርባ ዓመት፤* በ835-796 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው::

የቤርሳቤህ ከተማ ተወላጅ ነበረች። [2]ካህኑ
ዮዳሄ ያስተምረው በነበረበት ዘመን ሁሉ፣
ኢዮአስ *በእግዚአብሔር ፊት* መልካም ነገር
አደረገ። [3]ይሁን እንጂ የኰረብታ ማምለኪያ
ስፍራዎች አልተወገዱም፤ ሕዝቡም በእነዚህ
ቦታዎች መሠዋቱንና ማጠኑን እንደ ቀጠለ
ነበር።
[4]ኢዮአስ ካህናቱን እንዲህ አላቸው፤ "ከሕ
ዝብ ቈጠራ የተገኘውንና በስእለት የገባውን
እንዲሁም በራስ ፈቃድ ለቤተ መቅደሱ
የተሰጠውን የተቀደሰ ገንዘብ በሙሉ ሰብ
ስቡ። [5]እያንዳንዱም ካህን ገንዘቡን ከገንዘብ
ያዡ እጅ ይቀበል፤ እንደ አስፈላጊነቱም
በቤተ መቅደሱ ውስጥ የፈረሰውን ለማደስ
ይዋል።"
[6]ይሁን እንጂ እስከ ሃያ ሦስተኛው የኢ
ዮአስ ዘመነ መንግሥት ካህናቱ በቤተ
መቅደሱ ውስጥ የፈረሰውን አላደሱም
ነበር። [7]ስለዚህ ኢዮአስ ካህኑን ዮዳሄንና
ሌሎቹን ካህናት ጠርቶ፣ "በቤተ መቅደሱ
ውስጥ የፈረሰውን ያላደሳችሁት ለምንድን
ነው?" ሲል ጠየቃቸው፤ ቀጥሎም፣ "ከእን
ግዲህ ወዲያ ገንዘቡ በቤተ መቅደሱ ውስጥ
የፈረሰውን ለማደስ ይዋል እንጂ ከገንዘብ
ያዦች አትቀበሉ" አላቸው። [8]ካህናቱም
ከእንግዲህ ከሕዝቡ ገንዘብ ላለመሰብሰብና
ቤተ መቅደሱንም ራሳቸው ላለማደስ ተስ
ማሙ።
[9]ከዚያም ካህኑ ዮዳሄ አንድ ሣጥን ወስዶ
በመክደኛው ላይ ቀዳዳ አበጀለት፤ ወደ
*እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ በሚያስገባው
በስተቀኝ በኩል በመሠዊያው አጠገብ

12፥2 ዘዳ12፥25፤ 2ሳሙ8፥15
12፥3 1ነገ3፥3፤ 2ነገ18፥4
12፥4 ዘፀ25፥2፤ 30፡12፤35፥29፤ዘኍ 18፥19፤2ነገ22፥4
12፥5 2ነገ22፥5
12፥9 2ነገ25፥18፤ ኤር35፥4፤52፥24፤ ማር12፥41፤ሉቃ21፥1
12፥10 2ሳሙ8፥17
12፥12 2ነገ22፥5-6
12፥13 1ነገ7፥51
12፥15 2ነገ22፥7፤ 1ቆሮ4፥2
12፥16 ዘሌ4፥1-5፤ 5፥14-19፤7፥7

አኖረው። በሩን የሚጠብቁት ካህናትም
ወደ *እግዚአብሔር* ቤት የሚመጣውን ገን
ዘብ በሙሉ በሣጥኑ ውስጥ ያስገቡ ነበር።
[10]በሣጥኑም ውስጥ ብዙ ገንዘብ መኖሩን
በሚያዩበት ጊዜ ሁሉ፣ የንጉሡ ጸሐፊና ሊቀ
ካህናቱ መጥተው ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ የገባውን ገንዘብ ቈጥረው በየከ
ረጢቱ በማስገባት ቋጥረው ያኖሩት ነበር።
[11]የገንዘቡ ልክም ተመዝኖ ከታወቀ በኋላ፣
የቤተ መቅደሱን ሥራ በኀላፊነት እንዲያ
ሠሩ ለተመደቡት ሰዎች ገንዘቡን ያስጠ
ረክቧቸዋል፤ ይህም *የእግዚአብሔርን* ቤተ
መቅደስ ለሚሠሩ አናጢዎችና ግንበኞች፣
[12]ለድንጋይ ጠራቢዎችና ለድንጋይ ቅርጽ
አውጭዎች የሚከፈል እንዲሁም *የእግዚ
አብሔር* ቤተ መቅደስ ለሚታደስበት እን
ጨትና ጥርብ ድንጋይ መግዣ የሚውል
ነበር።
[13]ለቤተ መቅደሱ ከገባው ገንዘብ ግን
*ለእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ግልጋሎት
ለሚውሉ የብር ጽዋዎች፣ መኰስተሪያ
ዎች፣ ድስቶች፣ መለከቶችና ወይም ሌላ
ሎች የወርቅም ሆነ የብር ዕቃዎች መሥሪያ
አልዋለም፤ [14]የተከፈለው ግን ቤተ መቅደ
ሱን ለሚያድሱ ሠራተኞች ብቻ ነበር። [15]ለሠ
ራተኞቹ እንዲከፍሉ ገንዘቡ የተሰጣቸው
ሰዎች ፍጹም ታማኞች በመሆናቸው
ተቈጣጣሪ ማድረግ አላስፈለጋቸውም ነበር።
[16]ስለ በደል መሥዋዕትና ስለ ኀጢአት
መሥዋዕት የሚቀርበው ገንዘብ ግን የካህ
ናቱ በመሆኑ ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅ
ደስ አይገባም ነበር።

12፥2 *ካህኑ ዮዳሄ ያስተምረው በነበረበት ዘመን ሁሉ፤* ዮዳሄ ከሞተ በኋላ፣ ኢዮአስ ከእግዚአብሔር መንገድ ዘወር አለ (2ዜና 24፥17-27)።

12፥3 *ይሁን እንጂ የኰረብታ የማምለኪያ ስፍራዎች አልተወገዱም፤* እነዚህ ከፍታ ቦታዎች የጣዖት አማልክት የሚመለኩባቸው ሳይሆን፣ እግዚአብሔር የሚመለክባቸው ስፍራዎች ነበሩ (የ1ነገ15፥14 ማብ ይመ)፤ በኋላ ግን በእስራኤላውያን አምልኮ ውስጥ አንዳንድ የጣዖት አምልኮ ልምምዶች እንዲገቡ በር የከፈቱ ሳይሆኑ አልቀሩም (የ1ነገ 3፥2 ማብ ይመ)።

12፥4 *ለቤተ መቅደሱ የተሰጠውን የተቀደሰ ገንዘብ በሙሉ፤* ገንዘቡ የተሰበሰበው በሦስት የተለያዩ መንገዶች ነበር፤ (1) ከሕዝብ ቈጠራ የተገኘው፤ ሃያ ዓመት የሞላቸው እስራኤላውያን ወጣቶች ለውትድርና አገልግሎት መመዝገብና እያንዳንዳቸው ለቤተ መቅደሱ አገልግሎት የሚውል ግማሽ ሰቅል ስጦታ ማቅረብ ነበረባቸው (የ5፥26 ማብ ዘፀ30፥11-16፤38፥25-26፤ዘኍ 2፥32 ይመ)። (2) ከስእለት የገባ፤ የተለያዩ ስእለቶችና በገንዘብ ሲተመኑ ምን ያህል እንደሆኑ በዘሌ27፥1-25 በዝርዝር ተገልጾ አል። (3) በራስ ፈቃድ ለቤተ መቅደሱ የተሰጠ፤ በራስ ፈቃድ ስለሚቀርቡ ስጦታዎች ዘሌ22፥18-23፤ዘዳ16፥10 ይመ።

12፥5 *ከገንዘብ ያዡ፤* ሕዝቡ የሚያቀርበውን መሥዋዕትና ስጦታ ለቤተ መቅደስ አገልግሎት እንዲውል፣ በገንዘብ ጕዳይ ካህናቱን ከሚያግዙ አገልጋዮች አንዱ ነው። *በቤተ መቅደሱ ውስጥ የፈረሰውን ለማደስ፤* ኢዮአስ ከመንገሡ ከአንድ መቶ ሃያ አራት ዓመታት በፊት የቤተ መቅደሱ ግንባታ ተጠናቆ ነበር (ቍ1 እና የ1ነገ6፥38 ማብ ይመ)። ሆኖም ግን ብዙ ዘመን በመቈየቱ እንዲሁም በጐቶልያ ዘመን ባለመታደሱና እጅግ ከፍተኛ ጕዳት ስለደረሰበት መፈራረስ ጀምሮ ነበር (2ዜና 24፥7 ይመ)።

12፥6 *ሃያ ሦስተኛው የኢዮአስ ዘመነ መንግሥት፤* ኢዮአስ ቤተ መቅደሱን ለመጠገን ያቀደው ከዚህ ዘመን በፊት ነበር፤ አሁን ግን ዕድሜው ሠላሳ ዓመት በሆነ ጊዜ ሥልጣኑን በመጠቀም የቤተ መቅደሱን ጥገና ሥራ ጀመረ።

12፥7 *ከገንዘብ ያዦች አትቀበሉ፤* በቍ4 ላይ እንደ ተገለጸው ግብር መሰብሰብ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ገንዘብ ለካህናቱ ይሰጥ ነበር፤ ከዚህ በኋላ ግን ለካህናቱ እንዳይሰጥ ትእዛዝ ተሰጠ።

12፥8 *ካህናቱም ... ተስማሙ፤* በዚህ ስምምነት ካህናቱ ከእንግዲህ ገንዘብ ከሕዝቡ እንዳይቀበሉ ቢደረግም ከዚህ በፊት ቤተ መቅደሱን ለማደስ ሥራ ብለው ካህናቱ ስለተቀበሉት ገንዘብ ተጠያቂ ስለመሆናቸው የተነገ ነገር የለም።

12፥9 *በሩን የሚጠብቁት ካህናት፤* ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸው ሦስት ክህናት ሰው በማይገባው ሁኔታ ወደ ቤተ መቅደስ እንዳይገባ ለመከልከል ተሹመው ነበር (25፥18፤ኤር 52፥24 ይመ)። *ገንዘብ በሙሉ በሣጥኑ ውስጥ ያስገቡ፤* ሕዝቡ መባቸው ሙሉ በሙሉ ለቤተ መቅደሱ ጥገና እንደሚውል ማስተማመኛ በተሰጣቸው ጊዜ፣ በብዙ ልግስና መስጠት ጀመሩ። ይኸው ድርጊት በኢዮስያስም ዘመንም እንዲሁ ቀጥሎ ነበር (23፥3-7 ይመ)።

12፥10 *የንጉሡ ጸሐፊ፤* የ2ሳሙ 8፥17 ማብ ይመ። በቤተ መቅደሱ የሚካሄደውን የገንዘብ አስተዳደር በቀጥታ ለመቈጣጠር ንጉሥ ኢዮአስ ከቤተ መንግሥት ኀላፊ መድቦ ነበር።

12፥11 *ለተመደቡት ሰዎች፤* የቤተ መቅደሱ ጥገና ሥራ ሙሉ በሙሉ ከካህናቱ እጅ ወጣ።

12፥13 *ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ... የወርቅም ሆነ የብር ዕቃዎች፤* የተሰበሰበው ገንዘብ በመጀመሪያ የተመደበው ቤተ መቅደሱን ለመጠገን ነበር። የጥገና ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ላለው አገልግሎት ለሚያስፈልጉት የወርቅና የብር ዕቃዎች ተጨማሪ ገንዘብ አስፈለገ ነበር (2ዜና 24፥14 ይመ)።

12፥16 *ስለ በደል መሥዋዕትና ስለ ኀጢአት መሥዋዕት የሚቀርበው ገንዘብ፤* የበደል መሥዋዕት በሚቀርብበት ጊዜ ለካህናት ስለሚሰጠው ገንዘብ የተጠቀሰውን ዘሌ5፥16፤6፥5፤ዘኍ5፥7-10 ይመ። የኀጢአት መሥዋዕት በሚቀርብበት ጊዜ ለካህናት ስለሚሰጥ ገንዘብ በሙሴ መጻሕፍት የተጠቀሰ ነገር የለም፤ ይሁን እንጂ ዘሌ7፥7 ይመ።

[17]በዚህ ጊዜ የሶርያ ንጉሥ አዛሄል ወጣ፤
ጌትንም አደጋ ጥሎ ያዛት:: ከዚያም በኢ
የሩሳሌም ላይ አደጋ ለመጣል ፊቱን አዞረ::
[18]የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአስ ግን አባቶቹ የይ
ሁዳ ነገሥታት ኢዮሣፍጥ፣ ኢዮሆራም፣
አካዝያስ *ለእግዚአብሔር* ቀድሰው የለዩአ
ቸውን የተቀደሱ ዕቃዎች በሙሉ፣ እርሱ
ራሱ የቀደሳቸው ስጦታዎች እንዲሁም *በእ
ግዚአብሔር* ቤተ መቅደስና በቤተ መንግ
ሥቱ ዕቃ ቤቶች የተገኘውን ወርቅ ሁሉ
ሰብስቦ ለሶርያ ንጉሥ ለአዛሄል ላከለት፤
አዛሄልም ከኢየሩሳሌም ተመለሰ::
[19]ኢዮአስ በዘመነ መንግሥቱ ያከናወነው
ሌላው ተግባርና የፈጸመው ሥራ ሁሉ
በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ
አይደለምን? [20]ሹማምንቱም በእርሱ ላይ ዐመ
ፁበት፤ ቍልቍል ወደ ሲላ በሚወስደው
መንገድ ላይ በቤት ሚሎ ገደሉት:: [21]ገዳ
ዮቹ ሹማምትም የሰምዓት ልጅ ዮዛካርና
የሾሜር ልጅ ዮዛባት ነበሩ:: እርሱም ሞተ፤
እንደ አባቶቹም ሁሉ በዳዊት ከተማ
ተቀበረ:: ልጁ አሜስያስም በእግሩ ተተክቶ
ነገሠ::

## የእስራኤል ንጉሥ ኢዮአካዝ

**13** የይሁዳ ንጉሥ የአካዝያስ ልጅ ኢዮ
አስ በነገሠ በሃያ ሦስተኛው ዓመት፣
የኢዩ ልጅ ኢዮአካዝ በሰማርያ ከተማ በእ
ስራኤል ላይ ነገሠ፤ ዐሥራ ሰባት ዓመትም
ገዛ:: [2]እርሱም የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም
እስራኤልን ያሳተበትን ኀጢአት በመከተል
*በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ሥራ ሠራ፤ ከዚህ
ድርጊቱም አልተመለሰም:: [3]*የእግዚአብሔር*
ቍጣ በእስራኤል ላይ ነደደ፤ ስለዚህ የሶ
ርያ ንጉሥ አዛሄልና ልጁ ቤንሃዳድ በነበሩ
በት ዘመን ሁሉ አሳልፎ በእጃቸው ሰጣቸው::
[4]ከዚያም ኢዮአካዝ *እግዚአብሔርን* ለመነ፤
*እግዚአብሔርም* የሶርያ ንጉሥ እስራኤልን
እንዴት አድርጎ እንዳስጨነቀ አይቶአልና
ልመናውን ሰማው:: [5]ስለዚህ *እግዚአብሔር*
ለእስራኤል የሚታደጋቸውን ሰው ሰጠ፤
እነርሱም ከሶርያውያን ጭቍና ተላቀቁ፤
እንደ ቀድሞውም በየድንኳናቸው መኖር
ጀመሩ፤ [6]ይሁን እንጂ እስራኤልን ካሳተው
ከኢዮርብዓም ቤት ኀጢአት አልተመለ
ሱም፤ በዚያው ገፉበት:: የአሼራም ምስል
ዐምድ[*] በሰማርያ መመለኩ ቀጠለ::
[7]ከኢዮአካዝ ሰራዊት የተረፈው አምሳ
ፈረሰኞች፣ ዐሥር ሠረገሎችና ዐሥር ሺህ
እግረኛ ወታደር ብቻ ነው፤ ይህ የሆነበትም
ምክንያት የሶርያ ንጉሥ የቀረውን ስለ
አጠፋውና እንደ ዐውድማ ብናኝ ስለ አደ
ረገው ነበር::

12፥17 2ነገ8፥12
12፥18 1ነገ15፥18፡ 21፤2ነገ15፥20፤19፥3 6፤2ዜና21፥16-17
12፥20 መሳ9፥6፤ 2ነገ14፥5፡19፤15፥10፡ 14፡25፡30፤21፥23፤2 5፥25
13፥2 1ነገ12፥26-33
13፥3 ቍ24፤ዘዳ 31፥17፤1ነገ19፥17
13፥4 ዘኍ10፥9፤ ዘዳ4፥29፤26፥7፤2ሳ ሙ7፥10
13፥5 ዘፍ45፥7፤ ዘዳ28፥29፤መሳ2፥18
13፥6 1ነገ12፥30፤ 16፥33
13፥7 2ሳሙ22፥43፤ 2ነገ10፥32-33

[*]6 በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሁሉ ይህ የአሼራን ሴት ጣዖት የሚያመለክት ነው::

12፥17 *በዚህ ጊዜ፤* እነዚህ ሁኔታዎች የተከናወኑት ምናልባት በኢዮአስ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ላይ ነበር:: በ2ዜና 24፥17-24 በግልጽ እንደሚታየው፣ ሶርያውያን ጥቃት የሰነዘሩት ዮዳሄ ከሞተ በኋላ ኢዮአስ ከእግዚአብሔር ዘወር በማለቱ ነው:: የኢዮአስ ክህደት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው የዮዳሄን ልጅ ዘካርያስን በድንጋይ ባስወገረ ጊዜ ነበር (2ዜና 24፥22):: ቀደም ብሎ ኢዮአስ ቤተ መቅደሱን ለመጠገን የነበረውን ቅናት ስለሚያውቅ የነገሥት መጽሐፍ ጸሓፊ እነዚህን መጥፎ ድርጊቶች ለመጥቀስ የፈለገ አይመስልም:: *አዛሄል፤* (8፥7-15፡10፥32-33፡13፥3፡22 ይመ):: *ጌት፤* ከፍልስጥኤም ታላላቅ ከተሞች አንዱ ሲሆን (ኢሱ 13፥3)፣ ዳዊት አሸንፎ የያዘውና እስከ ኢዮርብዓም ዘመን ድረስ በይሁዳ ሥር ይተዳደር የነበረ ከተማ ነው (1ዜና18፥1፤2ዜና11፥8 ይመ):: በይሁዳ ንጉሥ በኢዮአስ ዘመነ መንግሥት የመጨረሻው ዓመታትና (ከ835-796 ዓ.ቅ.ክ) በእስራኤል ንጉሥ በኢዮአካዝ ዘመነ መንግሥት (ከ814-798 ዓ.ቅ.ክ) ሶርያውያን በግልጽ የሰሜኑን መንግሥት ወረሩ፤ ይህም ብዙ ችግር ሳይገጥማቸው ፍልስጤኤምንና የይሁ ዳን መንግሥት ተዋጉ (13፥3ና7 ይመ):: *በኢየሩሳሌም ላይ አደጋ ለመጣል ፊቱን አዞረ፤* 2ዜና24፥23-24 ይመ::

12፥18 *የተቀደሱ ዕቃዎች ... ወርቅ ... ለአዛሄል ላከለት፤* ቀደም ባሉት ዓመታት አሳ ከሶርያውያን ርዳታን ለማግኘት ይህን የመሰለ ስጦታ አድርጎ ነበር (1ነገ15፥18 ይመ)::

12፥19 *በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ14፥29 ማብ ይመ:: የኢዮአስ ዘመነ መንግሥት ሙሉ ታሪክ በ2ዜና22፥10-24፥27 ላይ ይገኛል::

12፥20 *በእርሱ ላይ ዐመፁበት፤* ዐመፁ የተነሣው፣ ኢዮአስ የካህኑን የዮዳሄን ልጅ ዘካርያስን ስለገደለ ነበር (2ዜና24፥25 ይመ):: *ቤት ሚሎ፤* ለሚሎ ትርጉም በመሳ 9፥6 ማብ ላይ የተጠቀሰውን ይመ:: ምናልባት እዚህ ላይ "ሚሎ" በተባለችው በዳዊት የጥንት ከተማ (2ሳሙ5፥9 እና ማብ፤ 1ነገ11፥27 ይመ) የተሠራውን ሕንጻ ወይም የወታደር መኖሪያዎችን የሚያመለክት ይሆናል:: ንጉሡ ከመገደሉ ጥቂት ቀደም ብሎ ከወታደሮቹ ጋር በዚህ ስፍራ ለጊዜው ተቀምጦም ይሆናል፤ ምክንያቱም በ2ዜና 24፥25 ላይ ንጉሡ በዐልጋው ላይ እንዳለ እንደ ተገደለ ተጠቅሶ አል:: *ሲላ፤* ከዳዊት ከተማ ወደ ቄድሮን ሸለቆ ቍልቍል የሚወርደውን መንገድ የሚያመለክት ይሆናል::

12፥21 *ሹማምንት፤* እናቶቻቸው አሞናውያንና ሞዓባውያን የሆኑ (2ዜና24፥26)፣ ባዕዳንን የሚያገለግሉ ቅጥረኛ የጦር መኰንኖችን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል:: *እንደ አባቶቹም ... ተቀበረ፤* 2ዜና 24፥25 ይመ:: *ልጁም አሜስያስ በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፤* ስለ አሜስያስ ዘመነ መንግሥት 14፥1-22 ይመ::

13፥1 *ኢዮአስ በነገሠ በሃያ ሦስተኛው ዓመት፤* በ814 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው (የ12፥1 ማብ እንዲሁም በ1ነገሥታት መግቢያ ሥር "የዘመን ቅደም ተከተል" የሚለውን ይመ):: *ዐሥራ ሰባት ዓመትም፤* 814-798 ድረስ ማለት ነው::

13፥2 *ኢዮርብዓም ... ኀጢአት፤* 1ነገ12፥26-32፤13፥33-34፡14፥16 ይመ::

13፥3 *አዛሄል፤* የ8፥12፡13፡15፤10፥33 ማብ ይመ:: *ቤንሃዳድ፤* ቍ24 ይመ:: የእርሱ ዘመነ መንግሥት በ806 ወይም በ796 ዓ.ቅ.ክ እንደ ተጀመረ ይገመታል::

13፥4 *እግዚአብሔርም ... ልመናውን ሰማው፤* በኢዮአካዝ ዘመን ከጠላቶቻቸው ነጻ ባይወጡም (ቍ22)፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ከገባው ቃል ኪዳን የተነሣ ሕዝቡ ምንም ያህል ኀጢአተኛ ቢሆንም እግዚአብሔር መሓሪ አምላክ ነበር (ቍ 23)::

13፥5 *ለእስራኤል የሚታደጋቸውን ሰው፤* ይህ ታዳጊ (1) ምናልባት የአሦር ገዥ ሓዳድኒራሪ ( በ810-783 ዓ.ቅ.ክ) ሊሆን ይችላል፤ እርሱም በ806 እና በ804 የደማስቆ ሶርያውያንን አጥቅቶ ስለነበር፣ በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን በሶርያውያን የተያዙባቸውን ግዛታቸውን ለማስለቀቅ ዕድል አግኝተው ነበር (ቍ25፡14፥25 ይመ)፤ (2) አለበለዚያም የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ (ቍ17፡19፡25)፤ (3) ወይም አሦራውያን የሶርያውያንን ወታደራዊ ይዞታ ካስለቀቁ በኋላ፣ የእስራኤልን ድንበር ወደ ሰሜን ያስፋፋው (14፥25፡27 ይመ) ዳግማዊ ኢዮርብዓም ሊሆን ይችላል::

13፥6 *የአሼራም ምስል ዐምድ ... መመለኩ ቀጠለ፤* ይህ ጣዖት የተተከለው በአክዓብ ነበር (1ነገ16፥33 ይመ)፤ ኢዩ የበአልን አምልኮ ከሰማርያ ባስወገደ ጊዜ ሳይፈርስ ቀርቶ ይሆናል (10፥27-28 ይመ) ወይም በኢዮአካዝ ዘመነ መንግሥት እንደ ገና ተተክሎ ሊሆን ይችላል::

13፥7 *ዐሥር ሠረገሎች፤* ጥቂት የፖሊስ ኀይል ለማለት ነው:: በአሦር ንጉሥ በሣልሳዊ ሻልማንኦር ታሪክ መጽሐፍ እንደ ተጠቀሰው፣ በቃርቃር ጦርነት ( በ853 ዓ.ቅ.ክ)አሦራውያንን ለመውጋት ተዘጋጅቶ ለነበረው የተባበረ ኀይል፣ አክዓብ ሁለት ሺህ ሠረገሎች አሰልፎ ነበር (የ1ነገ22፥1 ማብ ይመ):: *ዐሥር ሺህ እግረኛ ወታደር፤* በቃርቃር ጦርነት፣ አክዓብ አሦርን ለመውጋት ዐሥር ሺህ እግረኛ ወታደር ከተባበረው የጦር ኀይል ጎን አሰልፎ ነበር:: በዚያ ጊዜ ይህ ቍጥር የእስራኤልን የተወሰነ ሰራዊት ብቻ ይወክል ነበር፤ አሁን ግን የእስራኤልን እግረኛ አጠቃላይ የጦር ኀይል የሚወክል ቍጥር ሆኖ ቀርቦአል:: በ857 ዓ.ቅ.ክ አክዓብ በአንድ ቀን ጦርነት አንድ

8ኢዮአካዝ በዘመነ መንግሥቱ ያከናወነው
ሌላው ሥራ፣ ያደረገውና የፈጸመውም ሁሉ
በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ
አይደለምን? 9ኢዮአካዝ ከአባቶቹ ጋር አን
ቀላፋ፤ በሰማርያም ተቀበረ:: ልጁ ዮአስም
በእግሩ ተተክቶ ነገሠ::

**የእስራኤል ንጉሥ ዮአስ::**

10በይሁዳ ንጉሥ በኢዮአስ ዘመን፣ በሠ
ላሳ ሰባተኛው ዓመት፣ የኢዮአካዝ ልጅ
ዮአስ በሰማርያ ከተማ በእስራኤል ላይ ነገሠ፤
ዐሥራ ስድስት ዓመትም ገዛ:: 11እርሱም
*በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ሥራ ሠራ፤ የና
ባጥ ልጅ ኢዮርብዓም እስራኤልን ካሳተበት
ኀጢአት ሁሉ አልራቀም፤ በዚያው ገፋበት::
12ዮአስ በዘመነ መንግሥቱ ያከናወነው
ሌላ ሥራ፣ ያደረገውና የፈጸመው ሁሉ
እንዲሁም በይሁዳ ንጉሥ በአሜስያስ ላይ
ያካሄደው ጦርነት ጭምር በእስራኤል ነገ
ሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?::
13ዮአስም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ ኢዮር
ብዓም በእግሩ ተተክቶ በዙፋኑ ተቀመጠ::
ዮአስም በሰማርያ ከእስራኤል ነገሥታት
ጋር ተቀበረ::
14በዚህ ጊዜ ኤልሳዕ ለሞት ባደረሰው ሕመም
ታሞ ያጣጥር ነበር:: የእስራኤልም ንጉሥ
ዮአስ ሊጠይቀው ወርዶ አለቀሰለት፤ “ወየው
አባቴን! ወየው አባቴን! ወየው የእስራኤል
ሠረገሎችና ፈረሰኞች!” እያለም ጮኸ::
15ኤልሳዕም፣ “አንድ ቀስትና ፍላጾች
አምጣ” አለው፤ እርሱም አመጣ፤ 16የእስራ
ኤልንም ንጉሥ፣ “ቀስቱን በእጅህ ያዘው”
አለው፤ ቀስቱን በያዘውም ጊዜ ኤልሳዕ
እጆቹን በንጉሡ እጆች ላይ አኖረ::
17ቀጥሎም፣ “የምሥራቁን መስኮት ክፈት”
አለው፤ ከፈተውም፤ ኤልሳዕም፣ “በል
አስፈንጥረው” አለው፤ አስፈነጠረውም፤ ከዚ
ያም፣ “የ*እግዚአብሔር* የድል ቀስት! ሶርያ
ድል የምትሆንበት ቀስት!” አለ:: ኤልሳዕም
እንደገና “ሶርያውያንንም አፌቅ ላይ ፈጽ
መህ ድል ታደርጋቸዋለህ” አለው::
18ቀጥሎም፣ “በል ቀስቶቹን ውሰድ” አለው፤
ንጉሡም ወሰደ:: ኤልሳዕም፣ “መሬቱን
ውጋ” አለው:: እርሱም ሦስት ጊዜ ወግቶ
አቆመ::
19የእግዚአብሔርም ሰው ተቈጣውና፣ “መሬ
ቱን አምስት ወይም ስድስት ጊዜ መው
ጋት ነበረብህ፤ እንዲህ ብታደርግ ኖሮ ሶር
ያን ታሸንፍና ፈጽመህ ትደመስሳት ነበር፤
አሁን ግን የምታሸንፈው ሦስት ጊዜ ብቻ
ነው” አለው::
20ኤልሳዕ ሞተ፤ ቀበሩትም:: በዚህም ጊዜ
ሞዓባውያን አደጋ ጣዮች በየዓመቱ በጸደይ
ወራት ወደ እስራኤል ምድር እየሰረጉ ይገቡ
ነበር::
21አንድ ጊዜ እስራኤላውያን ሰው ሞቶ
ሲቀብሩ፣ አንድ የአደጋ ጣይ ቡድን በድን
ገት አዩ፤ ስለዚህ የሞተውን ሰው ሬሳ
ኤልሳዕ መቃብር ውስጥ ጣሉት፤ ሬሳው
የኤልሳዕን ዐፅም እንደ ነካም ወዲያውኑ
ሰውየው ድኖ በእግሩ ቆመ::
22በኢዮአካዝ ዘመነ መንግሥት ሁሉ፣
የሶርያ ንጉሥ አዛሄል፣ እስራኤልን ያስጨ
ንቃቸው ነበር:: 23*እግዚአብሔር* ግን ራራላ
ቸው፤ አዘነላቸው፤ ፊቱን መለሰላቸው፤
ይህም ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ
ጋር ስለ ገባው ኪዳን ሲል ነው፤ እስከ ዛሬ
ድረስ ሊያጠፋቸው አልፈለገም፤ ከፊቱም
አላስወገዳቸውም::

13፥12 1ነገ15፥31፤2ነገ14፥15
13፥13 2ነገ14፥23፤ ሆሴ1፥1
13፥14 2ነገ2፥12
13፥15 1ሳሙ 20፥20
13፥17 ኢሱ8፥18፤ 1ነገ20፥26
13፥19 ቍ25
13፥20 2ነገ5፥2
13፥21 ማቴ27፥52
13፥22 1ነገ19፥17
13፥23 ዘፀ2፥24፤ 33፥15፤ዘዳ29፥20፤ 2ነገ17፥18፤24፥3፡20

መቶ ሺህ የሶርያ እግረኛ ወታደር ላይ ጉዳት አድርሶ ነበር (1ነገ 20፥29 ይመ)::

13፥8 *በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ14፥19 ማብ ይመ::

13፥9 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1ነገ 1፥21 ማብ ይመ::

13፥10 *በኢዮአስ ዘመን፣ በሠላሳ ሰባተኛው ዓመት፤* በ798 ዓ.ቅ.ክ (የ12፥1 ማብ ይመ):: *ዐሥራ ስድስት ዓመትም፤* 798-782 ድረስ ማለት ነው::

13፥11 *ኢዮርብዓም ... ኀጢአት፤* 1ነገ12፥26-32፤13፥33-34፤14፥16 ይመ::

13፥12 *በአሜስያስ ላይ ያካሄደው ጦርነት፤* 14፥8-14፤ 2ዜና 25፥17-24 ይመ:: *በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ 14፥19 ማብ ይመ::

13፥13 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1ነገ1፥21 ማብ ይመ:: *ኢዮርብዓም በእግሩ ተተክቶ በዙፋኑ ተቀመጠ፤* ስለ ዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት 14፥23-29 ይመ::

13፥14 *ኤልሳዕ ታሞ ያጣጥር ነበር፤* ከዚህ በፊት በመጨረሻ ስለ ኤልሳዕ ተጠቅሶ የምናገኘው በምዕራፍ ዘጠኝ ላይ ነው:: በ841 ዓ.ቅ.ክ ኢዩ ተቀብቶ (የ10፥36 ማብ ይመ) ነገሠ፤ ኢዮአስ ደግሞ በ798 ዓ.ቅ.ክ መንገሥ ጀመረ (የቍ 10 ማብ ይመ)፤ ስለዚህ ኤልሳዕ ሲያደረገው አገልግሎት ሳይጠቀስ አርባ ሦስት ዓመት ሳይጠቀስ አልፏል ማለት ነው:: ከኤልያስ ጋር ያለውን ግንኙነት መሠረት በማድረግ፣ ኤልሳዕ ከ880 ዓ.ቅ.ክ በፊት ሳይወለድ አልቀረም፤ ስለዚህም ዕድሜው ከሰማንያ ዓመት በላይ ይሆናል ማለት ነው:: *የእስራኤል ሠረገሎችና ፈረሰኞች፤* ከእስራኤል የጦር ኀይል ይልቅ ኤልሳዕ ለጦር ኀይሉ ድል አድራጊነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደ ነበረው ዮአስ ገለጸ (የ2፥12ና6፥13፡16-23 ማብ ይመ)::

13፥16 *እጆቹን በንጉሡ እጆች ላይ አኖረ፤* በዚህ ትእምርታዊ ድርጊት አማካይነት ዮአስ የእግዚአብሔር በረከት በእርሱ ላይ ሆኖ ከአሦራውያን ጋር ጦርነት እንደሚገጥም ኤልሳዕ አመለከተ::

13፥17 *የምሥራቁን መስኮት፤* ከዮርዳኖስ ባሻገር ፊት ለፊት ሲሆን፣ በሶሪያውያን ቍጥጥር ሥር የሚገኝ ነው (10፥32-33 ይመ):: *አፌቅ፤* ከስድሳ ዓመት በፊት አክዓብ በአፌቅ ሶርያውያንና ዳግማዊ ቤንሃዳድ በከፍተኛ ድል አሸንፎአቸው ነበር (1ነገ 20፥26-30 እና የ1ነገ20፥26 ማብ ይመ)::

13፥18 *ሦስት ጊዜ ወግቶ አቆመ፤* ኤልሳዕ ለሰጠው መመሪያ ቀዝቀዝ ያለ ምላሽ በመስጠቱ፣ ኢዮአስ ለተሰጠው ኀላፊነት በቂ ትጋት እንዳልነበረው ያመለክታል::

13፥19 *የምታሸንፈው ሦስት ጊዜ ብቻ ነው፤* ኢዮአስ በቀስት መሬቱን ለመውጋት የነበረው ስሜት መጠነኛ ስለነበር፣ በሶርያውያንም ላይ የሚያገኘው ድል እንዲሁ መጠነኛ እንደሚሆን ያመለክታል:: የዮአስ ልጅ ዳግማዊ ኢዮርብዓም ነበር በሶርያውያን ላይ ሙሉ ድል ያገኘው (14፥25፡28 ይመ)::

13፥21 *ሬሳው የኤልሳዕን ዐፅም እንደ ነካም ወዲያውኑ ሰውየው ድኖ በእግሩ ቆመ፤* ኤልሳዕ የወከለው ሕይወትን የሚሰጠው የአምላክ ኀይል ስለ ኤልሳዕ በሚናገረው በመጨረሻው የብሉይ ኪዳን ክፍል ውስጥ እንደገና ተገለጠ (ከዚህ ቀደም ይህ ኀይል የተገለጠበትን ክፍል ለማወቅ 4፥32-37 እና 1ነገ 17፥17-24 ይመ፤ ኤልያስ ሳይሞት ወደ ሰማይ ስለመወሰዱ 2፥11-12 ይመ)::

13፥23 *እስከ ዛሬ ድረስ፤* የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ ጽሑፉን ያገኘበት ምንጭ እስከተጻፈበት ጊዜ ድረስ ማለት ነው (የ1ነገ 8፥8 ማብ እንዲሁም በ1ነገ መግቢያ ሥር “ጸሓፊ፣ ምንጭና የተጻፈበት ዘመን” የሚለውን ይመ):: *ሊያጠፋቸው አልፈለገም፤ ከፊቱም አላስወገዳቸውም፤* ጌታ በምሕረቱና በጸጋው፣ ሕዝቡን በመታገሥ የኪዳኑ ርግማን፣ የሆነው ከከነዓን መጋዝ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆን አላደረገም (የ10፥32 ማብ ይመ):: ይህ ፍርድ ተፈጻሚ ሳይሆን እንዲቆዩ መደረጉ፣ እስራኤል ንስሐ እንድትገባና ለኪዳኑ ታማኝ ሆና እንድትመለስ ዕድል ሰጣት::

24የሶርያ ንጉሥ አዛሄል ሞተ፤ ልጁ ቤን
ሃዳድም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ:: 25ከዚያም
የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ፣ አዛሄል ከአባቱ
ከኢዮአካዝ እጅ በጦርነት የወሰዳቸውን
ከተሞች ከአዛሄል ልጅ ከቤንሃዳድ አስመ
ልሶ ያዘ:: ዮአስ ሦስት ጊዜ ድል አደረገው፤
የእስራኤልንም ከተሞች በዚህ ሁኔታ መልሶ
ያዘ::

## የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ

14፥1-7 ተጓ ምብ - 2ዜና25፥1-4፤11-12
14፥8-22 ተጓ ምብ - 2ዜና25፥17- 26፥2

14 የእስራኤል ንጉሥ የኢዮአካዝ ልጅ
ዮአስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት፣
የይሁዳ ንጉሥ የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ ነገሠ::
2በነገሠም ጊዜ ዕድሜው ሃያ አምስት ዓመት
ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ሃያ ዘጠኝ
ዓመት ገዛ:: እናቱም ዮዓዳን የተባለች የኢ
የሩሳሌም ሴት ነበረች:: 3እርሱም *በእግዚ
አብሔር ፊት* መልካም ነገር አደረገ፤ ነገር
ግን አባቱ ዳዊት እንደ አደረገው ዐይነት
አልነበረም፤ በማናቸውም ረገድ የአባቱን
የኢዮአስን ፈለግ ተከተለ:: 4በየኰረብታው
ላይ ያሉት ማምለኪያዎች አልተወገዱም፤
ሕዝቡም በየኰረብታው ላይ መሥዋዕት
ማቅረቡንና ዕጣን ማጤሱን እንደ ቀጠለ
ነበር::

5አሜስያስ መንግሥቱን አጽንቶ ከያዘ
በኋላ፣ ንጉሡን አባቱን የገደሉትን ሹማም
ንት ገደላቸው፤ 6ይሁን እንጂ በሙሴ የሕግ
መጽሐፍ *እግዚአብሔር* [r]“እያንዳንዱ በራሱ
ኀጢአት ይገደል እንጂ አባቶች በልጆቻቸው፣
ልጆችም በአባቶቻቸው ኀጢአት አይገደሉ”
ሲል ያዘዘ በመሆኑ፣ የነፍስ ገዳዩን ልጆች
አልገደላቸውም::

7የጨው ሸለቆ በተባለው ቦታ ዐሥር ሺህ
ኤዶማውያንን ድል ያደረገ፣ ሴላን በጦር
ነት የያዘና እስከ ዛሬም ድረስ ዮቅትኤል
ተብላ የምትጠራበትን ስም ያወጣላት አሜ
ስያስ ነው::

8ከዚያም አሜስያስ የኢዩ የልጅ ልጅ፣
የኢዮአካዝ ልጅ ወደ ሆነው ወደ እስራኤል
ንጉሥ ወደ ዮአስ፣ “ናና ፊት ለፊት ይዋ
ጣልን” ሲል መልእክተኞች ላከበት::

9የእስራኤል ንጉሥ ዮአስ ግን ለይሁዳ
ንጉሥ ለአሜስያስ እንዲህ ሲል ላከበት፤
“አንድ የሊባኖስ ኰርንችት፣ ለአንድ የሊባ
ኖስ ዝግባ፣ ‘ሴት ልጅህን ለልጄ በሚስት
ነት ስጠው’ አለው፤ ከዚያም አንድ የሊባኖስ
ዱር አውሬ መጥቶ ኰርንችቱን በእግሩ
ረገጠው:: 10በእርግጥ ኤዶምን ድል አድርገ
ሃል፤ ታዲያ ልብህ አለመጠን አይኰራራ::
ድል በማድረግህ አትንጠራራ፤ እርፈህ
ተቀመጥ! ጠብ በመጫር የራስህን፣ የይሁ
ዳንስ ውድቀት ለምን ትሻለህ?”

11አሜስያስ ግን አልሰማም፤ ስለዚህ የእስ
ራኤል ንጉሥ ዮአስ ወጣ፤ እርሱና የይሁዳ
ንጉሥ አሜስያስም በይሁዳ ምድር በቤትሳ
ሚስ ፊት ለፊት ጦርነት ገጠሙ::

12ይሁዳ በእስራኤል ድል ሆነ፤ እያንዳን
ዱም ወደ ድንኳኑ ሸሸ:: 13የእስራኤል ንጉሥ
ዮአስም የአካዝያስን የልጅ ልጅ፣ የኢዮአ
ስን ልጅ የይሁዳን ንጉሥ አሜስያስን ቤት
ሳሚስ ላይ ማረከው:: ከዚያም ዮአስ ወደ
ኢየሩሳሌም ሄደ፤ ከኤፍሬም ቅጥር በር
አንሥቶ የማእዘን ቅጥር በር እስከተባለው
ድረስ ርዝመቱ አራት መቶ ክንድ[s] የሆነ

13፥24 ቍ3
13፥25 ቍ2ነገ 10፥32
14፥4 2ነገ12፥3
14፥5 2ነገ12፥20፤21፥24
14፥6 ዘኍ26፥11፤ዘዳ28፥6፤ኢዮ21፥20፤ኤር31፥30፤44:3፤ሕዝ18፥4:20
14፥7 መሳ1፥36፤2ሳሙ8፥13
14፥9 መሳ9፥8-15
14፥10 2ዜና26፥16፤32፥25
14፥11 ኢሱ15፥10
14፥12 1ነገ22፥36
14፥13 1ነገ3፥1፤2ዜና26፥9፤33፥14፤36፥19፤ነህ8፥16፤12፥39፤ኤር31፥38፤39፥2፤ዘካ14፥10

[r]6 ዘዳ 24፥16 ይመ:: [s]13 ዕብራይስጡ 180 ሜትር ይላል

*13፥24* ቤንሃዳድ፤ የቍ3 ማብ ይመ::

*13፥25* ከኢዮአካዝ ... የወሰዳቸውን ከተሞች፤ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ያለው አገር፣ በኢዩ ዘመን ተወስዶ ስለ ነበር (10፥32-33)፣ ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ ያሉትን ከተሞች ሳይሆን አይቀርም:: በዮርዳኖስ በስተ ምስራቅ ያለው አገር ሙሉ በሙሉ ወደ እስራኤል የተመለሰው በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመን ነበር (14፥25 ይመ):: ሦስት ጊዜ፤ ኤልሳዕ የተናገረው ትንቢት መፈጸሙን ያመለክታል (ቍ19)::

*14፥1* ዮአስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት፤ በ796 ዓ.ቅ.ክ (የ13፥10 ማብ ይመ)::

*14፥2* ሃያ ዘጠኝ ዓመት፤ ከ796-767ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው:: አሜስያስ የገዛበት ሃያ ዘጠኝ ዓመት ከልጁ ከዖዝያስ ጋር አብሮ የገዛ በትን ሃያ አራት ዓመት ይጨምራል (የቍ21 ማብ እና 15፥1-2 ይመ)::

*14፥3 አባቱ ዳዊት እንደ አደረገው ዐይነት አልነበረም፤* አሜስያስ ከጣዖት አምልኮ ሙሉ በሙሉ የተለየ ሰው አልነበ ረም (2ዜና 25፥14-16 ይመ):: ለእግዚአብሔር የነበረው ታማኝ ነት ከእርሱ በፊት ከነበሩት ከአሳና ከኢዮሣፍጥ እጅግ ያነሰ ነበር (1ነገ 15፥11:14፤22፥43፤ እንዲሁም 1ነገ 9፥4፤11፥4 ይመ)::

*14፥4 በኰረብታው ላይ ያሉት ማምለኪያዎች አልተወገዱም፤* የ1ነገ 15፥14 ማብ ይመ::

*14፥7 ዐሥር ሺህ ኤዶማውያንን ድል ያደረገ፤* ይሁዳ በኢዮራም ዘመነ መንግሥት ኤዶምያስን ማስገበር አልቻለም ነበር (8፥20-22 ይመ)፤ አሜስያስ በኢዮራም ዘመነ መንግሥት በኤዶምያስ ተወስደው የነበሩትን የይሁዳ ግዛቶች (8፥20-22 ይመ)፤ በጊዜያዊነት ማስመለስ ችሎ ነበር (2ዜና 28፥17 ይመ):: *የጨው ሸለቆ፤* ከሙት ባሕር በስተ ደቡብ አረባ ተብሎ በሚታወቀው፣ ዳዊት ኤዶማውያ ንን ድል ያደረገ በት ያው የጦር ሜዳ ነው (2ሳሙ8፥13፤1ዜና 18፥12፤ እንዲሁም የመዝ 60 ርእስ ይመ):: ሴላን፤ “ዐለት” ማለት ሲሆን፣ ቀድሞ የኤዶማው ያን ጠንካራ ምሽግ እንደ ነበር የሚነገርለት፣ አሁን ግን ፔትራ በመባል የሚታወቀው ነው (በግሪክ “ፔትራ” ማለት “ዐለት” ማለት ነው፤ መሳ1፥36፤ኢሳ16፥1፡42፥11፤አብ3 ይመ):: *እስከ ዛሬም ድረስ፤* ጸሓፊው የአሜስያስን ዘመነ መንግሥት ታሪክ እስከ ጻፈበት ጊዜ ማለት ነው (የ1ነገ8፥8፤ ማብ ይመ እንዲሁም በ1ነገ መግቢያ ሥር “ጸሓፊ፣ ምንጭና የተጻፈበት ዘመን” የሚለውን ይመ)::

*14፥8 ፊት ለፊት ይዋጣልን፤* ጦርነት እንዲታወጅ የሚገፋፋ አባባል ነው፤ ምክንያቱም ከይሁዳ ሰራዊት ከመባረራቸው የተነሣ (2ዜና 25፥10:13 ይመ) በሰሜን መንግሥት ያሉ ቅጥረኛ ወታደሮች ያነሣሡት ዐመፅ፣ እንዲሁም ዮአስ ከአሜስያስ ጋር ለመ ተባበር ፈቃደኛ ካለመሆኑ የተነሣ ሊሆን ይችላል (ቍ9 ይመ)::

*14፥9 ዮአስ ... ላከበት፤* ዮአስ በመልእክቱ፣ በአሜስያስ ላይ ተረት ተረተበት፤ በዚህም ራሱን እንደ ጠንካራ ዝግባ ሲቈጥር፣ አሜስ ያስን ደግሞ በቀላሉ በእግር ሊረገጥ እንደሚችል ትንሽ ኵጥኳጦ ቈጥሮታል (መሳ 9፥8-15 ይመ)::

14፥11 *አልሰማም፤* 2ዜና 25፥20 ይመ:: *በቤትሳሚስ፤* በይሁዳና በዳን መካከል ካለው ድንበር አጠገብ ከኢየሩሳሌም ሃያ አራት ኪሎ ሜትር ያህል ራቅ ብሎ በስተ ምዕራብ የሚገኝ ከተማ ነው (ኢሱ15፥10፤1ሳሙ 6፥9 ይመ)::

14፥13 *ዮአስም ... አሜስያስን ... ማረከው፤* አሜስያስ እንደ እስረኛ ሆኖ ወደ ሰሜን መንግሥት ሳይወሰድ አልቀረም፤ ከዮአስ ሞት በኋላ ወደ ይሁዳ እስከተመለሰበት ጊዜም ድረስ በዚሁ ኖረ (ቍ15-16 እና የቍ21 ማብ ይመ):: *ከኤፍሬም ቅጥር በር አንሥቶ የማእዘን ቅጥር በር፤* የማእዘን ቅጥር በር የተባለው (ኤር31፥38፤ዘካ 14፥10 ይመ)፣ በኢየሩሳሌም ቅጥር ዙሪያ፣ በሰሜን ምዕራብ ማእዘን ያለውን ነው:: የኤፍሬም ቅጥር በር የሚባለው ደግሞ ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን የሚገኘውን ከማእዘን ቅጥር በር በስተ ምሥራቅ ስድስት መቶ ጫማ ያህል የሆነውን ነው (ነህ12፥39 ይመ):: ይህ በሰሜን ምዕራብ ኢየሩ ሳሌም ያለው ቅጥር ለጥቃት እንድትጋለጥ የሚያደርጋት ቦታ ነበር::

ውን ቅጥር አፈረሰ:: 14*በእግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስና በቤተ መንግሥቱ ግምጃ ቤቶች
ያለውን ወርቅና ብር በሙሉ በዚያም የተገ
ኘውን ዕቃ ሁሉ በመውሰድ ምርኮኞችንም
ይዞ ወደ ሰማርያ ተመለሰ:: 15በዮአስ ዘመነ
መንግሥት የተከናወነው ሌላው ነገር፣ ያደ
ረገውና የፈጸመው ሁሉ በይሁዳ ንጉሥ
በአሜስያስ ላይ ያደረገው ጦርነት ጭምር
በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ
አይደለምን? 16ዮአስ ከአባቶቹ ጋር አንቀ
ላፋ፤ በሰማርያም ከእስራኤል ነገሥታት
ጋር ተቀበረ፤ ልጁ ኢዮርብዓምም በእግሩ
ተተክቶ ነገሠ:: 17የኢዮአስ ልጅ የይሁዳ
ንጉሥ አሜስያስም የእስራኤል ንጉሥ የኢ
ዮአካዝ ልጅ ዮአስ ከሞተ በኋላ ዐሥራ
አምስት ዓመት ኖረ:: 18በአሜስያስ ዘመነ
መንግሥት የተከናወነው ሌላው ነገር በይሁዳ
ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
19አሜስያስ በኢየሩሳሌም ሴራ ስለጠ
ነሰሱበት ሸሽቶ ወደ ለኪሶ ሄደ፤ እነርሱ
ግን የሚከታተሉት ሰዎች ወደዚያው ልከው
አስገደሉት፤ 20ሬሳውም በፈረስ ተጭኖ
መጥቶ በዳዊት ከተማ ከአባቶቹ ጋር በኢ
የሩሳሌም ተቀበረ::
21ከዚያም የይሁዳ ሕዝብ በሙሉ ዕድሜው
ዐሥራ ስድስት ዓመት የሆነውን ዓዛርያስን
ወስደው በአባቱ በአሜስያስ ፋንታ አነገሡት::

14፥15 2ነገ13፥12
14፥19 ኢሱ10፥31፤ 2ነገ12፥20
14፥20 2ነገ9፥28
14፥21 2ነገ15፥1፤ 2ዜና26፥23፤ኢሳ1፥1፤ ሆሴ1፥1፤አሞ1፥1
14፥22 1ነገ9፥26
14፥23 2ነገ13፥13፤ 1ዜና5፥17፤አሞ1፥1፤ 7፥10
14፥24 1ነገ15፥30
14፥25 ዘኁ13፥21፤ ዘዳ3፥17፤ዮና1፥1፤ ማቴ12፥39
14፥26 ዘዳ32፥36፤ 2ነገ13፥4፤መዝ 18፥41፤22፥11፤ 72፥12፤107፥12፤ ኢሳ63፥5፤ሰቆ1፥7
14፥27 ዘዳ29፥20፤ መሳ6፥14
14፥28 2ሳሙ8፥5፤ 9፤1ነገ15፥31

22አሜስያስ ከአባቶቹ ጋር ካንቀላፋ በኋላ
ኤላትን እንደገና ሠርቶ ወደ ይሁዳ የመለ
ሳት ይኸው ዓዛርያስ[x] ነበር::

### የእስራኤል ንጉሥ ዳግማዊ ኢዮርብዓም

23የኢዮስያስ ልጅ አሜስያስ በይሁዳ በነ
ገሠ በዐሥራ አምስተኛው ዓመት፣ የእስራ
ኤል ንጉሥ የዮአስ ልጅ ኢዮርብዓም በሰማ
ርያ ነገሠ፤ አርባ አንድ ዓመትም ገዛ:: 24 *በእ
ግዚአብሔርም* ፊት ክፉ ነገር አደረገ፤ የና
ባጥ ልጅ ኢዮርብዓም እስራኤልን ካሳተበት
ኀጢአት አልተመለሰም:: 25የእስራኤል አም
ላክ *እግዚአብሔር* በጋትሔፌር ነቢይ፣
በአማቴ ልጅ በባሪያው በዮናስ አማካይነት
እንደ ተናገረው፣ ከሐማት መተላለፊያ[ı]
አንሥቶ እስከ ሙት ባሕር[m] ድረስ የነበረ
ውን የእስራኤልን ድንበር ያስመለሰ ኢዮ
ርብዓም ነው::
26ባሪያም ይሁን ነጻ ዜጋ፣ በእስራኤል
የሚኖር ሁሉ እንዴት እጅግ ይሠቃይ
እንደ ነበር *እግዚአብሔር* አየ፤ የሚረዳቸ
ውም አልነበረም:: 27ይሁን እንጂ *እግዚ
አብሔር* የእስራኤልን ስም ከገጸ ምድር
እንደሚያጠፋ ስላልተናገረ፣ በዮአስ ልጅ
በኢዮርብዓም አማካይነት ታደጋቸው::
28በኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት የተከና
ወነው ሌላው ነገር፣ የፈጸመው ሁሉና ያደ

[x]21 *ኦዝያ* [ı]5 *ሊቦ* [m]25 *የዓረባ ባሕር*

14፥14 *ቤተ መቅደስና በቤተ መንግሥቱ ... ያለውን ወርቅና ብር በሙሉ በዚያም የተገኘውን ዕቃ ሁሉ፤* የተዘረፉት ዕቃዎች ዋጋ ይህን ያህል ውድ አይደለም፤ ምክንያቱም ዮአስ ቀደም ብሎ ለደማስቆው አዛሄል ለመገበር ቤተ መቅደሱንና ቤተ መንግሥቱን ባዶ አስቀርቶ ነበር (12፥17-18 ይመ):: *ምርኮኞችንም ይዞ፤* ምርኮኞቹ ምናልባት በጦርነት የሚገኘው ዝርፊያ አነስተኛ ቢሆን ለተጨማሪ የግብር ክፍያ በመያዣነት የተወሰዱ ሳይሆን አይቀርም::

14፥15 *በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ 14፥19 ማብ ይመ::

14፥16 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* 13፥12-13 ይመ፤ እንዲሁም 1ነገ1፥21ማብ ይመ::

14፥17 *ዮአስ ከሞተ በኋላ ዐሥራ አምስት ዓመት ኖረ፤* ዮአስ በ782 ዓ.ቅ.ክ ሲሞት አሜስያስ ደግሞ በ767 ዓ.ቅ.ክ ሞተ::

14፥18 *በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ 14፥29ማብ ይመ::

14፥19 *ሤራ ስለጠነሰሱበት፤* በ2ዜና25፥27 ላይ አሜስያስ ከእግዚአብሔር ዘወር ስላለ ይህ ዓመፅ እንደተነሣበት ተጠቅሶአል፤ የነገሥት መጽሐፍ ጸሓፊ ግን ይህን መጥቀስ የፈለገ አይመስልም:: *ለኪሶ፤* ከኬብሮን ሃያ አራት ኪሎ ሜትር ያህል በስተምዕራብ ርቃ የምትገኝ በደቡባዊ ይሁዳ ያለች የተመሸገች ከተማ ናት። በዚህ ዘመን ቴኪድ ዲዌር ተብላ ትጠራለች (18፥14፤ 2ዜና 11፥9 ይመ)::

14፥21 *የይሁዳ ሕዝብ በሙሉ ... የሆነውን ዓዛርያስን ወስደው፤* "ወይም የይሁዳ ሕዝብ ሁሉ ዓዛርያስን ዐሥራ ስድስት ዓመት ሲሆነው ወሰዱት፤ (አማራጭ ትርጒሙን ይመ):: *በአባቱ በአሜስያስ ፈንታ አነገሡት፤* ይህም አሜስያስ በዮአስ ታስሮ ከተወሰደ በኋላ ሳይሆን አይቀርም (ቊ 13 ይመ):: ስለዚህ የዓዛርያስ ዘመነ መንግሥትና የአባቱ የአሜስያስ ዘመን ጒልህ በሆነ መልክ ተደራርቦ ነበር (የቊ2 ማብ እና 15፥2 ይመ)::

14፥22 *ኤላትን እንደ ገና ሠርቶ ወደ ይሁዳ የመለሳት፤* ዓዛርያስ፣ አባቱ ኤዶማውያንን ለማስገበር የጀመረውን ሥራ በማስፋፋት (ቊ7 ይመ)፣/በአካባ ባሕረ ሰላጤ ላይ ያለውን ዋና ወደብ እስራኤላውያን እንደ ገና እንዲቈጣጠሩት አደረገ (1ነገ 9፥26 ይመ)::

14፥23 *አሜስያስ ... በዐሥራ አምስተኛው ዓመት፤* በ 782 ዓ.ቅ.ክ (የቊ2 ማብ ይመ):: ይህ ኢዮርብዓም ለብቻው መግዛት የጀመረበት ዓመት ነው:: ከዚህ ቀድሞ ከአባቱ ከዮአስ ጋር አብሮ ይገዛ ነበር:: *አርባ አንድ ዓመት፤* ከ793-753 ዓመት ሲሆን፣ ከአባቱ ጋር የገዛበትንም ዘመን ያጠቃልላል::

14፥24 *ኢዮርብዓም ... ኀጢአት፤* 1ነገ12፥26-32፤13፥33-34፤14፥16፤ አሞ3፥13-14፤ 4፥4-5፤5፥4-6፤7፥10-17 ይመ::

14፥25 *ከሐማት መተላለፊያ አንሥቶ፤* ዳግማዊ ኢዩርብዓም የሰሜኑ መንግሥት በአዛሄልና በቤንሃዳድ አገዛዝ ከሚሠቃዩበት ጭቈና ነጻ አውጥቶ ነበር (10፥32፤12፥17፤13፥3፡22፡25 ይመ)፤ አባቱ ዮአስ እንደ ጀመረው (13፥25 ይመ)፣ እርሱም የደማስቆ ሶርያውያን በእስራኤላውያን አስተዳደር ሥር እንዲሆኑ በማድረግ ግዛቱን አስፋፋ:: ስልምናሶር አራተኛው በ773ዓ.ቅ.ክ እንዲሁም ሣልሳዊው አሹር ዳን በ772 በደማስቆ ላይ ያደረጉትን ጥቃት ጨምሮ አሦራውያን *በሶርያውያን* ላይ ጫና ማድረጋቸው ሶርያ ውያንን ስላዳከማቸው ዳግማዊ ኢዩርብዓም በእነርሱ ላይ ድልን እንዲቀዳጅ አስችሎታል:: ብዙም ሳይቆይ አሦር የኢርብዓምን መስፋፋት ለመግታት ዐቅም እያጣ ሄደ:: *ሙት ባሕር፤* በአሞ 6፥14 መሠረት በዮርዳኖስ ማዶ የኢዮርብዓም መንግሥት ደቡባዊ ወሰን ሙት ባሕር ነበር፤ ይህም ከጨው ባሕር ጋር ሳይገናኝ አይቀርም (የቊ7 ማብ ይመ):: ይህ ከሆነም ኢዮርብዓም ሞዓብንና አሞናውያንን አስገብሮ ነበር ማለት ነው:: *በጋትሔፌር ነቢይ ... በዮናስ፤* ዮና1፥1 ይመ:: ጋትሔፌር ከናዝሬት በሰሜን ምሥራቅ በዛብሎን ነገድ የሚገኝ ነው (ኢሱ19፥13 ይመ):: በዚህ ስፍራ ዮናስ መጠቀሱ፣ የነቢዩን አገልግሎት ዘመን ለማወቅ ይረዳል::

14፥26 *ባሪያም ይሁን ነጻ፤* የ1ነገ14፥10 ማብ ይመ:: *ይሠቃይ፤* በሶርያውያን (10፥32-33፤13፥3-7 ይመ) በሞዓባውያንና (13፥20) በአሞናውያን (አሞ 1፥13) እጅ ማለት ነው::

14፥27 *ስላልተናገረ፤* የእስራኤላውያን ኀጢአት ጽዋ ገና አልሞላም ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ተጨማሪ የምሕረት ዘመን ሰጣቸው፤ ይኸውም ንስሐ እንዲገቡ ዕድል ለመስጠት ነው (የ13፥23 ማብ ይመ):: ሆኖም ግን በክህደትና በእምቢተኝነት መቀጠል ፍርድን ያመጣል (አሞ 4፥2-3፤ 6፥14 ይመ):: *በኢዮርብዓም አማካይነት ታደጋቸው፤* የ13፥5 ማብ ይመ::

14፥28 *የፈጸመው ሁሉ፤* ከዳዊትና ከሰሎሞን ዘመን በኋላ፣ በኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት በሰሜኑ መንግሥት ከማና

ረጋቸው ጦርነቶች እንዲሁም የይሁዳ ግዛት
የነበሩትን ደማስቆንና ሐማትን እንዴት
ለእስራኤል እንዳስመለሰ በእስራኤል ነገሥታት
ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን? 29 ኢዮ
ርብዓም ከአባቶቹ ከእስራኤል ነገሥታት
ጋር አንቀላፋ፤ ልጁ ዘካርያስም በእግሩ
ተተክቶ ነገሠ::

## የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ

15፥1-7 ተጓ ምብ - 2ዜና26፥3-4፡21-23

**15** የእስራኤል ንጉሥ ኢዮርብዓም በነ
ገሠ በሃያ ሰባተኛው ዓመት የይ
ሁዳ ንጉሥ የአሜስያስ ልጅ ዓዛርያስ ነገሠ::
2 ሲነግሥም ዕድሜው ዐሥራ ስድስት ዓመት
ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦ አምሳ ሁለት
ዓመት ገዛ:: እናቱም ይኮልያ የተባለች
የኢየሩሳሌም ሴት ነበረች:: 3 አባቱ አሜ
ስያስ እንዳደረገው ሁሉ ዓዛርያስም *በእግዚ
አብሔር ፊት* መልካም ነገር አደረገ::
4 ይሁን እንጂ በየኰረብታው ላይ ያሉት የማ
ምለኪያ ስፍራዎች አልተወገዱም፤ ሕዝቡም
በዚያ መሥዋዕት ማቅረቡንና ዕጣን ማጤ
ሱን እንደ ቀጠለ ነበር::
5 *እግዚአብሔርም* ንጉሡን እስከሚሞት
በት ቀን ድረስ በለምጽ[m] መታው፤ በተለየ
ቤትም ይኖር ነበር:: በዚያን ጊዜ ቤተ
መንግሥቱን በኀላፊነት የሚመራውና የአ
ገሩንም ሕዝብ የሚያስተዳድረው የንጉሡ
ልጅ ኢዮአታም ነበር::
6 በዓዛርያስ ዘመነ መንግሥት የተከናወ
ነው ሌላው ሥራ፣ የፈጸመውም ሁሉ በይ
ሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደ
ለምን? 7 ዓዛርያስ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤
በዳዊትም ከተማ በአባቶቹ መቃብር አጠገብ
ቀበሩት:: ልጁ ኢዮአታምም በእግሩ ተተክቶ
ነገሠ::

## የእስራኤል ንጉሥ ዘካርያስ

8 የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ በሠላሳ
ስምንተኛው ዓመት፣ የኢዮርብዓም ልጅ
ዘካርያስ በሰማርያ ከተማ በእስራኤል ላይ
ነገሠ፤ ስድስት ወርም ገዛ:: 9 አባቱ እንዳደ
ረገው ሁሉ፣ እርሱም *በእግዚአብሔር ፊት*
ክፉ አደረገ፤ የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም እስ
ራኤልን ካሳተበት ኀጢአት አልተመለሰም::
10 የያቤስ ልጅ ሰሎም በዘካርያስ ላይ
አሤረበት፤ በሕዝቡ[A] ፊት አደጋ ጥሎ ገደ
ለው፤ በእግሩም ተተክቶ ነገሠ:: 11 በዘካር
ያስ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው ሌላው
ሥራ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተመዝ
ግቦአል:: 12 በዚህም *እግዚአብሔር* ለኢዩ፣
"ልጆችህ እስከ አራት ትውልድ ድረስ
በእስራኤል ዙፋን ላይ ይቀመጣሉ"[B] ሲል
የተናገረው ቃል ተፈጸመ::

## የእስራኤል ንጉሥ ሰሎም

13 የይሁዳ ንጉሥ ዖዝያን በነገሠ በሠላሳ
ዘጠነኛው ዓመት የኢያቤስ ልጅ ሰሎም
በእስራኤል ላይ ነገሠ:: በሰማርያ ተቀምጦ
አንድ ወር ገዛ:: 14 የጋዲ ልጅ ምናሔም
ከቴርሳ ወጥቶ ወደ ሰማርያ በመሄድ አደጋ
ጥሎ የኢያቤስን ልጅ ሰሎምን ገደለው፤
ከዚያም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ::
15 በሰሎም ዘመነ መንግሥት የተከናወነው
ሌላው ሥራና የጠነሰሰውም ሤራ በእስራኤል
ነገሥታት ታሪክ ተጽፎአል::

15፥1 ቍ32፡2ነገ 14፥21
15፥3 1ነገ14፥8
15፥5 ቍ7:32፤ ዘፍ12፥17:41፥40፤ ዘሌ13፥46፤2ዜና 27፥1፤ሚክ1፥1
15፥7 ቍ5፤ኢሳ 6፥1፤14፥28
15፥9 1ነገ15፥26
15፥10 2ነገ12፥20
15፥11 1ነገ15፥31
15፥12 2ነገ10፥30
15፥13 1ነገ13፥32
15፥14 1ነገ5፥33፤ 2ነገ12፥20
15፥15 1ነገ15፥31

[m] 5 የዕብራይስጡ ቃል ቈዳን የሚያጠቃትን ማንኛውንም ዐይነት በሽታዎች ያመለክታል:: [A] 10 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል:: አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ግን፣ *በኢብለዓም* ይላሉ [B] 12 2ነገ 10፥30 ይመ::

ቸውም ዘመን ይልቅ ከፍተኛ ሀብትና ብልጽግና የሞላበት ጊዜ ነበር:: ሆኖም ግን ይህ ዘመን የሃይማኖት መልክ የነበረበት፣ እግዚአብሔርን ከማምለክም ያፈነገጡበትና ፍትሕ የተጓደለበት ዘመን ነበር (በኢዮርብዓም ዘመን ትንቢት የተናገሩትን የአሞጽንና የሆሴዕን መጽሐፍ ይመ):: *ደማስቆንና ሐማትን፤* የቍ25 ማብ ይመ:: *በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ14፥19 ማብ ይመ::

14፥29 *ከአባቶቹ ... ጋር አንቀላፋ፤* የ1ነገ 1፥21 ማብ ይመ:: *ልጁ ዘካርያስም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፤* ስለ ዘካርያስ ዘመነ መንግሥት 15፥8-12 ይመ::

15፥1 *የእስራኤል ንጉሥ ኢዮርብዓም በነገሠ በሃያ ሰባተኛው ዓመት፤* በ767 ዓ.ቅ.ክ ሲሆን፣ ይህም በ793 ኢዮርብዓም ከዮአስ ጋር አብሮ መግዛት የጀመረበትን ዘመን ያደረገ ነው (የ14፥23 ማብ ይመ):: *ዓዛርያስ ነገሠ፤* ከአባቱ ከአሜስያስ ጋር ሃያ አራት ዓመት ከገዛ በኋላ ለብቻው መግዛት የጀመረበትን ጊዜ የሚያመለክት ነው (የቍ2፤14፥2:21 ማብ ይመ):: በትክክል የገዛበት ዘመን ነገሠ ከተባለበት ዘመን አንድ ዓመት በኋላ ነው::

15፥2 *አምሳ ሁለት ዓመት፤* ከ792-740 ዓ.ቅ.ክ ነው፤ ይሁን እንጂ ከአባቱ ከአሜስያስ ጋር የገዛበት ዘመን ከ792-767 ዓ.ቅ.ክ ነበር (የቍ1 ማብ ይመ)::

15፥3 *አባቱ አሜስያስ እንዳደረገው፤* የ14፥3 ማብ ይመ::

15፥4 *በየኰረብታው ላይ ያሉት የማምለኪያ ስፍራዎች አልተወገዱም፤* 14፥4 ፣የ1ነገ15፥14 ማብ ይመ::

15፥5 *ንጉሡን... በለምጽ መታው፤* በቤተ መቅደስ መሠዊያ ላይ ዕጣን ማጠን የካህናት ሥራ ሆኖ ሳለ፣ በራሱ ፈቃድ ይህን ስላደረገ የመጣበት ቅጣት ነው (2ዜና26፥16-21 ይመ ከዘሌ13፥46 ጋር ያነጻጽሩ):: *ቤተ መንግሥቱን በኀላፊነት የሚመራውና የአገሩንም ሕዝብ የሚያስተዳድረው፤* በቀረው የዓዛርያስ የሕይወት ዘመን ልጁ ኢዮአ ታም በምትኩ ያስተዳድርለት ነበር (ከ750-740 ዓ.ቅ.ክ ነው፤ የቍ33 ማብ ይመ)::

15፥6 *የፈጸመውም ሁሉ፤* ዓዛርያስ በዘመኑ የሠራው ሥራ በዝርዝር በ2ዜና26፥1-15 ላይ ይገኛል:: *በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ14፥29 ማብ ይመ::

15፥7 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1ነገ1፥21 ማብ ይመ:: *ልጁ ኢዮ አታምም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፤* ስለ ኢዮአታም ዘመነ መንግሥት ቍ 32-38 ይመ::

15፥8 *ዓዛርያስ ... በሠላሳ ስምንተኛው ዓመት፤* በ753 ዓ.ቅ.ክ ነው (የቍ2 ማብ ይመ)::

15፥9 *ኢዮርብዓም ... ኀጢአት፤* 1ነገ12፥26-32፤13፥33-34፤ 14፥16 ይመ::

15፥11 *በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ 14፥19 ማብ ይመ::

15፥12 *እግዚአብሔር ... የተናገረው ቃል ተፈጸመ፤* አግራጭ ትርጕሙን ይመ:: የኢዩ ሥርወ መንግሥት ከወደቀ በኋላ፣ የሰሜኑ መንግሥት ከፍተኛ የፖለቲካ አለመረጋጋት ውስጥ ገባ (ሆሴ 1፥4 ይመ):: የቀሩት የሰሜኑ መንግሥት አምስት ነገሥታት፣ ዐሥር ዓመት ከገዛው ከምናሔምና አሥራውያን ካሰሩት ከሆሴዕ በቀር፣ ሁሉም የሞቱት ተገድለው ነው:: ባለጸጋና ጠንካራ ከነበረው ከዳግማዊ ኢዮር ብዓም ዘመን በኋላ የሰሜኑ መንግሥት አወዳደቅና ፍጻሜ እጅግ ፈጣን ነበር::

15፥13 *ዖዝያን በነገሠ በሠላሳ ዘጠነኛው ዓመት፤* በ752 ዓ.ቅ.ክ (የቍ2 ማብ ይመ):: ዓዛርያስ የዖዝያን ሌላ ስሙ ነበር (የ14፥21 ማብ ይመ)::

15፥14 *ምናሔም ከቴርሳ ወጥቶ ወደ ሰማርያ በመሄድ፤* ምናሔ ቀድሞ የሰሜኑ መንግሥት ዋና ከተማ በነበረችው በቴርሳ ለሰፈረው ጦር አዛዥ ሳይሆን አይቀርም (1ነገ14፥17፤15፥21:33 ይመ):: *በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፤* ስለ ምናሔም ዘመነ መንግሥት ከቍ17-22 ይመ::

15፥15 *በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ 14፥19 ማብ ይመ::


# አሦራውያን በእስራኤልና በይሁዳ ላይ የከፈቱት ዘመቻ

ከክርስቶስ ልደት በፊት በስምንተኛው ምእተ ዓመት አሦራውያን በእስራእላውያን ላይ የከፈቱት ዘመቻ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ አሳዛኝ የፖለቲካ ሁኔታ የፈጠረ ነበር።

የአሦር ጨካኝ ሰራዊት በዓለም እጅግ በረቀቀና በዘመናዊ የጦር መሣሪያ በተገነባና በበቂ የጦር መሐንዲሶቹ የሚመካ ነበር።

ሆኖም የሥነ ልቡና ጦርነት ማካሄድ ለአሦራውያን ጥሩ ውጤት ያስገኘላቸው መሣርያ (ዘዴ) ነበር። በዚህ ጭካኔ በተሞላበት ተግባራቸው የሰዎችን ራሳ በእንጨት ላይ ይሰኩ ነበር፤ የሰውን ጭንቅላት ዐንገቱ ላይ እየቈረጡ ይከምሩ ነበር፤ ምርኮኞችንም በሕይወት እያሉ ቈዳቸውን ይገፉ ነበር።

ለጦርነት ይደረግ የነበረው ክበባ እስራኤልንና ይሁዳን ማስጨነቁ ግልጽ ነው። ይህ ሁኔታ ነቢያትን ከማስጨነቁ የተነሣ እንዲጮኹና ሕዝቡም ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ ደጋግመው እንዲያሳስቡ አድርጓቸዋል።





## 3. ሰናክሬም በይሁዳ ላይ ያደረገው ዘመቻ (701 ዓ.ቅ.ክ)

ሕዝቅያስ በነገሠ በ14ኛው ዓመት አሦራውያን ይሁዳን ወጉ:: ሰናክሬም ሕዝቅያስን «ጨቋኝና ትዕቢተኛ» እንደሆነና ከፍልስጥኤምና ከግብፅ ጋር በመተባበር በአሦር ላይ እንዳመጸ ተናገረ::

በአልቴቅ የተደረገው ጦርነት በአሦር አሸናፊነት አበቃ፤ የግብፅና የከነዓን ሰረገሎች ሸሹ፤ ለኪሶ ተማረከች:: የአሦር ጥንታዊ መዝገብ «አይሁዳዊው ሕዝቅያስ ለእኔ አልገዛም አለ:: 46 የሚያህሉ ከተሞችንና አያሌ መንደሮችን ሁሉ በብዙና በተለያዩ የጦር ሰራዊቶች ከበብሁ:: 200,150 ያህል ሰዎች፣ ወጣቶችና አዛውንቶች፣ ወንዶችና ሴቶች፣ ፈረሶች፣ በቅሎች፣ አህዮች፣ ግመሎችና አያሌ የቀንድ ከብቶችን በምርኮ ወሰድሁ:: ሕዝቅያስንም በወጥመድ እንዳለች ወፍ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በኢየሩሳሌም እስረኛ አደረግሁት» ይላል::

ይሁን እንጂ ይህ እብሪተኛ የአሦር ንጉሥ በ2ኛ ነገ 19:35-36 እና በኢሳ 37:36-37 የተጠቀሰውን ዕልቂት በየትም ሥፍራ ዘግቦት አልተገኘም::




## 2. የስልምናሶር አምስተኛ ዘመቻ (725 - 722 ዓ.ቅ.ክ)

የእስራኤል የመጨረሻ ንጉሥ የሆነው ሆሴዕ ከግብፅ ጋር በማበር በየዓመቱ ለአሦር ይሰጥ የነበረውን ግብር አቆመ:: በስልምናሶር የተጀመረውን የሦስት ዓመት ከበባ ዳግማዊው ሳርጎን ከግብ አደረሰው፤ በዚህም የእስራኤል መንግሥት ፍጻሜ በ722 ዓ.ቅ.ክ ሆነ::

በዚያን ጊዜ በሸክላ ላይ የተጻፈ የአሦራውያን መዝገብ «እኔ (ሰርጎን) ሰማርያን በመክበብ ያዝኋት፤ 27, 290 ነዋሪዎችን ምርኮኛ በማድረግ አፈለስሁ፤ በተቀሩት ላይ የእኔን አለቆች በመሾም እንዲገብሩ አደረግሁ» ይላል::

16በዚያን ጊዜም ምናሔም ከቴርሳ
ወጥቶ በቲፍሳና በከተማዪቱ ነዋሪዎች ላይ
ሁሉ፣ በአካባቢዋም ጭምር አደጋ ጣለ፤
ይህን ያደረገውም የከተማዪቱን በሮች
ለመክፈት ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ነበር፤
ቲፍሳን መታት፤ የነፍሰጡሮችንም ሆድ ሁሉ
ቀደደ።

## የእስራኤል ንጉሥ ምናሔም

17የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ በሠላሳ
ዘጠነኛው ዓመት፣ የጋዲ ልጅ ምናሔም
በእስራኤል ላይ ነገሠ፤ በሰማርያ ተቀምጦም
ዐሥር ዓመት ገዛ። 18*በእግዚአብሔር ፊት*
ክፉ ነገር አደረገ፤ በዘመኑም ሁሉ የናባጥ
ልጅ ኢዮርብዓም እስራኤልን ካሳተበት
ኀጢአት አልተመለሰም።
19ከዚያም የአሦር ንጉሥ ቴልጌልቴልፌ
ልሰር[°] ምድሪቱን ወረረ፤ ምናሔም ርዳታ
ውን ለማግኘትና በመንግሥቱ ላይ ያለውን
ይዞታ ለማጽናት ሲል፣ አንድ ሺህ መክሊት[+]
ብር ሰጠው።
20ምናሔም ገንዘቡ እንዲዋጣ ያደረገው
ከእስራኤል ሲሆን፣ ይህንንም ያደረገው
ለአሦር ንጉሥ ይሰጥ ዘንድ እያንዳንዱ
ሀብታም አምሳ፣ አምሳ ሰቅል[T] ብር እንዲ
ያዋጣ በማስገደድ ነበር። ስለዚህ የአሦር
ንጉሥ በዚያች አገር አልቈየም፤ ተመልሶ
ሄደ።
21በምናሔም ዘመነ መንግሥት የተከና
ወነው ሌላው ሥራ የፈጸመውም ሁሉ በእስ
ራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ
አይደለምን? 22ምናሔም ከአባቶቹ ጋር አን
ቀላፋ፤ ልጁ ፋቂስ ያስም በእግሩ ተተክቶ
ነገሠ።

## የእስራኤል ንጉሥ ፋቂስያስ

23የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ በአም
ሳኛው ዓመት፣ የምናሔም ልጅ ፋቂስያስ
በሰማርያ ከተማ የእስራኤል ንጉሥ ሆነ፤
ሁለት ዓመትም ገዛ። 24ፋቂስያስ *በእግዚአ*
*ብሔር ፊት* ክፉ ነገር አደረገ፤ የናባጥ
ልጅ ኢዮርብዓም፣ እስራኤልን ካሳተበት
ኀጢአት አልተመለሰም። 25ከጦር አለቆቹ
አንዱ የሆነው የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ
አሤረበት፤ አምሳ የገለዓድ ሰዎች ይዞ
በመሄድ፣ ሰማርያ ቤተ መንግሥት ባለው
ምሽግ ፋቂስያስን ከአርጎብና ከአርያ ጋር
ገደለው፤ በእግሩም ተተክቶ ነገሠ።
26በፋቂስያስ ዘመነ መንግሥት የተከና
ወነው ሌላው ሥራ የፈጸመውም ሁሉ በእስ
ራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎአል።

## የእስራኤል ንጉሥ ፋቁሔ

27የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ በአምሳ
ሁለተኛው ዓመት የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ
በሰማርያ ከተማ፣ በእስራኤል ላይ ነገሠ፤
ሃያ ዓመትም ገዛ። 28እርሱም *በእግዚአብሔር*
*ፊት* ክፉ ነገር አደረገ፤ የናባጥ ልጅ ኢዮ
ርብዓም እስራኤልን ካሳተበት ኀጢአት አል
ተመለሰም።
29በእስራኤል ንጉሥ በፋቁሔ ዘመን፣
የአሦር ንጉሥ ቴልጌልቴልፌልሶር መጥቶ
ዒዮንን፣ አቤልቤትመዓካን፣ ያኖዋን፣ ቃዴስ
ንና ሐጾርን፣ ገለዓድንና ገሊላን፣ የንፍታሌ

[°]19 ቲግላት ፐሌሴርም ይባላል። [+]19 34 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው [T]20 0.6 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

15፥16 1ነገ14፥24፤ 2ነገ8፥12፤ሆሴ13፥16
15፥18 1ነገ15፥26
15፥19 1ዜና5፥6፡ 26
15፥20 2ነገ12፥18
15፥24 1ነገ15፥26
15፥25 2ነገ12፥20፤2ዜና28፥6፤ኢሳ7፥1
15፥27 2ዜና 28፥6፤ኢሳ7፥1፡4
15፥29 1ነገ 15፥20፤2ነገ16፥7፡9፤ 17፥6፡24፤24፥14-16፤ 1ዜና5፥22፡26፤2ዜና 16፥4፤28፥20፤ኢሳ 7፥9፤9፥1፤10፥9፡10፤ 14፥6፡17፤28፥1፤36፥ 17፡19፤37፥18፤45፥1 3፤ኤር50፥17

15፥16 *ቲፍሳ፤* ከሐማት በስተ ሰሜን (14፥25 ይመ) በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ የሚገኝ ስፍራ ነው (1ነገ 4፥24 ይመ)። ይሁን እንጂ የታለመችው ከተማ ይህች አልነበረችም። አንዳንዶች በሰብዓ ሊቃናት "ታፑአ" ተብሎ የተጻፈውን ስያሜ ይመርጣሉ። ታፑአ በምናሴና በኤፍሬም ድንበር መካከል ያለ ከተማ ነው (ኢሱ 16፥8፤17፥7-8)። ምናልባትም በእስራኤል ብቻ "ቲፍሳ" የተባለ ከተማ ሳይኖር አይቀርም። *የነፍሰጡሮችንም ሆድ ሁሉ ቀደደ፤* 8፥12 እና ማብ ይመ።

15፥17 *ዓዛርያስ በነገሠ በሠላሳ ዘጠኘኛው ዓመት፤* በ752 ዓ.ቅ.ክ (የቍ2 ማብ ይመ)፡ *ዐሥር ዓመት፤* ከ752-742 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው።

15፥18 *ኢዮርብዓም ... ኀጢአት፤* 1ነገ12፥26-32፤13፥33-34፤14፥16 ይመ።

15፥19 *ምድሪቱን ወረረ፤* ሣልሳዊው ቴልጌልቴልፌልሶር፣ በ743 ዓ.ቅ.ክ ከሰራዊቱ ጋር ወደ ምዕራብ በመጓዝ ከርከሚሽን፣ ሐማትን፣ ጢሮስን፣ ባይብሎስን፣ ደማስቆን፣ የምናሔ ምንና ሰማርያንም እንዳስገበረ ይናገራል። *አንድ ሺህ መክሊትን፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ፤ እጅግ ብዙ የገንዘብ መጠን ነው የብር መክሊት አንጻራዊ ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ የ5፥5 ማብ ይመ። *ርዳታውን ለማግኘትና በመንግሥቱ ላይ ያለውን ይዞታ ለማጽናት ሲል፤* ምናሔም ሥልጣንን ነጥቆ በመያዙ በዙፋኑ ላይ ተረጋግቶ መቀመጥ እንዳልቻለ ያመለክታል። ተቃውሞም ሊመጣበት የቻለው የፋቁሔን አመራር ከተከተሉ ሰዎች ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም ፋቁሔ የአሦርን ኀይል ለመቋቋም ከደማስቆ ሶርያውያን ጋር ተባብሮ ስለነበር ነው (የቍ27 ማብ ይመ)። ሆሴዕ ከአሦራውያን ርዳታ የመፈለግ ዕቅድን በማውገዝ ተግባራዊ እንደማይሆን ተናገረ (ሆሴ 5፥13-15)።

15፥20 *አምሳ ሰቅል፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ። ሊከፈል የታሰበውን የአንድ ሺህ መክሊት ግብር ለመሰብሰብ በግምት ሥልሳ ሺህ ሰው ያስፈልጋል ማለት ነው፤ ይህም በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመን የሰሜኑ መንግሥት የቱን ያህል ሀብታም እንደ ነበር ያመለክታል።

15፥21 *በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ14፥19 ማብ ይመ።

15፥23 *ዓዛርያስ በነገሠ በአምሳኛው ዓመት፤* በ742 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው (የቍ2 ማብ ይመ)። *ሁለት ዓመት፤* ከ742-740 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው ።

15፥24 *ኢዮርብዓም...ኀጢአት፤* 1ነገ12፥26-32፤13፥33-34፤14፥16 ይመ።

15፥25 *ከጦር አለቆቹ አንዱ፤* ፋቁሔ በዮርዳኖስ ማዶ ባሉ አገሮች ከፍተኛ ሥልጣን የነበረው ሰው ሳይሆን አይቀርም፤ ለምናሔና ለፋቂስያስ የነበረውም ታዛዥነት ከልብ እንዳልነበር ግልጽ ነው (የቍ27 ማብ ይመ)። *አሤረበት፤* በውጭ ጕዳይ ፖሊሲ የነበረው የተለየ አመለካከት፣ ፋቁሔ ተቃውሞውን እንዲያጠናክር ሳያደርገው አልቀረም። ፋቁሔ የአሦርን ወዳጅነት መፈለጉ የአባቱን የምናሔምን ፈለግ መከተሉን ያለጥርጥር ያመለክታል (ቍ20 ይመ)። ፋቁሔ ደግሞ ከአሦር ሊሰነዘር የሚችልን ወረራ ለመከላከል ከደማስቆ ሶርያውያን ጋር ተባበረ (16፥1-9፤ ኢሳ7፥1-2፡4-6 ይመ)።

15፥26 *በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ 14፥19 ማብ ይመ።

15፥27 *ዓዛርያስ በነገሠ በአምሳ ሁለተኛው ዓመት፤* በ740 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው (የቍ2 ማብ ይመ)። *ሃያ ዓመትም፤* ከ752-732 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው፤ ቀጥሎ ያለውን ግምት መሠረት በማድረግ፣ ምናሔም ሐሎምን በገደለ ጊዜ፣ ፋቁሔ በዮርዳኖስ ማዶ ባለው ግዛት ምናሔምን የሚቃወም መንግሥት አቋቋመ (የቍ17፡19፡25 ማብ ይመ)። ስለዚህ በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው የግዛት ዘመን የዐመፁን ዘመን ሁሉ ያጠቃልላል።

15፥28 *ኢዮርብዓም ... ኀጢአት፤* 1ነገ12፥26-32፤13፥33-34፤14፥16 ይመ።

15፥29 *የአሦር ንጉሥ ቴልጌልጌልፌልሶር መጥቶ፤* የቍ19 ማብ ይመ። የዚህ ወረራ ታሪካዊ ዳራ በ16፥5-9፤2ዜና28፥16-21፤ ኢሳ 7፥1-17 ላይ ይገኛል። *ዒዮንና...ንፍታሌምን፤* ከአንድ መቶ አምሳ ዓመት በፊት የደማስቆው ቀዳማዊ ቤንሃዳድ፣ የይሁዳ ንጉሥ ባደረገው ጥያቄ መሠረት፣ እነዚህን ግዛቶች ከሰሜን መንግሥት ቀምቶ

ምንም ምድር ጭምር ያዘ። ሕዝቡንም
ማርኮ ወደ አሦር ወሰደው። 30ከዚያም የኤላ
ልጅ ሆሴዕ በሮሜልዩ ልጅ በፋቁሔ ላይ
አሤረበት፤ አደጋ ጥሎም ገደለው፤ የዖዝያን
ልጅ ኢዮአታም በነገሠ በሃያኛው ዓመትም
ሆሴዕ በፋቁሔ እግር ተተክቶ ነገሠ።
31በፋቁሔ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው
ሌላው ሥራ የፈጸማቸውም ሁሉ በእስራ
ኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይ
ደለምን?

## የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአታም

15፥33-38 ተጓ ምብ - 2ዜና27፥1-4፤7-9

32የእስራኤል ንጉሥ የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ
በነገሠ በሁለተኛው ዓመት፣ የይሁዳ ንጉሥ
የዖዝያን ልጅ ኢዮአታም ነገሠ። 33ሲነግ
ሥም ዕድሜው ሃያ አምስት ዓመት ነበር፤
ኢየሩሳሌም ተቀምጦም ዐሥራ ስድስት
ዓመት ገዛ፤ እናቱም የሳዶቅ ልጅ ስትሆን፤
ኢየሩሳ ትባል ነበር። 34አባቱ ዖዝያን እንዳ
ደረገው ሁሉ እርሱም *በእግዚአብሔር* ፊት
መልካም ነገር አደረገ። 35ይሁን እንጂ፣ በየ
ኰረብታው ላይ ያሉት የማምለኪያ ስፍራ
ዎች አልተወገዱም፤ ሕዝቡም በዚያ መሥ
ዋዕት ማቅረቡንና ዕጣን ማጤሱን እንደ
ቀጠለ ነበር። ኢዮአታም *የእግዚአብሔርን*
ቤተ መቅደስ የላይኛውን በር መልሶ ሠራ።
36በኢዮአታም ዘመነ መንግሥት የተከና
ወነው ሌላው ሥራ፣ የፈጸመውም ሁሉ በይ
ሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደ
ለምን? 37በዚያን ጊዜ *እግዚአብሔር* የሶርያ
ንጉሥ ረአሶንና የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔን
ይሁዳን እንዲወጉ አደረገ። 38ኢዮአታምም
ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ አባቶቹ በተቀበሩ
በትም፤ በአባቱ በዳዊት ከተማ ተቀበረ። ልጁ
አካዝም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ አካዝ

16፥1-20 ተጓ ምብ - 2ዜና28፥1-27

16 የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ በነገሠ በዐ
ሥራ ሰባተኛው ዓመት፣ የይሁዳ
ንጉሥ፣ የኢዮአታም ልጅ አካዝ ነገሠ።
2አካዝ ሲነግሥ ዕድሜው ሃያ ዓመት ነበር፤
በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ዐሥራ ስድስት ዓመት
ገዛ። አባቱ ዳዊት ያደረገውን መልካም ነገር
በአምላኩ *በእግዚአብሔር* ፊት አላደረገም።
3እርሱም የእስራኤልን ነገሥታት መንገድ
ተከተለ፤ ይልቁንም *እግዚአብሔር* ከእስራ
ኤላውያን ፊት ያሳደዳቸውን የአሕዛብን
ርኵሰት ተከትሎ፣ ልጁን በእሳት የሚቃጠል

15፥30 2ነገ 12፥20፤17፥1
15፥31 1ነገ15፥31
15፥32 ቍ1:5፤ 1ዜና5፥17፤ኢሳ1፥1፤ ሆሴ1፥1
15፥34 1ነገ14፥8
15፥35 ዘፍ23፥10፤ 2ነገ12፥3፤2ዜና23፥20
15፥37 2ነገ16፥5፤ ኢሳ7፥1፤8፥6፤ 9፥11
16፥1 ኢሳ1፥1፤ 7፥1፤14፥28፤ሆሴ1፥1፤ ሚክ1፥1
16፥2 1ነገ14፥8
16፥3 ዘሌ18፥3: 21፤ ዘዳ9፥4፤2ነገ 3፥27፤17፥19፤

ነበር (የ1ነገ15፥19-20 ማብ ይመ)። *ሕዝቡንም ወደ አሦርም ወሰደው፤* 1ዜና5፥26 ይመ። እስራኤላውያን ከአገራቸው ተገደው መወሰዳቸው በቃል ኪዳኑ የተጠቀሰው የርግማን ቃል መፈጸሙን ያመለክታል (የ10፥32 ማብ ይመ)።

15፥30 *ሆሴዕ... በፋቁሔ ላይ አሤረበት፤* ሆሴዕ በሰሜኑ መንግሥት አሦርን ከመቃወም ይልቅ መተባበር ይሻላል ለሚለው ቡድን ተወካይ ሳይሆን አይቀርም፤ ሜልሳዊ ቴልጌልቴልፌልሶር ከታሪኩ በአንዱ፣ ሆሴዕን በሰሜኑ መንግሥት ዙፋን ላይ እንዳስቀመጠውና ዐሥር መክሊት ወርቅና አንድ ሺህ መክሊት ብር እንደሚያስገብረው ጠቅሶአል። *ኢዮአታም በነገሠ በሃያኛው ዓመት፤* በ732 ዓ.ቅ.ክ (የቍ32-33 ማብ ይመ)። የተጠቀሰው ዘመን ሥልጣን የያዘበትን ሃያኛው ዓመት ቢሆንም፣ ዘመነ መንግሥቱ በትክክል ሲቈጠር ግን ዐሥራ ዘጠኝ ዓመት ብቻ ነው።

15፥31 *በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ 14፥19 ማብ ይመ።

15፥32 *ፋቁሔ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት፤* በ750 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው (የቍ27ማብ ይመ)።

15፥33 *ዐሥራ ስድስት ዓመት፤* ከ750-735 ዓ.ቅ.ክ ማለት ሲሆን ኢዮአታም ከአባቱ ጋር የገዛበት ዘመን ከ750 -740 ዓ.ቅ.ክ ነበር (የቍ5 ማብ ይመ)። የኢዮአታም አገዛዝ ባልታወቀ መንገድ በ735 ዓ.ቅ.ክ ሲያበቃ፣ ልጁ አካዝ በምትኩ ነገሠ። ይሁን እንጂ ኢዮአታም እስከ 732 ዓ.ቅ.ክ ድረስ በሕይወት ነበር (የቍ 30:37 ማብ ይመ)።

15፥34 *አባቱ ዖዝያን እንዳደረገው ሁሉ፤* የቍ3 ማብ ይመ፤ እንዲሁም 2ዜና 27፥2 ይመ።

15፥35 *ይሁን እንጂ በየኰረብታው ላይ ያሉት የማምለኪያ ስፍራዎች አልተወገዱም፤* ቍ4 ይመ፤ እንዲሁም የ1ነገ 15፥14 ማብ ይመ። *ቤተ መቅደስ የላይኛውን በር፤* 2ዜና 23፥20፤ኤር 20፥2፤ ዕዝ 8፥3፤9፥2 ይመ። ስለ ኢዮአታም የቤተ መቅደሱ ግንባታ ሥራ ይበልጥ ለማወቅ 2ዜና27፥3-4 ይመ።

15፥36 *በኢዮአታም ዘመነ መንግሥት የተከናወነው ሌላው ሥራ፤* 2ዜና27፥1-6 ይመ። *በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ 14፥29 ማብ ይመ።

15፥37፤ ይህ በቅንፍ ውስጥ እንደሚገኝ የሚቈጠር ዐረፍተ ነገር ሲሆን፣ ለተወሰነ ዘመን ሁለቱም፣ ኢዮአታምና አካዝ በአንድ ግዛት ሥልጣን ላይ እንደ ነበሩ ያመለክታል (የቍ 33 ማብ ይመ)፤ ይሁን እንጂ 16፥5-12፤2ዜና28፥5-21፤ኢሳ7፥1-17 ያሉት ክፍሎች የሶርያ ንጉሥ ረአሶንና የእስራኤል ንጉሥ ፋቁሔ በይሁዳ ንጉሥ በአካዝ ዘመነ መንግሥት ያከናወኗቸውን ዐበይት ተግባራት ያመለክታሉ።

15፥38 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1ነገ1፥21 ማብ ይመ።

16፥1 *ፋቁሔ በነገሠ በዐሥራ ሰባተኛው ዓመት፤* በ735 ዓ.ቅ.ክ ሲሆን (የ15፥27 ማብ ይመ)፣ አካዝ ከኢዮአታም ጋር ለተወሰነ ጊዜ አንድ ላይ የገዛ ሲሆን፣ ይኸውም አካዝ ከ735 ጀምሮ ዋነኛ ሆኖ ያገለገለበት ነው (የ15፥33:37: ማብ እንዲሁም የቍ2 እና፡ የ17፥1ማብ ይመ)።

16፥2 *ሲነግሥ ዕድሜው ሃያ ዓመት ነበር፤* ምናልባት አካዝ ከአባቱ ከኢዮአታም ጋር በ735 ዓ.ቅ.ክ አብሮ መግዛት የጀመረበት ጊዜ ይሆናል (የቍ1 ማብ ይመ)። አለበለዚያ በተገለጸው ዕድሜና ዘመን መሠረት አካዝ ዕድሜው14 ወይም15 ሳይሆን፣ ልጁ ሕዝቅያስ በተወለደ ጊዜ (ከ18፥1-2ጋር ያነጻጽሩ) ዕድሜው11 ወይም12 ዓመት ነበር ማለት ነው። *ዐሥራ ስድስት ዓመት፤* የይሁዳን ነገሥታት የአካዝንና የሕዝቅያስን ዘመን፣ ከሰሜን መንግሥት ነገሥታት ከፋቁሔና ከሆሴዕ ዘመን ጋር ለማስተካከል መሞከር፣ በዘመን አቈጣጠር ቅደም ተከተል ላይ ችግር መፍጠሩ አይቀርም (የቍ1፤17፥1፤18፥1: 9-10 ማብ ይመ)። ስለዚህ እዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ዐሥራ ስድስት ዓመት፣ ኢዮአታም ከሞተ በኋላ አካዝ የገዛበት ዘመን ነው ማለት የተሻለ ይመስላል፤ ይህም ጊዜ ከ732-715 ዓ.ቅ.ክ ነበር (የ15፥30:33 ማብ ይመ)። በመጽሐፍ ቅዱስ አካዝ መንገሥ የጀመረበት ጊዜ በተለያየ መንገድ ተገልጾአል፤ ይኸውም (1) በ744 ወይም በ743 ዓ.ቅ.ክ ሲሆን የዐሥራ አንድ ወይም የዐሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ሳለ ከአያቱ ከዓዛርያስ ጋር አብሮ መግዛት እንደ ጀመረ የሚያመለክት ነው (17፥1 ይመ፤ (2) በ735 ዓ.ቅ.ክ ከኢዮአታም ጋር ዋነኛ ሆኖ አብሮ መግዛት የጀመረበት ጊዜ (ቍ1 ይመ)፤ (3) እንዲሁም በ732 ዓ.ቅ.ክ ኢዮአታም ከሞተ በኋላ ብቻውን መግዛት የጀመረበት ጊዜ ነው። *አባቱ ዳዊት ያደረገውን... አላደረገም፤* አካዝ እንደ አሜስያስ (14፥3)፣ እንደ ዓዛርያስ (15፥3) እና እንደ ኢዮአታም (15፥34) እንኳ በጎ ምስክርነት አልተሰጠውም።

16፥3 *የእስራኤልን ነገሥታት መንገድ፤* በቤቴልና በዳን ጥጃ እንዲመለክ ያደረገውን የቀዳማዊ የኢዮርብዓምን መንገድ አካዝም ተከትሎአል ለማለት አያስደፍርም (1ነገ 12፥26-32፤ 13፥33-34፤14፥16 ይመ)። እዚህ ላይ ያለው መግለጫ የሚያመለክተው በአክዓብ መንፈስ የነበረውን የበኣል አምልኮን ሳይሆን አይቀርም (የ1ነገ 16፥31-33 ማብ እና 2ዜና28፥2 ይመ)። *ልጁን... መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ፤* እስራኤላውያን ይህን በመሰለ የባዕድ አምልኮ ሥርዐት ውስጥ እንዳይገቡ ሙሴ አስጠንቅቆአቸዋል (ዘሌ18፥21፤ዘዳ 18፥10 ይመ)። የእያንዳንዱ እስራኤላዊ ቤተሰብ በኵር ወንድ ልጅ ከሆነ ለእግዚአብሔር ተለይቶ ይቀደስና አምስት ሰቅል ለካህናት በመክፈል ይቤዥ ነበር (ዘፀ13፥1:11-13፤ ዘኁ18፥16 ይመ)፤ እንዲሁም 3፥27፤17፥17፤ 21፥6፤ 23፥10፤ 2ዜና

መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ።[ሀ] 4እንዲሁም
ኰረብታ ላይ ባሉ ማምለኪያ ስፍራዎች፣
በኰረብታ አናቶችና ቅጠሉ በተንሰራፋው
ዛፍ ሥር ሁሉ ሠዋ፤ ዕጣንም አጤሰ።
5የሶርያ ንጉሥ ረአሶንና የእስራኤል ንጉሥ
የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ ኢየሩሳሌምን ለመ
ውጋትና አካዝን ለመክበብ ወጡ፤ ይሁን
እንጂ ሊያሸንፉት አልቻሉም። 6በዚያን ጊዜም
የሶርያ ንጉሥ ረአሶን የይሁዳን ሰዎች
አሳዶ፣ ኤላትን ወደ ሶርያ ግዛት መለሰ፤
ከዚያም ኤዶማውያን ወደ ኤላት መጥተው
እስከ ዛሬ በዚያ ይኖራሉ።
7ከዚህ የተነሣም አካዝ፣ ወደ አሦር ንጉሥ
ወደ ቴልጌልቴልፌልሶር፣ "እኔ አገልጋይ
ህም ልጅህም ነኝ፤ ስለዚህ መጥተህ ከሚወ
ጉኝ ከሶርያ ንጉሥና ከእስራኤል ንጉሥ እጅ
አድነኝ" ሲል መልእክተኞች ላከበት። 8አካ
ዝም *በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስና በቤተ
መንግሥቱ ግምጃ ቤቶች የሚገኘውን ብርና
ወርቅ አውጥቶ ለአሦር ንጉሥ ገጸ በረከት
ላከለት። 9የአሦር ንጉሥም፣ የአካዝን
ልመና በመቀበል፤ ደማስቆን አጥቅቶ ያዛት፤
ሕዝቧን ማርኮ ወደ ቂር አፈለሳቸው፤ ረአሶ
ንንም ገደለው።
10ከዚያም ንጉሥ አካዝ የአሦርን ንጉሥ
ቴልጌልቴልፌልሶርን ለመገናኘት ወደ ደማ
ስቆ ሄደ። በደማስቆም ያለውን መሠዊያ
አይቶ፣ ንድፉን ከዝርዝር ጥናቱ ጋር ለካህኑ

16፥4 ዘዳ12፥2፤ 2ነገ22፥17፤23፥5፤ ሕዝ6፥13
16፥5 2ነገ15፥37
16፥6 1ነገ9፥26፤ ኢሳ9፥12
16፥7 2ነገ15፥29፤ ኢሳ2፥6፤10፥20፤ ኤር2፥18፤3፥1፤ ሕዝ16፥28፤ 23፥5፤ሆሴ10፥6
16፥8 1ነገ15፥18፤ 2ነገ12፥18
16፥9 ዘፍ14፥15፤ 2ነገ15፥29፤ኢሳ22፥6፤ አሞ1፥5፤9፥7
16፥10 ቍ11፡15፡ 16፤ኢሳ8፥2
16፥12 2ዜና 26፥16
16፥13 ዘፀ29፥40፤ ዘሌ6፥8፤13፡14-23፤ 7፥11-21
16፥14 ዘፀ20፥24፤ 40፥6፤1ነገ8፥64
16፥15 ዘፀ29፥38-41፤1ሳሙ9፥9

ለኦርያ ላከለት። 11ካህኑ ኦርያም ንጉሥ
አካዝ ከደማስቆ በላከለት ዝርዝር ጥናት
መሠረት መሠዊያ ሠራ፤ ንጉሡ አካዝ
ከመመለሱም በፊት አጠናቀቀው። 12ንጉሡ
ከደማስቆ ተመልሶ በመጣ ጊዜ፣ መሠዊ
ያውን አየ፤ ቀርቦም በመሠዊያው ላይ ወጣ፤
13ከዚያም የሚቃጠል መሥዋዕቱንና የእህል
ቍርባኑን በመሠዊያው ላይ አቀረበ፤
የመጠጥ ቍርባኑን አፈሰሰ፤ የኅብረት
መሥዋዕቱንም[ለ] ደም በመሠዊያው ላይ
ረጨ። 14በአዲሱ መሠዊያና *በእግዚአብሔር*
ቤተ መቅደስ መካከል፣ *በእግዚአብሔር*
ፊት ቆሞ የነበረውን የናስ መሠዊያ፣ ከቦ
ታው አንሥቶ ከአዲሱ መሠዊያ በስተሰሜን
በኩል አኖረው።
15ከዚያም ንጉሥ አካዝ፣ ካህኑን ኦርያን
እንዲህ ሲል አዘዘው፤ "በዚህ በትልቁ አዲስ
መሠዊያ ላይ የጧቱን የሚቃጠል መሥዋዕ
ትና የማታውን የእህል ቍርባን፣ የንጉሡን
የሚቃጠል መሥዋዕትና የእህሉን ቍርባን
እንዲሁም የመላውን የአገሪቱን ሕዝብ የሚ
ቃጠል መሥዋዕት፣ የእህልና የመጠጥ
ቍርባናቸውን አቅርብ፤ የሚቃጠለውን መሥ
ዋዕት ደምና የሌላውን መሥዋዕት ደም
ሁሉ በመሠዊያው ላይ እርጨው፤ የናሱ
መሠዊያ ግን እኔ መመሪያ ለመጠየቅ
የምጠቀምበት ይሆናል።" 16ካህኑ ኦርያም

[ሀ]3 ወይም፣ *ልጁን ገደለ* [ለ]13 በትውፊት፣ *የሰላም መሥዋዕት*

28፥3፤ ኤር7፥31፤32፥35 ይመ።

16፥4 *ኰረብታ ላይ ባሉ ማምለኪያ ስፍራዎች፤* 15፥4፡35 ይመ፤ እንዲሁም የ1ነገ 15፥14 ማብ ይመ። እነዚህ ኰረብታ ላይ ያሉ ማምለኪያ ስፍራዎች ከአሕዛብ የበአል አምልኮ የተገኙና በቅይጥ የአምልኮ መንገድ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚጠቀሙባቸው ስፍ ራዎች ናቸው። ከእስራኤላውያን ቀደም ብለው ይኖሩ የነበሩ ከነዓናውያን ትላልቅ ዛፎች የልምላሜና የፍሬ ምልክት እንደ ሆኑ ያምኑ ነበር። ኢሥነምግባራዊ የሆኑ የአሕዛብ ሥርዐቶች በእነዚህ ዛፎች ሥር በነበሩ ቤተ ጣዖቶች ይፈጸሙ ነበር። ግልጽ በሆነ ሁኔታ ይህንን ከሚከለክለው የሙሴ ሕግ ተቃራኒ በሆነ መንገድ ይህ የአሕዛብ ልማድ እስራኤላውያንን ተጠናውቷቸው ነበር፤ (17፥10፤ 1ነገ14፥23፤ዘዳ12፥2፤ ኤር2፥20፤ 3፥6፤ 17፥2፤ ሕዝ6፥13፤ 20፥28፤ ሆሴ 4፥13-14 ይመ)።

16፥5 *ረአሶን ... ፋቁሔ ኢየሩሳሌምን ለመውጋት ... ወጡ፤* የ15፥25፡37 ማብ ይመ። *ሊያሸንፉት አልቻሉም፤* ኢሳ7፥1-17፤ 2ዜና 28፥5-21 ይመ። ረአሶንና ፋቁሔ አሦርን በመቃወም ያደ ራጁትን ኃይል የሚያግዝ ድጋፍ ለማግኘት አካዝን ከደቡብ መንግሥት ዙፋን በማውረድ የታቢልን ልጅ ለማንገሥ አስበው ነበር (የ15፥19፡ 25 ማብ ይመ)፤ ይሁዳና አካዝ ዐመፀኞች ቢሆኑም እንኳ፣ እግዚአብሔር ለዳዊት በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ከተቃጣባቸው ጥቃት ታደጋቸው (1ነገ11፥36፤ 2ሳሙ7፥13፤ ኢሳ7፥3-7፡14 ይመ)።

16፥6 *የሶርያ ንጉሥ ረአሶን ... ኤላትን ወደ ሶርያ ... መለሰ፤* የ14፥22 ማብ ይመ። *ከዚያም ኤዶማውያን ወደ ኤላት መጥተው፤* 2ዜና28፥17 ይመ። እንዲሁም ፍልስጥኤማውያን ቀደም ብሎ የደረሰባቸውን ሽንፈት ለመበቀል ይህን እድል ተጠቅመውበታል (2ዜና26፥5-7 ያለውን ከ2ዜና28፥18 ጋር ያነጻጽሩ)። *እስከ ዛሬ በዚያ ይኖራሉ፤* የ1ነገ8፥8 ማብ ይመ።

16፥7 *ቴልጌልቴልፌልሶር፤* 15፥19፡29 ማብ ይመ። *አገል ጋይህም ልጅህም፤* አካዝ በእግዚአብሔር ከመታዘዝና በቃል ኪዳኑ ተስፋ ከማመን ይልቅ ከአሦር ጋር በመስማማት ሰላምን ለይሁዳ ማምጣት ፈለገ (ዘፀ 23፥22፤ ኢሳ 7፥10-16 ይመ)።

16፥8 *በቤተ መቅደስ ... የሚገኘውን ብርና ወርቅ፤* በቤተ መቅደስ የሚገኘው ንብረት በመጠኑም ቢሆን በኢዮአታም ወደ ቦታው ሳይመለስ አልቀረም፤ (12፥18፤14፥14 ይመ)። የይሁዳው ኢዮአካዝ (አካዝ) ስም በ734 ዓ.ቅ.ክ ለቴልጌልቴልፌልሶር ከሚገ ብሩት የገዥዎች ዝርዝርና ከፍልስጥኤማውያን፣ ከአሞናውያን፣ ከሞዓባውያንና ከኤዶማውያን ጋር ተጠቅሶአል።

16፥9 *ደማስቆን አጥቅቶ ያዛት፤* በ732 ዓ.ቅ.ክ ቴልጌል ቴልፌልሶር ሣልሳዊ ደማስቆን በመውረር ደመሰሳት (በኢሳ 7፥16፤ አሞ1፥3-5 ላይ ያሉትን ትንቢቶች ይመ)። *ሕዝቧን ... ወደ ቂር አፈለሳቸው፤* በአሞ1፥5 ላይ የተነገረው ትንቢት እንዲፈጸም፣ ሶርያውያን ቀድሞ ወደ ነበሩበት ስፍራ ተወሰዱ (አሞ9፥7)። በኢሳ 22፥6 ላይ ከኤላም ጋር ብትጠቀስም፣ ቂር ያለችበት ስፍራ የት እንደ ሆነ አይታወቅም።

16፥10 *አካዝ ... ቴልጌልቴልፌልሶርን ለመገናኘት ወደ ደማ ስቆ ሄደ፤* አክብሮቱንና ታማኝነቱን ለባለ ድሉ የአሦር ንጉሥ ለመግለጽ በታዛዥ ንጉሥነቱ ይህን አደረገ። *በደማስቆም ያለውን መሠዊያ፤* ምናልባት ሬሞን የተባለው አምላክ መሠዊያ ሊሆን ይችላል (5፥18፤2ዜና28፥23 ይመ)፤ ይሁን እንጂ መሠዊያው የንጉሡ የቴልጌልቴልፌልሶር ነበር። አካዝ የመሠዊያውን አሠራር አይቶ በይሁዳ እንዲሠራ ማሰቡ፣ የበለጠ ለአሦራውያን መንበርከኩን ያመለክታል።

16፥13 *የሚቃጠል መሥዋዕቱንና የእህልን ቍርባኑን ... የመጠጥ ቍርባኑን ... የኅብረት መሥዋዕቱንም፤* ከመጠጡ ቍርባን በቀር፣ ሌሎቹ መሥዋዕቶቹ ቤተ መቅደሱ በተቀደሰ ጊዜ ቀርበው ነበር (1ነገ 8፥64)።

16፥14 *ከአዲሱ መሠዊያ በስተ ሰሜን በኩል፤* ከቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት ለናሱ መሠዊያ የተመደበለት ስፍራ ነበር፤ አካዝ ይህን መሠዊያ ከቦታው አንሥቶ በአዲሱ የድንጋይ መሠ ዊያ አጠገብ አስቀመጠው።

16፥15 *በትልቁ አዲስ መሠዊያ፤* እግዚአብሔር ሲመለክ እሳት ከሰማይ ወርዶ በነሐሱ መሠዊያ ላይ የቀረበውን ቢቀድሰ ውና ቢቀበለውም (2ዜና7፥1ይመ)፣ አካዝ በደማስቆ ለጣዖት አም ልኮ በተሠራው መሠዊያ መልክ በተሠራው ተካው። የነሐሱ መሠ ዊያ ትልቅ ቢሆንም (2ዜና4፥1ይመ)፣ አዲሱ መሠዊያ ከዚያ የበ ለጠ ነበር። *የጥዋቱን የሚቃጠል መሥዋዕት፤* 3፥20፤ ዘፀ29፥38-39፤ ዘኍ28፥3-4 ይመ። *የማታውን የእህል ቍርባን፤* የ1ነገ18፥29 ማብ ይመ። *የንጉሡን የሚቃጠል መሥዋዕትና የእህሉን ቍርባን፤* ሕዝቅ ኤል ወደ ፊት የሚመጣው ንጉሥ ስለሚያቀርበው መሥዋዕት ከተና ገረው በቀር (ሕዝ46፥12)፣ ከዚህ ሌላ ንጉሥ በብሉይ ኪዳን ስለሚ ያቀርበው ልዩ መሥዋዕት አልተጠቀሰም። *የናሱ መሠዊያ ግን እኔ መመሪያ ለመጠየቅ የምጠቀምበት ይሆናል፤* መልካም ወይም ክፉ ዕድል እንደሚያጋጥማቸው ምልክት ለማግኘት የተሠዋ እን ስሳትን ሆድ ዕቃ በመመርመር መረዳት የተለመደ እንደነበር በጥንት የቅርብ ምሥራቅ ጽሑፎች በሚገባ ተረጋግጦአል። ይህ

ንጉሡ አካዝ እንዳዘዘው ሁሉ እንዲሁ አደረገ።
17ንጉሡ አካዝም የጐንና የጐን ሳንቃዎቹን
ነቅሎ ወሰደ፤ በተንቀሳቃሹ መቆሚያ ላይ
ያሉትን የመታጠቢያ ሳሕኖች አስወገደ።
የውሃ ማጠራቀሚያውን ክብ ገንዳ ከታች
ተሸክመው ከያዙት ከዐሥራ ሁለቱ የናስ
ቅርጽ ኮርማዎች ላይ አውርዶ በጠፍጣፋ
ድንጋይ ላይ አስቀመጠው። 18የአሦርንም
ንጉሥ ለማስደሰት ሲል፣ በዕለተ ሰንበት
ንጉሣዊ ዙፋን* እንዲዘረጋበት በቤተ
መቅደሱ ውስጥ የተሠራውን ከፍ ያለ ስፍ
ራና ነገሥታቱ ወደ እግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ የሚገቡበትን በውጭ ያለውን
መግቢያ አነሣ።
19በአካዝ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው
ሌላው ሥራ፣ የፈጸመውም ሁሉ በይሁዳ
ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለ
ምን? 20አካዝም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤
ከእነርሱ ጋር በዳዊት ከተማ ተቀበረ። ልጁ
ሕዝቅያስም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

### ሆሴዕ የመጨረሻው የእስራኤል ንጉሥ

17፥3-7 ተጓ ምብ - 2ነገ18፥9-12

17 የይሁዳ ንጉሥ አካዝ በነገሠ በዐሥራ
ሁለተኛው ዓመት፣ የኤላ ልጅ
ሆሴዕ በሰማርያ ከተማ በእስራኤል ላይ ነገሠ፤
ዘጠኝ ዓመትም ገዛ። 2እርሱም በእግዚ
አብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረገ፤ ክፉ ሥራው
ግን ከእርሱ አስቀድሞ የነበሩት የእስራኤል
ነገሥታት የፈጸሙትን ያህል አልነበረም።

16፥17 1ነገ7፥27
16፥18 ሕዝ16፥28
16፥20 ኢሳ14፥28
17፥1 2ነገ15፥30
17፥2 ዘዳ4፥25
17፥3 መሳ3፥15፤ ሆሴ10፥14
17፥4 መዝ146፥3፤ ኢሳ30፥1:7፤36፥6፤ ኤር2፥36፤ሆሴ12፥1፤ 13፥10
17፥5 ሆሴ13፥16
17፥6 ቍ20፤ዘዳ4፥27፤24፥1፤2ነገ15፥29፤ 1ዜና5፥26፤ኢሳ10፥9፤ 42፥24፤አሞ7፥17
17፥7 ዘፀ14፥15-31፤ኢሱ7፥11
17፥8 ዘፀ34፥15፤ ዘሌ18፥3፤ዘዳ9፥4

3የአሦር ንጉሥ ስልምናሶር ሊወጋው መጣ፤
ሆሴዕም ተገዛለት፤ ገበረለትም። 4የአሦር
ንጉሥ ግን ሆሴዕ እንደ ከዳው ተገነዘበ፤
ምክንያቱም ወደ ግብፅ ንጉሥ ወደ ሲጐር
መልክተኞች ስለላከና በየዓመቱም ያደርግ
እንደነበረው ለአሦር ንጉሥ ስላልገበረ
ነው፤ ከዚህም የተነሣ ስልምናሶር ይዞ ወህኒ
ቤት አስገባው። 5የአሦርም ንጉሥ አገሩን
በሙሉ ወረረ፤ ወደ ሰማርያም ገሥግሦ
ሦስት ዓመት ከበባት። 6በሆሴዕ ዘመነ
መንግሥት በዘጠነኛው ዓመት፣ የአሦር
ንጉሥ ሰማርያን ያዘ፤ እስራኤላውያንንም
በምርኮ ወደ አሦር አፈለሳቸው። እነዚህም
በአላሔ፣ ጎዛን ውስጥ በአቦር ወንዝ አጠ
ገብ እንዲሁም በሜዶን ከተሞች እንዲ
ሰፍሩ አደረገ።

### እስራኤላውያን በኀጢአታቸው ምክንያት ተማረኩ

7እንግዲህ እስራኤላውያን ይህ ሁሉ ሊደር
ስባቸው የቻለው፣ ከግብፅ ምድር ከፈርዖን
አገዛዝ ከግብፅ ንጉሥ ያወጣቸውን አምላካ
ቸውን እግዚአብሔርን ስለ በደሉት ነው፤
እንዲሁም ሌሎች አማልክትን በማምለክ፣
8እግዚአብሔር ከፊታቸው አሳዶ ያወጣቸ
ውን የአሕዛብንና የእስራኤልም ነገሥታት
ወደ ምድሪቱ ያገቡትን አጸያፊ ልማድ ስለ
ተከተሉ ነበር።

*18 የሰብዓ ሊቃናት መሥዋዕት ትርጕም፣ የዙፋኑ ስሌዳ ይላል።

የሚያሳየን አካዝ የእግዚአብሔርን አመራር ለማወቅ የአሦራውያንን የጥንቆላ መንገድ ለመጠቀም መሞከሩን ነው።

16፥17 *የጐንና ጐን ሳንቃዎቹን ... በተንቀሳቃሹ መቆሚያ ላይ ያሉትን የመታጠቢያ ሳሕኖች፤* 1ነገ7፥27-39 ይመ። *ክብ ገንዳ ... የናስ ቅርጽ ኮርማዎች ላይ አውርዶ፤* 1ነገ 7፥23-26 ይመ። ምናልባት ናሱ የተፈለገው ቴልጌልቴልፌልሶር ሣልሳዊ የጠየቀውን ግብር ለመክፈል ይሆናል።

16፥18 *የአሦርንም ንጉሥ ለማስደሰት፤* እንደ ታማኝ የቴልጌልቴልፌልሶር አገልጋይ አካዝ ንጉሣዊ ሥልጣኑን የሚያሳዩትን አንዳንድ ምልክቶችን ለመተው ተገደደ።

16፥19 *በአካዝ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው ሌላው ሥራ፤* ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ በ2ዜና 28፥24 አካዝ፣ "የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በሮች" እስከ መቆለፍ ደርሶ ነበር የሚለውን ይመ። በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ፤ የ1ነገ 14፥29 ማብ ይመ።

16፥20 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1ነገ 1፥21 ማብ እንዲሁም፤ 2ዜና 28፥27 ይመ። *ልጁ ሕዝቅያስም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፤* ስለ ሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት 18፥1-20-21 ይመ።

17፥1 *አካዝ በነገሠ በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት፤* አካዝ ከዖዝርያስ ጋር አብሮ የገዛበትን በ744 ወይም በ743 ዓ.ቅ.ክ (የ 16፥1-2 ማብ ይመ) ግምት ውስጥ ስናስገባ በ732 ዓ.ቅ.ክ ይሆናል (የ 15፥30 ማብ ይመ)። አንዳንዶች አካዝ መግዛት የጀመረበት ጊዜ በ735 ዓ.ቅ.ክ እንደ ነበር ይናገራሉ። ይኸውም በዚህ ክፍል "በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት" የሚለው፣ ጽሑፉን የገለበጠው ሰው "በአራተኛው ዓመት" ማለት ሲገባው በስሕተት የጻፈው ነው ይላሉ፤ *ዘጠኝ ዓመት፤* ከ732-723 ዓ.ቅ.ክ ነው፤ (በ1ነገ መግቢያ ሥር "የዘመን ቅደም ተከተል" የሚለውን ይመ።

17፥3 *ስልምናሶር፤* በሣልሣዊው ቴልጌልቴልፌልሶር ዘመነ መንግሥት ሆሴዕ የአሦር ታማኝ አገልጋይ ሆኖ ነበር (የ15፥30 ማብ ይመ)። ሣልሣዊው ቴልጌልቴልፌልሶርም ከ727-722 ዓ.ቅ.ክ በገዛው በስልምናሶር አምስተኛ ተተካ።


17፥5 *ሦስት ዓመት፤* ከ725-722 ዓ.ቅ.ክ ሰማርያ በተጠናከረ ሁኔታ ተመሽጋ ስለ ነበር የምትደፈር ከተማ አልነበረችም፤ (የ1ነገ 16፥24 ማብ ይመ)።

17፥6 *በሆሴዕ ... በዘጠነኛው ዓመት፤* በ722 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው (የቍ 1ማብ ይመ)። *የአሦር ንጉሥ ሰማርያን ያዘ፤* ስልምናሶር አምስተኛ ከ722-721 ዓ.ቅ.ክ በክረምት ወር (በታኅሣሥ) ሳይገደል አልቀረም፤ ስለዚህም በ722/721-705 ዓ.ቅ.ክ ዳግማዊ ሳርጎን በአሦር ዙፋን ላይ ተቀመጠ። ዳግማዊ ሳርጎን በዙፋን ላይ እንደተቀመጠ ሰማርያን እንደ ያዘ፣ ስለ እርሱ በተጻፈው ታሪክ ተገልጾአል፤ ነገር ግን ሁኔታው ከአንድ ወቅት ወረራ ያላለፈ ነበር። *እስራኤላውያንንም ... አፈለሳቸው፤* የሰሜኑ መንግሥት ለኪዳኑ የመታዘዝ ግዴታውን ስላፈረሰ፣ የሰሜኑ መንግሥት የመጀመሪያ ንጉሥ ቀዳማዊ ኢዮርብዓም በነገሠበት ዘመን በነቢዩ አኪያ የተነገረውን ፍርድ እግዚአብሔር አመጣባቸው (የ1ነገ 14፥15 ማብ ይመ)። ዳግማዊ ሳርጎን ሀያ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና እስራኤላውያንን እንዳፈለሰ በታሪኩ ተገልጾአል። ከዚያም ከሌላ ቦታ ያፈለሳቸውን ሕዝቦች ባድማ በሆኑ በሰሜኑ መንግሥት ከተሞች ላይ አሰፈራቸው (ቍ 24 ይመ)። *በአላሔ፤* ይህ ስፍራ የት እንደ ሆነ አይታወቅም። *ጎዛን ውስጥ በአቦር ወንዝ፤* አሦር የአውራጃ ከተማ ሲሆን፣ በኤፍራጥስ ገባር ወንዝ ላይ የሚገኝ ነው። *በሜዶን ከተሞች፤* ከካስፒያን ባሕር በስተደቡብ ከጤግሮስ ወንዝ በስተ ሰሜን ምሥራቅ የሚገኙ ከተሞች ናቸው።

17፥7-23፤ የሰሜኑ መንግሥት በምን ምክንያት እንደ ወደቀ የሚያስረዳ ሥነ መለኮታዊ ማብራሪያ ነው። እስራኤል እግዚአብሔር በቸርነቱ ያደረገላትን ደጋግማ ናቀች፤ ነቢያትም ሊመጣ ስላለውም ፍርድ የተናገሩትን ማስጠንቀቂያ ተቃወመች (ቍ 13-14:23)፤ በቃል ኪዳንም የገባችውን ግዴታ ችላ አለች (ቍ 15)። ስለዚህም እስራ ኤላውያን ወደ ከነዓን ከመግባታቸው በፊት በሙሴ የተነገረው የቃል ኪዳኑ ርግማን ደረሰባቸው (ዘዳ 28፥49-68፤ 32፥1-47)።

17፥7 *ከግብፅ ምድር ... ያወጣቸውን፤* በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ከግብፅ ነጻ መውጣት መሠረታዊ የሆነ ቤዛነትን ያገኙበት ክሥተት ነበር። ከጌታ ቸርነትና ከኀይል ሥራው የተነሣ እስራኤል መንግሥት ሆና ለመታወቅ በቃች (ዘፀ20፥2፤ ዘዳ5፥15፤ 26፥8፤ ኢሱ 24፥5-7:17፤ መሳ10፥11፤ 1ሳሙ12፥6፤ ነህ9፥9-13፤ ሚክ 6፥4 ይመ)። *ሌሎች አማልክትን በማምለክ፤* እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር በነበራት ኪዳን እጅግ መሠረታዊ የሆነ ግዴታን ያፈረሰችበት (ቍ35፤ ዘዳ5፥7፤ 6፥14፤ ኢሳ24፥14-16:20፤ ኤር1፥16፤ 2፥5-6፤ 25፥6፤ 35፥15 ይመ)።

17፥8 *የአሕዛብንና ... አስጸያፊ ልማድ፤* ዘዳ18፥9፤ መሳ 2፥12-13 ይመ። *የእስራኤል ነገሥታት ወደ ምድሪቱ ያገቡትን አስጸያፊ ልማድ፤* ለምሳሌ ኢዩ (10፥31)፣ *ዳግማዊ ኢዮርብዓም* (14፥24)፣ *ቀዳማዊ ኢዮርብዓም* (1ነገ12፥28-33)፣ ዘንበሪ (16፥25-26) እና አክዓብ (16፥30-34) ይመ።




# የሰሜኑ መንግሥት በምርኮ መወሰድ

የማረኳቸውን ብዙዎችን የማፍለስ አሠራር በአሦራውያን ነገሥታት ዘንድ የታሰበ በት የጭከና ወረራ አንዱ ክፍል ነው:: ይህ ዓመፅን ለመቀስቀስ የታሰበ ቢሆንም ድህነት እንዲስፋፋና ጥላቻ እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል:: በመጨረሻም የአሦር ግዛት በፍጥነት እንዲከፋፈል ሰበብ ሆነ::

እስራኤል ለመጀመሪያ በቴልጌልቴልፌልሶር (745-727 ዓ.ቅ.ክ)፣ ከዚያም የሰማርያ ከተማ ስትፈርስ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ በሳርጎን (722-705) በምርኮ መወሰዷን የሚያረጋግጡ አንዳንድ ማስረጃዎች አሉ:: የኋለኛው ንጉሥ መዛግብት 27,290 የከተማውን ነዋሪዎች እንዳ ፈለሰ (ማርኮ እንደወሰደ) በትዕቢት የተናገረው ተጽፎ ይገኛል:: እንደ 2ነገ17:6 ዘገባ መሠረት ወደ አሦር የፈለሱት በአላሔና በጎዛን የአቦር ወንዝ ተሻግረው በግዛቱ ምሥራቃዊ ድንበር እንደሆነ ያስረዳል::

ከዚህ በመቀጠልም የሳርጎን መዛግብት ላይ የሚከ ተለው ሰፍሯል::"በምድረ በዳው የሚኖሩት አለ ቃም ሆነ አስተዳደር የማያውቁት፣ ለየትኛውም ንጉሥ ገና መገበር ያልጀመሩትን ዓረቦች ወደ ሰማርያ አፍልሼ በዚያ እንዲሰፍሩ አደረግሁ::"

የጠፉት አሥሩ የእስራኤል ነገዶች በሚል ርእስ ብዙ ተረቶች ይነገራሉ:: የአሦራውያን መዛግብት ጠለቅ ተብለው ሲመረመሩ በምርኮ የፈለሱት የገ ጉማውያን ቤተ ዘመዶች የሚያጠቃልል ከአጠቃ ላይ ሕዝብ ብዛት የተወሰነው ያህሉ ብቻ እንደወ ሰዱ ያመለክታሉ:: ብዙኀኑ በግብርና ሥራ ላይ የተሰማራው ለዚሁ ሥራ ሲባል እዚያው የተተወ ነበር (ባቢሎናውያን ካደረጉት ጋር ያነጻጽሩ 2ነገ 24:14፣25:12)

9እስራኤላውያን በአምላካቸው በእግዚ
አብሔር ላይ ትክክል ያልሆነ ነገር በስውር
አደረጉ፤ ከቃፊር መጠባበቂያ ማማ አንሥቶ
እስከ ተመሸገው ከተማ ባሉት መኖሪያዎቻ
ቸው ሁሉ በሚገኙት ኰረብቶች ላይ ማም
ለኪያ ስፍራዎችን ሠሩ። 10በእያንዳንዱ ኰረ
ብታ ላይና በእያንዳንዱም የተንሰራፋ ዛፍ
ሥር ዐምደ ጣዖትና የአሼራን ምስል ዐም
ዶች አቆሙ። 11እግዚአብሔር ከፊታቸው
አሳዶ ያስወጣቸው አሕዛብ እንዳደረጉትም
ሁሉ፣ በየኰረብታው ላይ ዕጣን አጤሱ፤
እግዚአብሔርንም የሚያስቈጣ ክፉ ነገር
አደረጉ። 12እግዚአብሔር ፣ "ይህን ማድረግ
አይገባችሁም" * ቢላቸውም እንኳ እነርሱ ጣዖ
ታትን አመለኩ፡ 13ይህም ሆኖ እግዚአብሔር፣
"ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ፤ አባቶቻችሁ
እንዲፈጽሙት ባዘዝኋቸው ሕግ ሁሉ መሠ
ረት እንዲሁም በአገልጋዮቼ በነቢያት አማ
ካይነት ለእናንተ ባስተላለፍሁት ሕግ መሠ
ረት፣ ትእዛዜንና ሥርዐቴን ጠብቁ" ብሎ
በነቢያቱና በባለ ራእዮች ሁሉ እስራኤልንና
ይሁዳን አስጠንቅቆ ነበር።

14ይሁን እንጂ እነዚህም አልሰሙም፤
እግዚአብሔር አምላካቸውን እንዳልታመኑ
በት እንደ አባቶቻቸው አንገታቸውን አደነ
ደኑ። 15ሥርዐቱንና ከአባቶቻቸው ጋር የገባ
ውን ኪዳን፣ ለእነርሱም የሰጣቸውን ማስጠንቀ
ቂያ ናቁ፤ ከንቱ ጣዖታትን ተከትለው ራሳ
ቸውም ከንቱ ሆኑ፤ እግዚአብሔር፣ "እነርሱ
የሚያደርጉትን እንዳታደርጉ" ብሎ ቢያዛ
ቸው እንኳ በዙሪያቸው ያሉትን አሕዛብ
ተከተሉ፤ እግዚአብሔር እንዳያደርጉ የከለከላ
ቸውንም ፈጸሙ እንጂ አልተውም። 16አም
ላካቸው እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ሁሉ አል
ፈጸሙም፤ አቅልጠውም ሁለት የጥጃ ምስ
ልና የአሼራን ምስል ዐምድ ሠሩ፤ ለሰማይ
ከዋክብት ሰገዱ፤ በኣልን አመለኩ፤ 17እንዲ
ሁም ወንዶችንና ሴቶች ልጆቻቸውን በእሳት
የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገው አቀረቡ።*
ጥንቈላና መተት አደረጉ፤ በእግዚአብሔ
ርም ፊት ክፉ ነገር ለማድረግ ራሳቸውን
ሸጡ፤ ለቍጣም አነሣሡት። 18ስለዚህ እግዚ
አብሔር በእነርሱ ላይ እጅግ ተቈጣ፤ የይሁዳ
ነገድ ብቻ ሲቀር እስራኤልን ከፊቱ አራቀ።
19ይሁዳም ቢሆን ከእስራኤል የተቀበለውን
ልማድ ተከተሉ እንጂ የአምላኩን የእግዚ
አብሔርን ትእዛዝ አልጠበቀም። 20ስለዚህ
እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ሁሉ
ተዋቸው፤ አስጨነቃቸው፤ ከፊቱ እስኪ
ያስወግዳቸውም ድረስ በማራኪዎቻቸው እጅ
አሳልፎ ሰጣቸው።

21እስራኤልን ከዳዊት ቤት ክለየ በኋላ፣
እነርሱ የናባጥን ልጅ ኢዮርብዓምን አነገሡ፤
ኢዮርብዓምም እስራኤል እግዚአብሔርን
እንዳይከተል በማሳት ትልቅ ኀጢአት እን
ዲሠራ አደረገ። 22እስራኤላውያንም በኢዮ
ርብዓም ኀጢአት ሁሉ ጸኑ፤ ከዚያም አልተ
መለሱም። 23እግዚአብሔር በባሪያዎቹ በነቢ
ያት ሁሉ አማካይነት ባስጠነቀቃቸው መሠ
ረት፣ ከፊቱ እስኪያስወግዳቸው ድረስ በዚ
ያው ቀጠሉበት፤ ስለዚህ የእስራኤል ሕዝብ
ከሀገሩ ተማርኮ ወደ አሦር ተወሰደ፤ እሁ
ንም በዚያው ይገኛል።

### አሦራውያን በሰማርያ ሰፈሩ

24የአሦርም ንጉሥ ሕዝቡን ከባቢሎን፣
ከኩታ፣ ከአዋና ከሐማት፣ ከሴፈርዋይም ከተ
ሞች አምጥቶ በእስራኤላውያን ቦታ እንዲ

17፥9 2ነገ18፥8
17፥10 ዘፀ23፥24፤ 34፥13፤ዘዳ12፥2፤ኢሳ 17፥8፤ሚክ5፥14
17፥12 ዘፀ20፥4
17፥13 መሳ6፥8፤ 1ሳሙ9፥9፤2ዜና7፥14፤ ኢዮ34፥33፤ኤር4፥1፤ 18፥11፤23፥22፤25፥5፤ 35፥15፤36፥3፤ሕዝ3፥ 17-19፤ ዘካ1፥4፤ማቴ 23፥34
17፥14 ዘፀ32፥9፤ ሐሥ7፥51
17፥15 ዘሌ26፥11፤ ዘዳ12፥4፤29፥25፤32 ፥21፤መሳ2፥20፤1ነገ 11፥11፤2ነገ18፥12፤ መዝ78፥10፤ኤር2፥5፤ ሕዝ5፥6፤ ሆሴ11፥2፤ ሚል2፥10፤ሮሜ1፥21 -23
17፥16 ዘፍ2፥1፤ዘፀ 32፥4፤ዘዳ16፥21፤ መሳ2፥11፤ኢሳ 40፥26፤ኤር 19፥13
17፥17 ዘሌ19፥26፤ ዘዳ12፥31፤18፥10-12፤ 1ነገ21፥20፤2ነገ16፥3፤ሕዝ 16፥21፤ሮሜ7፥14
17፥18 ዘፍ4፥14፤ ዘፀ33፥15፤2ነገ13፥23፤ 2ተሰ1፥9
17፥19 2ነገ16፥3፤ ኤር3፥6-10፤ሕዝ 23፥13፤
17፥20 ቍ6፤ኤር 7፥15፤15፥1፤
17፥21 1ሳሙ15፥27፤ 1ነገ11፥11፤12፥20፡30፤
17፥23 መሳ6፥8፤1ነገ 9፥7፤ሕዝ39፥23-24፤
17፥24 ቍ31፤2ነገ 15፥29፤18፥34፤19፥ 37፤ዕዝ4፥2፡10፤ኢሳ 36፥19፤37፥13፡38፤አሞ 6፥2

*12 ዘፀ 20፥4-5 *17 ወይም ልጆቻቸው ገደሉ

17፥9 ከተማ ባሉ መኖሪያዎቻቸው ሁሉ በሚገኙት ኰረብቶች ላይ ማምለኪያ ስፍራዎችን፤ 14፥4፤ 15፥4፡35 እንዲሁም የ16፥4፤ የ1ነገ 3፥2፤ የ15፥14 ማብ ይመ።

17፥10 ዐምደ ጣዖት፤ የ1ነገ14፥23 ማብ ይመ። የአሼራን ምስል ዐምዶች፤ የ1ነገ14፥15 ማብ ይመ። በእያንዳንዱ ኰረብታ ላይና በእያንዳንዱም የተንሰራፋ ዛፍ ሥር፤ 16፥4፤ 1ነገ14፥23፤ ኤር2፥20፤ 3፥6፡13፤ 17፥2 ይመ።

17፥11 ክፉ ነገር፤ ምናልባት ከጣዖት አምልኮ ሥርዐት ጋር የሚደረ ግን ዝሙት ሳይሆን አይቀርም (የ1ነገ14፥24 ማብ እና ሆሴዕ 4፥13-14 ይመ)፡

17፥12 ይህን ማድረግ አይገባችሁም፤ አማራጭ ትርጕሙን እንዲሁም ዘፀ 23፥13፤ ዘሌ26፥1፤ዘዳ5፥6-10 ይመ።

17፥13 በነቢያቱ ... እስራኤልንና ይሁዳን አስጠንቅቆ ነበር፤ እስራኤል የተላለፈችው በሲና የተሰጠውን የኪዳኑን ትእዛዛት ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ኪዳኑ ለመመለስ በምሕረቱ የላከውን የነቢያቱን ቃል ጭምር ንቃለች (ለምሳሌ1ነገ13፥1-3፤ 14፥6-16፤ መሳ 6፥8-10፤1ሳሙ3፥19-21 ይመ)። ባለ ራእዩ፤ የ1ሳሙ 9፥9 ማብ ይመ።

17፥14 አንገታቸውን አደነደኑ፤ በሬ ቀንበርን ላለመሸከም ከሚያደርገው ዐመፅ የተወሰደ አገላለጽ ነው (ዘዳ10፥16፤ ኤር 2፥20፤ 7፥26፡17፥23፤ 19፥15፤ ሆሴ 4፥16 ይመ)።

17፥15 ከንቱ ጣዖታትን ተከትለው፤ ዘዳ32፥21፤ ኤር2፥5፡ 8፥19፡ 10፥8፤ 14፥22፤ 51፥18 ይመ።

17፥16 አቅልጠውም ሁለት የጥጃ ምስል፤ የዳንና የቤቴል የወርቅ ጥጃዎችን ማለት ነው (1ነገ 12፥28-30 ይመ)። የአሼራ ምስል ዐምድ፤ የ1ነገ 14፥15ማብ ይመ። ለሰማይ ከዋክብት፤ እስራኤላውያን የጎረቤት አገር ሕዝቦች የሚያመልኳቸውን ከዋክብት እንዳያመልኩ ትእዛዝ ተሰጥቷቸው ነበር (ዘዳ 4፥19፤17፥3ይመ)። እንዲህ ዓይነቱ የጣዖት አምልኮ በአንደኛና በሁለተኛ ነገሥት መጽሐፍ ባይጠቀስም፣ ነቢዩ አሞጽ በሰሜኑ መንግሥት በተለይም በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመን ሕዝቡ በከዋክብት ያመልክ እንደ ነበር አመልክቶአል (የአሞ5፥26 ማብ ይመ)። ምናልባ በነገሡበት ዘመን በደቡብ መንግሥት ይህ አምልኮ ቈይቶ የተጀመረ ሲሆን (21፥3-5 ይመ)፤ በኢዮስያስ ተሐድሶ ዘመን ግን ተወገደ (23፥4-5፡12፤ሕዝ 8፥16 ይመ)።

17፥17 ወንዶችንና ሴቶች ልጆቻቸውን በእሳት የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገው አቀረቡ፤ የ16፥3 ማብ ይመ። ጥንቈላና መተት አደረጉ፤ በሙሴ ሕግ ይህ ልምምድ የተከለከለ ነበር (የ16፥15 ማብ እንዲሁም፤ ዘሌ19፥26፤ዘዳ18፥10 ይመ)።

17፥18 ከፊቱ አራቀ፤ የሰሜኑ መንግሥት ሕዝብ ተማርኮ መወሰዱን ያመለክታል (ቍ6፡23፥27 ይመ)። የይሁዳ ነገድ ብቻ ሲቀር፤ የደቡቡ መንግሥት የስምኦንና የብንያምን ነገዶች ያጠቃልላል፤ ቢሆንም በደቡብ ፍጹም ታማኝነቱን ጠብቆ የተገኘው የይሁዳ ነገድ ብቻ ነበር (የ1ነገ11፥31-32 ማብ እንዲሁም የ2ነገ 19፥4 ማብ ይመ)።

17፥20 አስጨነቃቸው _ በማራኪዎቻቸው እጅ አሳልፎ ሰጣቸው፤ 10፥32-33፤ 13፡3፡20፤ 24፥2፤ 2ዜና21፥16፤ 28፥18፤ አሞ1፥13 ይመ።

17፥21 እስራኤልን ከዳዊት ቤት ክለየ፤ 1ነገ11፥11፡31፤ 12፥24 ይመ። የእስራኤል መንግሥት የተከፈለው በእግዚአብሔር ሲሆን፣ በኀጢአታቸው ምክንያት የደረሰባቸው ቅጣት ነው። ኢዮርብዓም ... ትልቅ ኀጢአት እንዲሠራ አደረገ፤1ነገ12፥26-32፤13፥33-34 ይመ።

17፥23 በባሪያዎቹ በነቢያት ሁሉ አማካይነት ባስጠነቀቃቸው መሠረት፤ 1ነገ14፥15-16፤ ሆሴ10፥1-7፡ 11፥5፤ አሞ5፥27 ይመ።

17፥24 የአሦርም ንጉሥ ቀደም ብሎ ይህን ያደረገው ዳግማዊ ሳርጎን (722-705 ዓ.ቅ.ክ) ሲሆን፣ በኋላም ሌሎች የአሦር ገዦዎች ማለትም አስርሐዶን (681-669 ዓ.ቅ.ክ) እና አሹርባኒፓል (669-627 ዓ.ቅ.ክ) ሌሎች ሕዝቦችን በሰ ማርያ አስፍረው ነበር (ዕዝ 4፥2፡9-10 ይመ)። ከባቢሎን፣ ከኩታ፤ ባቢሎንና ኩታ ከባቢሎን ከተማ በስተ ሰሜን ምሥራቅ ዐሥራ ሦስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ በዳግማዊ ሳርጎን በ709 ዓ.ቅ.ክ በአሦር አጥዘዝ ሥር እንዲሆኑ ተገደው ነበር። ከአዋ፤ ምናልባት ከኢዋ ጋር ተመሳሳይ ሳይሆን አይቀርም (18፥34፡19፥13 ይመ)። ከሐማት፤ ከአርፋድና ከሴፈርዋይም

ገቡ በሰማርያ ከተሞች አሰፈራቸው፤ እነር
ሱም ሰማርያን ወርሰው በከተሞቿ ይኖሩ
ጀመር:: 25በዚያ መኖር እንደ ጀመሩም
*እግዚአብሔርን* አላመለኩም፤ ስለዚህ እግዚ
አብሔር አንበሶች ሰደደባቸው፤ ከእነርሱም
ጥቂቶቹን ሰብረው ገደሉ:: 26ለአሦርም
ንጉሥ፣ “ወደ ሰማርያ ከተሞች ወስደህ ያሰ
ፈርኸው ሕዝብ የዚያ አገር አምላክ የሚፈ
ልገውን አላወቀም፤ ከዚህም የተነሣ እግዚ
አብሔር ሰብሮ የሚገድል አንበሳ ላከበት”
የሚል ወሬ ደረሰው::
27ከዚያም የአሦር ንጉሥ፣ “ከሰማርያ
ማርካችሁ ካመጣችኋቸው ካህናት አንዱን፣
በእዚያው እንዲኖር መልሳችሁ ውሰዱትና
የአገሩ አምላክ ምን እንደሚፈልግ ሕዝቡን
ያስተምር” ሲል አዘዘ:: 28ስለዚህ ከሰማርያ
ማርከው ከወሰዷቸው ካህናት አንዱ ወደ
ቤቴል ተመልሶ *እግዚአብሔርን* እንዴት
ማምለክ እንደሚገባቸው አስተማራቸው::
29ያም ሆኖ ግን እያንዳንዱ ወገን በየ ሰፈ
ረበት ከተማ የራሱን አምላክ ሠራ፤ ያንንም
ቀድሞ የሰማርያ ሕዝብ በኰረብታው ላይ
በሠራው ማምለኪያ እየወሰደ አቆመ:: 30ከባ
ቢሎን የመጡት ሱኮትበኖትን፣ ከኩታ የመ
ጡት ኔርጋልን፣ ከሐማት የመጡት አስ
ማትን ሠሩ፤ 31አዋውያንም ኤልባዝርንና
ተርታቅ የተባሉትን አማልክት ሲሠሩ፣ ከሴ
ፈርዋይም የመጡት ደግሞ አድራሜሌክና
አናሜሌክ ለተባሉት አማልክታቸው ልጆቻ
ቸውን የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገው
አቀረቡ:: 32*እግዚአብሔርን* አመለኩ፤ ይሁን
እንጂ እያንዳንዱ ወገን የመጣበትን ሕዝብ
ልማድ ተከትሎ፣ በየኰረብታው ባሉት ቤተ
ጣዖታት የሚያገለግሉትን ካህናት ሾመ::
33በአንድ በኩል *እግዚአብሔርን* ሲያመልኩ፣
በሌላ በኩል ግን እንደየአገራቸው ልማድ
የየራሳቸውን አማልክት ያመልኩ ነበር::
34ይህንንም ልማዳቸውን እስከ ዛሬ ድረስ
አልተውትም፤ *እግዚአብሔርን* በአግባቡ
አያመልኩም፤ እንዲሁም እስራኤል ብሎ
ለጠራው ለያዕቆብ ዘሮች የሰጣቸውን
ሥርዐቶችና ደንቦች፣ ሕጎችና ትእዛዞችን
አይከተሉም:: 35*እግዚአብሔር* ከእስራኤላውያን
ጋር ኪዳን ሲገባ እንዲህ ሲል አዞአቸው
ነበር፤ “ሌሎችን አማልክት አታምልኳቸው፤
አትስገዱላቸው፤ አታገልግሏቸው፤ አትሠው
ላቸውም፤ 36ማምለክ የሚገባችሁ ግን በታላቅ
ኀይልና በተዘረጋች ክንድ ከግብፅ ምድር
ያወጣችሁን *እግዚአብሔርን* ብቻ ነው::
ለእርሱ ስገዱ፤ ለእርሱም መሥዋዕት አቅ
ርቡ:: 37የጻፈላችሁን ሥርዐቶችና ደንቦች፣
ሕጎችና ትእዛዞች ምን ጊዜም ተግታችሁ
ጠብቁ:: ሌሎች አማልክትን አታምልኩ::
38ከእናንተ ጋር የገባሁትን ኪዳን አትርሱ፤
ሌሎች አማልክትም አታምልኩ:: 39ይልቅስ
አምላካችሁን *እግዚአብሔርን* አምልኩ፤ ከጠ
ላቶቻችሁ ሁሉ እጅ የሚታደጋችሁ እርሱ
ነውና::”
40ነገር ግን በቀደመው ልማዳቸው ጸኑ
እንጂ አልተመለሱም:: 41እነዚህ ሕዝቦች
ምንም እንኳ በአንድ ወገን *እግዚአብሔርን*
ቢያመልኩት የተቀረጹ ምስሎቻቸውንም
ያገለግሉ ነበር:: ልጆቻቸውና የልጅ ልጆ
ቻቸውም አባቶቻቸው ያደረጉትን ዛሬም
እንደ ቀጠሉበት ነው::

17፥25 ዘፍ37፥20፤ ኢሳ5፥29፤15፥9፤ ኤር50፥17
17፥29 ዘሌ26፥30፤ 1ነገ12፥31፤ኤር 2፥28፤11፥13፤ ሚክ4፥5
17፥31 ቍ 24፤ 2ነገ19፥37
17፥32 1ነገ12፥31
17፥34 ዘፍ17፥5፤ 1ነገ18፥31
17፥35 ዘፀ20፥3፡5
17፥36 ዘፀ3፥20፤ መዝ136፥12
17፥37 ዘሌ19፥37፤ ዘዳ5፥32
17፥38 ዘዳ6፥12
17፥41 1ነገ18፥21፤ ዕዝ4፥2፤ማቴ6፥24

ጋር መጠቀሱ በሶርያ አካባቢ መሆኑን የሚያመለክት ነው:: *ከሐማት፤* በኦሮንቴስ ወንዝ አጠገብ የሚገኝ ስፍራ ነው (14፥25፤ 18፥34፤ የሕዝ 47፥15 ማብ ይመ)፣ *ዳግማዊ* ሳርጎን በ720 ዓ.ቅ.ክ የሐማትን መንግሥት የአሦር አውራጃ አደረገው:: ከሴፈርዋይም፤ በሶርያ ግዛት ምናልባትም በደማስቆና በሐማት መካከል የሚገኝ ሳይሆን አይቀርም:: *በሰማርያ፤* በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው የሰሜኑን መንግሥት በሙሉ ለማመልከት ነው (የ1ነገ 13፥32 ማብ ይመ)::

17፥25 *እግዚአብሔርን አላመለኩም፤* በአገራቸው የሚያመልኳቸውን አማልክት ያመልኩ ነበር:: *አንበሳ ላከበት፤* በከነዓን አንበሶች ምንጊዜም ነበሩ (1ነገ 13፥24፤20፥36፤ መሳ14፥5፡ 1ሳሙ17፥34፤ አሞ 3፥12 ይመ):: ከአሦራውያን ጋር በተፈጠረው ግጭት ሕዝቡ በመፈናቀሉና ቍጥሩም በመመናመኑ የአንበሶቹ ቍጥር እጅግ እየበዛ ሄደ (ዘፀ23፥29 ይመ):: ይህ ሁኔታ በምድሪቷ ነዋሪዎችና በነገሥት ጸሐፊ ዘንድ ከእግዚአብሔር እንደ መጣ ቅጣት ተቈጥሮ ነበር (ዘሌ 26፥21-22 ይመ)::

17፥26 *ለአሦርም ንጉሥ፤* ለዳግማዊ ሳርጎን ማለት ነው:: *የዚያ አገር አምላክ የሚፈልገውን፤* በዚያ ዘመን በነበረው የሃይማኖት አስተሳሰብ፣ የእያንዳንዱ አገር አምላክ የየራሱ ሥርዐትና ደንብ አለው ተብሎ ይታመን ነበር፤ ይህ ሥርዐትና ደንብ ቸል ከተባለ ወይም ከተጣሰ ክፉ ነገር በምድሪቱ ላይ ይመጣል ይባላል::

17፥27 *ካህናት አንዱን፤* በሰሜኑ መንግሥት በቀዳማዊ ኢዮርብዓም ዘመን የወርቁን ጥጃ ከሠሩት መካከል ማለት ነው፤ (1ነገ 12፥31 እና ማብ ይመ)::

17፥28 *ወደ ቤቴል ተመልሶ፤* ከቀዳማዊ ኢዮርብዓም ዘመን ጀምሮ ቤቴል እግዚአብሔርን የካደ አምልኮ ማዕከል ነበረች (የ1ነገ 12፥28-30 ማብ ይመ)::

17፥29 *የሰማርያ ሕዝብ፤* በቀድሞ የሰሜኑ መንግሥት ግዛት ድብልቅ የነበሩ ሕዝቦች ናቸው:: የእነዚህ ድብልቅ ሕዝቦች ቀደምት አባቶች ሳምራውያን በመባል ይታወቁ ጀመር:: በኃለኛው ዘመን እነዚህ ሕዝቦች ቀድሞ ይከተሉት የነበረውን የጣዖት አምልኮን በመቃወምና የሙሴን ትምህርት በመቀበል አንድ አምላክ የሆነውን እግዚአብሔርን ማምለክ ጀመሩ:: በአዲስ ኪዳን ዘመን ጌታችን ኢየሱስ ለሳምራዊቷ ሴት ወንጌልን መስከረላት (ዮሐ 4፥4-26)፤ በፊልጶስ አገልግሎትም ብዙ ሳምራውያን በወንጌል አመኑ (ሐሥ 8፥4-25)::

17፥32 *የሚያገለግሉትን ካህናት ሾመ፤* የ1ነገ፥31 ማብ ይመ::

17፥33 *እግዚአብሔርን ሲያመልኩ ... የየራሳቸውን አማልክት ያመልኩ ነበር፤* ቅይጥ የሆነን እምነት ደህና አድርጎ የሚገልጥ አባባል ነው::

17፥34 *እስከ ዛሬ ድረስ፤* የአንደኛና የሁለተኛ ነገሥት መጽሐፍ እስከተጻፈበት ጊዜ ማለት ነው:: *እግዚአብሔርን ... አያመልኩም፤* እዚህ ላይ የተገለጸው በትክክል አለማምለካቸውን ለማሳየት ነው:: በቍ32-33 “እግዚአብሔርን አመለኩ” ሲባል ከጣዖት አምልኮ ባልተለየ መልኩ ነው::

17፥35 *ሌሎችን አማልክት አታምልኳቸው፤* የሙሴ ሕግ እግዚአብሔር ብቻ መመለክ እንዳለበት ይገልጻል (ዘፀ20፥5፤ዘዳ 5፥9 ይመ):: የመጀመሪያውና ታላቁ ትእዛዝ ይህ ነው፤ እስራኤላውያንንም ከሌላው ሕዝብ ልዩ የሚያደርጋቸው ይኸው ነበር::

17፥36 *ማምለክ የሚገባችሁ ... ከግብፅ ምድር ያወጣችሁን እግዚአብሔርን ብቻ ነው፤* በቍጥር 7 ላይ እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገው ታላቅ የቸርነት ሥራ ነው፤ ከዚህም የተነሣ ቅይጥ ሳይኖርበት በሙሉ ልብ እስራኤል ታመልከው ዘንድ ገዴታ ነው::

17፥39 *ከጠላቶቻችሁ ሁሉ እጅ የሚታደጋችሁ፤* ዘፀ23፥22፤ ዘዳ20፥1-4፤23፥14 ይመ::

17፥41 *ዛሬም፤* የቍ34 ማብ ይመ::

## የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ

18፥2-4 ተጓ ምብ - 2ዜና29፥1- 2፥31፥1
18፥5-7 ተጓ ምብ - 2ዜና31፥20-21
18፥9-12 ተጓ ምብ - 2ነገ17፥3-7

**18** የእስራኤል ንጉሥ የኤላ ልጅ ሆሴዕ
በነገሠ በሦስተኛው ዓመት የይሁዳ
ንጉሥ የአካዝ ልጅ ሕዝቅያስ ነገሠ:: 2በነገ
ሠም ጊዜ ዕድሜው ሃያ አምስት ዓመት
ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ሃያ ዘጠኝ
ዓመት ገዛ:: እናቱ የዘካርያስ ልጅ ስትሆን
ስሟ አብያ ይባል ነበር:: 3አባቱ ዳዊት እን
ዳደረገው ሁሉ፣ እርሱም *በእግዚአብሔር*
*ፊት* መልካም ነገር አደረገ:: 4በየኰረብ
ታው ላይ ያሉትን ማምለኪያዎች አስወገደ፤
አዕማደ ጣዖታትን ሰባበረ፤ የአሼራን ምስል
ዐምዶች ቈራረጠ፤ ሙሴ የሠራውን የናስ
እባብ፣ እስራኤላውያን እስከዚያች ጊዜ
ድረስ ዕጣን ያጤሱለት ስለነበር ሰባበረው፤
ይህም ነሑሽታን[ሀ] ይባል ነበር::
5ሕዝቅያስም በእስራኤል አምላክ *በእግዚ*
*አብሔር* ታመነ፤ ከእርሱ በፊትም ሆነ
ከእርሱ በኋላ ከይሁዳ ነገሥታት ሁሉ፣
እንደ እርሱ ያለ አልነበረም:: 6*ከእግዚ*
*አብሔር* ጋር ተጣበቀ፤ እርሱን ከመከተል
ወደ ኋላ አላለም፤ *እግዚአብሔር* ለሙሴ
የሰጠውንም ትእዛዞች ጠበቀ:: 7*እግዚአብሔር*
ከእርሱ ጋር ስለ ነበር የሚያደርገው ሁሉ
ተከናወነለት:: በአሦር ንጉሥ ላይ ዐመፀ፤
ግብር መገበሩንም ተወ:: 8እስከ ጋዛና እስከ
ግዛቷ ዳርቻ በመዝለቅ ፍልስጤማውያንን
ከመጠበቂያ ማማ እስከ ተመሸገችው ከተማ
ድረስ ድል አደረጋቸው::
9ሕዝቅያስ በነገሠ በአራተኛው ዓመት፣
የእስራኤልም ንጉሥ የኤላ ልጅ ሆሴዕ በነገሠ
በሰባተኛው ዓመት፣ የአሦር ንጉሥ ስልምና
ሶር ወደ ሰማርያ ገሥግሦ ከተማዪቱን ከበ
ባት፤ 10በሦስተኛውም ዓመት መጨረሻ ያዛት::
ሰማርያ የተያዘችውም ሕዝቅያስ በነገሠ በስ
ድስተኛው ዓመት፣ ሆሴዕ በእስራኤል ላይ
በነገሠ በዘጠነኛው ዓመት ነበር:: 11የአሦር
ንጉሥ እስራኤልን ማርኮ ወደ አሦር በማ
ፍለስ በአላሔ፣ በጎዛን ውስጥ በአቦር ወንዝ
አጠገብና በሜዶን ከተሞች አስፈራቸው::
12ይህ የደረሰባቸውም *የእግዚአብሔር* ባሪያ
ሙሴ ያዘዘውን የአምላካቸውን *የእግዚአ*
*ብሔርን* ቃል ሁሉ ከመስማት ይልቅ ኪዳ
ኑን ስላፈረሱ ነበር፤ ትእዛዞቹን አላደመጡም፤
ደግሞም አልፈጸሙም::
13ሕዝቅያስ በነገሠ በዐሥራ አራተኛው
ዓመት፣ የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም የተመሸ
ጉትን የይሁዳን ከተሞች ሁሉ አደጋ ጥሎ

18፥1 ኢሳ1፥1፤ ሆሴ1፥1፤ሚክ1፥1
18፥2 ቍ13፤ኢሳ 38፥5
18፥3 1ነገ14፥8፤ ኢሳ38፥5
18፥4 ዘፀ23፥24፤ ዘኍ21፥9፤2ነገ12፥3፤ 21፥3፤2ዜና31፥1፤ኢሳ 36፥7
18፥5 ቍ19፤ 1ሳሙ7፥3፤2ነገ 19፥10፤መዝ21፥7፤ 125፥1፤ምሳ3፥26
18፥6 ዘዳ6፥18፤ 10፥20
18፥7 ዘፍ39፥3፤ 2ነገ24፥1፤ዕዝ 4፥19፤ኢዮ 22፥25፤ ኢሳ36፥5
18፥8 2ነገ17፥9
18፥9 ኢሳ1፥1፤ 36፥1
18፥11 ኢሳ 37፥12፤ሕዝ 16፥39፤23፥9
18፥12 1ነገ9፥6፤ 2ነገ17፥15፤21፥8፤ ዳን9፥6:10
18፥13 ቍ2፤ኢሳ 1፥7፤ሚክ1፥9

[ሀ]2 በዕብራይስጡ *አብያ* ማለት *አብያ* ማለት ነው:: [ሀ]4 *ነሑሽታን* የሚለው ቃል ድምፅ *ነሓሽ* እባብ እንዲሁም ርኵስ ነገር ከሚለው የቃል ድምፅ ጋር አንድ ዐይነት ነው::

18፥1 *ሆሴዕ በነገሠ በሦተኛው ዓመት ... ሕዝቅያስ ነገሠ፤* በ729 ዓ.ቅ.ክ ነው (17፥1 ይመ):: ሕዝቅያስ ከአባቱ ከአካዝ ጋር ከ729-715 ዓ.ቅ.ክ ገዝቶ ነበር (የ16፥2 ማብ ይመ)::

18፥2 *በነገሠም ጊዜ፤* ብቻውን ይሁዳን በገዛበት ዘመን ማለት ነው:: *ሃያ ዘጠኝ ዓመት፤* ከ715-686 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው:: በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት ስለተፈጸሙት ነገሮችና ቤተ መቅ ደስም ስለተደረገው ተሐድሶ በይበልጥ ለመገንዘብ 2ዜና 29፥32 እና ኢሳ36-39 ይመ:: ከሥራዎቹ የመጀመሪያው፣ አባቱ አካዝ ዘግቶት የነበረውን ቤተ መቅደስ መክፈት ነበር (የ16፥19 ማብ እና 2ዜና 29፥3 ይመ)::

18፥3 *አባቱ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ እርሱም ... መልካም ነገር አደረገ፤* በመልካም ተግባራቸው ከዳዊት ጋር ከሚነጻጸሩት ጥቂት ነገሥታት መካከል ሕዝቅያስ አንዱ ነበር፤ ሌሎቹም ነገሥታት አሳ (1ነገ 15፥11)፣ ኢዮሣፍጥ (1ነገ22፥43) እና ኢዮስያስ (2ነገ22፥2) ናቸው:: ይሁን እንጂ አሳና ኢዮሣፍጥ በከፍታ ቦታ ላይ ያሉትን የማምለኪያ ኰረብቶች አላስወገዱም ነበር (1ነገ15፥14፤ 22፥43 ይመ)::

18፥4 *በየኰረብታው ላይ ያሉትን ማምለኪያዎች አስወገደ፤* በየኰረብታው ላይ ያሉትን የማምለኪያ ስፍራዎች ለማስወገድ፣ ሕዝቅ ያስ የመጀመሪያው ንጉሥ አልነበረም (የ1ነገ3፥2፤ 15፥14 ማብ ይመ)፤ እግዚአብሔር እንዲመለከበት በተቀደሱት ስፍራዎች ላይ የነበሩትን ማምለኪያዎች በማጥፋት ረገድ ግን የመጀመሪያው ነበር (12፥3፤ 14፥4፤ 15፥5:35፤ 17፥9፤ 1ነገ 22፥43 ይመ):: ይህ ንንም የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም እንኳ አውቆታል (ቍ22 ይመ):: *አዕማደ ጣዖታትን፤* 3፥2፤10፥26-27፤ 17፥10ይመ፤ የ1ነገ14፥23 ማብ ይመ:: *የአሼራን ምስል ዐምዶች፤* 13፥6፤ 17፥10:16፤ 1ነገ 16፥23 ይመ:: እንዲሁም የ1ነገ14፥15 ማብ ይመ:: *እስራኤላው ያን እስከዚያች ጊዜ ድረስ ዕጣን ያጤሱለት ነበር፤* እስራኤላው ያን እንደ ሕዝብና መንግሥት በምድር ላይ ከታወቁበት ጊዜ ጀምሮ የናሱ እባብ የሚመለክ ጣዖት ሆኖ መቈየቱ የማይመስል ነው፤ የናሱ እባብ መቼ ጣዖት ሆኖ መመለክ እንደ ጀመረ አይ ታወቅም፤ ምናልባት በሕዝቅያስ አባት በአካዝ ዘመን እንደ ጣዖት መመለክ ጀምሮ ይሆናል (ም16 ይመ):: በጥንት ቅርብ ምሥራቅ አገሮች እባብን በተለያየ መንገድ ማምለክ የተለመደ ነበር::

18፥5 *ከእርሱ በፊትም ሆነ ከእርሱ በኋላ... እንደ እርሱ ያለ አልነበረም፤* ይህ ዐረፍተ ነገር በ23፥25 ላይ ስለ ኢዮስያስ ከተነገረው ጋር ሲነጻጸር የአጽንዖት ልዩነት ይታይበታል:: ይሁን እንጂ ሕዝቅያስን ልዩ የሚያደርገው በእግዚአብሔር መታመኑ ሲሆን፣ ኢዮስያስ ደግሞ የሙሴን ሕግ በፍጹም ልቡ መጠበቁ ነበር::

18፥7 *በአሦር ንጉሥ ላይ ዐመፀ፤* በአካዝ ዘመን ይሁዳ በአሦር ሥር ነበር (16፥7 ይመ)፤ ከአሦር ሥር መሆን ደግሞ አማ ልክታቸው እንዲመለኩ ያስገድድ ነበር:: ስለዚህም ሕዝቅያስ የአባቱን የአካዝን ሥርዐት በመለወጥ ከአሦር አገዛዝ ነጻ ሊሆን የሚችልበትን መንገድ ፈለገ:: በ705 ዓ.ቅ.ክ በኋላ ብዙም ሳይ ቈይ ሰናክሬም በዳግማዊ ሳርጎን ቦታ ሲተካ፣ ሕዝቅያስ ለአሦራ ውያን መክፈል የሚገባውን ዓመታዊ ግብር ላለመክፈል ወሰነ::

18፥8 *ፍልስጥኤማውያንን ... ድል አደረጋቸው፤* በአካዝ ዘመን ፍልስጥኤማውያን በኰረብታማ አገርና በኔጌቭ የነበሩትን አይሁድ ከያዙበት ተቃራኒ ሁኔታ (2ዜና28፥18 ይመ)፤ ሕዝ ቅያስ ፍልስጥኤማውያንን እንደገና ለመቈጣጠር ችሉአል:: ምና ልባትም ሕዝቅያስ በአሦራውያን ሥርዐት ላይ ላደረገው ዐመፅ ፍልስጥኤማውያንን ሳያስገድድ አልቀረም:: ሰናክሬም በተጻፈው ታሪኩ ውስጥ፣ የአስቀሎና ከተማ ንጉሥ የሆነውን ንጉሥ ፖዲን ሕዝ ቅያስ በኢየሩሳሌም አስሮት ስለ ነበር እንዲፈታለት አስገድዶት እንደ ነበር ጠቅሶአል:: ይህም በ701 ዓ.ቅ.ክ ሰናክሬም ካደረገው የጦርነት ዘመቻ ጋር ተያይዞ ነበር::

18፥9 *ሕዝቅያስ በነገሠ በአራተኛው ዓመት፤* በ725 ዓ.ቅ.ክ ሲሆን፣ ይህም ሕዝቅያስ ከአካዝ ጋር አብሮ የገዛበት አራተኛ ዓመት ነው (የቍ1፡17፥1 ማብ ይመ)::

18፥10 *በሦስተኛውም ዓመት፤* የ17፥5 ማብ ይመ:: *በሆሴዕ ... በዘጠነኛው ዓመት፤* የ17፥6 ማብ ይመ::

18፥11 *የአሦር ንጉሥ እስራኤልን ... ወደ አሦር በማፍለስ፤* የ17፥6 ማብ ይመ::

18፥12 *ኪዳኑን ስላፈረሱ፤* 17፥7-23 ይመ::

18፥13 *በዐሥራ አራተኛው ዓመት፤* ሕዝቅያስ ብቻውን የገዛበት ዘመን ነው፤ ይህም በ701 ዓ.ቅ.ክ ነው (የቍ 2 ማብ ይመ):: *ሰናክሬም አደጋ ጥሎ፤* ከቍ13-16 የተጠቀሰው በ701 ዓ.ቅ.ክ ሰናክሬም በፊንቄ፣ በይሁዳና በግብፅ ላይ ካደረገው ከራሱ የዘመቻ ታሪክ ጋር በጣም ይመሳሰላል:: *ያዛቸው፤* ሰናክሬም ስለ እርሱ በተጻፈው ታሪኩ፣ የተመሸጉ አርባ ስድስት የሕዝቅያስን የተመሸጉ ከተሞችንና አያሌ ያልተመሸጉ ከተሞችን ከሕዝቅያስ እንደ ወሰደ፣ ሁለት መቶ ሺህ አንድ መቶ አምሳ ሰዎችን በመ ማረክ እንደ አጋዘ ተናግሮአል:: ከዚህም በላይ ሕዝቅያስን፣ “በጎጆዋ ውስጥ እንዳለች ወፍ፣ በራሱ ቤተ መንግሥት፣ በኢየሩ ሳሌም እስረኛዬ አደረግሁት” ብሏል፤ ይሁን እንጂ ኢየሩሳሌምን

ያዛቸው:: 14ስለዚህ የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅ
ያስ፣ "በደለኛው እኔ ነኝ፤ ተመለስልኝ፤
እኔም የምትጠይቀኝን ሁሉ እከፍላለሁ፤"
ሲል በለኪሶ ወደ ሰፈረው ወደ አሦር ንጉሥ
ይህን መልእክት ላከ:: የአሦርም ንጉሥ፣
የይሁዳን ንጉሥ ሕዝቅያስን ሦስት መቶ
መክሊት[*] ብርና ሠላሳ መክሊት[†] ወርቅ
እንዲያገባለት ጠየቀው::
15ስለዚህ ሕዝቅያስ *በእግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስና በቤተ መንግሥቱ ግምጃ ቤቶች
የሚገኘውን ብር ሁሉ ሰጠው::
16በዚህ ጊዜም የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ፣
*በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ መዝጊያዎ
ችና መቃኖች ላይ የለበጠውን ወርቅ ነቃ
ቅሎ ለአሦር ንጉሥ ሰጠው::

### ሰናክሬም ኢየሩሳሌምን አስፈራራ

18፥13፤17-37 ተጓ ምብ - ኢሳ36፥1-22
18፥17- 35 ተጓ ምብ - 2ዜና32፥9-19

17የአሦርም ንጉሥ ከለኪሶ የጦሩን ጠቅ
ላይ አዛዥ፣ ዋና አዛዡንና የጦር መሪውን
ከታላቅ ሰራዊት ጋር የይሁዳ ንጉሥ ወዳለ
በት ወደ ኢየሩሳሌም ላከ፤ እነርሱም ወደ
ኢየሩሳሌም መጥተው፣ ወደ ልብስ አጣቢው
ዕርሻ በሚወስደው መንገድ ላይ የሚገኘው
የላይኛው ኩሬ ውሃ በመስኖ የሚወርድበ
ትን ስፍራ ያዙ:: 18ወደ ንጉሡም ላኩበት፤
ከዚያም የቤተ መንግሥቱ አዛዥ የሆነው
የኬልቅያስ ልጅ ኤልያቄም፣ ጸሓፊው ሳም
ናስ እንዲሁም ታሪክ ጸሐፊው የአሳፍ ልጅ
ዮአስ ወደ እነርሱ ሄደ:: 19የጦር መሪውም
እንዲህ አላቸው፤ "ሕዝቅያስን እንዲህ
በሉት፤
"'ታላቁ የአሦር ንጉሥ የሚለው ይህ
ነው፤ "ለመሆኑ እንዲህ የልብ ልብ እንድ
ታገኝ ያደረገህ ምንድነው? 20የጦር ስልትና
ኀይል አለኝ ትላለህ፤ ነገር ግን ወሬ ብቻ
ነው:: በእኔ ላይ እንዲህ ያመፅኸውስ በማን
ተመክተህ ነው? 21እነሆ፤ እንዲህ የምትመ
ካበት ግብፅ፣ የሚደገፍባትን ሰው እጅ ወግታ
የምታቈስል የተቀጠቀጠች ሸንበቆ ናት::
የግብፅ ንጉሥ ፈርዖንም ለሚመኩበት ሁሉ
እንደዚሁ ነው:: 22ደግሞም፣ "የምንመካው
በአምላካችን *በእግዚአብሔር* ነው" የምትለኝ
ከሆነም፣ ሕዝቅያስ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን፣
"ማምለክ ያለባችሁ ኢየሩሳሌም ባለው በዚህ
መሠዊያ ፊት ነው" ብሎ የኰረብታ ላይ
መመለኪያዎቹንና መሠዊያዎቹን ያስፈረሰ
እርሱ አይደለምን? 23"'ከሆነልህ ከጌታዬ
ከአሦር ንጉሥ ጋር ውርርድ ግጠም፤ የሚ
ጋልቧቸው ሰዎች ማግኘት የምትችል ከሆነ፣
ሁለት ሺህ ፈረሶች እሰጥሃለሁ:: 24የምት
መካው በግብፅ ሠረገሎችና[°] ፈረሶች ሆኖ
ሳለ ከጌታዬ የበታች የጦር ሹማምንት እንኳ
አንዱን እንዴት መመለስ ትችላለህ? 25ከዚ
ህም በቀር አደጋ ጥዬ ይህችን ስፍራ ለማ
ጥፋት የመጣሁት፣ ያለ *እግዚአብሔር* ፈቃድ
ይመስልሃል? በዚች አገር ላይ ዘምቼ
እንዳጠፋት የነገረኝ ራሱ *እግዚአብሔር*
ነው::' "
26ከዚያም የኬልቅያስ ልጅ ኤልያቄም
ሳምናስና ዮአስ የጦር መሪውን፣ "እኛ አገ
ልጋዮችህ ስለምንሰማ፣ እባክህን በሶርያ ቋንቋ
ተናገር፤ በቅጥሩ ላይ ያሉት ሰዎች በሚሰ
ሙት በዕብራይስጥ አትናገረን" አሉት::

18፥14 2ነገ19፥8፤ ኢሳ24፥5፤33፥8
18፥15 1ነገ15፥18፤ኢሳ39፥2
18፥16 2ዜና29፥3
18፥17 2ነገ20፥20፤ 2ዜና32፥4፡30፤ነህ2፥14፤ኢሳ20፥1፤22፥9
18፥18 ቍ26:37፤ 2ነገ19፥2፤ኢሳ22፥15፤22፥20፤ 6፥36፥3:11:22፤ 37፥2
18፥19 ቍ5፤ኢዮ4፥6
18፥21 2ነገ24፥7፤ ኢሳ20፥5:6፤ 30፥5:7፤31፥1፤ ኤር25፥19፤37፥7፤ 46፥2፤ሕዝ29፥6
18፥24 ኢሳ10፥8
18፥25 2ነገ19፥6: 22፤24፥3፤2ዜና 35፥21
18፥26 ዕዝ4፥7

[*]14 10ሜትሪክ ቶን ያህል ነው:: [†]14 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው::
[°]24 ወይም፣ *ሰረገለኞች*

መያዙን አልተናገረም::

18፥14 *ሦስት መቶ መክሊት ብርና ሠላሳ መክሊት ወርቅ፤* ሕዝቅያስ ለሰናክሬም መገበር የሚገባውን በተመለከተ፣ በአሦራውያን ታሪክና በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው ሠላሳ መክሊት ወርቅ ተመሳሳይ ነው፤ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰውን ሦስት መቶ መክሊት ብርን፣ ሰናክሬም ስምንት መቶ መክሊት ብር በማለት በአሦራውያን መጽሐፍ ጠቅሶአል:: ለዚህ ዓይነት የብር መጠን መለያየት ምክንያት ሊሆን የሚች ለው፣ ወይ የእስራኤልና የአሦር የብር መክሊት ሚዛን ተመሳሳይ አለመሆን፣ አለበለዚያ አሦራውያን አጋንነው ከመናገራቸው የተነሣ ሊሆን ይችላል:: በዚህ ላይ የተጠቀሰውን የብርና የወርቅ ሚዛን ይበልጥ ለመረዳት የ5፥5 ማብ ይመ::

18፥15 *በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና በቤተ መንግሥቱ ግምጃ ቤቶች የሚገኘውን ብር፤* 12፥10:18፤14፥14፤16፥8፤1ነገ 7፥51፤41፥26፤15፥18 ይመ::

18፥17-19፥37፤ ኢሳ 36-37 ይመ፤ ከ2ዜና 32 ጋር ያነጻ ጽሩ::

18፥17 *ለኪሶ፤* የኢሳ 36፥2 ማብ ይመ:: *በመስኖ ... ስፍራ፤* የኢሳ 7፥3 ማብ ይመ:: አካዝ በእርሱ ላይ ከአሦርና ከሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ከሚመጣበት አስጊ ሁኔታ፣ ከአሦር ጋር ከመተባበር ይልቅ በእግዚአብሔር እንዲታመን ኢሳይያስ ባስጠነ ቀቀበት በዚያ ስፍራ ላይ የአሦር አለቆች ይሁዳ እጁን እንዲሰጥ መጠየቃቸው ምፀት ነው (16፥5-10፤ ኢሳ 7፥1-17ይመ)::

18፥18 *የቤተ መንግሥቱ አዛዥ፤* የ1ነገ 4፥6 ማብ ይመ:: ጸሐፊው፤ የ2ሳሙ 8፥17 ማብ ይመ:: *ታሪክ ጸሐፊው፤* የ2ሳሙ 8፥16 ማብ ይመ::

18፥19 *ታላቁ ...! ንጉሥ፤* ስለ አሦራውያን ነገሥታት ተዘውትሮ የሚጠቀስ ማዕረግ ሲሆን፣ ለእግዚአብሔርም ይህ ማዕ ረግ አልፎ አልፎ ይሰጥ ነበር (መዝ 47፥2፤ 48፥2፤ 95፥3፤ ሚል 1፥14፤ ማቴ 5፥35 ይመ):: *የሚለው ይህ ነው፤* ይህ አባባል፣ ሆን ተብሎ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎችን ልብ አቅልጦ፣ ተቃውሞአቸውን ለማ ክሸፍ የተደረገ ማስፈራራትና የሥነ ልቡና ጦርነት ነው (ቍ26-27 ይመ)::

18፥21 *የምትመካበት ግብፅ፤* 19፥9፤ ኢሳ 30፥1-5፤31፥1-3 ይመ::

18፥22 *ሕዝቅያስ ... የኰረብታ ላይ መመለኪያዎቹንና መሠዊያዎቹን ያስፈረሰበት እርሱ አይደለምን?* አሦራውያን በሕዝቅያ ስና በሕዝቡ መካከል መለያየት ለመፍጠር ብልሃት በሞላበት መንገድ ሙከራ አድርገዋል:: ሕዝቅያስ ተሐድሶ ማድረጉንና የኰረብታ ማምለኪያ ቦታዎችን ማጥፋቱን በሚቃወሙት መካ ከል የሚፈጠረውን ማንኛውንም ቍጣ ሊያተርፉበት ጥረት አድ ርገዋል (የቍ 4 ማብ ይመ)::

18፥23 *የሚጋልቡአቸው ሰዎች ማግኘት የምትችል ከሆነ፤* አሦራውያን በዚህ ሥላቃዊ ትንኰሳ አይሁድ ችሮታ ቢደረ ግላቸው እንኳ በወታደራዊ አመራር ደካማ ከመሆናቸው የተነሣ ዕድሉን ለመጠቀም አለመቻላቸውን በትክክል ገልጸዋል:: ከአሦር ሰራዊት አኳያ በንጽጽር ሲታይ የይሁዳ ሰራዊት በአብዛኛው እግረኛ ወታደር ነበር:: የተከበበችው ከተማ ጥቂት የጦር ሠረገሎች ይኖራት ይሆናል፤ ሆኖም ግን ለዚህ ጦርነት እስራኤላውያን ፈረሰኛ ጦር አዘጋጅተው እንደ ነበር የሚታወቅ ነገር የለም::

18፥25 *የነገረኝ ራሱ እግዚአብሔር ነው፤* የአሦር ሰላዮች ኢሳይያስና ሚክያስ የተናገሩትን ትንቢት ለሰናክሬም ሳይነግሩት አይቀርም::

18፥26 *በሶርያ ቋንቋ፤* በጊዜው በቅርብ ምሥራቅ አገሮች የሚነገር ዓለም አቀፍ ቋንቋ ሲሆን፣ የንግድና የዲፕሎማሲ ሰዎች የሚጠቀሙበት ቋንቋ ነበር:: ሌላው በዚህ ስፍራ የተጠቀሰውና የሚያስደንቀው፣ የአሦር ባለሥልጣኖች የተራውን የይሁዳን ሕዝብ ቋንቋ ዕብራይስጥን መናገር መቻላቸው (2ዜና 32፥18ይመ)::

27የጦር አዛዡም፣ "ለመሆኑ ጌታዬ ይህን
እንድናገር የላከኝ፣ ለጌታችሁና ለእናንተ
ብቻ ነውን? እነርሱም እንደ እናንተው ገና
ኵሳቸውን ይበሉ ዘንድ፣ ሽንታቸውንም
ይጠጡ ዘንድ በቅጥሩ ላይ ለተቀመጡት
ጭምር አይደለምን?
28ከዚያም የጦር አዛዡ ቆሞ ድምፁን
ከፍ በማድረግ በዕብራውያን ቋንቋ እንዲህ
ሲል ተናገረ፤ "እንግዲህ የታላቁን የአሦርን
ንጉሥ ቃል ስሙ! 29ንጉሡ የሚለውም ይህ
ነው፤ 'ከእጄ ሊያድናችሁ አይችልምና ሕዝ
ቅያስ እንዳያታልላችሁ፤ 30ደግሞም ሕዝቅ
ያስ፣ "እግዚአብሔር ያለ ጥርጥር ያድነ
ናል፤ ይህችም ከተማ ለአሦር ንጉሥ አልፋ
አትሰጥም' በማለት በእግዚአብሔር እንድት
ታመኑ የሚነግራችሁን አትቀበሉ::"
31"ሕዝቅያስንም አትስሙት፤ የአሦር ንጉሥ
የሚለው ይህ ነው፤ 'ከእኔ ጋር ሰላም
መሥርቱ፤ እጃችሁን ስጡ፤ ከዚያም
ከእናንተ እያንዳንዱ ከገዛ ወይኑና ከገዛ
በለሱ ይበላል፤ ከገዛ ጕድጓዱም ውሃ ይጠጣል፤
32ይህም የሚሆነው የእናንተኑ ወደምትመስ
ለው ምድር እህልና የወይን ጠጅ፣ ዳቦና
የወይን ተክል፣ የወይራ ዛፍና ማር ወዳለበት
እስካገባችሁ ድረስ ነው፤ እናንተም ሞትን
ሳይሆን ሕይወትን ምረጡ::'
"ሕዝቅያስ፣ 'እግዚአብሔር ይታደገናል'
በማለት ስለሚያሳስታችሁ አትስሙት:: 33ለመ
ሆኑ ከአሕዛብ አማልክት ምድሩን ከአሦር
ንጉሥ እጅ የታደገ ማን አለ? 34የሐማትና
የአርፋድ አማልክት እስቲ የት አሉ? የሴ
ፌርዋይም፣ የሄናና የዒዋም አማልክት
ታዲያ የት ደረሱ? ሰማርያን ከእጄ አድነዋ
ታልን? 35ከእነዚህ አገሮች አማልክት ሁሉ
አገሩን ከእኔ ለማዳን የቻለ ማን አለ? ታዲያ
እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ከእጄ ሊታደ
ጋት እንዴት ይችላል?"
36ነገር ግን ሕዝቡ ዝም አለ፤ ምንም
መልስ አልሰጠም፤ ንጉሡ፣ "መልስ እንዳት
ሰጡ" ሲል አዝዞ ነበርና::
37ከዚያም የቤተ መንግሥቱ አዛዥ የኬ
ልቅያስ ልጅ፤ ኤልያቄም፣ ጸሐፊው ሳምናስ
እንዲሁም ታሪክ ጸሐፊው የአሳፍ ልጅ ዮአስ
ልብሳቸውን ቀደዱ፤ ወደ ሕዝቅያስም መጥ
ተው የጦር አዛዡ ያላቸውን ነገሩት::

**ኢየሩሳሌም ከጠላት እጅ እንደምትድን አስቀድሞ መነገሩ**

19፥1-13 ተጓ ምብ - ኢሳ37፥1-13

19ንጉሥ ሕዝቅያስ ይህን ሲሰማ ልብ
ሱን ቀደደ፤ ማቅ ለብሶም ወደ
እግዚአብሔር ቤተመቅደስ ገባ:: 2ከዚያም
የቤተ መንግሥቱን አዛዥ ኤልያቄምን፣
ጸሐፊውን ሳምናስንና ዋና ዋናዎቹን ካህ
ናት ማቅ ለብሰው ወደ አሞጽ ልጅ ወደ
ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲሄዱ ሁሉንም ላካቸው::
3እነርሱም እንዲህ አሉት፤ "ሕዝቅያስ የሚ
ለው ይህ ነው፤ 'እንግዲህ ይህች ዕለት የመ
ከራ፣ የዘለፋና የውርደት ቀን ናት፤ ይህችም
ቀን ልጆች ሊወለዱ ምጥ እንዳፋፋመበት፣
ነገር ግን ለመገላገል ዐቅም እንደ ታጣበት
ሰዓት ናት:: 4ሕያው እግዚአብሔርን ያንቋሽሽ
ዘንድ በጌታው በአሦር ንጉሥ የተላከውን
የጦር አዛዡን ቃል ሁሉ እግዚአብሔር
አምላክህ ሰምቶ ይሆናልና፣ ስለሰማውም
ቃል እግዚአብሔር እንዲገሥጸው በሕይወት
ስለተረፉት ወገኖቻችን እባክህ ጸልይ::"

18፥29. 2ነገ19፥10
18፥31 ዘኍ13፥23፤1ነገ4፥25፤ኤር14፥3፤ሰቆ4፥4
18፥32 ዘዳ30፥19
18፥33 2ነገ19፥12
18፥34 2ነገ17፥24፤ኢሳ10፥9፤ኤር49፥23
18፥35 መዝ2፥12
18፥37 ቍ18፤2ነገ6፥30፤ኢሳ33፥7፤36፥3፡22
19፥1 ዘፍ37፥34፤ዘኍ14፥6
19፥2 ዘፍ37፥34፤2ነገ18፥18፤ኢሳ1፥1፤ኤር19፥1
19፥3 ሆሴ13፥13
19፥4 ዘፍ45፥7፤1ሳሙ17፥26፤2ሳሙ16፥12፤ኤር37፥3

18፥27 *በቅጥሩ ላይ ለተቀመጡት፤* አሦራውያን በዚህ ጊዜ የያዙት ዘዴ ሕዝቡ እየሰማቸው ከንጉሡ ጋር በመደራደር ሕዝቡን ተስፋ አስቆርጠው በሕዝቅያስ ላይ ለማነሣሣት ነበር:: *ኵሳቸውን ይበሉ ዘንድ ሽንታቸውን ይጠጡ ዘንድ፤* የረጅም ጊዜ ከበባ የቱን ያህል እንደሚያሠቃይ የሚያሳዩ ሥዕላዊ የሆነ መግለጫ ነው::

18፥29 *ንጉሡ የሚለውም ይህ ነው፤* የቍ19-27 እንዳደረጉት የአሦር ባለሥልጣኖች ለሕዝቅያስ ሹማምንት ሳይሆን መልእክታቸውን በቀጥታ ለሕዝቡ አስተላለፉ:: *ሕዝቅያስ እንዳያታልላችሁ፤* በዚህ ቁጥር ላይና በቍ30-31 ሦስት ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ሕዝቡ በሕዝቅያስ ላይ በዐመፅ እንዲነሣሣ የታሰበ ነው::

18፥30 *ይህችም ከተማ ለአሦር ንጉሥ አልፋ አትሰጥም፤* ሕዝቅያስ ይህን የተናገረው እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ መሠረት ነው (20፥6፤ የኢሳ 38፥6 ማብ ይመ)::

18፥31 *እያንዳንዱ ከገዛ ወይኑና ከገዛ በለሱ ይበላል፤ ከገዛ ጕድጓዱም ውሃ ይጠጣል፤* የሰላምና የብልጽግና ዘመን መጥቀሱ ነው (1ነገ4፥25፤ሚክ4፥4፤ዘካ3፥10 ይመ)::

18፥32 *የእናንተኑ ወደምትመስለው ምድር ... እስካገባችሁ ድረስ፤* በመሠረቱ ለአሦር መገዛት፣ ወደ አሦር መጋዝን የሚያስ ከትል ነው፤ ይሁን እንጂ ሰናክሬም እጅግ የሚያጓጓ ነገር አድርጎ አቅርቦታል:: *ሞትን ሳይሆን ሕይወትን ምረጡ፤* ለሕዝቡ የተሰጡት አማራጮች (1) በእግዚአብሔርና በሕዝቅያስ ተማምኖ መሞት ወይም (2) በአሦራውያን ተማምኖ በሰላምና በብልጥግና በሕይወት መኖር ናቸው:: እነዚህ አማራጮች ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ በዘዳ 30፥15-20 ከሰጣቸው ምርጫ ጋር በቀጥታ የሚቃረኑ ናቸው::

18፥33-35 *ለመሆኑ ከአሕዛብ አማልክት ምድሩን ከአሦር ንጉሥ እጅ የታደገ ማን አለ? . ታዲያ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ከእጄ ሊታደጋት እንዴት ይችላል?* (ዘዳ32፥21)፤ (19፥4፡6፤ 2ዜና32፥13-19፤ ኢሳ10፥9-11 ይመ)::

18፥34 *የሐማት፤* የ14፥25፤17፥24 ማብ ይመ:: *የአርፋድ፤* ከሐማት አጠገብ ያለች ስትሆን፣ በ740 ዓ.ቅ.ክ በአሦራውያን የተያዘች ከተማ ናት (19፥13፤ኢሳ10፥9፤ኤር49፥23 ይመ):: *ሴፈርዋ ይመ፤* የ17፥24 ማብ ይመ:: *የሄና፤* ከተጠቀሱት ከተሞች አካባቢ ያለች ከተማ ልትሆን ትችላለች:: *የዒዋ፤* የ17፥24 ማብ ይመ::

18፥36 *ንጉሡ፤ "መልስ እንዳትሰጡ" ሲል አዝዞ ነበርና፤* አሦራውያን በሕቅዝያስ አመራርና ሥልጣን ላይ እንዲነሣ ያሰቡት የሕዝብ ዐመፅ አልተሳካም::

18፥37 *ልብሳቸውን ቀደዱ፤* የተሰማቸውን ታላቅ ስሜት መግለጻቸው ነው (6፥30፤1ነገ21፥27 ይመ):: ይህ ሊሆን የቻለው አሦራውያን እውነተኛውን አምላክ እግዚአብሔርን ስለ ተሳደቡ ሊሆን ይችላል (19፥4፡6፤ ማቴ 26፥65፤ ማር 14፥63-64 ይመ)::

19፥1 *ማቅ፤* የ6፥30 ማብ ይመ::

19፥2 *የቤተ መንግሥቱን አዛዥ፤* የ1ነገ 4፥6 ማብ ይመ:: *ጸሐፊውን፤* የ2ሳሙ 8፥17 ማብ ይመ:: *ዋና ዋናዎቹን ካህናት፤* ምናልባት ከቆዩ የካህናት ወገኖች የቆዩ አባላትን ሊሆን ይችላል (ኤር 19፥1 ይመ)፤ ችግሩ የሚመለከተው የኢየሩሳሌምን ከተማ ብቻ ሳይሆን፣ ቤተ መቅደሱንም ጭምር ነበር:: *ነቢዩ ኢሳይያስ፤* ኢሳይያስ በዖዝያን፣ በኢዮአታምና በአካዝ ዘመን አገልጋይ የነበረ ቢሆንም (ኢሳ 1፥1)፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በነገሥት መጽሐፍ ስሙ የተጠቀሰው በዚህ ክፍል ነው::

19፥3 *ልጆች ሊወለዱ ምጥ እንዳፋፋመበት፣ ነገር ግን ለመገላገል ዐቅም እንደ ታጣበት ሰዓት ናት፤* የኢየሩሳሌም ከተማ ያለችበትን አስጨናቂ ሁኔታ የሚገልጽ ነው::

19፥4 *ሕያው እግዚአብሔርን፤* አምላክ ካልሆኑ አማልክት ጋር ሲነጻጸር ነው (18፥33-35 ይመ)፤ እውነተኛውና ሕያው አምላክ ስለተሰደበበት በተጨማሪ 1ሳሙ17፥26፡36፡45 ይመ:: *ጸልይ፤* የምልጃ ጸሎት በነቢያት አገልግሎት ከፍተኛ ስፍራ ነበረው (ሙሴና ሳሙኤል ስላደረጉት የምልጃ ጸሎት ዘፀ32፥31-32፡33፥12-17፤ዘኍ14፥13-19፤ 1ሳሙ7፥8-9፤ 12፥19፡23፤ መዝ99፥6፤ ኤር15፥1 ይመ):: *በሕይወት ስለ ተረፉት፤* ሰናክሬም ብዙ ከተሞችንና ሕዝቦችን ማርኮ ከያዘ

5የንጉሥ ሕዝቅያስ ሹማምንት ወደ ኢሳ
ይያስ በመጡ ጊዜ፣ 6ኢሳይያስ እንዲህ
አላቸው፤ "ለጌታችሁ እንዲህ ብላችሁ ንገሩት፤
'እንግዲህ *እግዚአብሔር* የሚለው ይህ ነው፤
"የአሦር ንጉሥ አገልጋዮች በእኔ ላይ የወ
ረወሯቸውን የስድብ ቃላት በመስማትህ
አትፍራ:: 7እነሆ፣ አንድ ዓይነት መንፈስ
አሳድርበታለሁ፤ የሆነ ወሬም ሲሰማ ወደ
አገሩ ይመለሳል፤ እዚያም በሰይፍ እንዲ
ወድቅ አደርገዋለሁ::' "
8የጦር አዛዡም የአሦር ንጉሥ ለኪሶን
ትቶ መሄዱን ሲሰማ ተመለሰ፤ ንጉሡንም
ልብናን ሲወጋ አገኘው::
9በዚህም ጊዜ የግብፅ ንጉሥ ኢትዮጵያ
ዊው ቲርሐቅ፣ ሊወጋው በመገሥገሥ ላይ
መሆኑን ሰናክሬም ሰማ፤ ስለዚህ ወደ ሕዝ
ቅያስ እንደ ገና እንዲህ ሲል መልእክተኞች
ላከ፤ 10"ሂዱና ለይሁዳ ንጉሥ ለሕዝቅያስ
እንዲህ በሉት፤ 'የምትመካበት አምላክ፣
"ኢየሩሳሌም በአሦር ንጉሥ እጅ አትወድ
ቅም" በማለት እንዳያታልልህ:: 11መቼም
የአሦር ነገሥታት በአገሮች ሁሉ ላይ ምን
እንዳደረጉ ሰምተሃል፤ ፈጽሞ አጥፍተዋቸ
ዋል፤ ታዲያ አንተስ ከዚህ የምታመልጥ
ይመስልሃልን? 12የቀድሞ አባቶቼ ያጠፏቸ
ውን ሕዝቦች ማለትም ጎዛንን፣ ካራንን፣ ራፌ
ስን እንዲሁም በተላሳር የነበሩትን የዔድ
ንን ሰዎች አማልክታቸው አድነዋቸዋልን?
13ለመሆኑ የሐማትና የአርፋድ ነገሥታት
የት አሉ? የሴፈርዋይም ከተማ ንጉሥስ
የት አለ? ደግሞስ የሄና ወይም የዒዋ ነገ
ሥታት የት አሉ?

### የሕዝቅያስ ጸሎት

19፥14-19 ተጓ ምብ - ኢሳ37፥14-20

14ሕዝቅያስም ደብዳቤውን ከመልእክተ
ኞቹ ተቀብሎ አነበበው፤ ከዚያም ወደ *እግ
ዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ወጥቶ ደብዳቤ
ውን *በእግዚአብሔር* ፊት ዘረጋው:: 15ከዚ
ያም ሕዝቅያስ እንዲህ ሲል ወደ *እግዚ
አብሔር* ጸለየ፤ "በኪሩቤል ላይ በዙፋንህ
የተቀመጥህ የእስራኤል አምላክ *እግዚ
አብሔር* ሆይ፤ በምድር ነገሥታት ሁሉ
ላይ አምላክ አንተ ብቻ ነህ፤ ሰማይንና
ምድርን የፈጠርህም አንተ ነህ:: 16*እግዚ
አብሔር* ሆይ፤ አሁንም ጆሮህን አዘንብልና
ስማ፤ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ዐይንህንም ክፈ
ትና እይ፤ ሰናክሬም ሕያው *እግዚአብሔርን*
ይሰድብ ዘንድ የላከውንም ቃል አድምጥ::
17"*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የአሦር ነገሥታት
እነዚህን አሕዛብንና ምድራቸውን በእርግጥ
አጥፍተዋል:: 18አማልክታቸው በእሳት ውስጥ
ጥለው አቃጥለዋቸዋል፤ በሰው እጅ የተሠሩ
እንጨትና ደንጊያ ብቻ እንጂ አማልክት
አልነበሩምና:: 19አሁንም *እግዚአብሔር* አምላ
ካችን ሆይ፤ የምድር መንግሥታት ሁሉ
*እግዚአብሔር* አንተ ብቻ አምላክ መሆንህን
እንዲያውቁ፣ ከእጁ አድነን::"

### ኢሳይያስ ስለ ሰናክሬም መውደቅ ትንቢት ተናገረ

19፥20-37 ተጓ ምብ - ኢሳ37፥21-38
19፥35-37 ተጓ ምብ - 2ዜና32፥20-21

20ከዚያም የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ ወደ
ሕዝቅያስ እንዲህ ሲል መልእክት ላከ፤
"የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የሚለው
ይህ ነው፤ 'በአሦር ንጉሥ በሰናክሬም ላይ
ወደ እኔ ያቀረብኸውን ልመና ሰምቻለሁ::
21እንግዲህ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ
የተናገረው ቃል ይህ ነው፤

" 'ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ፣
 ትንቅሃለች፤ ታቃልልሃለችም፤
የኢየሩሳሌም ልጅ፣
 አንተ በላይዋ ስትበር ራሷን
  ትነቀንቅብሃለች::
22ለመሆኑ የሰደብኸውና ያቃለልኸው ማንን
  ነው?
 ድምፅህንስ ከፍ ያደረግኸው?
ዐይንህንስ በኵራት ያነሣኸው በማን ላይ
  ነው?
 በእስራኤል ቅዱስ ላይ ነው እንዴ?

19፥6 ዘዳ3፥2፤ኢሱ 1፥9፤2ነገ18፥25
19፥7 ቍ37፤ ዘፀ14፥24፤2ዜና32፥21፤ኢሳ10፥12፤ ኤር51፥46
19፥8 ዘኍ33፥20፤ 2ነገ8፥22፤18፥14
19፥10 2ነገ18፥5፡29
19፥12 ዘፍ11፥31፤ 2ነገ17፥6፤18፥33፤ 2ዜና32፥17
19፥13 ኢሳ10፥9-11፤ኤር49፥23
19፥14 2ነገ5፥7
19፥15 ዘፍ1፥1፤ 3፥24፤ዘፀ25፥22፤ ኢሱ2፥11
19፥16 ዘዐ3፥16፤ 1ነገ8፥29፤መዝ31፥2፤ 71፥2፤88፥2፤102፥2
19፥18 ዘዳ4፥28፤ መዝ115፥4፤ኢሳ 44፥9፤11፤ኤር10፥3-10፤ ሐሥ17፥29
19፥19 ኢሱ 4፥24፤1ሳሙ12፥ 10፤17፥46፤1ነገ8፥43፤ 1ዜና16፥8፤ኢዮ6፥23፤ መዝ3፥7፤71፥4
19፥20 1ነገ9፥3
19፥21 ኢዮ16፥4፤ መዝ44፥14፤53፥5፤ 64፥8፤109፡25፤ምሳ1 ፥26፤3፥34፤ኢሳ10፥ 5፤33፥1፤47፥1፤ኤር14፥ 17፡18፥13፡16፤31፥4፤ 46፥11፤ሰቆ2፥13፤አሞ 5፥2
19፥22 ዘሌ19፥2፤ 1ሳሙ2፥2፤2ነገ18፥2 5፤ኢዮ6፥10፤መዝ 16፥10፤ 22፥3፤71፥22፤78፥41፤ 89፥18፤ኢሳ1፥4፤ 6፥3፤57፥15፤ሆሴ 11፥9

በኋላ በይሁዳ የተረፉትን ለማለት ነው (የ18፥13 ማብ ይመ፤ ከኢሳ 10፥28-32 ጋር ያነጻጽሩ):: የሥነ ቅርስ ጥናት እንደሚያስረዳው፣ አሦራውያን የሰሜኑን የእስራኤል መንግሥት አስጨንቀው ቢያዙ ጊዜ፣ አያሌ እስራኤላውያን ወደ ይሁዳ ፈልሰው በዚያ ሰፈሩ፤ ስለዚህ የይሁዳ መንግሥት የቅሬታዎች መሰብሰቢያ ሆነ::

19፥7 *መንፈስ፤* የፍርሃትና የሥጋት መንፈስ ማለት ነው:: *ወሬም፤* አንዳንድ ሰዎች ይህ ዜና ሰናክሬምን ለመቋቋም ከግብፅ ንጉሥ ከቲርሐቅ (ቍ9) የመጣ ነው ይላሉ:: ሌሎች ደግሞ ከራሱ ከሰናክሬም አገር የመጣ፣ የሚያውክ ዜና ነው ይላሉ:: *በሰይፍ እንዲወድቅ፤* ቍ37 ይመ፤ በዚህ ክፍል የሰናክሬም መገደል ሕያው እግዚአብሔርን ከመሰደቡ ጋር በመያያዝ ተጠቅሶአል::

19፥8 *ለኪሶ፤* 18፥17 ይመ (እንዲሁም የኢሳ 36፥2 ማብ ይመ):: *ልብና፤* የ8፥22 ማብ ይመ::

19፥9 *ቲርሐቅ፤* የኢሳ 37፥9 ማብ ይመ::

19፥12 *ጎዛን፤* የ17፥6 ማብ ይመ:: *ካራን፤* የዘፍ11፥31 ማብ ይመ፤ ካራን በአሦራውያን መቼ እንደ ተያዘ አይታወቅም:: *ራፊስን፤* ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተ ደቡብ ከሐማት በስተ ሰሜን ምሥራቅ የሚገኝ ነው:: *ዔድን፤* በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ ከካራን በስተደቡብ የሚገኝ አውራጃ ነው፤ ሕዝ27፥23፤አሞ1፥5 ይመ:: ወደ አሦር ግዛትም የተጠቃለለችው በሣልሳዊ ስልምናሶር በ855 ዓ.ቅ.ክ ነው:: *ተላሳር፤* ይህ ስፍራ የት እንደ ሆነ አይታወቅም::

19፥13 *ሐማትና ... የዒዋ፤* የ18፥34 ማብ ይመ::

19፥14 *ደብዳቤውን፤* 2ዜና32፥17 ይመ::

19፥15 *በኪሩቤል ላይ በዙፋንህ የተቀመጥህ፤* የዘፀ 25፥18፤ 1ሳሙ 4፥4 ማብ ይመ:: *አምላክ አንተ ብቻ ነህ፤* የ18፥33-35፤የዘዳ6፥4 ማብ ይመ::

19፥18 *በሰው እጅ የተሠሩ፤* ጣዖት አምልኮ ከንቱነትና ሞኝነት ስለ መሆኑ መዝ 115፥3-8፤135፥15-18፤ኢሳ 2፥20፤ 40፥19-20፡ 41፥7፤44፡9-20 ይመ::

19፥20 *ያቀረብኸውን ልመና ሰምቻለሁ፤* በዚህ ሁኔታ ኢሳይያስ ለንጉሡ ሕዝቅያስ ያስተላለፈው መልእክት ንጉሡ ያልጠበቀው ነበር (ቍ 2 ይመ)::

19፥21-28፤ የአሦራውያን እብሪት እንዲሁም በእስራኤላውያንና በአምላካቸው በእግዚአብሔር ላይ የሰነዘሩት የስድብ ቃል በከንቱ ትምክህት ላይ የተመሠረተ ነበር (ኢሳ10፡5-34 ይመ)፤ ስለዚህም እግዚአብሔር በፈዝ ከባድ ፍርድን በአሦራውያን አጉል ኩራት ላይ አወረደ (ከመዝ 2 ጋር ያነጻጽሩ)::

19፥21 *ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ፤* ኢየሩሳሌምንና ነዋሪዎቿን በሰውኛ ዘይቤ የሚገልጽ ነው::

19፥22 *በእስራኤል ቅዱስ፤* ነቢዩ ኢሳይያስ የእስራኤልን አምላክ የሚጠራበት የራሱ የሆነ አገላለጽ ነው (የኢሳ1፥4 ማብ ይመ)::

[23]በመልእክተኞችህ አማካይነት፣
በአምላክ ላይ የስድብ መዓት
አውርደሃል፤
እንዲህም ብለሃል፤
“በብዙ ሠረገሎቼ፣
የተራሮቹን ከፍታ፣
የሊባኖስንንም የመጨረሻ ጫፍ
ወጥቻለሁ፤
ረጃጅም ዝግባዎቹን፣
ምርጥ የሆኑ ጥዶቹንም ቈርጫለሁ፤
ወደ ሩቅ ዳርቻዎቹ፣
ወደ ውብ ደኖቹም ደርሻለሁ።”
[24]“በሌሎች አገሮችም የውሃ ጕድጓዶች
ቈፍሬአለሁ፤
በዚያም ውሃ ጠጥቻለሁ፤
በእግሬ ጫማዎችም፣
የግብፅን ምንጮች ሁሉ ረግጬ
አድርቄአለሁ።”

[25]“ ‘ከብዙ ጊዜ በፊት፣
ይህን እኔ እንዳደረግሁት አልሰማህም
ነበርን?
ዕቅዱን ገና ድሮ አውጥቼ፣
አሁን ግን እንዲፈጸም አደረግሁት፤
ይህም የተመሸጉትን ከተሞች፣
አንተ የድንጋይ ክምር ማድረግህ ነው።
[26]የሚኖሩባቸውም ሰዎች ኀይላቸው ተሟጦ
አልቆአል፤
ደንግጠውም የኀፍረት ማቅ ለብሰዋል፤
ሜዳ ላይ እንደ በቀለ ተክል፣
ገና እንዳልጠነከረ የቡቃያ ሥር፣
በቤት ጣራ ላይ በቅሎ፣
ገና ሳያድግ እንደ ጠወለገ ሣርም
ሆነዋል።

[27]“ ‘የት እንደምትቀመጥ፣
መቼ መጥተህ መቼ እንደምትሄድ፣
በእኔም ላይ የተቈጣኸውን ቍጣ
ዐውቃለሁ።
[28]በእኔ ላይ በመቈጣትህ፣
ንቀትህም ወደ ጆሮዬ ስለ ደረሰ፣
ስናጋዬን በአፍንጫህ አደርጋለሁ፤
ልጓሜን በአፍህ አገባለሁ፤
በመጣህበትም መንገድ
እንድትመለስ አደርጋለሁ።’

[29]“ሕዝቅያስ ሆይ፤ ምልክቱ ይህ ነው፤

“በዚህ ዓመት በገዛ እጁ የበቀለውን፣
በሚመጣው ዓመት ደግሞ የገበውን እህል
ትበላላችሁ፤
በሦስተኛው ዓመት ግን ትዘራላችሁ፤
ታጭዳላችሁ፤
ወይንም ትተክላላችሁ፤ ፍሬውንም
ትበላላችሁ።
[30]አሁንም ከዳዊት ቤት የተረፉት፣
ሥራቸውን ወደ ታች ይሰዳሉ፤ ወደ
ላይም ፍሬ ያፈራሉ።
[31]ከኢየሩሳሌም በሕይወት የተረፉት፣
ከጽዮን ተራራም ከሞት ያመለጡት
ይወጣሉና።

የእግዚአብሔር ቅናት ይህን ታደርጋለች።

[32]“እንግዲህ እግዚአብሔር ስለ አሦር
ንጉሥ የሚለው ይህ ነው፤
“ወደዚች ከተማ ፈጽሞ አይገባም፤
አንዲትም ፍላጻ አይወረውርባትም፤
ጋሻ አንግቦ ወደ እርሷ አይቀርብም፤
በዐፈርም ቍልል አይከባትም።
[33]በመጣበት መንገድ ተመልሶ ይሄዳል፤
ተመልሶ ይሄዳታል እንጂ ወደዚች ከተማ
ፈጽሞ አይገባም፤
ይላል እግዚአብሔር ።
[34]ስለ ራሴና ስለ ባሪያዬም ስለ ዳዊት ስል፣
ይህችን ከተማ አድናት ዘንድ
እጋርዳታለሁ።

[35]በዚያችም ሌሊት የእግዚአብሔር መልአክ ወጥቶ ከአሦራውያን ሰፈር መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ሰው ገደለ። በማግስቱም ሰዎቹ ሲነቁ ቦታው ሬሳ በሬሳ ሆኖ ተገኘ።

19፥23 መዝ20፥7፤ ኢሳ10፥18፡34፤ 14፥8፤33፥9፤ኤር21፥14፤50፥37፤ሕዝ 20፥47፤31፥3
19፥25ኢሳ 22፥11፤ 40፥21፡28፤ሚክ 1፥6
19፥26 ኢዮ8፥12፤ መዝ6፥10፤37፥2፤ 71፥24፤83፥17፤ 129፥6፤ኢሳ4፥2፤ 11፥1፤13፥7፤ 41፥23፤53፥2፤ኤር 8፥9፤23፥5፤ሕዝ 7፥17፤ሰፎ3፥16፤
19፥27 መዝ 139፥14፤
19፥28 ቍ33፤ 2ዜና33፥11፤ኢሳ 30፥28፤ሕዝ19፥9፤ 29፥4፤38፥4፤ አሞ4፥2፤
19፥29 ዘፀ7፥9፤ ዘሌ25፥5፤ዘዳ13፥2፤ መዝ107፥37፤ኢሳ 65፥21፤ አሞ9፥14፤ ሉቃ2፥12
19፥30 ዘፍ45፥7፤ ኢሳ5፥24፤11፥1፤ 27፥6፤ሕዝ17፥22፤ አሞ2፥9
19፥31 ዘፍ45፥7፤ ኢሳ9፥7፤66፥19፤ ሰፎ2፥9፤ዘካ14፥16
19፥33 ቍ28
19፥34 2ሳሙ 7፥15፤2ነገ20፥6
19፥35 ዘፍ19፥13፤ ዘፀ12፥23፤ኢዮ24፥24፤ኢሳ17፥14፤ 41፥12፤ናሆ3፥3

19፥24 *የግብፅን ምንጮች ሁሉ፣ ረግጬ አድርቄአለሁ፤* ግብፅን እንኳ አሸንፎ የማያውቅ የከንቱ ትምክህት ንግግር ነው።

19፥25 *ዕቅዱን ... አውጥቼ ... እንዲፈጸም አደረግሁት፤* የእስራኤል አምላክ የመንግሥታት ሁሉና የታሪክ ገዥ ነው። አሦራውያን በደረሱበት ሁሉ የተቀዳጁት ድል ከሰራዊታቸው ኀያልነት የተነሣ እንደ ሆነ ያስባሉ። ኢሳይያስ ግን እግዚአብሔር ራሱ እነዚህን ድሎች እንደሰጣቸው ይናገራል (ኢሳ10፥5-19 ይመ፤ ከሕዝ30፥24-26 ጋር ያነጻጽሩ)።

19፥27 *ዐውቃለሁ፤* መዝ 121፥8 ይመ።

19፥28 *ስናጋዬን በአፍንጫህ፤* በአንድ የአሦር ረጅም አራት ማእዘን የድንጋይ ሐውልት ጫፍ ላይ፣ የአሦር ንጉሥ ምናልባትም በ681-669 ዓ.ቅ.ክ ይገዛ የነበረው አስራዶን፣ በአፍንጫቸው ቀለበት ላይ ገመድ ከታሰረባቸው አራት ጠላቶቹ ጋር የሚታይበት ምስል ነበር። በዚህ ክፍል ኢሳይያስ የሚናገረውም ተመሳሳይ ሁኔታ በሰናክሬም ላይ እንደሚፈጸምበት ነው (የኢሳ 37፥29 ማብ ይመ፤ ከሕዝ 38፥4፤ ከአሞ 4፥2 ጋር ያነጻጽሩ)።

19፥29 *በዚህ ዓመት በገዛ እጁ የበቀለውን ... ትበላላችሁ፤* ምናልባት ሰናክሬም ባለፈው መፀው የተዘራውን እህል ሁሉ አጥፍቶት ወይም ዘርፎ ወስዶ ሊሆን ይችላል፤ ስለዚህ ሕዝቡ ሊያገኝ የሚችለው ካለፈው ዓመት አዝመራ ከረገፈው ፍሬ የተገኘውን እህል ብቻ ሊሆን ይችላል (ዘሌ 25፥5 ይመ)። በተጨማሪም ይህ የሚመለከተው ሰናክሬም ወደ ይሁዳ የመጣው በመከር ወራት ማለትም በመጋቢትና በሚያዝያ ነበር ማለት ነው። *በሚመጣው ዓመት ደግሞ የገበውን እህል፤* በመካከለኛው ምስራቅ እህል በመስከረምና በጥቅምት ይዘራል፤ ለሚመጣው ዓመት እህል ዘርቶ ለማድረስ በመፀው ወራት የሰንከሬም ለቆ መውጣት በእጅጉ ጊዜው ካለፈ ይሆናል። በፓሌስቲና ብዙውን ጊዜ እህል የሚዘራው በመስከረም እና በጥቅምት ነው። *በሦተኛው ዓመት ግን ትዘራላችሁ ታጭዳላችሁ፤* መዝራትም ሆነ ማጨድ በመደበኛው ወቅት የሚከናወነው በሚመጣው ዓመት ነው። “ሦስተኛው ዓመት” የሚያመለክተው ሦስተኛውን የአዝመራ ዓመት ሊሆን ሲችል፣ ይኸው በአሦራውያን የተነሣ ከንቱ ሆኖ ቀርቷል።

19፥30-31፤ *የተረፉት፤* የቍ4 ማብ ይመ፤ “የተረፉት” የሚለው ቃል ወደፊት በሚገለጠው በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ውስጥ ተካፋይ ለሚሆኑት ሰዎች እንደ መጠሪያ ስም አገልግሎት ላይ ውሏል፤ ኢሳ 11፥11፡16፤ 28፥5፤ ሚክ4፥7፤ ሮሜ 11፥5 ይመ።

19፥32 *ወደዚች ከተማ ፈጽሞ አይገባም፤* በዚህ ጊዜ በልብና (ቍ8 እንዲሁም የ8፥22 ማብ ይመ) የነበረው ሰናክሬም፣ እንደ ፎከረው ኢየሩሳሌምን ለማጥቃት አልቻለም ነበር (የ18፥13 ማብ ይመ)።

19፥34 *ስለ ባሪያዬም ስለ ዳዊት፤* የ1ነገ 11፥13 ማብ ይመ።

19፥35 *የእግዚአብሔር መልአክ፤* የዘፍ 16፥7 ማብ ይመ። መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ፤ ኢሳ 37፥36 ይመ።

36የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ከዚያ ተነሥቶ
ሄደ፤ ወደ ነነዌም ተመልሶ በዚያ ተቀመጠ።
37አንድ ቀንም ናሳራክ በተባለው አምላኩ
ቤተ ጣዖት ገብቶ በመስገድ ላይ ሳለ፣ አድ
ራሜሌክና ሳራሳር የተባሉ ልጆቹ በሰይፍ
ገደሉት፤ ከዚያም አምልጠው ወደ አራራት
ሸሹ። ልጁ አስራዶንም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

### የሕዝቅያስ መታመም

20፥1-11 ተጓ ምብ - 2ዜና32፥24-26፤ኢሳ38፥1-8

**20** በዚያ ጊዜ ሕዝቅያስ በጠና ታሞ
ሊሞት ተቃርቦ ነበር። የአሞጽ ልጅ
ነቢዩ ኢሳይያስም ወደ እርሱ ሄዶ፣ "እግዚ
አብሔር፣ 'ትሞታለህ ከእንግዲህ በሕይወት
አትኖርምና ቤትህን አስተካክል' ብሎሃል"
አለው።
2ሕዝቅያስም ፊቱን ወደ ግድግዳው
መልሶ እንዲህ ሲል ወደ እግዚአብሔር
ጸለየ፤ 3"እግዚአብሔር ሆይ፤ በታማኝነትና
በፍጹም ልብ በፊትህ እንደ ሄድሁ፣ አን
ተን ደስ የሚያሰኝህንም እንዳደረግሁ አስብ፤"
ሕዝቅያስም ምርር ብሎ አለቀሰ።
4ኢሳይያስ የመካከለኛውን አደባባይ አልፎ
ከመሄዱ በፊት የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ
ሲል ወደ እርሱ መጣ፤ 5"ተመለስና የሕ
ዝቤን አለቃ ሕዝቅያስን እንዲህ በለው፤
'የአባትህ የዳዊት አምላክ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ "ጸሎትህን ሰምቻለሁ፤ እንባ
ህንም አይቻለሁ፤ እነሆ፣ እፈውስሃለሁ።
ከዛሬ ሦስት ቀን በኋላ ወደ እግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ ትወጣለህ፤ 6በዕድሜህ ላይ ዐሥራ
አምስት ዓመት እጨምርልሃለሁ፤ አንተንና
ይህችንም ከተማ ከአሦር ንጉሥ እጅ እታ
ደጋለሁ፤ ስለ እኔ ስለ ራሴና ስለ ባሪያዬ
ስለ ዳዊት ስል ይህችን ከተማ እከላከልላ
ታለሁ።' "
7ከዚያም ኢሳይያስ፣ "ትኵስ የበለስ
ጥፍጥፍ አዘጋጁ" አላቸው፤ እነርሱም አዘ
ጋጅተው ዕባጩ ላይ አደረጉለት፤ ተፈወሰም።
8ሕዝቅያስም፣ "እግዚአብሔር እኔን ስለ
መፈወሱ፣ ከሦስት ቀን በኋላም ወደ እግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስ ስለ መውጣቴ ምል
ክቱ ምንድን ነው?" ሲል ኢሳይያስን ጠየ
ቀው።
9ኢሳይያስም፣ "እግዚአብሔር የሰጠውን
ተስፋ እንደሚፈጽም ምልክቱ ይህ ነው፤
ጥላው ዐሥር ደረጃ ወደ ፊት ይቅደምን?
ወይስ ዐሥር ደረጃ ወደ ኋላ ይመለስ?" ሲል
ጠየቀው።
10ሕዝቅያስም መልሶ፣ "ጥላው ዐሥር
ደረጃ ወደ ፊት መሄዱ ቀላል ነገር ነው፤
ይልቁን ዐሥር ደረጃ ወደ ኋላ ይመለስ"
አለ።
11ከዚያም ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ እግዚ
አብሔር ጮኸ፤ እግዚአብሔርም አካዝ በሠ
ራው ደረጃ ላይ የወረደውን ጥላ ዐሥር
ደረጃ ወደ ኋላው እንዲመለስ አደረገ።

### ከባቢሎን የመጡ መልእክተኞች

20፥12-19 ተጓ ምብ - ኢሳ39፥1-8
20፥20-21 ተጓ ምብ - 2ዜና32፥32-33

12በዚያን ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ የባልዳን ልጅ
መሮዳክ ባልዳን የሕዝቅያስን መታመም ሰምቶ
ስለነበር፣ ደብዳቤና ገጸ በረከት ለሕዝቅያስ ላከለት።

19፥36 ዘፍ10፥11፤ 2ነገ12፥18
19፥37 ቍ7፤ዘፍ 8፥4፤2ነገ17፥24:31
20፥3 ዘፍ5፥22፤ 8፥1፤1ነገ2፥4፤2ዜና 31፥20፤ነህ1፥8፤5፥19፤ 13፥14
20፥5 2ነገ9፥31፤ መዝ6፥6:8፤39፥12፤5 6፥8
20፥6 2ነገ19፥34፤ 1ዜና17፥19
20፥7 ዘፀ9፥9
20፥9 ዘዳ13፥2፤ ኢር44፥29
20፥10 2ነገ3፥18
20፥11 ኢሱ 10፥13፤2ዜና32፥31

19፥36 *ነነዌም፤* የአሦር መንግሥት ዋና ከተማ ናት።

19፥37 *ናሳራክ፤* የዚህ አምላክ ስም በአሦር ታሪክ ጽሑፎች ውስጥ አይገኝም። *አድራሜሌክና ሳራሳር የተባሉ ልጆቹ፤* የጥንት ፅሑፎች ሰናክሬም ስሙ ባልተጠቀሰ ልጁ፣ በቴቤት ወር በሃያኛው ቀን በዘመነ መንግሥቱ በሃያ ሦስተኛው ዓመት፣ እንደ ተገደለ ጠቅሰዋል። *አራራት፤* የዘፍ 8፥4 ማብ ይመ። *ልጁ አስራዶንም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፤* ከ681-669 ዓ.ቅ.ክ ገዛ። በድንጋይ ላይ የተቀረጹ የአሦር ታሪክ ጽሑፎች፣ የሰናክሬም ልጆች የአባታቸውን ዙፋን ለመውረስ እርስ በርሳቸው ተጋጭተው እንደ ነበር ያመለክታሉ። ሰናክሬም ከወንድሞቹ ሁሉ ታናሽ የሆነውን ልጁን የአሦር ዙፋን ወራሽ እንዲሆን መሰየሙ፣ አድራሜሌክና ሰራሳር ያልተሳካውን የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ እንዲያካሂዱ ሳይገፋፋቸው አልቀረም።

20፥1 *በዚያ ጊዜ፤* የሕዝቅያስ መታመም (ቍ1-11) እንዲሁም የባቢሎን መልእክተኞችን የተቀበለበት ጊዜ (ቍ12-19)፣ በ701 ዓ.ቅ.ክ ከተደረገው የአሦር ዘመቻ ሳይቀድም አይቀርም (ቍ6 እንዲሁም የቍ12-13 ማብ ይመ)። የባቢሎናውያን ጽሑፎችም፣ መሮዳክ ባልዳን (ቍ12) ከባቢሎን በ703 ዓ.ቅ.ክ ከተባረረ በኋላ በኤላም እንደ ሞተ ጠቅሰዋል። *ቤትህን አስተካክል፤* የኑዛዜ ቃል ዐይነት ሲሆን፣ በተለይ ዙፋኑን ማን እንደሚወርስ በተ መለከተ ነው። *ትሞታለህ፤* ሕዝቅያስ ብቻውን መግዛት በጀመረበት ጊዜ በ715 ዓ.ቅ.ክ የሃያ አምስት ዓመት ጎልማሳ ነው ተብሎ ቢገመት (18፥2 ይመ)፣ ከሞቱም ከዐሥራ አምስት ዓመት በፊት ቢታመም (የቍ6 ማብ ይመ)፣ በዚህ ጊዜ የሠላሳ ሰባት ወይም የሰላሣ ስምንት ዓመት ጕልማሳ ይሆናል ማለት ነው።

20፥3 *በታማኝነት ... በፊትህ እንደ ሄድሁ፣ አንተን ደስ የሚያሰኝህንም እንዳደረግሁ፤* ሕዝቅያስ የሚጸልየው በሠራው መልካም ሥራ የተነሣ እግዚአብሔር ምሕረት እንዲያደርግለት ሳይሆን፣ በታማኝነት የሚያገለግሉትን እግዚአብሔር እንደሚታደግ በማስብ ነው (የ2ሳሙ 22፥21 ማብ ይመ)።

20፥5 *እነሆ እፈውስሃለሁ፤* የሚመጣውንና የሚያልፈውን ሁሉ በሉዐላዊነቱ አስቀድሞ የሚወስን እግዚአብሔር ነው (መዝ139፥16፤ ኤፌ 1፥11)። የሕዝቅያስ ልመናና የእግዚአብሔር መልስ የሚያመለክተው፣ (1) መለኮታዊ ሉዐላዊነት ጸሎትን ከንቱ አያደርግም፤ ነገር ግን ያድነዋል፤ (2) ጸሎትና ለጸሎት የእግዚአብሔር መልስ፣ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ዕቅድ ውስጥ እንደሆነ ግንዛቤ እንዲደረግ ያስፈልጋል፤ (1ነገ 21፥29፤ ሕዝ 33፥13-16 ይመ)።

20፥6 *በዕድሜህ ላይ ዐሥራ አምስት ዓመት እጨምርልሃለሁ፤* ሕዝቅያስ በ686 ዓ.ቅ.ክ ሞተ፤ ዕድሜም የተጨመረለት ከ702 ዓ.ቅ.ክ በኋላ አይደለም። *ስለ እኔ ስለ ራሴና ስለ ባሪያዬ ስለ ዳዊት ስል፤* 19፥34 እንዲሁም የ1ነገ 11፥13 ማብ ይመ።

20፥7 *የበለስ ጥፍጥፍ፤* እግዚአብሔር ሕዝቅያስን ፈወሰው (ቍ5 ይመ)፤ ይህም ቢሆን መለኮታዊ ፈውስ ጠቃሚ መድኃኒቶችን መጠቀም አይከለክልም።

20፥9 *ደረጃ፤* ቍ11 ይመ (እንዲሁም የኢሳ38፥8 ማብ ይመ)።

20፥12 *የባልዳን ልጅ መሮዳክ፤* "ማርዱክ (የተባለው አምላክ) ወንድ ልጅ ሰጠኝ" ማለት ነው። ከ721-710 ዓ.ቅ.ክ ድረስ ባቢሎንን ገዛ፤ ይህም በአሦር ገዥ በዳግማዊ ሳርጎን ለአሦር ይገዛ ዘንድ ከመገደዱ በፊት ነበር። ሳርጎን በ705 ዓ.ቅ.ክ ከሞተ በኋላ፣ የባልዳን ልጅ መሮዳክ ሰናክሬም በ703 ዓ.ቅ.ክ እንዲሰደድ እስካደረገ ጊዜ ድረስ ባቢሎንን ገዛ፤ ነጻነቷንም አስከበረ (የቍ1 ማብ ይመ)። *ደብዳቤና ገጸ በረከት ለሕዝቅያስ ላከለት፤* 2ዜና32፥31፤ኢሳ39ይመ። መሮዳክ ባልዳን ይህን ያደረገው በአሦር ላይ ለማመፅ የሕዝቅያስን ትብብር በመፈለጉ ነበር። ቀደም ብሎ አባቱ አካዝ ከአሦር ጋር የነበረውን ትብብር ሕዝቅያስ በመቃወም 16፥7 በአሦር ላይ ቢያምፅም (18፥7 ይመ)፣ የእስራኤልን ድነት አስተማማኝ ለማድረግ ከባቢሎንና ከግብፅ ጋር ወዳጅነት በመፍጠሩ ተሳሳተ (2ዜና32፥31፤ ኢሳ30፥31፤ የ1ሳሙ17፥11፤የ1ነገ15፥19 ማብ ይመ)።

13ሕዝቅያስም መልክተኞቹን ተቀብሎ በዕቃ
ቤቱ ያለውን ሁሉ ብሩን፣ ወርቁን ቅመማ
ቅመሙንና ከፍ ያለ ዋጋ ያለውን ዘይት
የጦር መሣሪያ ግምጃ ቤቱንና በቀረውም
ግምጃ ቤት ያለ ውን በሙሉ አሳያቸው።
በቤተ መንግሥቱም ሆነ በመላው ግዛቱ ሕዝ
ቅያስ ሳያሳያቸው የቀረ ምንም ነገር
አልነበረም።
14ከዚያም ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ ሕዝቅያስ
ሄዶ፣ "እነዚያ ሰዎች ምን አሉህ? የመጡ
ትስ ከወዴት ነው?" ሲል ጠየቀው።
ሕዝቅያስም መልሶ፣ "የመጡት ከሩቅ
አገር ከባቢሎን ነው" አለው።
15ነቢዩም፣ "በቤተ መንግሥትህ ምን
ምን አዩ?" ሲል ጠየቀው።
ሕዝቅያስም፣ "በቤተ መንግሥቴ ያለውን
ሁሉ አይተዋል፤ በግምጃ ቤቶቼ ሳላሳያቸው
የቀረ ምንም ነገር የለም"አለ።
16ከዚያም ኢሳይያስ ሕዝቅያስን እንዲህ
አለው፤ "*የእግዚአብሔርን ቃል ስማ፤* 17*በቤተ
መንግሥትህ ያለው ሁሉ አባቶችህም እስከ
ዛሬ ድረስ ያከማቹት በሙሉ ወደ ባቢሎን
የሚወሰድበት ጊዜ በእርግጥ ይመጣል፤
አንዳች የሚቀር ነገር የለም ይላል እግዚ
አብሔር።* 18*የሥጋህ ቁራጭ የአጥንትህ
ፍላጭ ከሚሆኑት፣ ከምትወልዳቸው ልጆ
ችህ አንዳንዶቹ በምርኮ ይወሰዳሉ፤ በባቢ
ሎንም ቤተ መንግሥት ጃንደረቦች ይሆ
ናሉ።"* 19ሕዝቅያስም፣ "የተናገርኸው *የእግ
ዚአብሔር* ቃል መልካም ነው"ሲል መለሰ፤
"እኔ እስካለሁ ድረስ ሰላምና ጸጥታ ከተገኘ
የሆነው ይሁን" ብሎ አሰቦአልና። 20 በሕዝ
ቅያስ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው ሌላው
ሥራ፣ የፈጸመውም ሁሉ ኵሬውንና ውሃ
ውን ወደ ከተማዪቱ ያመጣበትን የመሬት
ለመሬት ቦይ እንዴት አድርጎ እንደ ሠራው
በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይ
ደለምን? 21ሕዝቅያስም ከአባቶቹ ጋር አንቀ
ላፋ፤ ልጁ ምናሴም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

20፥17 2ነገ 24፥13፤2ዜና36፥10፤ ኤር20፥5፤27፥22፤ 52፥17-23
20፥18 2ነገ 24፥15፤ዳን1፥3፤ ሚክ4፥10
20፥20 2ሳሙ5፥8፤ 2ነገ18፥17
21፥1 ኢሳ62፥4
21፥2 ቍ16፤ዘዳ 4፥25፤9፥4፤18፥9፤ 1ነገ14፥24፤2ነገ 16፥3፤ኤር15፥4
21፥3 ዘኍ2፥1፤ዘዳ 16፥21፤17፥3፤ መሳ6፥28፤1ነገ 3፥3፤2ነገ18፥4፤ ኤር19፥13
21፥4 ዘፀ20፥24፤ 2ሳሙ7፥13፤ ኢሳ66፥4፤ኤር4፥1፤ 7፥30፤23፥11፤ 32፥34፤ሕዝ 23፥39
21፥5 1ነገ7፥12፤ 2ነገ23፥12
21፥6 ዘሌ18፥21፤ 19፥31፤ዘዳ18፥10፡1 4፤2ነገ3፥27፤ 23፥26

## የይሁዳ ንጉሥ ምናሴ

21፥1-10 ተጓ ምብ - 2ዜና33፥1-10
21፥17-18 ተጓ ምብ - 2ዜና33፥18-20

21 ምናሴ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ዐሥራ
ሁለት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም
ተቀምጦም አምሳ አምስት ዓመት ገዛ፤ እና
ቱም ሐፍሴባ ትባል ነበር። 2ምናሴ *እግዚአ
ብሔር* ከእስራኤላውያን ፊት አሳዶ ያወጣቸ
ውን የአሕዛብን አስጸያፊ ልማድ በመከተል
*በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ።
3አባቱ ሕዝቅያስ ያፈረሰውን የየኰረብታ
ውን ማምለኪያ ስፍራ መልሶ ሠራ፤ የእስራ
ኤል ንጉሥ አክዓብ እንዳደረገው ሁሉ፣ እር
ሱም ለበኣል መሠዊያዎችን አቆመ፤ የአሼ
ራንም ምስል ዐምድ ሠራ። እንዲሁም ለሰ
ማይ ከዋክብት ሰራዊት ሁሉ ሰገደ፤ አመለ
ካቸውም። 4*እግዚአብሔር*፣ "ስሜን በኢየሩ
ሳሌም አኖራለሁ" ባለበት *በእግዚአብሔር*
ቤተ መቅደስ መሠዊያዎችን ሠራ። 5በሁለ
ቱም *የእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ አደባባ
ዮች ለሰማይ ከዋክብት ሰራዊት ሁሉ መሠ
ዊያ ሠራ። 6የገዛ ልጁን የሚቃጠል መሥ
ዋዕት አድርጎ አቀረበ†፤ መተተኛና ጠንቋይ
ሆነ፤ ሙታን አነጋጋሪዎችንና መናፍስት ጠሪ
ዎችን ምክር ጠየቀ፤ *እግዚአብሔርን* ለቍጣ

†6 ወይም፣ የራሱን ልጅ በእሳት ውስጥ እንዲያልፍ አደረገ።

20፥13 *መልእክተኞቹን ተቀብሎ... በሙሉ አሳያቸው፤* ሕዝቅያስ ለባቢሎን መልእክተኞች ያደረገው አቀባበል ከሚገባ በላይ ነበር። ምናልባትም ይህን ያደረገው የመንግሥቱን ሀብትና ብልጥግና አሳይቶ ባቢሎናውያንን በማስደነቅ የይሁዳን ደህንነት ከእነርሱ ጋር በሚመሠረተው ወዳጅነት ለማጠናከርና በአሦር ላይ በጋራ ለማመፅ ፈልጎ ሳይሆን አይቀርም። ይህ ሐሳብ በመሠረቱ የንጉሡን ኀላፊነት በተመለከተ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያደረገውን ኪዳን የሚጻረር ነው (የ2ሳሙ 24፥2 ማብ ይመ)። *ብሩን ... ዘይት፤* በኢየሩሳሌም የዚህ ሀብት መገኘት የሚያመለክተው፣ ይህ ሁኔታ የተፈጸመው ለሰናክሬም በ701ዓ.ቅ.ክ ግብር መገበር ከመጀመሩ በፊት ነበር፤ (18፥15-16 ይመ)።

20፥14 *እነዚያ ሰዎች ምን አሉህ?* ሕዝቅያስ የባቢሎን መልእ ክተኞች የመጡበትን የፖለቲካ ጉዳይ በተመለከተ፣ ኢሳይያስ ላቀረበለት ጥያቄ መልስ አልሰጠም።

20፥17 *ወደ ባቢሎን የሚወሰድበት፤* ሕዝቅያስ የባቢሎንን መልእክተኞች በሞቀ ሁኔታ ስለተቀበለ በተቃራኒው ያልፈለገውና ያልጠበቀው ነገር ገጠመው። ኢሳይያስ ወደ ባቢሎን ስለመማረክ የተናገረው ትንቢት ከመፈጸሙ ከአንድ መቶ ዐሥራ አምስት ዓመት በፊት መሆኑ እጅግ የሚያስገርም ነው፤ ምክንያቱም ትንቢቱን በተናገረ ጊዜ ይሁዳን የሚያስፈራና ታላቅ የዓለም መንግሥት የነበረው አሦር እንጂ ባቢሎን አልነበረምና።

20፥18 *ከምትወልዳቸው ልጆችህ አንዳንዶቹ ... ይወሰዳሉ፤* የሕዝቅያስ ልጅ ምናሴ በአሦራውያን ተወስዶ፣ በባቢሎን ለጥቂት ጊዜ እስረኛ ሆኖ ነበር (2ዜና33፥11 ይመ)፤ በኋላም ከዳዊት ቤት ብዙዎች ተማረኩ (24፥15፤ 25፥7፤ ዳን1፥3 ይመ)።

20፥19 ... *ቃል መልካም ነው፤* ይመጣባችኋል ተብሎ የተነገረውን የፍርድ ቃል እርሱን በቀጥታ ባለመንካቱ በአንድ በኩል ሲታይ ራስ ወዳድነቱን ያንጸባረቀ አባባል ቢመስልም፣ የእግዚአብሔርን ፍርድ እሺ ብሎ በትሕትና የተቀበለ መሆኑን ማስተዋሉ የተሻለ ነው (2ዜና 32፥26)፤ ከዚህም በላይ እግዚአብሔር በምሕረቱ ለሕዝቡ የሰጠውን ሰላም በአክብሮት መቀበሉን ያሳያል።

20፥20 *ኵሬውንና .... የመሬት ለመሬት ቦይ፤* ሕዝቅያስ የመሬት ለመሬት ቦይ የሠራው ከግዮን ወንዝ እስከ ጒድጓድ ውሃው ድረስ (1ነገ1፥33፡38፤ 2ዜና 32፥30 ይመ) በከተማዪቱ ቅጥር ሥር ነበር። የኢየሩሳሌም ከተማ ውሃ በማያቋርጥ መንገድ ከማግኘቷ የተነሳ በአካባቢዎቿ ሊደረግ የነበረውን ጥቃት በእጅጉ ቀንሶላታል። በ1880 ዓ.ም በመስኖው ግድግዳ ላይ የተገኘው ጽሑፍ የውሃ መተላለፊያ ቦዩ እንዴት እንደ ተሠራ ይገልጻል። ይህ የመሬት ለመሬት ቦይ በዐለታማ መሬት ላይ የተቆፈረው ከአምስት መቶ ዐሥራ ስምንት ሜትር በላይ ርዝማኔ ያለው ሲሆን፣ ከፍታው ከዐሥር ወይም ዐሥራ አንድ ሜትር እስከ ሦስት ሜትር ተኩል የሚደርስ፣ ስፋቱ በአማካይ ግማሽ ሜትር ነበር። *በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ 14፥29 ማብ ይመ።

20፥21 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1ነገ 1፥21 ማብ ይመ።

21፥1 *ዕድሜው ዐሥራ ሁለት ዓመት ነበር፤* ምናሴ የተወለደው አባቱ ሕዝቅያስ በጠና ታሞ ከነበረበት ጊዜ በኋላ ነው (20፥6 ይመ)። *አምሳ አምስት ዓመት፤* ከ697-642 ዓ.ቅ.ክ ድረስ ያለውን ሲሆን፣ ይህም ከአባቱ ከሕዝቅያስ ጋር ዐሥር ዓመት አብሮ የገዛበትን ዘመን (ከ697-686 ዓ.ቅ.ክ) ይጨምራል። በእስራኤልም ሆነ በይሁዳ ከነገሡት ነገሥታት ዘመነ መንግሥት ረጅሙ ይህ ነው።

21፥2 በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ድርጊት፤ ምናሴ አባቱ ሕዝቅያስ የነበረውን የሃይማኖት አቋም በመገልበጥ (18፥3-5 ይመ)፣ የአካዝን መንገድ መከተል ጀመረ (16፥3ይመ)።

21፥3 *ሕዝቅያስ ያፈረሰውን የየኰረብታውን ማምለኪያ ስፍራ፤* የ18፥4 ማብ እንዲሁም 2ዜና31፥1 ይመ። *የአሼራንም ምስል ዐምድ፤* 1ነገ 14፥15፡23፤ 15፥13፤16፥33 ይመ። *አክዓብ እንዳደረገው ሁሉ፤* ምናሴ የይሁዳው አክዓብ ነበረ (1ነገ16፥30-33ይመ)። *ለሰማይ ከዋክብት ሰራዊት ሁሉ ሰገደ፤* የ17፥16 ማብ ይመ።

21፥4 *ስሜን በኢየሩሳሌም አኖራለሁ፤* 1ነገ8፥20፡29፤9፥3 ይመ።

21፥6 *የገዛ ልጁን የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ፤* የ16፥3 ማብ እና 17፥17 ይመ። *መተተኛና ጠንቋይ ሆነ፤* የ16፥15፤ 17፥17 ማብ ይመ። *ሙታን አነጋጋሪዎችንና መናፍስት ጠሪዎችን ምክር ጠየቀ፤* ዘሌ19፥31፤ዘዳ18፥11፤ 1ሳሙ 28፥3፡7-9 እና ማብ ይመ።

የሚያነሣሣውን ክፉ ድርጊት በፊቱ ፈጸመ::
7የሠራውን የአሼራን የተቀረጸ ምስል ዐምድ
ወስዶ በቤተ መቅደሱ ውስጥ አስቀመጠ፤
ይህም እግዚአብሔር ለዳዊትና ለልጁ ለሰ
ሎሞን፣ "በዚህ ቤተ መቅደስና ከእስራኤል
ነገዶች ሁሉ በመረጥኋት በኢየሩሳሌም
ስሜን ለዘላለም አኖራለሁ" ያለው ስፍራ
ነው:: 8እንዲሁም፤ "ብቻ ያዘዝኋቸውን ሁሉ
ተጠንቅቀው በመፈጸምና ባሪያዬ ሙሴ የሰጣ
ቸውንም ሕግ በሙሉ በመጠበቅ ይጽኑ እንጂ
ከእንግዲህ የእስራኤላውያን እግር፣ ለአባቶ
ቻቸው ከሰጠኋቸው ምድር ወጥቶ እንዲንከ
ራተት አላደርግም" ያለው ስለዚሁ ስፍራ
ነው:: 9ሕዝቡ ግን አልሰሙም፤ እግዚአብሔር
በእስራኤላውያን ፊት ካጠፋቸው አሕዛብ
ይልቅ ክፉ ድርጊት እንዲፈጽሙ ምናሴ
አሳታቸው::
10እግዚአብሔር በባሪያዎቹ በነቢያት አማ
ካይነት እንዲህ ሲል ተናገረ፤ 11"የይሁዳ
ንጉሥ ምናሴ ይህን ሁሉ አስጸያፊ ኀጢ
አት ሠርቶአል፤ ከእርሱ በፊት ከነበሩት
አሞራውያን ይልቅ ክፉ ድርጊት ፈጽሞአል፤
ይሁዳንም በጣዖታቱ አስቶአል:: 12ስለዚህ
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የሚለው
ይህ ነው፤ 'ለሚሰማ ሁሉ ጆሮዎቹ ጭው
እንዲሉ የሚያደርግ ክፉ መከራ በኢየሩ
ሳሌምና በይሁዳ ላይ አመጣለሁ:: 13በሰ
ማርያ ላይ ያዘጋጀሁትን መለኪያ ገመድ፣
የአክዓብንም ቤት የለካሁበትን ቱንቢ በኢ
የሩሳሌም ላይ እዘረጋለሁ፤ አንድ ሰው ሳሕን
እንደሚወለውል ከወለወለም በኋላ እንደሚ
ገለብጠው እኔም ኢየሩሳሌምን ወልውዬ
እገለብጣታለሁ:: 14የርስቴንም ቅሬታ እተዋ
ቸዋለሁ፤ ለጠላቶቻቸው አሳልፌ እሰጣቸዋ
ለሁ፤ ለጠላቶቻቸውም ሁሉ ብዝበዛና ምርኮ
ይሆናሉ:: 15ይህን የማደርገውም የቀድሞ
አባቶቻቸው ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ
አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ በፊቴ ክፉ ድርጊት
ስለ ፈጸሙና ለቍጣ ስላነሣሡኝ ነው::"
16ይልቁንም ምናሴ፣ በእግዚአብሔር ፊት
ክፉ ድርጊት እንዲፈጽም ይሁዳን ካሳተበት
ኀጢአት ሌላ፣ ኢየሩሳሌምን ከዳር እስከ
ዳር እስኪሞላት ድረስ ብዙ ንጹሕ ደም
አፈሰሰ::
17በምናሴ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው
ሌላው ሥራ፣ የሠራውን ኀጢአት ጨምሮ
የፈጸመው ድርጊት ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት
ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን? 18ምና
ሴም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ "የዖዛ አትክ
ልት" በሚባለው በቤተ መንግሥቱ አትክ
ልት ውስጥ ተቀበረ:: ልጁ አሞንም በእግሩ
ተተክቶ ነገሠ::

## የይሁዳ ንጉሥ አሞን

21፥19-24 ተጓ ምብ - 2ዜና33፥21-25

19አሞን ሲነግሥ ዕድሜው ሃያ ሁለት ዓመት
ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ሁለት ዓመት
ገዛ፤ እናቱ ሜሶላም ትባላለች፤ እርሷም
የዮጥባ አገር ሰው የሐሩስ ልጅ ነበረች::
20አባቱ ምናሴ እንዳደረገው ሁሉ እርሱም
በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ::
21አባቱ በሄደበት መንገድ ሁሉ ሄደ፤ አባቱ
ያመለካቸውን አማልክት አመለከ፤ ሰገደላቸ
ውም:: 22የአባቶቹን አምላክ እግዚአብሔርን
ተወ፤ በእግዚአብሔርም መንገድ አልሄደም::
23የአሞንም ሹማምንት ዐመፁ፤ ንጉ
ሡንም በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ገደሉት::
24ከዚያም የአገሩ ሕዝብ በንጉሥ አሞን
ላይ ያመፁትን ሁሉ ገደሉ፤ ልጁን ኢዮስ
ያስንም በእግሩ ተክተው አነገሡት::

21፥7 ዘፀ20፥24፤ ዘሌ15፥31፤ዘዳ 16፥21፤2ሳሙ 7፥13፤2ነገ23፥4
21፥8 2ሳሙ 7፥10፤ 2ነገ18፥12
21፥9 ዘዳ9፥4፤ 1ነገ14፥9፤ሕዝ5፥7
21፥11 ዘፍ15፥16፤ 1ነገ14፥9፤ሕዝ 18፥12
21፥12 1ሳሙ 3፥11፤2ነገ23፥26፤ 24፥3፤ኤር15፥4፤ሕዝ 7፥5
21፥13 2ነገ 23፥27፤ኢሳ28፥17፤ 34፥11፤ሰቆ2፥8፤ አሞ7፥7፥9
21፥14 2ነገ19፥4፤ ዕዝ9፥8፤ነህ1፥2፤መዝ 78፥60፤ኢሳ1፥9፤ 10፥21፤ኤር6፥9፤ 12፥7፤21፥22፤ 23፥33፤40፥15፤42፥2፤ 44፥7፥28፤50፥20፤ ሚክ2፥12-21
21፥15 ዘፀ32፥22፤ ኤር25፥7
21፥16 ቍ2፥11፤ 2ነገ24፥4፤ኢዮ22፥ 14፤መዝ10፥11፤94፥ 7፤106፥38፤ኢሳ 29፥15፤47፥10፤ 59፥3፥7፤ኤር2፥34፤ 7፥6፤19፥4፤22፥17፤ ሰቆ4፥13፤ሕዝ7፥23፤ 8፥12፤9፥9፤23፥34፤ ሆሴ4፥2፤ሰፎ1፥12፤
21፥18 ቍ26፤ አስ1፥5፤7፥7
21፥20 1ነገ15፥26
21፥22 1ሳሙ 8፥8፤ 1ነገ11፥33
21፥23 2ነገ12፥20
21፥24 2ነገ14፥5፤ 2ዜና33፥21፤ሰፎ1፥1

21፥7 *የአሼራን የተቀረጸ ምስል ዐምድ፤* የ1ነገ 14፥15 ማብ ይመ:: *ለዳዊትና፤* 2ሳሙ 7፥13 ይመ:: *ለሰሎሞን፤* 1ነገ 9፥3 ይመ:: *ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ በመረጥኋት፤* 1ነገ 11፥13፡32፡36 ይመ::

21፥9 *እግዚአብሔር ... ካጠፋቸው አሕዛብ፤* 1ነገ14፥24፤ ዘዳ 12፥29-31፤31፥3 ይመ::

21፥10 *በባሪያዎቹ በነቢያት፤* 2ዜና 33፥10፡18 ይመ::

21፥11 *ከአሞራውያን ይልቅ ክፉ ድርጊት፤* የ1ነገ21፥26 ማብ ይመ::

21፥12 *ለሚሰማ ሁሉ ጆሮዎቹ ጭው እንዲሉ የሚያደርግ፤* ኤር 19፥3 ይመ::

21፥13 *መለኪያ ገመድ ... የለካሁበትን ቱንቢ፤* ሕንጻ ለመሥራት የሚያገለግሉት እነዚህ መሣሪያዎች፣ የጥፋት ምልክት ሆነው ቀርበዋል (ኢሳ 34፥11፤ አሞ 7፥7-9፡17 ይመ)::

21፥14 *እተዋቸዋለሁ፤* ይህ የተባለው ለፍርድ አሳልፎ ከመስጠት (ኤር 12፥7 ይመ) አንጻር እንጂ ቃል ኪዳንን ከመሻር አኳያ አይደለም (1ሳሙ12፥22፤ኢሳ43፥1-7 ይመ):: *የርስቴንም ቅሬታ፤* የሰሜኑ መንግሥት ሲጠፋ ይሁዳ ለእግዚአብሔር ከጥፋት የተረፈ ርስቱ ነበር (1ነገ8፥51፤ ዘዳ4፥20፤ 1ሳሙ10፥1፤ መዝ 28፥9፤ እንዲሁም የ2ነገ 19፥4 ማብ ይመ)::

21፥15፤ ከኀጢአታቸው የተነሣ የእስራኤል ታሪክ በአጠቃላይ ኪዳንን የማፍረስ ታሪክ ነበር:: በምናሴ ዘመን የእግዚአብሔር የቍጣ ጽዋ ከመሙላቱ የተነሣ፣ ከተስፋዪቱ ምድር በምርኮ የመጋዝ ፍርድ (የ17፥7 ማብ ይመ) የማይቀር ጉዳይ ሆነ (24፥1-4 ይመ)::

21፥16 *ንጹሕ ደም፤* እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎችን የሚያመለክት ሲሆን፣ የምናሴን ክፉ ሥራ በመቃወም ሰማዕት የሆኑትን ነቢያትንም ይጨምራል (ቍ10-11):: በአይሁድ ትውፊት ነቢዩ ኢሳይያስ በይሁዳ ንጉሥ በምናሴ ሁለት ቦታ በመጋዝ እንደ ተሰጠነቀ ይነገራል (ከዕብ 11፥37 ጋር ያነጻጽሩ)::

21፥17 *በምናሴ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው ሌላው ሥራ፤* 2ዜና 33፥12-19 ይመ:: *በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ 14፥29 ማብ ይመ::

21፥18 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1ነገ 1፥21 ማብ ይመ:: *ዖዛ፤* የዖዝያን ስም በአጭሩ ሲጠቀስ ሊሆን ይችላል፤ በ14፥21-22 እና በ15፥ 1-7 የተጠቀሰው ዓዛርያስ ሌላ ስሙ ነው (2ዜና26 ይመ)::

21፥19 *ሁለት ዓመት፤* ከ642-640 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው:: *ዮጥባ፤* አንዳንዶች በዘኍ33፥33-34 እና በዘዳ 10፥7 የተጠቀሰው ከዔጽዮንጋብር አጠገብ ያለው ዮጥባታ ነው ይላሉ፤ ሌሎች ደግሞ የቤተ ክርስቲያን አባት የሆነውን የሮምን ጨምሮ ዮጥባ የምትገኘው በይሁዳ እንደ ሆነ ይናገራሉ::

21፥20 *ክፉ ድርጊት፤* አሞን አባቱ ምናሴ በዕድሜው መጨረሻ ላይ ያሳየውን ዐይነት የልብ ለውጥ አልታየበትም (2ዜና 33፥12-19 ይመ):: አባቱ ምናሴ አስወግዶት የነበረውን የጣዖት አምልኮን መልሶ የጀመረ ይመስላል፤ ምክንያቱም በኢዮስያስ ዘመን እንደዚሁ የጣዖት አምልኮ ነበረ (23፥5-7፡12 ይመ)::

21፥23 *ዐመፁ፤* ይህ የቤተ መንግሥት ዐመፅ በሃይማኖት ሳቢያ ይሁን ወይም በአስተዳደራዊ ምክንያት እንደ ተቀነባበረ አይታወቅም::

21፥24 *የአገሩ ሕዝብ፤* የአገሪቱ ዜጋ የሆኑት በአጠቃላይ ማለት ነው (11፥14፡18፤14፥21፤23፥30 ይመ):: *በንጉሥ አሞን ላይ ያመፁትን ሁሉ ገደሉ፤* ሕዝቡ ይህን ድርጊት የፈጸሙት ለዳዊት ቤት ካላቸው ታማኝነት የተነሣ ይሁን በሌላ ምክንያት አይታወቅም::

25በአሞን ዘመነ መንግሥት የተከናወነው
ሌላው ሥራ፣ የፈጸመውም ድርጊት ሁሉ
በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ
አይደለምን? 26እርሱም በዖዛ አትክልት
ውስጥ ባለው መቃብሩ ተቀበረ፤ ልጁ ኢዮ
ስያስም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

## የሕጉ መጽሐፍ ተገኘ

22፥1-20 ተጓ ምብ - 2ዜና34፥1-2፤8-28

**22** ኢዮስያስ ሲነግሥ ዕድሜው ገና
ስምንት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳ
ሌም ተቀምጦም ሠላሳ አንድ ዓመት ገዛ።
እናቱም የባሱሮት አገር ሰው የአዳያ ልጅ
ይዲዳ ነበረች። 2ኢዮስያስም *በእግዚአብሔር*
ፊት መልካም ነገር አደረገ፤ ወደ ቀኝም
ወደ ግራም አላለም፤ አባቱ ዳዊት በሄደበት
መንገድ ሁሉ ሄደ።

3ብዘመነ መንግሥቱ በዐሥራ ስምንተኛውም
ዓመት ኢዮስያስ የሜሶላምን የልጅ ልጅ
የኤዜልያስን ልጅ ጸሓፊውን ሳፋንን ወደ
*እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ላከው፤ እንዲ
ህም አለው፤ 4"ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ኬል
ቅያስ ውጣ፤ የበር ጠባቂዎች ከሕዝቡ ሰብ
ስበው ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ የገ
ባው ገንዘብ ምን ያህል እንደ ሆነ ራሱ እን
ዲቈጥረው አድርግ፤ 5ይህም የቤተ መቅደ
ሱን ሥራ እንዲቈጣጠሩ ለተሾሙት ሰዎች
ይሰጥ፤ እነርሱም *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅ
ደስ ለሚያድሱት ይክፈሉአቸው፤ 6የሚከፍ
ሉትም ለአናጺዎች፣ ለግንበኞችና ለድን
ጋይ ጠራቢዎች ነው። እንዲሁም ለቤተ
መቅደሱ እድሳት ሥራ የሚሆኑ ሳንቃዎ
ችና የተጠረቡ ድንጋዮች ይግዙበት። 7ሰዎቹ
ታማኞች ስለሆኑም የተሰጣቸውን ገንዘብ
መቈጣጠር አያስፈልግም።"

8ሊቀ ካህናቱ ኬልቅያስ ጸሓፊውን ሳፋንን፣
"የሕጉን መጽሐፍ እኮ በ*እግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ ውስጥ አገኘሁት" ብሎ ሰጠው፤
እርሱም ተቀብሎ አነበበው። 9ከዚያም ጸሓ
ፊው ሳፋን ሄዶ ለንጉሡ፣ "ሹማምንትህ
*በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ውስጥ የነበ
ረውን ገንዘብ አውጥተዋል፤ ቤተ መቅደሱን
እየተቈጣጠሩ ለሚያሠሩትም አስረክበዋል"
አለው። 10ከዚያም ጸሓፊው ሳፋን ለንጉሡ፣
"ሊቀ ካህናቱ ኬልቅያስ መጽሐፍ ሰጥቶ
ኛል" ብሎ ነገረው። ሳፋንም ለንጉሡ ከመ
ጽሐፉ አነበበለት።

11ንጉሡም የሕጉን መጽሐፍ ቃል ሲሰማ
ልብሱን ቀደደ። 12ከዚያም ካህኑን ኬልቅያ
ስን፣ የሳፋን ልጅ አኪቃምን፣ የሚክያስን
ልጅ ዓክቦርን፣ ጸሓፊውን ሳፋንንና የንጉ
ሡን የቅርብ አገልጋይ ዓሳያን እንዲህ ሲል
አዘዛቸው፤ 13"ሂዱና ስለ እኔ፣ ስለ ሕዝቡና
ስለ ይሁዳም ሁሉ በተገኘው በዚህ መጽሐፍ
የተጻፈው ምን እንደ ሆነ *እግዚአብሔርን*
ጠይቁ፤ ምክንያቱም አባቶቻችን ለዚህ መጽ
ሐፍ ቃል ባለመታዘዛቸው፣ እኛን በተመለ
ከተም በዚሁ ላይ የተጻፈውን ሁሉ ባለመፈ
ጸማቸው፣ በእኛ ላይ የሚነደው *የእግዚ
አብሔር* ቍጣ ታላቅ ነውና።"

14ካህኑ ኬልቅያስ፣ አኪቃም፣ ዓክቦርና፣
ሳፋን፣ ዓሳያም የሐርሐስ የልጅ ልጅ፣ የቲ
ቁዋ ልጅ የአልባሳት ጠባቂውን የሴሌምን
ሚስት ነቢዪቱን ሕልዳናን ለመጠየቅ ሄዱ።
እርስዋም የምትኖረው ኢየሩሳሌም ውስጥ
በሁለተኛው ሰፈር ነበር።

21፥26. ቍ18
22፥1 ኢሱ15፥39፤ ኤር1፥2፤25፥3
22፥2 ዘዳ5፥32፤ 17፥19፤1ነገ14፥8
22፥3 2ዜና34፥20፤ ኤር39፥14
22፥4 2ነገ12፥45፤ ዕዝ7፥1
22፥5 2ነገ12፥5
22፥6 2ነገ12፥11-12
22፥7 2ነገ12፥15
22፥8 ዘዳ28፥61፤ 31፥24፤ ሐጌ3፥10
22፥10 ኤር36፥21
22፥11 ቍ28
22፥12 1ሳሙ 8፥14፤2ነገ25፥22፤ ኤር26፥24፤39፥14
22፥13 ዘፍ25፥22፤ ዘዳ29፥24-28፤31፥17፤ 1ሳሙ9፥9፤ኢሳ5፥25፤ 42፥25፤አሞ2፥4
22፥14 ዘፀ15፥20

21፥25 *በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ 14፥29 ማብ ይመ።

21፥26 *በዖዛ፤* የቍ 18 ማብ ይመ።

22፥1 *ሠላሳ አንድ ዓመት፤* ከ640-609 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው (የ21፥19 ማብ ይመ)። *ባሱሮት፤* በይሁዳ የሚገኝና በለኪሶ አካባቢ ያለ ስፍራ ነው (ኢሱ 15፥39 ይመ)።

22፥2 አባቱ ዳዊት በሄደበት *መንገድ፤* የ18፥3 ማብ ይመ። ኢዮስያስ ከምርኮ በፊት ከዳዊት ሥርወ መንግሥት ከነበሩ ነገሥታት መካከል እግዚአብሔርን የሚፈራ የመጨረሻው ንጉሥ ነበር። በኢዮስያስ ዘመን ትንቢት ይናገር የነበረው ኤርምያስ ስለ እርሱ መልካም ተናግሮአል (ኤር1፥2፤22፥15-16)። ነቢዩ ሶፎን ያስም በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት በመጀመሪያው ላይ ትንቢት ተናግሮአል (ሶፎ 1፥1)።

22፥3 *በዐሥራ ስምንተኛው ዐመት፤* በ622 ዓ.ቅ.ክ ነው። በዚህ ጊዜ ኢዮስያስ የሃያ ስድስት ዓመት ጎልማሳ ነበር (ቍ1 ይመ)። በዐሥራ ስድስት ዓመቱ እግዚአብሔርን በታማኝነት ማገልገል ጀመረ፤ ይህም በነገሠ በስምንተኛው ዓመት ነበር (2ዜና 34፥3)። ሃያ ዓመት ሲሞላው ማለትም በነገሠ በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት (2ዜና 34፥3)፣ በአገሪቱ የነበረውን የጣዖት አምልኮ ማስወገድ ጀመረ። *ጸሓፊውን ሳፋንን፤* የ2ሳሙ 8፥17 ማብ ይመ። ከዚህ ሰው ጋር አብረው የተጠቀሱ ሁለት ሰዎች በ2ዜና 34፥8 ላይ ይገኛሉ።

22፥4 *ኬልቅያስ፤* ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን በደመሰሱ ጊዜ የተገደለው የዓዛርያስ አባት እንዲሁም የሰራያ አያት ሊቀ ካህናቱ ነው (ነገ 25፥18-20 ይመ)። ይህ ኬልቅያስ የነቢዩ ኤርምያስ አባት አይደለም (ኤር 1፥1ይመ)። *የበር ጠባቂዎች ከሕዝቡ ሰብስበው...የገባውን ገንዘብ፤* ኢዮስያስ ቤተ መቅደሱን ለማደስ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማሰባሰብ የኢዮአስን ዘዴ ተጠቀመ (12፥1-16፤ 2ዜና 34፥9 ይመ)።

22፥5 *እንዲቈጣጠሩ ለተሾሙት፤* 2ዜና34፥12-13 ይመ።

22፥8 *የሕጉን መጽሐፍ፤* አንዳንድ አስተማሪዎች በዚህ ጊዜ የተገኘው አምስቱ የሙሴ መጽሐፍ ነው ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ የዘዳግም መጽሐፍ በሙሉ ወይም በከፊል ነው ይላሉ (ዘዳ 31፥24፡26፤ 2ዜና 34፥14 ይመ)።

22፥11 *ልብሱን ቀደደ፤* የ18፥37 ማብ ይመ። ኢዮስያስ ከመጽሐፉ በተነበበለት ጊዜ ያሳየውን ሁኔታ፣ ኢዮአቄም ነቢዩ ኤርምያስ የጻፈው መጽሐፍ በተነበበለት ጊዜ ካሳየው ሁኔታ ጋር ያነጻጽሩ (ኤር 36፥24)። ኢዮስያስ በዚህ መንገድ ሐዘኑን የገለጸው ምናልባት በዘሌ 26 እና በዘዳ 28 ወይም ከሁለቱ በአንዱ የተነገረው የኪዳኑ ርግማን የመጨረሻው አስከፊ ነገር መማረክ መሆኑን ስለተገነዘበ ሊሆን ይችላል።

22፥12 *አኪቃም፤* በናቡከደነፆር የይሁዳ ገዥ ሆኖ የሚሾመው የጎዶልያስ አባት ነው (25፥22፤ ኤር 39፥14 ይመ)፤ በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥትም የኤርምያስ ሕይወት በአደጋ ላይ በነበረ ጊዜ ኤርምያስን የረዳ ሰው ነው (ኤር 26፥24 ይመ)። *ዓክቦር፤* ልጁ ኤልናታን በ24፥8፤ ኤር 26፥22፤36፥12 ላይ ተጠቅሶአል። *ጸሓፊውን ሳፋንንና፤* የቍ3 ማብ ይመ።

22፥14 *ነቢዪቱን ሕልዳናን፤* መልእክተኞቹ ከኤርምያስና ከሶፎንያስ ይልቅ ለምን ወደ ሕልዳና እንደ ሄዱ አይታወቅም፤ ምናልባትም በኢየሩሳሌም ስለ ነበረች ይሆናል። *የአልባሳት ጠባቂውን የሴሌምን፤* ምናልባት በኤር 32፥7 የተጠቀሰው የኤርምያስ አጎት ይሆናል። *በሁለተኛው ሰፈር፤* የከተማው አንዱ ክፍል ነው፤ በዕብራይስጡ ትርጕም ይህን ሐረግ "አዲስ መኖሪያ ሰፈር" ይለዋል (ሶፎ 1፥10)፤ ስለዚህ ይህ ስፍራ ምናልባት በሰሜን ምዕራብ ኢየሩሳሌም በመጀመሪያውና በሁለተኛው ቅጥር መካከል ባለው አዲስ በተሠራው አካባቢ የሚገኝ ሳይሆን አይቀርም። (2ዜና33፥14 ይመ)።

15ነቢዪቱም፣ “የእስራኤል አምላክ እግዚ
አብሔር የሚለው ይህ ነው፤ ወደ እኔ ለላካ
ችሁ ሰው እንዲህ ብላችሁ ንገሩት፤ 16“እግ
ዚአብሔር የሚለው ይህ ነው፤ የይሁዳ
ንጉሥ ባነበበው መጽሐፍ የተጻፈውን ሁሉ
በዚህ ቦታና በሕዝቡ ላይ አመጣለሁ::
17እኔን ስለተውኝና ለሌሎች አማልክት ዕጣን
ስላጠኑ፣ እጆቻቸው በሠሯቸውም አማል
ክት ሁሉ* ስላስቈጡኝ፣ ቍጣዬ በዚህ ቦታ
ላይ ይነዳል፤ አይጠፋምም::’” 18እግዚአብ
ሔርን እንድትጠይቁ ወደዚህ ቦታ ለላካ
ችሁ ለይሁዳ ንጉሥ ይህን ንገሩት፣ ‘ስለ ሰማ
ኸው ነገር የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
የሚለው ይህ ነው፤ 19“ርግማንና ለጥፋት
የተዳረጉ ስለመሆናቸው በዚህ ቦታና በሕ
ዝቡ ላይ የተናገርኩትን ስትሰማ ልብህ
ስለተነካና ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ስላ
ዋረድህ፣ ልብስህንም ቀደህ በፊቴ ስላለቀ
ስህ እግዚአብሔር ሰምቼሃለሁ ብሏል:: 20ስለ
ዚህ ወደ አባቶችህ እሰበስብሃለሁ፤ ወደ መቃ
ብር በሰላም ትወርዳለህ፤ በዚህ ቦታም የማ
መጣውን መከራ ሁሉ ዐይኖችህ አያዩም::’”
ሰዎቹም መልሱን ለንጉሡ ይዘውለት ሄዱ::

## ኢዮስያስ ኪዳኑን ዐደሰ

23፥1-3 ተጓ ምብ - 2ዜና34፥29-32
23፥4-20 ተጓ ምብ - 2ዜና34፥3-7፡33
23፥21-23 ተጓ ምብ - 2ዜና35፥1፡18-19
23፥28-30 ተጓ ምብ - 2ዜና35፥20-36፥1

23 ከዚያም ንጉሡ የይሁዳንና የኢየሩ
ሳሌምን ሽማግሌዎች ሁሉ ጠራ::
2የይሁዳን ሰዎች ሁሉ፣ የኢየሩሳሌምን ከተማ
ነዋሪዎች በሙሉ፣ ካህናቱንና ነቢያቱን
ሁሉ ከልጅ እስከ ዐዋቂ አንድም ሰው
ሳይቀር ይዞአቸው ወደ እግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ መጣ:: በእግዚአብሔር ቤተ መቅ
ደስ የተገኘውንም የኪዳኑን መጽሐፍ ቃል
በጆሮአቸው እንዲሰሙት በሙሉ አነበበላ
ቸው:: 3ንጉሡም በዐምደ ወርቁ አጠገብ
በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ እግዚአብሔርን
እንደሚከተል ትእዛዞቹን፣ ደንቦቹን፣ ሥርዐ
ቶቹን በፍጹም ልቡ፣ በፍጹምም ነፍሱ
እንደሚጠብቅ፣ በዚህም መጽሐፍ የተጻፈ
ውን ኪዳን እንደሚያጸና በእግዚአብሔር
ፊት ኪዳኑን አደሰ፤ ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ
ለኪዳኑ ያላቸውን ታማኝነት አረጋገጡ::
4ንጉሡም ለበአል፣ ለአሼራና ለሰማይ
ከዋክብት ሰራዊት ሁሉ የተሠሩትን የመገ
ልገያ ዕቃዎች በሙሉ፣ ከእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ እንዲያወጡ ሊቀ ካህናቱን ኬል
ቅያስን በሁለተኛ ማዕረግ ያሉትን ካህናትና
የቤተ መቅደሱን በር ጠባቂዎች አዘዘ:: ዕቃ
ዎቹንም ከኢየሩሳሌም ውጭ በቄድሮን ሸለቆ
ሜዳ ላይ አቃጠላቸው፤ ዐመዱንም ወደ ቤቴል
ወሰደው:: 5በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳሌም
ዙሪያ በሚገኙ ኰረብቶች ላይ ዕጣን እንዲ
ያጥኑ የይሁዳ ነገሥታት የሾሙአቸውን
የጣዖት ካህናት አባረረ እንዲሁም ለበአል፣
ለፀሓይና ለጨረቃ፣ ለስብስብ ከዋክብትና
ለመላው የሰማይ ከዋክብት ሰራዊት የሚያ
ጥኑትን አስወገደ:: 6የአሼራንም ምስል ዐምድ
ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አውጥቶ ከኢ
የሩሳሌም ውጭ ወዳለው ወደ ቄድሮን
ሸለቆ ወስዶ አቃጠለው፤ አድቅቆ ፈጭቶም
በሕዝቡ መቃብር ላይ በተነው:: 7እንዲሁም
ስለ አምልኮ ባዕድ ሥርዐት በእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ ውስጥ የቤተ ጣዖት ወንደቃዎ
ችን ክፍሎችና ሴቶች ለአሼራ መጋረጃ የሚፈ
ትሉባቸውን ክፍሎች አፈረሰ::
8ኢዮስያስ የቤተ ጣዖት ካህናትን ሁሉ
ከይሁዳ ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም አወጣቸው፤
ከጌባ ጀምሮ እስከ ቤርሳቤህ ድረስ፣ ካህናቱ

*17 ወይም፣ *በሠሩት ሥራ ሁሉ*

22፥16 ዘዳ31፥29፤ ኢያ23፥15፤ ኤር6፥19፤11፥11፤18፥11፤35፥17፤ ዳን9፥11
22፥17 1ነገ9፥9
22፥18 ኤር21፥2፤37፥3፡7
22፥19 ዘፀ10፥3፤ ዘሌ26፥31፤ ኢሳ57፥15፤61፥1፤ ኤር24፥9፤25፥18፤26፥6፤ ሚክ6፥8
22፥20 1ነገ21፥29፤ ኢሳ47፥11፤57፥1፤ ኤር18፥11
23፥2 ዘፀ24፥7፤ ዘዳ31፥11
23፥3 ዘዳ13፥4፤ 1ነገ7፥15፤ 2ነገ11፥12
23፥4 2ነገ21፥7፤25፥18፤ ኤር35፥4
23፥5 2ነገ16፥4፤ ኤር8፥2፤ ኤር43፥13
23፥6 ዘፀ32፥20፤ ዘኍ19፥16፤ ኤር26፥23፤31፥40
23፥7 ዘፍ38፥21፤ 1ነገ14፥24፤ ሕዝ16፥16
23፥8 ኢያ18፥24፤ 1ነገ15፥22

22፥16 *በዚህ ቦታና፤* ኢየሩሳሌምን ነው::

22፥19 *ልብህ ስለ ተነካ፤* ቍ 11 ይመ::

22፥20 *ወደ አባቶችህ እሰበስብሃለሁ፤* የ1ነገ 1፥21 ማብ ይመ:: *ወደ መቃብር በሰላም ትወርዳለህ፤* ኢዮስያስ ከግብፅ ንጉሥ ከፈርዖን ኒካው ጋር ሲዋጋ ቢሞትም (23፥29-30)፤ የዚህ ትንቢት ሐሳብ ኢየሩሳሌም በእግዚአብሔር ፍርድ በናቡከደነፆር ከመደምሰሷ በፊት ንጉሡ መሞቱን የሚያመለክት ትንቢት ነው:: ኢዮስያስ በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላይ የሚመጣው የመጨረሻው ፍርድ በእርሱ ዘመን እንደማይሆን ተረጋግጦለታል::

23፥1 *ሽማግሌዎች፤* የ10፥1 ማብ ይመ::

23፥2 *የኪዳኑን መጽሐፍ፤* ይህ ስያሜ ዘፀ20-23 በተመለከተ በዘፀ24፥7 ላይ ቢጠቀስም፣ እዚህ ላይ የሚያመለክተው ግን በከፊል የዘዳግም መጽሐፍን በሙሉ ወይም በከፊል ወይም የሙሴን ሕግ በሙሉ ነው:: የትኛውም ይሁን መጽሐፉ በዘሌ 26 እና በዘዳ 28 ወይም ከሁለቱ በአንዱ ያለውን ርግማን ቃል የያዘ ነው (የቍ21፤22፥8፡11ማብ ይመ)::

23፥3 *በዐምደ...፤* የ11፥14 ማብ ይመ:: *እግዚአብሔርን እንደሚከተል፤* የ1ሳሙ 12፥14፡20 ማብ ይመ:: *ኪዳኑን ዐደሰ፤* ኢዮስያስ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል የነበረውን ኅብረት የማደስ ተግባር አከናወነ፤ ከሙሴ (ዘፀ24፥3-8፤ዘዳ1፥34)፣ ከኢያሱ (ኢያ24)፣ ከሳሙኤል (1ሳሙ11፥14-12፥25) እና ከዮዳሄ (2ነገ 11፥17) ጋር ያነጻጽሩ:: *ለኪዳኑ ያላቸውን ታማኝነት አረጋገጡ፤* ሕዝቡ በአንድ ላይ ሆነው ለቃል ኪዳኑ ታማኝ መሆናቸውን በመሐላ ለማረጋገጥ የፈጸሙት ሥርዐት የነበረ ይመስላል:: ይህ በምልክት ይገለጽ (ኤር34፥18) ወይም በቃል (ዘዳ27፥11-26) አይታወቅም::

23፥4 *በር ጠባቂዎች፤* 12፥9 ይመ:: *ለበአል፣ ለአሼራ፤* የ1ነገ 14፥15 ማብ ይመ:: *ለሰማይ ከዋክብት ሰራዊት፤* የ17፥16 ማብ ይመ:: *ዐመዱንም ወደ ቤቴል ወሰደው፤* ቍ 15-16 ይመ:: ቤቴል በይሁዳና በቀድሞው የሰሜኑ ግዛት ድንበር መካከል በአሦር ቍጥጥር ሥር የምትገኝ ናት:: የአሦር መንግሥት በመውደቅ ላይ ስለ ነበር፣ ኢዮስያስ የራሱን ግዛት ወደ ሰሜን ለማስፋት ችሎ ነበር:: ዐመዱንም ሆን ብሎ ወደ ቤቴል የወሰደው (የቍ14 ማብ ይመ) በወርቅ ጥጃ አምልኮ ረክሶ የነበረውን ምድር ለተመሳሳይ አገልግሎት እንዳይውል ለማድረግ ነበር (የ1ነገ 12፥28፡30 ማብ ይመ)::

23፥5 *ኰረብቶች፤* የ18፥4 ማብ ይመ:: *የይሁዳ ነገሥታት፤* ምናሴንና አሞጽን ምናልባትም ከእነርሱ በፊት የነበረውን አካዝን የሚያመለክት ነው:: *የጣዖት ካህናት፤* ሆሴ 10፥5፤ ሶፎ 1፥4 ይመ::

23፥6 *የአሼራንም ምስል ዐምድ፤* የ1ነገ 14፥15 ማብ ይመ:: እነዚህ ምስሎች በሕዝቅያስ ተወግደው ነበር (18፥4)፤ ነገር ግን እንደ ገና በምናሴ ዘመን ተተከሉ (21፥7):: ምናሴ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር ሲመለስ እነዚህን ምስሎች አስወገደ (2ዜና33፥15 ይመ)፤ ይሁን እንጂ በአሞጽ ዳግም ተተከሉ (2ነገ21፥21፤2ዜና33፥22):: *ፈጭቶም በሕዝቡ መቃብር ላይ በተነው፤* የድኾችን መቃብር ለማርከስ ሳይሆን፣ ይህችን ጣዖተ አምላክ ለማዋረድ ነበር (ኤር 26፥23 ይመ)::

23፥7 *የቤተ ጣዖት ወንደቃዎችን፤* የ1ነገ 14፥24 ማብ ይመ::

23፥8 *የኰረብታ ማምለኪያ ስፍራዎችን አረከሰ፤* የ18፥4 ማብ ይመ:: *ከጌባ ጀምሮ እስከ ቤርሳቤህ፤* ጌባ በደቡብ መንግሥት በስተ ሰሜን ያለ ድንበር (1ነገ15፥22 ይመ) ሲሆን፣ ቤርሳቤህ ደግሞ በስተ ደቡብ ድንበር ያለ ነው (የ1ሳሙ3፥20 ማብ ይመ)::

ዕጣን ያጥኑባቸው የነበሩትን የኰረብታ
ማምለኪያ ስፍራዎችን አረከሰ:: ከከተ
ማዪቱ በር በስተግራ በኩል፣ በከተማዪቱ
ገዥ በኢያሱ በር መግቢያ አጠገብ የነበሩ
ትን የበሮቹን ማምለኪያ ስፍራዎችʾ አፈ
ረሰ:: 9የየኰረብታው ማምለኪያ ካህናት ኢየ
ሩሳሌም ባለው *በእግዚአብሔር* መሠዊያ
ላይ ባያገለግሉም እንኳ ከካህናት ወንድ
ሞቻቸው ጋር እርሾ ያልነካው ቂጣ ይበሉ
ነበር::

10በሄኖም ሸለቆ የነበረውን ቶፌት የተ
ባለውን ማምለኪያ አረከሰ፤ ይኸውም ማንም
ሰው ወንድ ወይም ሴት ልጁን ለሞሎክ
በእሳት የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ እን
ዳያቀርብበትʾ ነው:: 11የይሁዳ ነገሥታት
ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ መግቢያ
ላይ ለፀሓይ አምልኮ የሰጡአቸውን ፈረሶች
ከዚያ አስወገደ:: እነዚህም ናታን ሜሌክ
በተባለ በአንድ ሹም ቤት አጠገብ በአደባባዩ
ላይ ነበሩ:: ኢዮስያስም ለፀሐይ አምልኮ የተ
ሰጡትን ሠረገሎች አቃጠለ::

12የይሁዳ ነገሥታት በላይኛው የአካዝ
እልፍኝ አጠገብ በሰገነቱ ላይ ያቆሟቸውን
መሠዊያዎች፣ ምናሴም በሁለቱ *የእግዚ
አብሔር* ቤተ መቅደስ አደባባዮች ላይ ያሠ
ራቸውን መሠዊያዎች አስወገደ፤ ስብርብራ
ቸውን አወጣ፤ ድቃቂውንም አንሥቶ ወደ
ቄድሮን ሸለቆ ጣለው:: 13እንዲሁም ከኢየሩ
ሳሌም በስተ ምሥራቅ ከርኵሰት ኰረብታ
በስተ ደቡብ የነበሩትን የእስራኤል ንጉሥ
ሰሎሞን ለሲዶናውያን የርኵሰት አምላክ
ለአስታሮት፣ ለሞዓብ ሕዝቦች የርኵሰት
አምላክ ለካሞሽ፣ ለአሞን ሕዝቦች የርኵ
ሰት አምላክ ለሞሎክ ያሠራቸውን የኰረ
ብታ ላይ ማምለኪያዎች ንጉሡ አረከሰ::
14አሁንም ኢዮስያስ ማምለኪያ የድንጋይ
ሐውልቶችን ሰባበረ፤ የአሼራን ምስል ዐም
ዶች ቈራረጠ፤ ስፍራውንም በሙታን ዐጥ
ንት ሞላው::

15እስራኤልን ባሳተው በናባጥ ልጅ በኢ
ዮርብዓም የተሠራውን መሠዊያ፣ በቤቴል
የነበረውን ያን የኰረብታ ማምለኪያ ስፍራ፣
መሠዊያው ያለበትን ያን የኰረብታ ማምለ
ኪያ ስፍራ እንኳ እንደዚሁ አፈረሰ፤ ድንጋ
ዮቹን ሰባበረ፤ እንደ ዱቄትም አደቀቃ
ቸው፤ የአሼራንም ምስል ዐምድ አቃጠለ::
16ኢዮስያስ ዘወር ሲል በኰረብታው ላይ
የነበሩትን መቃብሮች አየ፤ ዐፅሞቹንም ከየ
መቃብሩ አስወጣ፤ ያ የእግዚአብሔር ሰው አስ
ቀድሞ እንደ ተናገረው፣ *የእግዚአብሔር*
ቃል ይፈጸም ዘንድ፣ መሠዊያውን ለማር
ከስ ሲል ዐፅሞቹን በላዩ ላይ አቃጠለበት::

17ንጉሡም፣ "ያ የማየው የመቃብር ሐው
ልት የማን ነው?" ሲል ጠየቀ

የከተማዪቱም ሰዎች፣ "ከይሁዳ መጥቶ
አሁን አንተ ያደረግኸውን ነገር ሁሉ በቤ
ቴል መሠዊያ ላይ እንደሚደርስ የተናገረ
የዚያ የእግዚአብሔር ሰው መቃብር ነው"
አሉት::

18ኢዮስያስም፣ "በሉ እንዳለ ተዉት፤ ዐፅ
ሙን ማንም ሰው ከቦታው እንዳያንቀሳቅ
ሰው" አለ፤ ስለዚህ የእርሱንና ከሰማርያ
የመጣውን ነቢይ ዐፅም ሳይነኩ እንዳለ
ተውት:: 19ኢዮስያስም በቤቴል እንዳደረ
ገው ሁሉ በሰማርያም ከተሞች ኰረብቶች
ላይ የእስራኤል ነገሥታት አሠርተዋቸው
የነበሩትንና *እግዚአብሔርን* ያስቈጡበትን
ቤተ ጣዖቶች ሁሉ አስወገደ፤ አረከሳቸ
ውም:: 20ኢዮስያስ እነዚያን የየኰረብታውን
ማምለኪያ ቦታ ካህናትን ሁሉ፣ በየመሠዊ
ያው ላይ ዐረዳቸው፤ በመሠዊያዎቹ ላይ
የሰው ዐፅም አቃጠለ፣ ከዚያም ወደ ኢየሩ
ሳሌም ተመለሰ::

ʾ8 ወይም *ከፍተኛ ቦታዎች* ʾ10 ወይም *ወንድ ወይም ሴት ልጅን የሆለ*

23፥9 ሕዝ44፥10-14
23፥10 ዘሌ18፥21፤ዘዳ18፥10፤ኢሱ15፥8፤ኢሳ30፥33፤ኤር7፥31:32፤19፥6
23፥11 ቍ 5:19፤ዘዳ4፥19፤ነህ9፥34፤ኤር44፥9
23፥12 2ሳሙ15፥23፤2ነገ21፥5፤2ዜና33፥15፤ኤር19፥13፤ሶፎ1፥5
23፥13 ዘዳ27፥15፤1ነገ11፥7፤ኤር11፥13
23፥14 ዘፀ23፥24፤ዘኍ19፥16፤መዝ53፥5
23፥15 ኢሱ7፥2፤1ነገ12፥33፤13፥13
23፥16 1ነገ13፥2:32
23፥18 1ነገ13፥29:31
23፥20 ዘፀ22፥20፤1ነገ13፥2፤2ነገ11፥18

23፥9 *ከካህናት...ጋር እርሾ ያልነካው ቂጣ ይበሉ ነበር፤* እነዚህ ካህናት በቤተ መቅደሱ መሠዊያ ላይ እንዲያገለግሉ ባይፈቀድላቸውም፣ ለካህናት የተመደበውን ድርሻ በመካፈል ራሳቸውን ይመግቡ ነበር (ዘሌ 2፥10፤6፥16-18 ይመ)፤ ይህም መብት የአካል ጉዳት ካለባቸው ካህናት መብት ጋር ይመሳሰላል (ዘሌ 21፥16-23)::

23፥10 *ቶፌት፤* በሄኖም ሸለቆ ሕጻናትን መሥዋዕት አድርገው የሚያቀርቡበት መሠዊያ ያለበት ስፍራ ነው (ኢሳ 30፥33፤ ኤር 7፥31፤19፥5-6 ይመ):: *ወንድ ወይም ሴት ልጁን ... የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ፤* 17፥17፤ 21፥6 ይመ፤ እንዲሁም የ16፥3 ማብ ይመ:: *ሞሎክ፤* የ1ነገ 11፥5 ማብ ይመ::

23፥11 *ለፀሓይ አምልኮ የተሰጡትን ሠረገሎች፤* ፈረሶቹ ካልተሠዉ የፀሓይ አምላክ ምስሎችን የሚሸከሙ ሠረገሎችን የሚጐትቱ ይሆናሉ:: በቅርብ ጊዜ ከጥንታዊቷ የኢየሩሳሌም ቅጥሮች ውጪ፣ የጣዖት አምልኮ ይፈጸምባቸው በነበረ ስፍራ ትንንሽ የፈረስ ምስሎች ተገኝተዋል:: *ናታን ሜሌክ፤* ምናልባት የሠረገሎቹ ኀላፊ ሊሆን ይችላል::

23፥12 *በሰገነቱ ላይ ያቆሙአቸውን መሠዊያዎች፤* የሰማይ ከዋክብትን ሰራዊት ለማምለክ የተዘጋጁ መሠዊያዎች ናቸው (ኤር 19፥13፤ሶፎ 1፥5 ይመ):: እነዚህ መሠዊያዎች በአካዝ (2ነገ 16፥3-4:10-16)፣ በምናሴና (21፥3) በአሞጽ (21፥21-22) የተሠሩ ናቸው::

23፥13 *ሰሎሞን ... ያሠራቸውን የኰረብታ ላይ ማምለኪያዎች፤* የ1ነገ 11፥15 ማብ ይመ::

23፥14 *ስፍራውንም በሙታን ዐጥንት ሞላው፤* ዐጥንቶቹ ስፍራውን ስለሚያረክሱ፣ ለወደፊት የማምለኪያ ስፍራ እንዳይሆን ያደርጉታል (ዘኍ 19፥16 ይመ)::

23፥15 *መሠዊያ፣ በቤቴል የነበረውን፤* 1ነገ12፥23-33 ይመ:: የሰሜኑ መንግሥት ተማርኮ ወደ አሦር በሄደ ጊዜ፣ የወርቁ ጥጃ ግብር ሆኖ ለአሦራውያን ስለ ተላከ፣ ስለ ጥጃው የተባለ ምንም ነገር የለም (ሆሴ 10፥5-6)::

23፥16 *መቃብሮች፤* ቤቴል በሚገኘው ቤተ ጣዖት የሚያገለግሉ ካህናት መቃብሮች ናቸው (1ነገ 13፥2 ይመ):: *ያ የእግ ዚአብሔር ሰው አስቀድሞ እንደ ተናገረው፤* 1ነገ 13፥1-2:32 ይመ:: *መሠዊያውን ለማርከስ ሲል ... አቃጠለበት፤* የቍ 6፥14 ማብ ይመ::

23፥18 *ከሰማርያ የመጣውን ነቢይ፤* 1ነገ 13፥31-32 ይመ:: ሰማርያ ተብሎ የተጠቀሰው በዚህ ስም የሚታወቀውን ከተማ አይደለም፤ ምክንያቱም ነቢዩ የመጣው ከቤቴል ነው (1ነገ 13፥11 ይመ)፤ በኋላ ሰማርያ ተብላ የታወቀችው ከተማም በዚህ ጊዜ አልነበረችም (1ነገ 16፥24 ይመ):: ከዚህ ይልቅ ሰማርያ የቀድሞውን የሰሜን መንግሥት በአጠቃላይ የሚያመለክት ስም ነው (የ17፥24:29፤ 1ነገ 13፥32 ማብ ይመ)::

23፥20 *የኰረብታውን ማምለኪያ ቦታ ካህናትን ሁሉ ... ዐረዳቸው፤* በቀድሞ የሰሜን መንግሥት ግዛት ላይ የጣዖት አምልኮን የሚፈጽሙ ሌዋውያን ያልሆኑ ካህናት ናቸው (የ17፥27-28:33-34 ማብ ይመ)፤ በይሁዳ እንደ ነበሩ የጣዖት አምልኮ ካህናት ተደረገባቸው (ቍ 5 ይመ)፤ በይሁዳ የኰረብታ ማምለኪያ ቦታ ካህናት ላይ ግን ኢዮስያስ እንዲህ አላደረገም (ቍ 8-9 ይመ)፤ የኢዮስያስ ድርጊት በዘዳ 13፥17፥2-7 ከተጠቀሰው ጋር ይስማማል::

21ንጉሡም መላውን ሕዝብ፣ "በዚህ በኪ
ዳኑመጽሐፍ በተጻፈው መሠረት የአምላካ
ችሁን የእግዚአብሔርን ፋሲካ አክብሩ"
ብሎ አዘዘ። 22እስራኤልን ከመሩ ከመሳፍ
ንት ዘመን ጀምሮ፣ በእስራኤልና በይሁዳ
ነገሥታት ዘመን ሁሉ፣ እንደዚህ ያለ ፋሲካ
መቼም ተከብሮ አያውቅም። 23በኢዮስያስ
ዘመነ መንግሥት በዐሥራ ስምንተኛው
ዓመት ግን ይህ ፋሲካ በኢየሩሳሌም ለእግ
ዚአብሔር ተከበረ። 24ከዚህም በቀር ኢዮ
ስያስ ሙታን አነጋጋሪዎችንና መናፍስት
ጠሪዎችን፣ የየቤተ ሰውን አማልክት፣ ጣዖ
ታትን እንዲሁም በይሁዳና በኢየሩሳሌም
የተገኙትን ሌሎች አስጸያፊ ነገሮች ሁሉ
አስወገደ፤ ይህን ያደረገውም ካህኑ ኬልቅ
ያስ ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ባገኘው
መጽሐፍ የተጻፈው የሕጉ ቃል ተፈጻ
ሚነት እንዲኖረው ለማድረግ ነው።
25በሙሴ ሕግ በተጻፈው መሠረት በፍጹም
ልቡ፣ በፍጹም ነፍሱ፣ በፍጹም ኀይሉ ወደ
እግዚአብሔር የተመለሰ፣ እንደ ኢዮስያስ
ያለ ንጉሥ፣ ከእርሱ በፊትም ሆነ ከእርሱ
በኋላ ፈጽሞ አልተነሣም። 26ይህም ሆኖ
እንኳ ለቍጣ እንዲነሣሣ ምናሴ ካደረጋ
ቸው ነገሮች ሁሉ የተነሣ፣ እግዚአብሔር
በይሁዳ ላይ ከነደደው ከአስፈሪው ቍጣው
ገና አልበረደም ነበር። 27ስለዚህ እግዚ
አብሔር፣ "እስራኤልን እንዳስወገድሁ ሁሉ
ይሁዳንም ከፊቴ አስወግዳለሁ የመረጥኋትን ከተማ
ኢየሩሳሌምንና፣ 'ስሜ በዚያ ይሆናል'[ገ]
ብዬ የተናገርሁለትን ይህን ቤተ መቅደስ
እተዋ ለሁ" አለ።

28በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት የተከናወ
ነው ሌላው ሥራ፣ የፈጸመውም ሁሉ በይ
ሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይ
ደለምን?

29ኢዮስያስ ንጉሥ በነበረበት ዘመን የግ
ብፅ ንጉሥ ፈርዖን ኒካዑ የአሦርን ንጉሥ
ለመርዳት ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ ወጥቶ
ነበር፤ ንጉሥ ኢዮስያስም ጦርነት ሊገጥመው
ወጣ፤ ሆኖም ፈርዖን ኒካዑ ፊት ለፊት ገጥ
ሞት መጊዶ ላይ ገደለው። 30የኢዮስያስም
አገልጋዮች ከመጊዶ ሬሳውን በሠረገላ ወደ
ኢየሩሳሌም አምጥተው በገዛ መቃብሩ ቀበ
ሩት። የአገሩም ሰዎች የኢዮስያስን ልጅ
ኢዮአክስን ወሰዱት፤ ቀብተውም በአባቱ
እግር አነገሡት።

## የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአክስ

23፥31-34 ተጓ ምብ - 2ዜና36፥2-4

31ኢዮአክስ ሲነግሥ ዕድሜው ሃያ ሦስት
ዓመት ነበር፤ እርሱም በኢየሩሳሌም ተቀ
ምጦ ሦስት ወር ገዛ። እናቱ አሚጣል
ትባላለች፤ እርሷም የልብና ሰው የኤርምያስ
ልጅ ነበረች። 32አባቶቹ እንዳደረጉ ሁሉ፣
እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ።
33በኢየሩሳሌም ተቀምጦ እንዳይገዛም ፈር
ዖን ኒካዑ በሐማት ምድር ሪብላ በምትባል
ቦታ በሰንሰለት አሰረው[ጠ]፤ በይሁዳም ላይ
መቶ መክሊት[ጨ] ብርና አንድ መክሊት[ጰ]

23፥21 ዘፀ12፥11፤ 24፥7፤ዘዳ16፥18
23፥23 ዘፀ12፥11፤ ዘኍ28፥16
23፥24 ዘፍ31፥19፤ ዘሌ19፥31፤ዘዳ7፥26፤ 18፥11፤2ነገ16፥3
23፥25 1ሳሙ 7፥3፤ኤር22፥15
23፥26 2ነገ21፥6፡ 12፤ኤር23፥20፤30፥24
23፥27 ዘፀ33፥15፤ 2ነገ21፥13፤24፥3፤ ኤር27፥10፤32፥31
23፥29 ቍ33-35፤ 2ነገ19፥27፤ኤር46፥2
23፥30 2ነገ9፥28
23፥31 2ነገ24፥18፤ 1ዜና3፥15፤ኤር22፥11
23፥32 1ነገ15፥26
23፥33 ዘኍ34፥11፤ 1ነገ8፥65

[ገ]27 1ነገ8፥29 ይመ። [ጠ]33 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ግን (2ዜና 36፥3 ይመ)፣ ኒካዑ በሐማት ምድር ሪብላ በምትባል ላይ አስወገደው [ጨ]33 3.4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው። [ጰ]33 34 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

23፥21 *ፋሲካ አክብሩ፤* ይህን ሥርዐት እንዴት እንዳከበሩ በ2ዜና 35፥1-19 ላይ በዝርዝር ተገልጾአል። *በኪዳኑ መጽሐፍ በተጻፈው መሠረት፤* የቍ2 ማብ ይመ። ይህ ፋሲካ በቤተ ሰብ ደረጃ የሚከበረው ሳይሆን (ዘፀ12፥1-14:43-49)፣ በቤተ መቅደስ ማኅበሩ በጋራ የሚያከብረው በዓል ነው (ዘፀ 23፥15-17፤34፥23-24፤ ዘሌ 23፥4-14 ይመ) ይህም በዘጸ 16፥1-8 ላይ ከተገለጠው ጋር ይስማማል።

23፥22፤ በኢዮስያስ ዘመን የነበረውን የፋሲካ በዓል አከባበር ልዩ የሚያደርገው፣ የፋሲካ በጎች በሙሉ በካህናቱ ብቻ መታረዳቸው ነው (2ዜና 35፥1-19ይመ፤ በሕዝቅያስ ዘመን የፋሲካ በዓል እንዴት እንደሚከበር በ2ዜና30፥2-3:17-20 ላይ ካለው ጋር ያነጻጽሩ።

23፥23 *በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት፤* የ22፥3 ማብ ይመ።

23፥24 *የየቤተ ሰውን አማልክት፤* የዘፍ 31፥19 ማብ ይመ። *የሕጉ ቃል ተፈጻሚነት እንዲኖረው፤* የቍ 2፤22፥8 ማብ ይመ።

23፥25 *በፍጹም ልቡ፣ በፍጹም ነፍሱ፣ በፍጹም ኀይሉ፤* ዘዳ 6፥5 ይመ። *እንደ ... ያለ ንጉሥ፤* የ18፥5 ማብ ይመ።

23፥26 *እግዚአብሔር ... ከነደደው ከአስፈሪ ቍጣው ገና አልበረደም፤* በኢዮስያስ አማካይነት ተሐድሶ ቢገኝም እንኳ፣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ ሊመጣ ያለው ፍርድ ይራዘም እንጂ መፈጸሙ አይቀርም (የ21፥15፤ 22፥20 ማብ ይመ)።

23፥27 *እስራኤልን እንዳስወገድሁ፤* 17፥18-23 ይመ። *የመረጥኋትን ከተማ ኢየሩሳሌምን፤* 21፥4:7:13 ይመ። *'ስሜ በዚያ ይሆናል' ብዬ የተናገርሁለትን ይህን ቤተ መቅደስ፤* የ1ነገ 8፥16 ማብ ይመ።

23፥28 *በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ፤* የ1ነገ 14፥29 ማብ ይመ።

23፥29 *የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን ኒካዑ፤* ከ610-595 ዓ.ቅ.ክ የገዛው ንጉሥ ነው። *የአሦርን ንጉሥ ለመርዳት፤* ፈርዖን ኒካዑ የመጨረሻውን ያአሦር ንጉሥ ዳግማዊ አሹር-ኡባሊትን ለመር ዳት አሰበ። ይህን ያደረገውም ዳግማዊ አሹር ኡባሊት ኀያል መሆን ከጀመረው ከባቢሎን ንጉሥ ከናቦፖላሳር ጋር በጊዜው በጦርነት ላይ ስለ ነበረ ነው። የአሦራውያን ዋና ከተማ የሆነችው ነነዌ በ612 ዓ.ቅ.ክ በባቢሎናውያንና በሜዶናውያን ቍጥጥር ሥር ወድቃ ነበር (የትንቢተ ናሆምን መጽሐፍ ይመ)። ከጦርነቱ የተረፈው የአሦር ሰራዊት በካራን እንደ ገና ተሰባስቦ ነበር፤ ይሁን እንጂ በ609 ዓ.ቅ.ክ ወደ ምዕራብ ኤፍራጥስ ለመ ሄድ ተገደው ነበር። እንግዲህ ፈርዖን ኒካዑ የአሦርን ጦር ለመር ዳት የመጣው በዚህ ጊዜ ይመስላል። *ንጉሥ ኢዮስያስም ጦርነት ሊገጥመው ወጣ፤* የሚኒካዑ ሰራዊት በመጊዶን በኩል እንዳያልፍ ኢዮስያስ የከለከለው ይመስላል (2ዜና35፥20-24 ይመ)፤ ይህን ያደረገውም የግብፅም ሆነ የአሦር ጦር፣ በዚያ እንዲያልፍ ከተፈቀደለት ውሎ አድሮ የይሁዳን ነጻነት ሊደፍር ይችላል ብሎ በማሰብ ነው።

23፥30 *በገዛ መቃብሩ ቀበሩት፤* 2ዜና35፥24-25 ይመ። *የአገሩም ሰዎች፤* የ21፥24 ማብ ይመ። *የኢዮስያስ ልጅ ኢዮአክስን፤* ኢዮአክስ አራተኛውና የመጨረሻው የኢዮስያስ ልጅ ነው፤ የኢዮአክስ የመጀመሪያ ስም ሰሎም ነበር (1ዜና3፥15፤ኤር22፥11 ይመ)፤ ስሙ ኢዮአክስ የተባለው ዙፋኑ ላይ በተቀመጠ ጊዜ ሊሆን ይችላል። ከኤልያቄም ይልቅ ኢዮአክስ በሕዝቡ ሳይወደድ አልቀ ረም፤ ምክንያቱም ኤልያቄም አባቱ ኢዮስያስና ወንድሙ ኢዮአ ክስ የሚቃወሙትን የግብፃውያንን የፖለቲካ ዐላማ የሚደግፍ ስለ ነበር። *ቀብተውም፤* የ1ሳሙ9፥16 ማብ ይመ።

23፥31 *ሦስት ወር፤* በ609 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው። *የልብና፤* የ8፥22 ማብ ይመ። *የኤርምያስ፤* ነቢዩን ኤርምያስን ማለት አይ ደለም (ኤር 1፥1 ይመ)።

23፥32 *አባቶቹ እንደ አደረጉ ሁሉ ... ክፉ አደረገ፤* 16፥3፤ 21፥2:21፤ሕዝ19፥3 ይመ።

23፥33 *ሪብላ በምትባል ቦታ በሰንሰለት አሰረው፤* ግብፃውያን በማ ታለል ወይም በኀይል አስገድደው፣ ኢዮአክስን ማርከው ለመውሰ ድና በይሁዳ ላይ ግብር ለመጣል ችለዋል (2ዜና36፥3 ይመ)። ኢዮአክስም ሪብላ በሚገኘው በኦሮንቴስ ወንዝ ባለ በኒካዑ ዋና የጦር ሰፈር ታሰረ። በኋላም ናቡከደነፆር የጦር ሰፈሩን በዚሁ ስፍራ አድርጎ ነበር (25፥6:20 ይመ)።

ወርቅ ግብር ባለበት። [34]ፈርዖን ኒካው የኢዮስያስን ልጅ ኤልያቄምን በአባቱ በኢዮስያስ እግር አነገሠው፤ ኤልያቄም የተባለ ስሙንም ኢዮአቄም ብሎ ለወጠው። ነገር ግን ኢዮአክስን በምርኮ ወደ ግብፅ ወሰደው፤ እርሱም በዚያ ሞተ። [35]ኢዮአቄምም ፈርዖን ኒካው የጠየቀውን ብርና ወርቅ ከፈለ፤ ይህን ለማድረግም የመሬት ግብር ባለ፤ የአገሩም ሰዎች እንደ ዝቢው መጠን ብሩንና ወርቁን እንዲከፍሉ አደረገ።

## ኢዮአቄም የይሁዳ ንጉሥ

23፥36-24 ተጓ ምብ - 2ዜና36፥5-8

[36]ኢዮአቄም ሲነግሥ ዕድሜው ሃያ አምስት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም *ዐሥራ* አንድ ዓመት ገዛ። እናቱ ዘቢዳ ትባላለች፤ እርሷም የሩማ ተወላጅ የፈዳያ ልጅ ነበረች። [37]ኢዮአቄም አባቶቹ እንደ አደረጉት ሁሉ፣ እርሱም *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ነገር አደረገ።

**24** በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ምድሪቱን ወረረ፤ ኢዮአቄምም ሦስት ዓመት ገበረለት፤ ከዚያ በኋላ ግን ሐሳቡን ለውጦ በናቡከደነፆር ላይ ዐመፀ። [2]*እግዚአብሔርም* በኢዮአቄም ላይ ባቢሎናውያን*፣ ሶርያውያን፣ ሞዓባውያንና አሞናውያን አደጋ ጣዮችን ላከበት፤ በአገልጋዮቹ በነቢያቱ አማካይነት በተነገረው *በእግዚአብሔር ቃል* መሠረት ይሁዳን ያጠፉ ዘንድ እነዚህን ላከ። [3]ከፊቱ ያርቃቸው ዘንድ እነዚህ ነገሮች ሁሉ *እግዚአብሔር* ባዘዘው መሠረት በይሁዳ ላይ በትክክል ሊፈጸሙ ችለዋል፤ ይህም ምናሴ ስለ ሠራው ኀጢአትና ስለ ፈጸመውም ሁሉ፣ [4]እንዲሁም ንጹሕ ደም ስላፈሰሰ ነው። ኢየሩሳሌምም በንጹሕ ደም እንድትጥለቀለቅ በማድረጉ፤ *እግዚአብሔር* ይቅርታ ለማድረግ አልፈለገም።

[5]በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት የተከናወነው ሌላው ሥራ የፈጸመውም ድርጊት ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን? [6]ኢዮአቄምም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ ልጁ ዮአኪንም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

[7]የባቢሎንም ንጉሥ ከግብፅ ደረቅ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ የነበረውን ግዛቱን ሁሉ ወስዶበት ስለ ነበር፣ የግብፅ ንጉሥ ከአገሩ ዳግም ለዘመቻ አልወጣም።

## የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን

24፥8-17 ተጓ ምብ - 2ዜና36፥9-10

[8]ዮአኪን ሲነግሥ ዕድሜው ዐሥራ ስምንት ዓመት ነበር፤ እርሱም በኢየሩሳሌም ተቀምጦ ሦስት ወር ገዛ። እናቱ ኔስታ ትባላለች፤ እርሷም የኢየሩሳሌም ሰው የኤልናታን

*2 ወይም ከለዳውያን

23፥34 2ነገ24፥6፤ 1ዜና3፥15፤2ዜና36፥5-8፤ኤር1፥3፤22፥12
23፥35 ኤር2፥16
23፥36 ኤር26፥1
23፥37 1ነገ15፥26
24፥1 ቍ10፤2ነገ18፥7፤25፥11፤ዕዝ5፥12፤ኤር4፥7፤25፥1፡9፤35፥11፤39፥1፤40፥1፤50፥17፤52፥15፤ሕዝ 32፥2፤ዳን1፥1፤7፥4
24፥2 2ነገ5፥2፤ኢሳ28፥18፡19፤ኤር5፥15፤12፥7፡9፤25፥1፤26፥1፤35፥11፤36፥1፤ሕዝ23፥23፤ዳን1፥2፤ዕን1፥6
24፥3 1ነገ14፥9፤2ነገ13፥23፤18፥25፤21፥12፤ኤር15፥4
24፥4 ዘፀ23፥21፤2ነገ21፥16፤ኤር22፥3፤ሰቆ3፥42
24፥5 ኤር22፥18-19
24፥6 1ዜና3፥16፤ኤር22፥19፡24፡28፤36፥30፤ሕዝ19፥1
24፥7 ዘፍ15፥18፤2ነገ18፥21፤ኤር1፥14፤25፥9፤46፥24፡25
24፥8 ቍ15፤1ዜና3፥16፤ኤር13፥18፤22፥24፡26፤29፥2፤37፥1

23፥34 *የኢዮስያስን ልጅ ኤልያቄምን፤* ኤልያቄም የኢዮአክስ ታላቅ ወንድም ነው (1ዜና3፥15 ይመ)። ምናልባት ቀድሞውኑ ወራሽ እንዳይሆን የተደረገው ግብፃውያንን የሚደግፍ አቋም ስለ ነበረው ሊሆን ይችላል። *ኤልያቄም የተባለ ስሙንም ኢዮአቄም ብሎ ለወጠው፤* የእነዚህ ሁለት ስሞች ትርጕም አንድ ነው። "ኤልያቄም" ማለት፣ "እግዚአብሔር መሠረተው" ማለት ሲሆን፣ "ኢዮአቄም" ማለት ደግሞ፣ "ያህዌ መሠረተው" ማለት ነው። ምናልባት ፈርዖን ኒካው፣ "ኢዮአቄም" የሚለውን ስም የመረጠው፣ የፈጸመውን ድርጊት የይሁዳ አምላክ፣ "ያህዌ" እንዳጸደቀለት ለማመልከት ሊሆን ይችላል (18፥25፤ 2ዜና 35፥21 ይመ)። ያም ሆነ ይህ፣ የስሙ ለውጥ ኢዮአቄም ከፈርዖን ኒካው ሥልጣን ስር እንደሆነ ያመለክታል። *ኢዮአክስን ... ወደ ግብፅ ወሰደው፤ እርሱም በዚያ ሞተ፤* 2ዜና36፥4፤ ኤር 22፥10-12 ይመ።

23፥35 *የአገሩም ሰዎች፤* የኢዮአክስን ንጉሥ መሆን (ቍ30 ይመ) በሚደግፈው ሕዝብ ላይ የተመደበው ቀረጥ፣ ለፈርዖን ኒካው የሚሰጠውን ግብር ከፍ አድርጎት ነበር። የሰሜኑ መንግሥት ንጉሥም ናሔም ይህንኑ ዓይነት ስልት ተጠቅሞ ለግብር የሚሰጠውን ስጦታ አሳድጎት ነበር (15፥20 ይመ)።

23፥36 *ዐሥራ አንድ ዓመት፤* ከ609-598 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው።

23፥37 *በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረገ፤* ኢዮአቄም የቂርያትይዓሪም አገር ሰው የነበረውን ነቢዩ ኦርዮንን በማስገደሉ ተጠያቂ ነው (ኤር26፥20-24)፤ አገዛዙም ፍትሕ የተጓደለበት፣ ጭቈና የበዛበትና ታማኝነት የሌለበት ነበር (ኤር 22፥13-19 ይመ)። በተጨማሪም በቤተ መቅደስ ውስጥ የጣዖት አምልኮን ዳግም ያስጀመረ (ሕዝ8፥1 ይመ)፣ በነቢዩ በኤርምያስ በኩል የመጣውን የእግዚአብሔርን ቃል የተቃወመ ሰው ነበር (ኤር36)። *አባቶቹ፤* ምናሴና (21፥1-18) አሞጽ (21፥19-26)።

24፥1 *ናቡከደነፆር፤* ማለት "አቤቱ (አምላኬ) ናቡ ሆይ፤ ልጄን ጠብቅ" ማለት ነው። የናቡፖላሳር ልጅ ሲሆን፣ (የ23፥29 ማብ ይመ)፣ ከ605-562 ዓ.ቅ.ክ የነገሠ (ዳን 1-4 ይመ) የአዲሲቱ ባቢሎን መንግሥት (612-539 ዓ.ቅ.ክ) እጅግ ኀያል ንጉሥ ነበር። *ምድሪቱን ወረረ፤* ከዓ.ቅ.ክ በ605 ዓመት፣ ናቡከደነፆር አልጋ ወራሽና የባቢሎን ሰራዊት ጠቅላይ አዛዥ በመሆን፣ ፈርዖን ኒካውንና የግብፅን ሰራዊት በካርከሚሽ ጦርነት በኋላም በሐማት ጦርነት አሸነፋቸው (23፥29፤ ኤር46፥2 ይመ)። እነዚህ ድሎች በምሥራቅ ሜድትራኒያን ባሕር ባሉ አገሮች መልክአ ምድራዊ የፖለቲካ መዋቅር ላይ ሥር የሰደደ ተጽዕኖ አድርገዋል። ከዚህ በኋላ ናቡከደነፆር "የሐቲ- አገር" የተባሉትን በሙሉ፣ እንደ ባቢሎናውያን የታሪክ ሰነድ አገላለጽም፣ "የይሁዳን ከተማ" ጨምሮ ሊይዝ ወጣ። ከይሁዳ ወደ ባቢሎን ከተጋዙት መሐል ነቢዩ ዳንኤልም ነበር (ዳን 1፥1)፤ ምናልባት በመስከረም 6፣ 605 ዓ.ቅ.ክ አባቱ እንዳረፈ ዙፋኑን ሳይወርስ አልቀረም። *ሦስት ዓመት፤* ምናልባት ከ604-602 ዓ.ቅ.ክ ሊሆን ይችላል። በ604 ዓመት ናቡከደነፆር ፊቱን ወደ ምዕራብ ዘወር በማድረግ "ከሐቲ - ምድር ነገሥታት ሁሉ" ግብር ይቀበል ነበር፤ ኢዮአቄምም ከነዚሁ ነገሥታት አንዱ ሳይሆን አይቀርም። *ሐሳቡን ለውጦ ... ዐመፀ፤* በ601 ዓ.ቅ.ክ ናቡከደነፆር እንደ ገና ወደ ምዕራብ ተመልሶ በግብፅ ላይ ዘመተ፤ ነገር ግን በዚህ ጊዜ የግብፃውያን ተቃውሞ ብርቱ ነበር። ምንም እንኳ ኤርምያስ ስለ ሁኔታው ቢያስጠነቅቀውም (ኤር27፥9-11፣ ይህ ሁኔታ ኢዮአቄም እንዲያምፅ አበረታታው።

24፥2 *ባቢሎናውያን፣ ሶርያውያን፣ ሞዓባውያን፣ አሞናውያን አደጋ ጣዮችን ላከበት፤* በኢዮአቄም ዐመፅ ምክንያት የመጣው ጥፋት እጅግ ፈጣን ነበር። በሶርያ የሠፈሩ የባቢሎን ወታደሮች ከሌሎች ታዛዥ ወታደሮች ጋር በመሆን የይሁዳን ዐመፅ ለማምከን ተልከው ነበር።

24፥3 *ምናሴ ስለ ሠራው ኀጢአት፤* 21፥11-12፤ 23፥26-27፤ ኤር 15፥3-4 ይመ።


24፥4 *ንጹሕ ደም፤* የ21፥16 ማብ ይመ። *ይቅርታ ለማድረግ አልፈለገም፤* 22፥17 ይመ።

24፥5 *በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ፤* የ1ነገ14፥29 ማብ ይመ።

24፥6 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ* የ1ነገ 1፥21 ማብ ይመ። ኢየሩሳሌም በባቢሎን ከመያዟ በፊት ትንሽ ቀደም ብሎ ኢዮአቄም ሞተ (ቍ8-12 ይመ)። አሟሟቱ በሕመም ይሁን ወይም በፖለቲካ ተንኰል አይታወቅም።

24፥7 *የግብፅ ንጉሥ ከአገሩ ዳግም ለዘመቻ አልወጣም፤* ይህ የሆነው በ605 ዓ.ቅ.ክ ግብፅ በካርከሚሽ ስለ ተሸነፈች ነበር (ኤር 46፥2 ይመ)፤ ይህም ኢዮአቄም በባቢሎን ላይ ባመፀ ጊዜ ከግብፅ ድጋፍ ያላገኘው ለምን እንደ ሆነ ያመለክታል። *ከግብፅ ደረቅ ወንዝ፤* የ1ነገ8፥65 ማብ ይመ።


24፥8 *ሦስት ወር፤* በዓ.ቅ.ክ ከ598-597 ዓመት የነበሩ የባቢሎናውያን ጽሑፎች፣ ኢየሩሳሌም መጋቢት 16 በ597 ዓ.ቅ.ክ በናቡከደነፆር እንደ ተያዘች ይናገራሉ። ይህ ደግሞ፣ ዮአኪን ሦስት ወር ከዐሥር ቀን የገዛበት ጊዜ (2ዜና 36፥9-10)፣ በታኅሣሥ 598 ዓ.ቅ.ክ መጀመሩን ያመለክታል።


ናቡከደነፆር በይሁዳ ላይ ያደረገው ዘመቻ
605-586 ዓ.ቅ.ክ
በይሁዳ ያለው ሁኔታ ከኢዮስያስ መሞት በፊት በፍጥነት እየተለወጠ ሄደ:: ፈርዖን ኒካው አጋጣሚውን በመጠቀም አዲሱን ገዥ በማፍለስ የኢዮስያስን ልጅ ኢዮአቄምን ንጉሥ አድርጎ ሾመ::
በ546 ዓ.ቅ.ክ የሊዲያ በፋርስ መያዝ ግሪክን ከፋርስ ጋር እንድትጋጭ ምክንያት ሆነ:: የዚህ ዝርዝር ዘገባ በሄሮድስ ተጽፎአል::
ታላቁ ባሕር
ነቢዩ ኤርምያስ ከይሁዳ ወደ ግብጽ የሄዱት ስደተኞች በባቢሎን ከተያዙት ግዛቶች ሲኮበልሉ ተይዞ ሄደ:: የነቢይነት አገልግሎቱን በጣፍናስ ማከናወን ቀጠለ::
ካራን
ቲፍሳ
ሐማት
ሪብላ
ሲዶና
ጢሮስ
ይሁዳ
አሞን
ቄዳር
ኢየሩሳሌም
ጣፍናስ
ሚግዶል
ኤዶም
ሜምፎስ
ግብጽ
የኢየሩሳሌም መያዝ 597 ዓ.ቅ.ክ
ዋነኛ የባቢሎን ሠራዊት የተጓዘበት
ምርኮኞች የፈለሱበት
በባቢሎን የተደረገ ወረራ
602 ዓ.ቅ.ክ
ታላቁ ባሕር
የገሊላ ባሕር
ሜጊዶ
ሰማርያ
ሴኬም
ሴሎ
ምጽጳ
ጊብዖን
ራማ
ኢየሩሳሌም
ዓዜቃ
ላኪሶ
ኬብሮን
ሙት ባሕር
ማይልስ
ኪ.ሜ

ከዚያም በሰሜኑ በኩል ጠንካራ ኀይል ያለውና የአሦራውያንን የጭካኔ መመሪያ ለመከተል የወሰነ የከለዳውያን ንጉሥ ናቡከደነፆር ተነሣ።

የናቡከደነፆርን መምጣት ሲሰማ ኢዮአቄም በሩቁ ግብሩን ይከፍል ነበር። እንደ ባቢሎን መንግሥት ተወካይ ለሦስት ዓመት ከቆየ በኋላ ከባቢሎን፣ ከአራም፣ ከሞአብና ከአሞን ከተውጣጡ ጥቂት ሽፍቶች ጋር በመሆን ዐመፀ (602 ዓ.ቅ.ክ)። በመጨረሻም የናቡከደነፆር ሠራዊት የግብፅን ሰሜናዊ ረግረግ ስፍራን ጨምሮ የባሕር ዳርቻውን በሙሉ ተቆጣጠረ።

የ18 ዓመት ዕድሜ ያለው ኢዮአኪን ለሦስት ወራት ብቻ እንደ ነገሠ (597 ዓ.ቅ.ክ) የባቢሎን ሠራዊት ኢየሩሳሌምን ያዘ፤ ንጉሡንም ምርኮኛ አድርጎ ወደ ባቢሎን ወሰደ። ዐሥር ሺህ ሰዎችንም አፈለሰ።



ልጅ ነበረች:: 9አባቱ እንዳደረገው ሁሉ
እርሱም *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ አደረገ::
10በዚያን ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ የናቡከደ
ነፆር ጦር አለቆች ወደ ኢየሩሳሌም መጥ
ተው ከበቧት፤ 11የጦር አለቆቹ ከበባ በሚያ
ደርጉበትም ሰዓት ናቡከደነፆር ራሱ ወደ
ከተማዪቱ መጣ:: 12የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን፣
እናቱ፣ የክብር አጃቢዎቹ፣ መሳፍንቱና ሹማ
ምንቱ ሁሉ እጃቸውን ለባቢሎን ንጉሥ
ሰጡ:: የባቢሎን ንጉሥ በነገሠ በስምንተ
ኛው ዓመት ዮአኪንን ማርኮ ወሰደው::
13*እግዚአብሔር* አስቀድሞ እንደ ተናገረው፣
ናቡከደነፆር *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስና
የቤተ መንግሥቱን ሀብት በሙሉ አጋዘ፤
የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን *ለእግዚአብሔር*
ቤተ መቅደስ ያሠራቸውንም የወርቅ ዕቃዎች
ሁሉ ወሰደ:: 14ደግሞም የኢየሩሳሌምን ሕዝብ
እንዳለ የጦር አለቆቹንና ተዋጊዎቹን በሙሉ፣
የእጅ ባለሙያዎችንና ቀጥቃጮችን ሁሉ
ጨምሮ ባጠቃላይ ዐሥር ሺህ ሰው በምርኮ
ወደ አገሩ ወሰደ:: በዚያ የቀሩት የመጨረ
ሻዎቹ ያገሪቱ ድኾች ብቻ ነበሩ::
15ናቡከደነፆር ዮአኪንን ማርኮ ወደ ባቢ
ሎን ወሰደው እንዲሁም የንጉሡን እናት፣
ሚስቶቹን፣ ሹማምንቱንና በአገር የታወቁ
ትን ታላላቅ ሰዎችም ከኢየሩሳሌም ወደ
ባቢሎን ወሰደ:: 16ደግሞም የባቢሎን ንጉሥ
በአጠቃላይ ብርቱ የሆኑትንና ለጦርነት
ብቃት ያላቸውን ሰባት ሺህ ተዋጊዎች
አንድ ሺህ የእጅ ባለሙያዎችንና ቀጥቃጮ
ችን በምርኮ ወደ ባቢሎን ወሰደ:: 17ከዚ
ያም የዮአኪንን አጎት ማታንያን በምትኩ

24፥9 1ነገ15፥26፤
24፥10 ቍ11፤
24፥12 2ነገ 25፥27፤ ኤር13፥18፤22፥24-30፤24፥1፤ 29፥2፤
24፥13 1ነገ7፥51፤ 2ነገ20፥17፤25፥14፤15፤ ዕዝ 1፥7፤ኢሳ39፥6፤ 42፥22፤ኤር15፥13፤17፥3፤ 20፥5፤27፥16፤ 28፥3፤ሕዝ7፥21፤ዳን 1፥2፤5፥2፤23፤ሰቆ1፥13
24፥14 ዘዳ15፥11፤ 28፥36፤2ነገ25፥12፤2ዜና36፥20፤ኢዮ5፥16፤ መዝ9፥18፤ኢሳ3፥13፤ ኤር40፥7፤52፥16፤ ማቴ1፥11
24፥15 ቍ8፤1ነገ 2፥19፤2ነገ20፥18፤አስ 2፥6፤ኢሳ39፥7፤ሰቆ2፥ 9፤ሕዝ1፥2፤17፥12-14፤ 19፥9፤ ዳን1፥3
24፥16 ዕዝ 2፥1፤ኤር24፥1
24፥17 1ዜና3፥15፤ 2ዜና36፥11፤ኤር1፥3፤ 37፥1፤52፥1፤ሕዝ 17፥13
24፥18 2ነገ23፥31፤ 1ዜና3፥16፤ኤር39፥1
24፥19 1ነገ15፥26፤ ኤር37፥2
24፥20 ዘፀ33፥15፤ ዘዳ4፥26፤29፥27፤2ነገ 13፥23
25፥1 ኢሳ23፥13፤ 29፥3፤ኤር4፥16-17፤ 21፥2፤32፥1፡2፤33፥4፤ 34፥1-7፤ሕዝ21፥22፤ 24፥2
25፥3 ዘሌ26፥26፤ ኢሳ22፥2፤ኤር14፥18፤ 37፥21፤ሰቆ2፥20፤4፥9

አነገሠው፤ ስሙንም ሴዴቅያስ አለው::

## የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ

24፥18-20 ተጓ ምብ - 2ዜና36፥11-16፤ኤር52፥1-3

18ሴዴቅያስ ሲነግሥ ዕድሜው ሃያ አንድ
ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ዐሥራ
አንድ ዓመት ገዛ:: እናቱ አሚጣል ትባላለች፤
እርሷም የልብና ሰው የኤርምያስ ልጅ
ነበረች:: 19ኢዮአቄም እንዳደረገው ሁሉ፣ እር
ሱም *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ነገር አደ
ረገ:: 20እንግዲህ ይህ ሁሉ በኢየሩሳሌምና
በይሁዳ ላይ ሊደርስ የቻለው *ከእግዚአብሔር*
ቍጣ የተነሣ ነበር፤ በመጨረሻም ከፊቱ አራ
ቃቸው::

## የኢየሩሳሌም መውደቅ

25፥1-12 ተጓ ምብ - ኤር39፥1-10
25፥1-21 ተጓ ምብ - 2ዜና36፥17-20፤ኤር52፥27
25፥22-26 ተጓ ምብ - ኤር40፥7- 9፤41፥1-3፤16-18

በዚህ ጊዜ ሴዴቅያስ በባቢሎን ንጉሥ
ላይ ዐመፀ::

**25** በይሁዳ ንጉሥ በሴዴቅያስ ዘመነ
መንግሥት በዘጠነኛው ዓመት በዐ
ሥረኛው ወር፣ ከወሩም በዐሥረኛው ቀን
የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር መላ ሰራዊቱን
ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ዘመተ፤ ከከተማዪቱ
ቅጥር ውጭ ሰፈረ፤ ዙሪያውንም በሙሉ በዕ
ርድ ከበባት:: 2ከተማዪቱም እስከ ሴዴቅያስ
ዘመነ መንግሥት ዐሥራ አንደኛ ዓመት
ድረስ እንዲሁ እንደ ተከበበች ቈየች:: 3በአ
ራተኛው[o] ወር በዘጠነኛው ቀን በከተማዪቱ
ውስጥ የተከሠተው ራብ ጽንቶ ስለነበር ሕዝቡ
የሚቀምሰው አጣ:: 4ምንም እንኳ ባቢሎና

[o]3 ኤር52፥6 ይመ::

24፥9 *አባቱ እንዳደረገው ሁሉ፤* 23፥37፤ ኤር22፥20-30 ይመ::

24፥11 *ራሱ ናቡከደነፆር ወደ ከተማዪቱ መጣ፤* የባቢሎናውያን የታሪክ ሰነዶች፣ ናቡከደነፆር "የይሁዳን ከተማ ከከበበ በኋላ፣ በአዳር ወር በሁለተኛው ቀን (መጋቢት 16 597 ዓ.ቅ.ክ) ከተማዪቱን ይዞ፣ ንጉሡንም ማረከ" ይላሉ::

24፥12 *በስምንተኛው ዓመት፤* በሚያዝያ ወር በ597 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው (2ዜና 36፥10፤ እንዲሁም የተለየ የቀን አቈጣጠር የታየበትን የኤር 52፥28 ማብ ይመ)::

24፥13 *እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደ ተናገረው፤* 20፥13፡ 17 ይመ::

24፥14 *ዐሥር ሺህ፤* ይህ አኀዝ በቍ 16 ላይ የተጠቀሱትን ሰባት ሺህ ተዋጊዎችና አንድ ሺህ የእጅ ባለሙያዎችን ይጨምራል (የተለየ የምርኮኞች የተጠቀሰበትን የኤር 52፥28 ማብ ይመ)::

24፥15 *ዮአኪንን ማርኮ ወደ ባቢሎን ወሰደው፤* የኤርምያስ ትንቢት ፍጻሜ ነው (ኤር 22፥24-27፤ 2ነገ 25፥27-30 ይመ)::

24፥17 *የዮአኪንን አጎት ማታንያን፤* ማታንያ የኢዮስያስ ልጅ (1ዜና 3፥15፤ ኤር1፥3)፣ የዮአኪን አባት፣ የኢዮአቄም ወንድም ነው:: *ስሙንም ሴዴቅያስ አለው፤* "የያህዌ ስጦታ" የሚል ትርጕም ያለው የማታንያ ስም፣ "የያህዌ ጽድቅ" የሚል ትርጕም ወዳለው፣ ሴዴቅያስ" ወደሚለው ስም ተለውጦ ነበር:: ምናልባትም ናቡከደነፆር ይህን ያደረገው፣ እርሱ በኢየሩሳሌምና በዮአኪን ላይ ያደረገው ትክክል መሆኑን ለመግለጽ ፈልጎ ይሆናል:: ያም ሆነ ይህ፣ የስም ለውጡ ለናቡከደነፆር መገዛታቸውን ያመለክታል (የ23፥34 ማብ ይመ)::

24፥18 *ዐሥራ አንድ ዓመት፤* ከ597-586 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው:: *ኤርምያስ፤* የ23፥31 ማብ ይመ:: *ልብና፤* የ8፥22 ማብ ይመ::

24፥19 *ኢዮአቄም እንዳደረገው ... ክፉ ነገር አደረገ፤* የ23፥37 ማብ ይመ:: በሴዴቅያስ ዘመነ መንግሥት ጣዖት አምልኮ በኢየሩሳሌም እጅግ እየበዛ ወጥቶ ነበር (2ዜና 36፥14፤ ሕዝ 8፥11 ይመ):: በኤርምያስ በኩል የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ ያልታዘዘ (2ዜና 36፥12) እንዲሁም ደካማና ውሳኔ መስጠት የማይችል ገዥ ነበር (ኤር 38፥5፡19 ይመ)::

24፥20 *ሴዴቅያስ ... ዐመፀ፤* ብዙ ምሁራን የሴዴቅያስን ዐመፅ፣ በ589 ዓ.ቅ.ክ ዙፋን ላይ ከወጣው ባለ ብርቱ ፍላጎት ከሆነው ከፈርዖን አፍሪ ጋር ያያይዙታል:: ሴዴቅያስ ታማኝነቱን ለናቡከደነፆር በመሐላ ገልጾ ነበር (ሕዝ 17፥13)፤ ስለዚህም መልእክተኞችን ወደ ባቢሎን ልኮአል (ኤር 51፥59 ይመ)፤ ራሱም ባቢሎንን ጐብኝቶአል (ኤር 20፥3 ይመ)፤ ይሁን እንጂ ከባቢሎን አገዛዝ ነጻ ለመውጣት ሲል አሳዛኝ በሆነና ብልሃት በጎደለው ግምት ተነሣሥቶ ጸረ ባቢሎናውያን በሆነው ኀሮፓጋንዳና በኢየሩሳሌም በሚኖሩ አፍቃሬ ግብፃውያን ኀሮፓጋንዳ ተገፋፍቶ መንገዱን የሳተ ይመስላል (ኤር 37፥5፤ ሕዝ 17፥15-16 ይመ)::

25፥1 *በዘጠነኛው ዓመት፣ በዐሥረኛው ወር፣ ከወሩም በዐሥረኛው ቀን፤* ጥር 15 588 ዓ.ቅ.ክ ነው (ኤር39፥1፤ 52፥4፤ ሕዝ 24፥1-2 ይመ):: *ናቡከደነፆር ...ወደ ኢየሩሳሌም ዘመተ፤* ቀደም ብሎ ናቡከደነፆር ከለኪሶና ከአዜቃ በቀር (ኤር 34፥7 ይመ) በይሁዳ ያሉትን የተመሸጉ ከተሞች በሙሉ ተቈጣጥሮ ነበር:: እ.ኤ.አ በ1935 እና በ1938 በለኪሶ የዕብራይስጥ ጽሑፍ የተቀረጸባቸው ብዙ የሸክላ እቃ ስብርባሪዎች ተገኝተዋል:: እነዚህ በለኪሶ የተገኙ ጽሑፎች፣ ባቢሎናውያን ለኪሶንና አዜቃን ከበው በያዙ ጊዜ የነበረውን ሁኔታ ይገልጻሉ::

25፥2-3 *ዐሥራ አንደኛው ዓመት ... በአራተኛው ወር በዘጠነኛው ቀን፤* ሐምሌ 18 በ586 ዓ.ቅ.ክ ነው (ኤር39፥2፤52፥5-7 ይመ):: አንዳንድ ምሁራን ለየት ያለ የጊዜ አቈጣጠር በመከተል፣ ኢየሩሳሌም በ587 ዓ.ቅ.ክ በበጋው ወራት ተያዘች ይላሉ::

25፥3 *በከተማዪቱ ውስጥ የተከሠተው ራብ ጽንቶ ስለነበር፤* ኤር 38፥2-9 ይመ::

ውያን[a] ከተማዪቱን እንደ ከበቧት ቢሆንም
የከተማዪቱ ቅጥር ተጣሰ፤ ሰራዊቱም ሁሉ
በንጉሡ አትክልት አጠገብ ባሉት በሁለቱ
ቅጥሮች መካከል በሚገኘው በር አልፎ በሌ
ሊት ሸሸ፤ ሸሽቱም ወደ ዮርዳኖስ ሸለቆ[b]
ነበር:: 5ይሁን እንጂ የባቢሎን[c] ሰራዊት
ንጉሡን ተከታትሎ በኢያሪኮ ሜዳ ላይ
ደረሰበት:: ወታደሮቹ ሁሉ ተለይተውት
ተበታትነው ነበር:: 6እርሱም ተያዘ፤ በዚያን
ጊዜ ሪብላ ወደ ነበረው ወደ ባቢሎን ንጉሥ
አመጡት፤ ቅጣትም ተፈረደበት:: 7ሴዴቅ
ያስ ዐይኑ እያየም የገዛ ልጆቹን ገደሉበት፤
ከዚያም ሁለት ዐይኖቹን በማውጣት በናስ
ሰንሰለት አስረው ወደ ባቢሎን ወሰዱት::
8የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር በነገሠ በዐ
ሥራ ዘጠነኛው ዓመት፣ በአምስተኛው ወር
ከወሩም በሰባተኛው ቀን የክብር ዘቡ ሰራ
ዊት አዛዥና የባቢሎን ንጉሥ ከፍተኛ ባለ
ሥልጣን የሆነው ናቡዛረዳን ወደ ኢየሩሳ
ሌም መጣ:: 9*የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ፣
ቤተ መንግሥቱንና በኢየሩሳሌም የሚገኙ
ትን ቤቶች ሁሉ አቃጠለ፤ እያንዳንዱንም
ታላላቅ ሕንጻ ለእሳት ዳረገው:: 10በክብር
ዘቡ አዛዥ የተመራው መላው የባቢሎን ሰራ
ዊትም በኢየሩሳሌም ዙሪያ የነበረውን ቅጥር
አፈረሰው:: 11የክብር ዘቡ አዛዥም በከተ
ማዪቱ ቀርቶ የነበረውን፣ ከድቶም በዚያ
የተገኘውን ሰው ሁሉ ወደ ባቢሎን ንጉሥ
የገባውን ጭምር በምርኮ ወደ ባቢሎን ወሰ
ደው:: 12ሆኖም አዛዡ ከአገሬው ሰዎች
ምንም የሌላቸውን ድኾች ወይን እንዲ
ተክሉ፣ ዕርሻም እንዲያርሱ እዚያው ተዋ
ቸው:: 13ባቢሎናውያን የናስ ዐምዶቹን፣
በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበሩትን ተንቀሳቃሽ
የዕቃ ማስቀመጫዎችንና ከናስ የተሠራውን
የውሃ ማጠራቀሚያ ክብ በርሜል ሰባብረው
ናሱን ወደ ባቢሎን ወሰዱ:: 14እንዲሁም
ምንቸቶቹን፣ መጫሪያዎቹን፣ መኰስተሪያ
ዎቹን፣ ጭልፋዎቹን፣ ባጠቃላይም ከናስ የተ
ሠሩትን የቤተ መቅደሱን መገልገያ ዕቃዎች

25፥4 ኢዮ30፥14፤ መዝ144፥14፤ኤር4፥17፤6፥3፤50፥15፤51፥44:58፤ሕዝ 33፥21
25፥5 ዘሌ26፥36፤ ሕዝ 12፥14፤ 17፥21
25፥6 ዘኍ34፥11፤ ኢሳ22፥3፤ኤር38፥23
25፥7 ዘዳ28፥36፤ ኤር21፥7፤32፥45፤ 34፥3:21፤ሕዝ 12፥11፤19፥9፤40፥1
25፥9 ዘዳ13፥16፤ ነህ1፥3፤መዝ74፥38፤ 79፥1፤ኢሳ ነህ1፥3፤ 60፥7፤63፥15:18፤ 64፥11፤ኤር2፥15፤ 17፥27፤21፥10፤26፥6፡ 18፤ሰቆ4፥11፤አሞ 2፥5፤ሚክ3፥12
25፥10 ኤር50፥15
25፥11 ዘሌ26፥44፤ ዘዳ28፥36፤2ነገ24፥1
25፥12 2ነገ24፥14
25፥13 1ነገ7፥50
25፥14 ዘኍ7፥14፤ 2ነገ24፥13፤ዕዝ1፥7

[a]4 በዚህና በቍጥር 13:25 እንዲሁም 26 ላይ፣ *ከለዳውያን*
[b]4 ወይም፣ *በዓረባ* [c]5 በዚህም ሆነ በቍጥር 10 እና 24 ላይ፣ ከለዳውያን

25፥6 *ሪብላ ወደ ነበረው ወደ ባቢሎን ንጉሥ፤* የ23፥33 ማብ ይመ፤ እንዲሁም ኤር 39፥5፤52፥9 ይመ::


25፥7 *ሴዴቅያስም ... የገዛ ልጆቹን ገደሉበት ... ዐይኖቹን በማውጣት ... ወደ ባቢሎን ወሰዱት፤* ኤር 32፥4-5፤34፥2-3፤ 38፥18፤ 39፥6-7፤52፥10-11 ይመ:: ነቢዩ ሕዝቅኤል ሴዴቅያስ ወደ ባቢሎን እንደሚወሰድ ነገር ግን እንደማያያት ትንቢት ተናግሮ ነበር (ሕዝ 12፥13)፡ ኤርምያስ የተናገረውን ቃል ሰምቶ ቢሆን ኖሮ፣ ሴዴቅያስ ሕይ ወቱን ባዳነ፣ ኢየሩሳሌምንም ባተረፈ ነበር (ኤር 38፥14-28 ይመ)::

25፥8 *በዐሥራ ዘጠነኛው ዓመት፣ በአምስተኛው ወር ከወሩም በሰባተኛው ቀን፤* ነሐሴ 14 ቀን 586 ዓ..ቅ.ክ ማለት ነው (ኤር 52፥12 ይመ)::

25፥9 *የእግዚአብሔን ቤተ መቅደስ ... አቃጠለ፤* 2ዜና36፥19፤ ኤር39፥8፤ 52፥13 ይመ::

25፥13 *የናስ ዐምዶቹን፤* 1ነገ 7፥15-22 ይመ:: *ተንቀሳቃሽ የዕቃ ማስቀመጫዎችንና፤* 1ነገ 7፥27-39 ይመ:: *ከናስ የተሠራውን የውሃ ማጠራቀሚያ ክብ በርሜል፤* 1ነገ 7፥23-26 ይመ::

25፥14 *ከናስ የተሠሩትን የቤተ መቅደሱን መገልገያ ዕቃዎች ሁሉ፤* 1ነገ 7፥40:45 ይመ::




## የደቡቡ መንግሥት በምርኮ መሄድ

ከእስራኤልና ከይሁዳ ተማርከው ስለተወሰዱት ሰዎች ዕጣ ፈንታ፣ ሰማርያ በተያዘችበትና በኋላም ኢየሩሳሌም በፈረሰችበት ዘመን እጅግም አይታወቅም ነበር::

አሦራውያን ባቢሎናውያንን በምርኮ የሚይዟቸውን ሕዝቦች የሚያስተዳድሩት ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ነው፤ የሥነ ልቡና ፍርሃት ለማሳደር ከፍተኛ ቍጥር ያለው ሰራዊት ማሰለፍና ከዚህ ጋር ብዙዎችን ማፍ ለስ እንዲሁም ከባድ ግብር መጫን::

በኤር 52:28-30 ሦስት የሕዝብ ማፍለሶች ተጠቅሰዋል፤ ከፍተኛውን ቍጥር የያዘው 3023 አይሁዶች ከንጉሥ ኢዮአኪን ጋር በ597 ዓ.ቅ.ክ ወደ ባቢሎን የተወሰዱት ናቸው::

ኢየሩሳሌም በባቢሎን የሰራዊት አለቃ በናቡዛርዳን ከወደመች በኋላ ከሴዴቅያስ ልጆች በተጨማሪ 61 ሰዎች ተገደሉበት ወደ ሪብላ በመቶ የሚቈጠሩ ምርኮኞች ተወሰዱ::

ዮአኪንና ቤተ ሰቡ በባቢሎን ቆዩ:: በዚያም ስሙ የተ ጻፈበት (የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ የሚያረጋግጥ) ሸክላ በሥነ ጥንት ተመራማሪዎች ተገኝቶአል::

ሕዝ 1:1-3 እና 3:15 እንደሚያመለክቱት ሌሎች ምርኮኞች በቴል አቢብና በኮበር ወንዝ አካባቢ እንዲ ቀመጡ ተደረገ:: በዕዝ 2:59፥8:15:17፤ በነህ 7:61 ላይ እንደተጠቀሱት ሌሎች መንደሮች ከላይ የተጠቀ ሱትም ምናልባት በኒፋር አካባቢ ሰፍረው ይሆናል::

ሁሉ ወሰዱ:: 15የክብር ዘቡ አዛዥም ከን
ጹሕ ወርቅና ብር የተሠሩትን ጽናዎችና
የመርጫ ወጭቶችን ወሰደ::
16ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
መገልገያ ብሎ ከናስ ያሠራቸው ሁለት ዐም
ዶች፣ የውሃ ማጠራቀሚያው ኩብ በርሜልና
ተንቀሳቃሽ የዕቃ ማስቀመጫዎቹ ክብደታ
ቸው ከሚዛን በላይ ነበር:: 17እያንዳንዱ ዐምድ
ዐሥራ ስምንት ክንድ[ዶ] ሲሆን፣ የናስ ጒልላት
ነበረው፤ የጒልላቱ ርዝመት ሦስት ክንድ[ጆ] ሆኖ፣
ዙሪያውን በሙሉ የናስ መርበብና የሮማን
ፍሬዎች ቅርጽ ነበረው፤ ሌላውም ዐምድ
ከነቅርጾቹ ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ነበር::
18የክብር ዘብ አዛዡም ሊቀ ካህኑን ሠራ
ያን፣ በማዕረግ ከእርሱ ቀጥሎ ያለውን
ካህኑን ሶፎንያስንና ሦስቱን የበር ጠባቂዎች
እስረኛ አድርጎ ወሰዳቸው:: 19እስከዚያች ጊዜ
ድረስ በከተማዪቱ ውስጥ ከቀሩትም የተዋ
ጊዎቹን አለቃና አምስት የንጉሡን አማካ
ሪዎች ወሰዳቸው:: ደግሞም የአገሩን ሕዝብ
ለውትድርና የሚመለምለውን ዋና የጦር
አለቃ የነበረውን ጸሓፊውንና በከተማዪቱ
ውስጥ የተገኙትን የጸሓፊውን ሥልሳ ሰዎች
ወሰዳቸው:: 20አዛዡ ናቡዘረዳንም እነዚህን
ሁሉ ይዞ ልብና ወዳለው ወደ ባቢሎን ንጉሥ
አመጣቸው:: 21ንጉሡም ሰዎቹን በሐማት ምድር
እዚያው ልብና ውስጥ አስገደላቸው:: ይሁዳም
ከምድሩ በዚህ ሁኔታ ተማርኮ ሄደ::
22የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር፣ የሳፋን
የልጅ ልጅ የሆነውን የአኪቃምን ልጅ
ጎዶልያስን እዚያው በቀረው በይሁዳ ሕዝብ
ላይ አለቃ አድርጎ ሾመው:: 23መላው የሰ
ራዊቱ ጦር አለቆችና ሰዎቻቸው የባቢሎን
ንጉሥ፣ አገረ ገዥ አድርጎ ጎዶልያስን
መሾሙን ሲሰሙ፣ እርሱ ወዳለበት ወደ ምጽጳ
መጡ፤ እነርሱም የናታንያ ልጅ እስማኤል፣
የቃሬያም ልጅ ዮሐናን፣ የነጦፋዊው የተ
ንሑሜት ልጅ ሠራያ የማዕካታዊው ልጅ
ያእዛንያና ሰዎቻቸው ነበሩ:: 24ጎዶልያስም፣
“የባቢሎናውያንን ሹማምንት አትፍሩ፤ እዚሁ
አገር ኑሩ፤ የባቢሎንን ንጉሥ አገልግሉ፤ ሁ
ሉም ነገር ይሳካላችኋል” ሲል ይህንኑ በቃለ
መሐላ አረጋገጠላቸው:: 25ነገር ግን በሰባተ
ኛው ወር ንጉሣዊ ዝርያ የነበረው የኤሊሳማ
የልጅ ልጅ የሆነው የናታንያ ልጅ እስማኤል
ዐሥር ሰዎች ይዞ መጥቶ ጎዶልያስንና በም
ጽጳ አብረውት የነበሩትን የይሁዳን ሰዎችና
ባቢሎናውያንን ገደለ:: 26ባቢሎናውያንን ከመ
ፍራታቸው የተነሣም ትንሽ ትልቅ ሳይባል ሕዝቡ
ሁሉ ከሰራዊቱ የጦር አለቆች ጋር ወደ
ግብፅ ሸሹ::

## ዮአኪን ከእስራት ተፈታ

25፥27-30 ተጓ ምብ - ኤር52፥31-34

27የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን በተማረከ በሠላሳ
ሰባተኛው ዓመት፣ በዐሥራ ሁለተኛው ወር
ከወሩም በሃያ ሰባተኛው ቀን ዮርማሮዴቅ[ነ]
በባቢሎን በነገሠ በዓመቱ ዮአኪንን ከእስራቱ
ፈታው:: 28በርኅራኄም መንፈስ አነጋገረው፤
በባቢሎን አብረውት ከነበሩት ነገሥታት
ይልቅ ከፍ ያለውን የክብር ቦታ ሰጠው::
29ዮአኪንም የእስር ቤት ልብሱን ጣለ፤ እስከ
ዕድሜው ፍጻሜ ድረስ ከንጉሡ ማዕድ ዘወ
ትር ይመገብ ጀመር፤ 30ንጉሡም ለዮአኪን
እስከ ዕድሜው ፍጻሜ ድረስ የዕለት ቀለ
ቡን ይሰጠው ነበር::

25፥15 2ነገ 24፥13፤ኤር15፥13፤ 20፥5፤27፥16-22
25፥17 1ነገ7፥15-22
25፥18 ቍ1821፤2ነገ12፥9፤ 23፥4፤1ዜና6፥14፤ ዕዝ7፥1፤ነህ11፥11፤ ኤር21፥1፤29፥25፤ 37፥3
25፥21 ዘፍ12፥7፤ ዘኊ34፥11፤ኢሱ 23፥13፤1ነገ8፥46፤ ኤር34፥21፤
25፥22 2ነገ22፥12፤ ኤር39፥14፤ 40፥5፡7፤41፥18፤
25፥25 2ነገ12፥20፤ ዘካ7፥5
25፥26 ኢሳ30፥2፤ ኤር43፥7፤
25፥27 2ነገ24፥12
25፥28 1ነገ8፥50፤ ዕዝ5፥5፤7፥6፡28፤ 9፥9፤ነህ2፥1፤ዳን 2፥48
25፥29 2ሳሙ9፥7
25፥30 ዘፍ43፥34፤ አስ2፥9፤9፥22፤ ኤር28፥4

[ዶ]17 8. 1 ሜትር ያህል ነው:: [ጆ]17 1.3 ሜትር ያህል ነው::
[ነ]27 *አሜል ማርዶክ* ይባላል::

25፥17 *የናስ ጒልላት ... ርዝመት ሦስት ክንድ፤* በ1ነገ 7፥16 እና በኤር 52፥22 የጒልላቱ ርዝመት አምስት ክንድ እንደ ሆነ ተጠቅሶ አል፤ የሁለቱ ክንድ ልዩነት ምናልባት ሊኖር የቻለው ይህን ጽሑፍ የገለበጠው ሰው ባደረገው ግድፈት ሊሆን ይችላል::

25፥18 *ሊቀ ካህኑ ሠራያ፤ ሠራያ* የኬልቅያስ የልጅ ልጅ ነው (የ22፥4 ማብ እና 22፥8፤ 1ዜና 6፥13-14 ይመ):: ልጁ ኢዮሴዴቅ ተማርኮ ወደ ባቢሎን ተወሰደ፤ ከኢዮሴዴቅ ዘር አንዱ ዕዝራ ነው (ዕዝ7፥1 ይመ)::

25፥20 *ልብና ወዳለው ወደ ባቢሎን ንጉሥ አመጣቸው፤* ቍ6 እና ማብ ይመ::

25፥21 *ይሁዳም ከምድሩ በዚህ ሁኔታ ተማርኮ ሄደ፤* ይሁዳ ተማርኮ ከከነዓን ምድር ወደ ባቢሎን መወሰዱ በምናሴ ዘመን የተነገረው የእግዚአብሔር ፍርድ መፈጸሙን ያሳየናል (23፥27 ይመ):: በምርኮ መውሰዱ በኪዳኑ ከተጠቀሱ ርግማኖች አንዱና እጅግ የከፋው ነበር (ዘሌ26፥33፤ዘዳ28፥36፤ኤር25፥8-11 ይመ)::

25፥22 *ጎዶልያስ፤* የ22፥12 ማብ ይመ:: ጎዶልያስ ኤርምያስ እንዳደረገው ባቢሎናውያንን መቃወም አይገባም የሚል አቋም የነበ ረው ሰው ነው (ቍ24 ይመ)፤ ስለዚህም ከባቢሎናውያን ታማ ኝነትን አትርፎ የይሁዳ ገዥ ሆኖ ተሾመ (ኤር41፥10 ይመ)::

25፥23 *ምጽጳ፤* በእስራኤል ንጉሣዊ አገዛዝ ከመመሥረቱ በፊት ሕዝብ የሚሰበሰብበት ታዋቂ የፖለቲካ ከተማ ነበር (የ1ሳሙ 7፥5 ማብ ይመ):: ኤርምያስ ጎዶልያስን ያገኘው በዚህ ስፍራ ነበር (ኤር40፥16 ይመ) *የናታንያ ልጅ እስማኤል፤* ቍ25 ላይ የትውልዱ ዝርዝር በሙሉ ተጠቅሶአል:: የእስማኤል አያት የሆነው ኤሊሳማ በኢዮአቄም ቤተ መንግሥት ጸሓፊ ነበር (ኤር 36፥12):: *የማዕካታዊው ልጅ ያእዛንያ፤* እ.ኤ.አ በ1932 ቴል ኤን- ናስቤህ (ምጽጳ) በተባለ ቦታ ያእዛንያ የሚል ስም የተቀረጸበት በኅብረቀለም ያሸበረቀ ሸክላ ተገኝቶአል፤ ከስሙም ጋር የተጻፈው፣ “ይህ የንጉሡ አገልጋይ የያእዛንያ ነው” የሚል ነበር፤ ምናልባት በሸክላው ላይ የተቀረጸው ይህ ስም በዚህ ቁጥር ላይ የተጠቀሰውን ስም የሚያመለክት ሊሆን ይችላል::

*25፥24፤* ለባቢሎናውያን መገዛት፣ የእግዚአብሔር ፍርድ ስለ ሆነ ጎዶልያስ ለሕዝቡ ጥሪ አቀረበ። በስሙ ጊዜ እንደሚኖሩት በጸጥታ እንደ ወትሮው እንዲኖሩ ጥሪ አቀረበ (ኤር27 ይመ):: ኤርምያ ስም እንዲሁ በ597 ዓ.ቅ.ክ ተማርከው ወደ ባቢሎን ለሄዱት ተመሳ ሳይ መልእክት አቅርቦ ነበር (ኤር 29፥4-7 ይመ)::

25፥25 *በሰባተኛ ወር፤* ጥቅምት 586 ዓ.ቅ.ክ ነው:: *ጎዶልያስንና ...ገደለ፤* ጎዶልያስ እንዴት እንደ ተገደለ የሚገልጽ ዝርዝር በኤር 40፥13-41፥15 ባለው ላይ ተጠቅሶአል:: ጎዶልያስ ለባቢ ሎናውያን መገዛቱን የተቃወመውና በባቢሎናውያን የኀይል አገዛዝ ተጨንቀው ባሉ አሞናውያን ሊገፋፉ የቻለው እስማኤል ዙፋኑን በግሉ የመያዝ ዕቅድ ስለነበረው ነው (ኤር 40፥14፤41፥10፡15)::

25፥26 *ወደ ግብፅ ሸሹ፤* በዚህ ጊዜ ፈርዖን ሆፍራ የግብፅ ንጉሥ ነበር (የ24፥20 ማብ ይመ)::

25፥27 *በሠላሳ ሰባተኛው ዓመት በዐሥራ ሁለተኛው ወር ከወሩም በሃያ ሰባተኛው ቀን፤* በመጋቢት 561 ዓ.ቅ.ክ ነው:: *ዮርማሮዴቅ በባቢሎን በነገሠ በዓመቱ፤* በ561 ዓ.ቅ.ክ ነው፤ አንዳንድ ምሁራን ዮርማሮዴቅ የነገሠው በጥቅምት 562 ዓ.ቅ.ክ ነው ይላሉ (የ24፥1 ማብ ይመ):: የስሙ ትርጓሜ “የመሮዳክ (የአምላክ) ሰው”ማለት ነው:: *ዮአኪንን ከእስራቱ ፈታው፤* የባቢሎናውያንን የአስተዳደር ሁኔታ የሚያሳዩ የድንጋይ ላይ ቅርጽ ጽሑፎች በባቢሎን ለእስረኞች የሚሰጠውን የዘይትና የገብስ ድርሻ ከመጥቀሳቸውም በላይ የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን ከአምስት ወንዶች ልጆቹ ጋር እንደ ታሰረም አመልክተዋል (ከ24፥15 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ስለ ዮአኪን መፈታት ግን የተጠቀሱ ምክንያቶች የሉም:: ምናልባት የርማሮዴቅ በነገሠ ጊዜ ከሰጠው አጠቃላይ የምሕረት ዐዋጅ የተነሣ ሊሆን ይችላል::

25፥28 *በርኅራኄም መንፈስ አነጋገረው፤ ... ከፍ ያለውን የክብር ቦታ ሰጠው፤* የነገሥት መጽሐፍ ታሪኩን በተስፋ ቃል ይደመድማል፤ ተማርኮ በመወሰድ የተገለጠው የእግዚአብሔር ፍርድ እስራኤልን ወይም የዳዊትን ቤት አያጠፋም፤ እግዚአብሔር ለዳዊት ቤት የገባውን የተስፋ ቃል ይጠብቃል (2ሳሙ 7፥14-16 ይመ)::